በቦረና ኦሮሞ የበኩር ልጅ ስም ስያሜ በዓል አከባበር ፎክሎራዊ ገፅታ

በ
ደስታ አማረ

አማካሪ
አቶ ዘሪሁን አስፋው

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነፅሁፍ ትምህርት ክፍል
የሥነጽሑፍና ፎክሎር ድህረምረቃ መርሃ ግብር

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

2000

በቦረና አሮሞ የበኩር ልጅ ስም ስያሜ በዓል አከባበር ፎክሎራዊ ገፅታ

በ

ደስታ አማረ

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል

የሥነጽሑፍና ፎክሎር ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

ዘሪሁን ካሳ ኩሉ

አማካሪ

ማሞ ሄቦ

ፈታኝ

ፈቃዱ ኪዛዛ

ፈታኝ

ምስጋና

ውድ ጊዜያቸውን ሰውተው ጥናታዊ ጽሑፌን በማረምና በማስተካከል የአሁን መልኩን እንዲይዝ ላደረጉልኝ አማካሪዬ ለአቶ ዘሪሁን አስፋው ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

የጥናቱን ሥራ የማከናውንበት በጀት በመመደብ ከፍተኛ እገዛ ያደረገልኝ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ምስጋና ይገባዋል።

ይህን የትምህርት ዕድል እንድጠቀም የፈቀዱልኝ የኦሮሚያ ማስታወቂያና ህዝብ ግንኙነት ቢሮ ኃላፊ የነበሩት አቶ እሸቱ ደሴ ትልቅ ባለውለታዬ ስለሆኑ በጣም አመሰግናቸዋለሁ።

ስለህዝባቸው ባህልና ታሪክ የሚያውቁትን እንዲያካፍሉኝ በጠየቅኳቸው አጋጣሚ ሁሉ ሳይሰለቹ በቂ መረጃ ለሰጡኝ ለአብ ቦርቦር ቡሌ፣ አብ ካሉ ጂሎ፣ አብ ጃተኒ ዲዳና አብ ሰለሞን ጎዳና ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው።

በመስክ መረጃ አሰባሰብ ሂደት ላይ ለተባበሩኝ የቦረና ዞን መስተዳድር የባህልና ቱሪዝም፣ የማስታወቂያና ህዝብ ግንኙነት መሥሪያ ቤቶች ሠራተኞች ምስጋናዬ ይድረሳቸው።

መረጃውን የሰበሰብኩበት በዓል አዘጋጅ አብ አባሩፋ ጀተኒ የተሟላ መረጃ እንድሰበስብ ከፍተኛ እገዛና ትብብር ስላደረጉልኝ አመሰግናለሁ።

ለቤተሰቤ ማዋል የሚገባኝን ጊዜ ለትምህርቴና የጥናት ሥራዬ አድርጌ፣ በእርጋታ እንድከታተልና እንድሰራ በትዕግሥት ከጐኔ ለቆሙት ባለቤቴና ልጆቼም ምስጋና ይገባቸዋል።

ይህን የጥናት ሥራዬን ከዳር እስከ ዳር አንብበው ገንቢ አስተያየታቸውን ለሰጡኝ ጓደኛዬ አጋረደች ጀማነህና ወንድሜ አቶ አሳዬ በቀለ ምስጋናዬ ወሰን የለውም።

በመጨረሻም ጥናታዊ ጽሑፌን በኮምፒዩተር ለግፈችልኝና ላረመችልኝ ወለተማርያም ሰይፉ ምስጋናዬ የላቀ ነው።

አጠቃሎ

የቦረና ኦሮሞ ከሌሎች አካባቢ ኦሮሞዎች በተሻለ ሁኔታ ጥንታዊ ሃይማኖቱን፣ ባህሉንና የገዳ ሥርዓቱን ጠብቆ እየተገለገለበት ይገኛል። በመሆኑም የብዙ አጥኚዎች የጥናት ርዕሰ ጉዳይ ሆኖ ቆይቷል። የገዳ ሥርዓቱና አንዳንድ የባህል ዘርፎች በዝርዝር የተጠኑ ሲሆኑ አንዳንዶቹ በዘገባ መልክ ተነካክተው አልፈዋል።

ቦረናዎች ከፍተኛ ቦታ የሚሰጡት፣ የማንነታቸው መገለጫ መሆኑን የሚናገሩለትና የተለያዩ ክዋኔዎችን በውስጡ የያዘው የበኩር ልጅ ስያሜ በዓል በወጉ ሳይጠኑ ከታለፉት ጉዳዮች አንዱ ነው። ይህን ጥናት እንዳደርግ ያነሳሳኝ፣ የኦሮሞ የስም ስያሜ ሥርዓት እየተለወጠና እየቀረ ባለበት ሁኔታ በቦረናዎች ዘንድ በተግባር መከወኑ፣ በፎክሎር የበለፀገ መሆኑና እስከዛሬ በጥናታዊ መልክ አለመቅረቡ ነው።

የጥናቱ አቀራረብ ገለፃዊ ትንተና ሲሆን መረጃዎቹን ለመሰብሰብ ቃለመጠይቅና ምልከታ የምርምር ዘዴዎች ተግባራዊ ተደርገዋል።

በቃለመጠይቅ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ አማካይነት የቦረናን ኦሮሞ ባህል ጠንቅቀው ያውቃሉ፣ ጥሩ አድርገው ያስረዳሉ ተብለው ከተመረጡት ቁልፍ የመረጃ አቀባዮች፣ ስለህዝቡ አጠቃላይ ባህልና ስለጉቢሣ በዓል አከባበር ዝርዝር ክዋኔዎች መረጃ ተሰብስቧል።

እንዲሁም በ1999 ዓ.ም. በቦረና ኦሮሞዎች ዘንድ ከተከበሩት የጉቢሣ በዓል መሀከል በቦረና ዞን በደዲ የገጠር ቀበሌ ከሰኔ 14-17 ቀን 1999 ዓ.ም. በተከበረው የአባሩሩ ጃተኒ ልጅ የጉቢሣ በዓል ላይ በአካል በመገኘትና በመመልከት በቃለመጠይቅ የተገኙትን መረጃዎች በተጨባጭ መቃኘት ተችሏል

በዚሁ መሠረት በቦረናዎች ከፍተኛ ቦታ ተሰጥቶት በጥበቅ ህግ የሚመራው ጉቢሣ፣ የተለያዩ የፎክሎር ዝርያዎች መከሰቻ መሆኑን ጥናቱ ያሳያል። የተገኙት የፎክሎር ዝርያዎች፣ ቃል ግጥም፣ ቁሳዊ ባህል፣ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባትና ሀገረሰባዊ ልማድ የሚጠቃለሉ ናቸው። እነዚህ የፎክሎር ዝርያዎች የቦረናዎችን የልጅ አያያዝ፣ የመተጋገዝ ባህል የምጣኔ ሐብት አደረጃጀትና የማህበራዊ ደረጃዎች ተዋረድን የሚያሳዩ ናቸው።

መሰል በተግባር ያሉ የተለያዩ የቦረና የባህል ዘርፎች እንዲሁ ቢጠኑ ስለቦረና ኦሮሞ ማህበራዊ ሕይወት የሚያስጨብጡ የፎክሎር አይነቶችን በብዛት ለመቅረስ እገዛ ያደርጋሉ።

ማውጫ

ገፅ

ምስጋና

አጠቃሎ

1. መግቢያ 1

1.1 የጥናቱ ዓላማ 3

1.1.1 ዓቢይ አላማ 3

1.1.2 ዝርዝር አላማዎች 3

1.2 የጥናቱ አስፈላጊነት 3

1.3 የጥናቱ ገደብ 4

1.4 የጥናቱ ዘዴዎች 5

1.4.1 ቃለ መጠይቅ 6

1.4.2 ምልከታ 7

1.5 መቼት 7

1.6 ያጋጠሙ ችግሮች 8

1.7 የተወሰዱ መፍትሔዎች 8

2. የጥናቱ አካባቢና ህዝቡ 10

2.1. የቦረና ዞን መልክዓምድራዊ ገፅታ፣ መሠረተ ልማትና ማህበራዊ አገልግሎቶች 10

2.1.1. መልክዓምድራዊ ገፅታ 10

2.1.2. መሠረተ ልማትና ማህበራዊ አገልግሎቶች 11

2.2. የህዝቡ ታሪካዊ ዳራ 12

2.2.1. ቋንቋ 15

2.2.2. ጋብቻ 15

2.2.3. ባህላዊ የጊዜ አቆጣጠር 18

2.2.4. ገዳ 20

2.2.5. ሃይማኖት 23

2.2.6. ቃሉ 23

2.2.7. ምጣኔ ሀብት 24

3. ክለሳ ድርሳን 25
3.1. የተዛማጅ ሥራዎች ዳሰሳ 25
3.1.1. የቦረና ኦሮሞን ባህል /የፎክሎር ዘሮች/ መነሻ አድርገው የቀረቡ ተዛማጅ ሥራዎች 25
3.1.2. በስም ስያሜ ላይ የቀረቡ ተዛማጅ ሥራዎች 30
3.2. ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት 37
3.2.1. ከፎክሎር ዘርፍ አንፃር 37
3.2.2. ከስም አንፃር 39

4. የቦረና የስም ስያሜ ሥርዓትና የፎክሎር መከሰቻ አውድ 42
4.1. የስም ስያሜ በቦረና 42
4.1.1. Moggaasaa (ሞጋሣ)..... 42
4.1.2. Gubbisaa (ጉቢሣ)..... 42
4.1.2.1. Gubbisaa-Dabballee (የደበሌ ጉቢሣ)..... 42
4.1.2.2. Gubbisaa Angafaa (የበኩር ልጅ ስም ስያሜ) 44
4.2. የበኩር ልጅ ስም ስያሜ በዓል ክዋኔዎች ሂደት 47
4.2.1. Muka muraa (የመጀመሪያው ዕለት-ሙከሙራ) 49
4.2.2. Yayyabaa (ሁለተኛው ቀን - የየባ) 54
4.2.3. Jila Guddaa (Galma afaan goodan) (ሦስተኛው ቀን ጂለ ጉዳ).. 57

5. በስም ስያሜ አጋጣሚ የቀረቡ የፎክሎር ዝርያዎች ትንታኔ 69
5.1. ለበኩር ልጅ የሚወጡ ስሞች 69
5.2. ቃል ግጥሞች 71
5.2.1. Iyyaangaloo (ኢያንገሎ) 71
5.2.2. Bultumoo bulee (ቡልቱም ቡሌ)..... 73
5.2.3. Sagadee Mallayyoo (ሰገዴ መለዮ)..... 75
5.2.4. Ashanee Dooyyoo (አሸኔ ዶዮ)..... 76
5.2.5. Ilmee Hooyoo (እልሜ ሆዮ)..... 77
5.2.6. Alii Aliyoo (አሊ አልዮ)..... 79
5.2.7. Kaarilee jila Gubbisaa (ካሪሌ ሴቶች የሚያዜሙት)..... 80
5.2.8. Sirba jaalalaa kuchuu (ኩቹ የሚባሉ ወጣቶች የሚያዜሙት የፍቅር ዘፈን) 81

5.3. ቁሳዊ ባህል 82
5.3.1. አልባሳት 83
5.3.1.1. Kalloo (ከሎ) 83
5.3.1.2. Marxoo (መርጦ) 84
5.3.1.3. Gorfoo (ጎርፎ) 84
5.3.1.4. Surree ruufaa (ሱሬ ሩፋ) በራስ ላይ የሚጠመጠም.. 85
5.3.2. በእጅ ላይ የሚጠለቁና የሚያዙ ቁሶች..... 85
5.3.2.1. Daannisaa (ዳኒሣ) 85
5.3.2.2. Lichoo (ሊቾ) 85
5.3.2.3. Meedhichaa (ሜዲቻ) 86
5.3.2.4. Siinqee (ሲንቄ) 86
5.3.2.5. Saqqaa (ሰቃ) 87
5.3.3. መሰየሚያ ገልማውና በውስጡ የሚካተቱ 87
5.3.3.1. Galma Jila Gubbisaa (መሰየሚያ ገልማ)..... 87
5.3.3.2. Waddeessaa (ወዴሣ)..... 88
5.3.3.3. Qotii (ቆቲ) 88
5.3.3.4. Handaraaka (ሀንዶራክ) 89
5.3.4. ሌሎች 89
5.3.4.1. Gumaata (ጉማቶ) 89
5.3.4.2. Kochee (ኮቼ) 90
5.3.4.3. Gaadii (ጋዲ) 90
5.4. መንፈሳዊ ይዘት ያላቸው
5.4.1. Bunaqalaa (ቡና ቀላና) 91
5.4.2. Buna Dhahaa (ቡና ደሃ) 91
5.4.3. Daraaraa (ዶራራ) 92
5.4.4. Eebba (ምርቃት) 93

6. ማጠቃለያ 96
የዋቢዎች ዝርዝር 99
አባሪ ጽሑፎችና ፎቶዎች

BORENA ADMINISTRATIVE ZONE



Source :- Oromiya Planning & Economic Development Bureau, 2002

N.B:-The delineation of the Regional and International Boundaries shown on this map must not be considered Authoritative.

ሙዳየ ቃላት

ኦሮምኛ	የአማርኛ ፍች
1. Jila (ጂላ/	በዓል
2. Angafa /አንገፋ /	ታላቅ
3. Gubbisa/ጉቢሣ/	ስምመሰየም /ለበኩር ልጅ/
4. Madhaa /መዳ/	ታናሽ
5. Moggaasaa /ሞጋሳ/	ስምስያሜ /ለሴትና ለታናናሽ/
6. Torban jilaa/ቶርበንጂላ/	ሰባቱ የጉቢሣ በዓል አስፈፃሚ አባላት
7. Qadadduu /ቀደዱ/	የሰባቱ የጉቢሣ በዓል አስፈፃሚ አባላት መሪ
8. Abbaa jilaa /አባጂላ/	የበዓሉ አባት /ባለጉዳይ/ የተሰያሚው ልጅ አባት
9. Haadha jilaa /ሃደጂላ/	የበዓሉ እናት /የተሰየሚው ልጅ እናት/
10. Gaarayyuu /ጋረዩ/	ተጨማሪ ፍቅረኛ /ወዳጅ/
11. Faroo /ፈሮ/	ገድ
12. Ayyaantuu /አያንቱ /	ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው፣ የሚገለፅለት
13. Gada /ገዳ/	የመተዳደሪያ ሥርዓት
14. Aduulaa /አዱላ/	የገዳ ሥርዓት አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት
15. Gumii /ጉሚ/	ጉባኤ
16. Buusaa /ቡሣ/	መዋጮ
17. Dabballee/ደበሌ /	በገዳ ሥርዓት የዕድሜ ክፍፍል የመጀመሪያው ደረጃ /የገዳ ሥርዓቱ የሥራ አስፈፃሚ አባላት በመጀመሪያ ደረጃ ውስጥ ያሉ ወንዶች ልጆች

18. Gaammee /ጋሜ/ ---------- ሁለተኛ ደረጀ የገዳ ሥርዓቱ የሥራ አስፈፃሚ ወንዶች ልጆች

19. Kuusaa /ኩሣ/ ---------- በገዳ ሥርዓቱ የዕድሜ ክልል ሶስተኛው ደረጃ

20. Gada mojjii /ገደሞጂ/ -------- በገዳ ሥርዓቱ የዕድሜ ክልል የመጨረሻው ደረጃ

21. Waaqaa/ዋቃ / ---------- ፈጣሪ

22. Qaalluu /ቃሉ/ ---------- መንፈሳዊ አባት

23. Handhuura/ሀንዱረ/ ---------- እምብርት /መነሻ መጀመሪያ/ ስጦታ

24. Gumaata /ጉማቱ/ ---------- ስጦታ፣መጠየቂያ

25. galma /ገልመ/ ---------- የበዓል ማክበሪያ፣ ግብ

26. Odaa /አዳ ---------- የእንጨት ዓይነት /ዋርካ/፣ መሰብሰቢያ፣ ጥላ

27. Warra jilaa /ወረጂላ/ ---------- የበዓሉ ባለጉዳዮች

28. Bitaa /ቢታ/ ---------- ከቦረና ቀን አቆጣጠር የአንዱ ወር ስም /ጥሩገድ የሌለው /ግራ የሆነ/

29. Gidaadaa /ጊዳዳ/ ---------- ከወሩ አንድ ቀን /ጥሩ ገድ የሌለው/

30. Kalloo /ከሎ/ ---------- ቆዳ /ለጉቢሣ/ የሚዘጋጅና ከወገብ በላይ በልብስ ላይ የሚደረብ

31. Jila tolchuu /ጂለቶልቹ/ --------- በዓላት ማዘጋጀት፣ ሁኔታዎች ማመቻቸት

32. Daraaraa tanboo /ደራራ ተንቦ/ --ለምለም፣መመረቂያ ማማለጃ

33. Hayyuu /ሀዩ / ---------- የገዳን ሥርዓት ህጐች ጠንቅቀው የሚያውቁ /አዋቂ/፣ ባለሙያ

34. Waddeessa /ወዴሠ/ ---------- የእንጨት አይነት ለስም ስያሜ በዓል ማክበርያ ከማቆረጡ እንጨቶች የመጀመሪያው

35. Surree Ruufaa /ሱሬ ሩፋ/ ---------- ቀይና ጥቁር ቀለማት ያለው በእራስ ላይ የሚጠመጠም የቦረና ኦሮሞዎች መለያ

36. Horooroo /ሆሮሮ/ ---------- አባ ገዳ የሚይዘው የሥልጣን በትር

37. Lichoo /ሊቾ/ ---------- አለንጋ መሳይ፣ የህግ ማስከበርያ፣ በበዓል ጊዜ የሚያዝ

38. Butumee /ቡቱሜ/ ---------- የከበት በረት በር አካባቢ የሚቀመጥ፣ ከብቶች መኖራቸውን የሚያበስር እንጨት

39. Daannisaa /ዳኒሣ / ---------- የእንጨት ዓይነት፣ የበዓል በለገዳይ የሚይዘው በትር የሚሠራበት እንጨት

40. muka muraa /መኩመራ / ------ እንጨት ቆረጣ፣ የገቢሣ በዓል የመጀመሪያ ዕለት ክዋኔ

41. Gorfoo /ጎርፎ/ ---------- ቀሚስ መሰል ከቆዳ የሚሰራ የሴት ባህላዊ ልብስ

42. Saqqaa /ሰቃ/ ---------- የበኩር ልጅ እናት እጅ ላይ የምታጠልቀው ከቆዳ የተሠራ ቁስ

43. Siinqee /ሲንቄ/ ---------- ሴቶች ከተዳሩበት ቀን ጀምሮ በበዓላት ቀን በእጅ የሚይዙት በትር

44. Marxoo /መርጦ/ ---------- ሽርጥ /ወንዶች/ በበዓላት ጊዜ የሚለብሱት

45. Handaraaka/ ሀንደራክ/ ------ የእንጨት አይነት -የገቢሣ በዓል አደራሽ ሲሠራ እንደመሠረት መጀመሪያ የሚቀመጥ

46. Kaarilee/ካርሌ / ---------- የዘፈን ዓይነት /ሴቶች የሚዘፍኑት/

47. Bishaan Haroo/ቢሻን ሀሮ/ -- የሀይቅ ውሃ /የኩሬ ውሃ/

48. Guutuu /ጉቱ/ ---------- መሀል አናት ከሌለው የራስ ፀጉር እንዲረዝም ተደረገ

49. Qotii /ቆቲ/ ---------- የበዓል እንጨት

50. Wayyoo msuu /ወዮ ምሱ/ -- ማክበር

51. Buna dhahaa /ቡና ዳሃ/ ------ የገድ መመልከቻ ቡና

52. Kochee /ኮቼ/ ---------- የምግብ ዓይነት፣ ለወጣቶች በጉቢሣ በዓል ላይ የሚዘጋጅ

53. Muudaa/ መ·ዳ/ ---------- ሥልጣን ማስጠት፣ መሰየም

54. Dibbee /ደቤ / ---------- ኮቼ የተባለ የምግብ ዓይነት የሚቀርብበት የወግ ዕቃ፣ከበሮ

55. Meedhicha /ሜዲቻ/ --------- በእጅ ላይ የሚጠለቅ ከቆዳ የሚዘጋጅ የበዓል አዘጋጅ ወይም ታዳሚነት መግለጫ

Horii meedhichaa/ሆሪሜዲቻ/ --- ለሜዲቻ ለዕርድ የሚቀርብ ከብት /የመመረቂያ ከብት/

56. Areerrii /አሬሪ/ ---------- ለሜዲቻ ዕርድ የሚቀረብ ከብት የሚመረቅበት ሥርዓት

57. Gaadii /ጋዲ/ ---------- ላም ስትታለብ እግር የሚታሰርበት

58. Afaan goodan /አፋን ጎደን / -- መዝጊያ ማበጀት

59. Kuchuu /ኩቹ/ ---------- ዕድሜያቸው ከ16 በላይ የሆኑ ወጣቶች

60. Gulmaa /ጉልማ/ ---------- ዛጎል

61. Buna qalaa /ቡናቃላ / ------ ልዩ ባህላዊ የቡና ዝግጅት

62. Baaraa/ባራ/ ---------- ከመሬት ተቆፍሮ የሚወጣና የሚበላ

63. Dharraa /ደራ/ ---------- ናፍቆት፣ምኞት

64. Marabbaa /መረባ/ --------- ተመስገን

65. Karra /ከረ/ ---------- በር

66. Dhiibuu /ዲቡ/ ---------- ሸለቆ፣ ወደ ውስጥ

67. Sageetoo / ሰጌቶ// ---------- ጦር /አነሰተኛ ጦር/

68. Ardaa / አርዳ / ---------- መንደር /በዓል የሚከበርበት/

69. Curruxxee /ጩሩጤ / ------ ድኽኽ

70. Sifeessuu /ስፊሱ/ ---------- መባረክ /መስማማት

71. Daaxxe /ዳጤ / ---------- ተንቆጠቆጠ፣ አማረ

72. Cirrii /ጭሪ / ---------- የወፍ አይነት፣ ቆንጆ

73. Guntuta /ጉንቱተ/ ---------- አጎጥጉጤ /ለጡት/ አገጠጠጤ

74. Lookoo /ሎኾ/ ---------- ረኽቦም፣ ዘንካታ፣ መለሎ

1. መግቢያ

ከኢትዮጵያ ብሔረሰቦች መሀከል ኦሮሞ አንዱ ነው። ኦሮሞ አንድ ቋንቋ የሚናገር በኦሮሚያ 17 ዞኖችና በሀገሪቷ የተለያዩ ክፍሎች የሚኖር ህዝብ ነው። አብዛኛዎቹ ኦሮሞዎች በተለያዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ምክንያት ሲደርሱባቸው በቆዩት ተዕዕኖዎችና ከሌሎች አጎራባች ብሔር ብሔረሰቦች ጋር ባላቸው ግንኙነት የተነሳ ነባር ባህላቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተለወጠ ሲሆን የቦረናና የጉጂ ኦሮሞዎች ግን በተሻለ ሁኔታ ባህላቸውን ይዘው ቆይተዋል።

በውልደት ታላቅ ነው ተብሎ በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ የሚነገርለት የቦረና ኦሮሞ የማንነቱ መለዮ የሆኑ የተለያዩ የባህል ገፅታዎች አሉት። እነዚህ ባህላዊ ገፅታዎች በተግባር ያሉ ሆነው በስፋት አልተጠኑም።

ከነዚህ ካልተጠኑ የባህል (የፎክሎር) ገፅታዎች መሀከል አንዱ ጉቢሣ (Gubbisaa)፣ የበኩር ልጅ ስም ስያሜ በዓል ነው።

የቦረና ኦሮሞ ለስም አሰያየም ደረጃ ወስኖ የሚከውነው ሲሆን፣ የበኩር ልጅ ስም ስያሜ ልዩ ትኩረትና ቦታ ይሰጠዋል። ይህ በዓል የተለያዩ ክዋኔዎች የሚቀርቡበት ቢሆንም አልተጠናም። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አንዳንድ የመገናኛ አውታሮች ካቀረቡዋቸው አጫጭር ዘገባዎች በቀር የህዝቡን ባህል ያጠኑ የውጭ ተመራማሪዎች ጉዳዩን በደፈናው ገልያ ከማለፍ ውጭ ምን ምን ፎክሎራዊ ገፅታዎች በውስጡ እንደሚታዩ በጊዜና በቦታ ለይተው፣ ከክዋኔያቸው አጣምረው ያመለከቱበት ጥናት አላጋጠመኝም። በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል በ1960ዎቹ መጀመሪያ ጀምሮ የኦሮሞ የሥነቃል አይነቶች ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍነት ቀርበው ተጠንተዋል። (ፈቃደ አዘዘ፣ 1984፣8)።

እነዚህ ከ1960ዎቹ ጀምሮ የቀረቡት የኦሮሞ ሥነቃል የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፎች በየጥናቶቹ ውስጥ (የፈቃደ የጥናት ሥራዎች ውስጥ) በተጠቀሱበት ሁኔታ ሲቃኙ፣ የቦረናን ኦሮሞ የሚመለከት አካተው አላገኘሁም።

በሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት ረገድ ግን፣ ሳህሉ ኪዳኔ ከቋንቋዎች ጥናት ተቋም እ.ኤ.አ. በ1996 ዓ.ም.፣ በማህበረሰብ ትምህርት ክፍል (Social anthropology) ገመቹ ታዬ በ2002፣ የቦረናን ኦሮሞ ባህል አጥንተዋል። የእነርሱንም ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያገናኘው የህዝቡን አጠቃላይ ሕይወት በማየቱ አቅጣጫ ካልሆነ ከፎክሎር ዘርፉ የበኩር ልጅ ስም ስያሜን የሚመለከት ጉዳይ አካትተው ተገኝተው አይደለም።

ስለዚህ ይህ በቦረና ኦሮሞ የበኩር ልጅ ስም ስያሜ በዓል ላይ ያተኮረው ጥናት የተለያዩ የህዝቡን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፤ እምነትና ፍልስፍና፣ የህይወት

አመራርን ነቅሶ ማውጣት የሚቻልበት አጋጣሚ ይሆናል የሚል እምነት አለኝ። የቦረናን ኦሮሞ አንዳንድ ባህላዊ ጉዳዮች በተለያዩ አጋጣሚዎች ተመልክቻቸዋለሁ። የጉቢሣን በዓል ይዘት የሚዳስሱ አጫጭር ጽሑፎችንም በጋዜጣ ላይ ወጥተው ሳነባቸው የተመለከትኩዋቸውና ትኩረት ተሰጥቷቸው በበዓሉ ወቅት የሚከወኑ ድርጊቶች፣ እኔም በዓሉን እንድመረምረው ስለገፋፉኝ በዚህ ጥናቴ ልመለከተው መርጫለሁ።

ይህ ጥናት፣ በበዓሉ ላይ ምን ምን የፎክሎር ዝርያዎች ይኖራሉ? ምን ምን ፋይዳ አላቸው? እንዴት እየተላለፉ እዚህ ደረሱ? የህዝቡ ተሳትፎ ምን ይመስላል? የሚሉትን ነጥቦች ያነሳል።

ጥናቱ ስድስት ምዕራፎች አሉት። የመጀመሪያው ክፍል መግቢያውን መነሻ አድርጎ፣ በውስጡ ለጥናቱ መነሻ የሆኑ ጥያቄዎች፣ የጥናቱ ዋናና ዝርዝር ዓላማዎች፣ የጥናቱን አስፈላጊነት (ረቡን)፣ የጥናቱን ገደብና ስፋት፣ ጥናቱ የቀረበባቸውን ዘዴዎች፣ ዘዴዎቹ ተግባራዊ ተደርገው ሲሠራ ያጋጠሙ ችግሮች፣ ችግሮቹን ለመቋቋም የተመረጡ መንገዶችና የተገኙ መፍትሔዎች በቅደም ተከተል ይዟል።

በሁለተኛው ምዕራፍ የጥናቱ አካባቢና ህዝቡ ተቃኝተዋል። ስለቦረና ዞን መልክዓምድራዊ ገፅታ፣ ስለህዝቡ ታሪክ፣ ባህል በተለይ ከበኩር ልጅ ስም ስያሜ በዓል ጋር የጠበቀ ቁርኝት ያላቸውና የበዓሉ ገላጭ ጉዳዮች ነጥብ በነጥብ ተቀምጠዋል።

በሦስተኛው ምዕራፍ ክለሳ ድርሳን ቀርቧል። በዚህም ክፍል በቦረና ኦሮሞ ባህል ዘርፎች ላይ የቀረቡ ጥናቶች፣ የስም ስያሜም ርዕሰ ጉዳያቸው ያደረጉ የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ስምንት ጽሑፎች፣ በተለያዩ ኮንፈረንሶችና በሚዲያ ላይ የቀረቡ መጣጥፎችና ፕሮግራሞች ተቃኝተዋል። በንድፈ ሀሳባዊ ክፍሉም እንዲሁ የስም ስያሜን ፎክሎራዊነትና በበዓል ሲከወን የፎክሎር ዝርያዎች መከሰቻ መሆኑን የሚገልፁና በስም ስያሜ ላይ ያተኮሩ ንድፈ ሀሳባዊ ጽሑፎች ታይተዋል።

የጥናቱ አራተኛ ምዕራፍ የቦረና ኦሮሞ የስም ስያሜ አሰጣጥ ሥርዓቶች፣ የፎክሎር መከሰቻ የስም ስያሜ በዓል ቀናትና የየቀናቱ ክዋኔዎች የተቃኙበት ነው።

በአምስተኛው ምዕራፍ በበዓሉ መከወኛ የሦስት ቀናት ቆይታ ውስጥ በታዩት ክዋኔዎች ውስጥ ጎልተው የወጡትና የስያሜ በዓል መለዮ የሆኑት የፎክሎር ገፅታዎች፣ በዝርያ በዝርያ ተከፍለው ተገልፀዋል፣ ተተንትነዋል።

በስድስተኛው ምዕራፍ፣ ጥናቱ ባለፈባቸው ሂደቶች ውስጥ የተገኙትን ውጤቶች በማጉላት ማጠቃለያና አስተያየት ተሰጥቷል። በመጨረሻም ዋቢ መጻሕፍትና አባሪዎችም ተያይዘዋል።

1.1 የጥናቱ ዓላማ

ጥናቱ ዓቢይና ዝርዝር ዓላማዎች አሉት።

1.1.1. ዓቢይ ዓላማ

የቦረና ኦሮሞን የበኩር ልጅ ስም ስያሜን ሥርዓቶች ምንነት፣ አፈፃፀማቸውን፣ በበኩር ልጅ ስም ስያሜ ወቅት የሚዘጋጀውን በዓል አከዋወን መመዝገብ፣ በበዓሉ አጋጣሚ በሚከወኑት የፎክሎር ዝርያዎች ላይ ትንታኔ መስጠት የጥናቱ አቢይ ዓላማ ነው።

1.2.2. ዝርዝር ዓላማዎች

በህዝቡ ባህል፣ ለበኩር ልጅ የሚሰጥ የስም ስያሜ፣ መነሻ የሚያደርጋቸው ጉዳዮች ምን ምን እንደሆኑ፣ እንዲሁም ከበኩር ልጅ ውጭ የሆኑት ሌሎች ወንዶችና ሴቶች እንዴት እንደሚሰየሙ ያለውን ልዩነት ማሳየትና መተንተን።

በቦረና ኦሮሞዎች ስያሜ መቼ መቼ እንደሚፈፀም፣ ከጊዜ አንፃር የሚፈፀምበትንና ሲሰየም ማን ስያሜ እንደሚሰጥ፣ እንዴት እንደሚረጋገጥ ማሳየት ነው።

በቦረና ለስም ስያሜ በተለይ ለበኩር ልጅ ስም ሲሰየም በዓል ለምን እንዳስፈለገ፣ በዓሉ ምን መልክ እንዳለው አዘገጃጀቱን ጭምር ማሳየት።

በዚህ በስም ስያሜ በዓል ላይ የሚቀርቡ ፎክሎራዊ ድርጊቶች፣ የሚዜሙ ዜማዎች (ቃል ግጥም)፣ የድርጊቶች መከወኛ ቁሳቁሶች ምን ምን እንደሆኑ፣ መግለፅና መተንተን ነው።

የበዓሉ ተሳታፊዎች እነማን እንደሆኑ ለይቶ ከማውጣት በተጨማሪ፣ በበዓሉ የሦስት ቀን ቆይታ ውስጥ ያላቸውን ድርሻ ማሳየት የዚህ ጥናት አንዱ አላማ ነው። በቦረናዎች ዘንድ በስም ስያሜ ሥርዓቶች (የበኩር ልጅ ስም ስያሜ በዓል) መነሻ በማድረግ ለልጆች የሚሰጠውን ቦታ፣ የስም ስያሜ አከዋወኑ በልጆች የወደፊት ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ህይወት ዝግጅት ውስጥ የሚጫወተውን ሚና የአውዱን ክንዋኔዎች መሠረት አድርጎ ማስቃኘት ነው።

1.2. የጥናቱ አስፈላጊነት

የቦረና ኦሮሞ የበኩር ልጅ ስም ስያሜና ለስያሜው የሚዘጋጀው በዓል አከባበር መጠናቱ የህዝቡን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት፣ አመለካከቱን ለይቶ ለማወቅ ለሚሹ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በመረጃነት ሊጠቅም ይችላል።

ይህ የቦረና የስም ስያሜ ባህል፣ በተግባር እየተገለገሉበት ያለ ቢሆንም፣ ፎክሎር ወይም ባህል በባህርይው ተለዋዋጭ (dynamic) በመሆኑ ይህ የፎክሎር ገፅታ በጊዜ፣ በቦታና ሁኔታዎች መቀያየር ሊለወጥ ይችላል። ስለዚህ በበዓሉ ወቅት የሚከወኑ ድርጊቶች፣ የአከባበር ሥርዓቱ፣ በበዓሉ ወቅት የሚታየው የርስበርስ ግንኙነትና መተጋገዝ ተጠንተው መቀመጣቸው የህዝቡን ታሪክ ወግና ልማድ ለተከታዩ ትውልድ በጽሑፍ ለማስተላለፍ ስለሚያግዝ መጠናቱ አስፈላጊ ነው። (Martha C. Sims & Martine, 2005:74-82)

ይህን የቦረናን አሮሞ የስም ስያሜ አከዋወን ከሌሎች የአሮሞ ጎሣዎች የስም ስያሜ አፈፃፀም ጋር በንፅፅር ወይም የፎክሎርን የመለዋወጥ ባህርይ ከስም ስያሜ አንፃር ተከታይ ጥናት ማድረግ ለሚሻ ሌላ ባለሙያ መነሻና ማነፃፀሪያ በመሆን በመረጃ ምንጭነት ሊያገለግል ይችላል።

የህዝቡን ፎክሎር መሠረት አድርገው ለሚተለሙ የባህል ጥናት፣ የህዝቡ የማህበራዊና የምጣኔ ሐብት ደረጃ ጥናት ፕሮጀክቶች ዝግጅትና ተግባራዊነትም መረጃ በመስጠት ጠቀሜታ ሊኖረው ይችላል።

1.3. የጥናቱ ገደብ

የስም ስያሜ በኦሮሚያ ክልል በተለያዩ ቦታዎች እንደ አካባቢው ባህልና እምነት ይፈፀማል። ይህ ጥናት መሠረት የሚያደርገው የቦረና ኦሮሞ ስም ስያሜን ብቻ ነው። በቦረና ኦሮሞዎች ዘንድም ለልጅ ስም ስያሜ የተለያዩ የአፈፃፀም ሥርዓቶች ቢኖሩም በጥናቱ ላይ አፅንዖት የሚሰጠው በበኩር ልጅ ስም ስያሜ በዓል ፎክሎራዊ ገፅታዎች ላይ ነው። "በዓሉ በዞኑ ባሉት ወረዳዎችና ቀበሌዎች ሁሉ ተመሳሳይ ገፅታ አለው። ሰቦና ጎና በጥምር የሚከውኑት ነው። "በማለት የጥናት ረዳቶቼ አብ ቦርቦር ቡሌና አብ ካሉ ጂሎ ተመሳሳይ ምላሽ ሰጥተውኛል። በተጨማሪም ከነዚህ ቁልፍ መረጃ አቀባዮቼ በቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ፣ በቦረናዎች የበዓሉ አከባበር ቅደም ተከተል ያለው፣ በጥብቅ ባህላዊ መመሪያ የሚከወንና የአፈፃፀም ህግጋቱን ማክበር የግድ እንደሆነ ያስገነዝባል። በመሆኑም የዚህ ጥናት በያቤሎ ወረዳ ላይ በተከበረ አንድ በዓል ላይ እንዲያተኩር ተደርጓል።

የፎክሎር ገፅታዎች ሲባል ወሰን የለውም። ሆኖም በዚህ ጥናት በበኩር ልጅ ስም ስያሜ የሦስት ቀን ቆይታ፣ በመረጃ አቀባዮቼ ለበዓሉ ክዋኔዎች ተግባራዊነት ወሳኝ የሆኑ የጉቢጣ በዓል መለዮዎች ናቸው የተባሉትን፣ ስሞች፣ ቃል ግጥሞች፣ ባህላዊ ቁሳቁሶች (material culture) መንፈሳዊ ይዘት ያላቸው ምርቃቶችን መግለፅና መተንተን

ነው። ሌሎች በበዓሉ ላይ የታዩ ለበዓሉ ድምቀት ሲባል የቀረቡ እንደ አስፈላጊነታቸው ሊተነተኑ ይችላሉ። መቅረባቸው ግን የግድ አይሆንም።

በበዓሉ ላይ የታዩ የፎክሎር ዝርያዎች በዝርያ፣ በይዘትና በቅርፅ የተለያዩ ናቸው። የጥናቱ ዓላማ በበዓሉ ላይ የተከሰቱትን መለየትና መተንተን ነው የሚል ቢሆንም፣ በጥናቱ ለመዳሰስ የተሞከረው ዋና ዋናና ጎልተው የሚታዩት ስም፣ ቃል ግጥም፣ ቁሳዊ ባህል፣ ምርቃትና አንዳንድ ጉልህ ድርጊቶች ናቸው። ለፎክሎር ዝርያዎች የተሰጣቸው መጠሪያ ሀገረሰባዊ ስያሜን (ህዝቡ በሚጠራቸው ስማቸው) መሠረት ያደረገ ነው።

ቃል ግጥሞቹን በትንታኔም ሆነ በአባሪነት በቀረቡበት ክፍሎች ወደ አማርኛ ስተረጉማቸው ግጥም በግጥም ሳይሆን እያንዳንዱ ስንኝ የሚያስተላልፈውን ሀሳብ በመውሰድ ነው። የአንድን ቋንቋ ግጥም ወደ ሌላ ቋንቋ በግጥም መተርጎም ከባድ ነው። የሀሳብ መዛባት ሊከተል ይችላልና። (Austin, 1994:26)

የበዓሉን የፎክሎር ገፅታዎች ጥናት በተለያየ አቅጣጫ መቃኘት ይቻላል። እዚህ ላይ አቅጣጫውን የሚወስነው በበዓላት ላይ ያለው የንድፈ ሐሳብ አቀራረብ ነው። የአጥኝ ውም ምርጫ የራሱ የሆነ ቦታ ይኖረዋል። ፎክሎሩን ወይም የፎክሎሩን አውድ አለበለዚያ ሁለቱንም አጣምሮ ማቅረብ ይችላል። ግን የበዓል ጉዳይ ፎክሎሩን ከአውዱ አንፃር ማየት ላይ እንዲተኮር ግፊት ያደርጋል። ምክንያቱም ፎክሎር ሕይወት ዘርቶ እንዲህ ነው መባል የሚችለው ከሚቀርብበት አውድ ማህበራዊና ባህላዊ ገፅታ አንፃር ሲቃኝ ነው። የበኩር ስም ስያሜ በዓል ላይ የምንቃኛቸው የፎክሎር ዝርያዎችም ምንነትና ፋይዳ ግልፅ ሆኖ ሊታይ የሚችለውም በዓሉ ላይ ባለው አቀራረቡና ይዘቱ ስለሆነ በበዓሉ ወቅት ባላቸው ይዘትና ቅርፅ አንፃር ታይተው ተተንትነዋል። ከዚህም በተጨማሪ በምዕራፍ አራትና አምስት ውስጥ ለአቀራረብ እንዲመችና ገፁ በትርጉም እንዳይጣበብ ከመረጃ አቀባዮች በቀጥታ ጥቅስ ከማቅረብ ሀሳቡን በመውሰድ (Paraphrase) ተገልግያለሁ።

1.4. የጥናቱ ዘዴዎች

ጥናቱን ለማከናወን ሁለት የአጠናን ዘዴዎች ተግባራዊ ሆነዋል። አብዛኛው ጥናት መሠረቱ ከቤተመጻሕፍት በንባብ ከሚገኙና በመስክ ላይ በቃለመጠይቅና ምልከታ ከሚሰበሰቡ መረጃዎች ነው። (Bartis, 2002:3)

በመሆኑም ስለቦረና ህዝብ ባህል፣ ስለ ስም ስያሜ አጠቃላይ ጽንሰ ሀሳብ የሚያስገነዝቡ ጽሑፎችን ከቤተመጻሕፍትና ከኢንተርኔት በማፈላለግ መረጃ የማደራጀት ሂደት ተካሂዷል።

በሁለተኛው የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ የመስክ ሥራ፣ ቃለመጠይቅና ምልከታ አማካይነት ስለ ቦረና የስም ምንነት፣ የስም አሰጣጥ ሥርዓቶችና የበዓሉ አከዋወን መረጃዎች ተሰብስበዋል።

በመስክ ሥራው መረጃዎች ለማሰባሰብ ወደ ቦረና ዞን ያቤሎ ወረዳ በመጓዝ መረጃዎችን ለመሰብሰብ በጥናቱ ትልም ላይ የያዝኩትን ጊዜ በሁለት ዙር ከፋፍዬ ተጠቅሜያለሁ። በመጀመሪያው ዙር ከሚያዝያ 8 ቀን 1999 ዓ.ም. እስከ ግንቦት 10 ቀን 1999 ዓ.ም. ድረስ መስክ ወጣሁ። በዚህ ጊዜ ውስጥ በዞኑ አስተዳደር የተለያዩ ጽህፈት ቤቶች በመገኘት፣ ስለ ዞኑ መልክዓምድራዊ አቀማመጥ፣ ስለህዝቡ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ህይወት፣ ባህልና ታሪክ የሚገልው በጽሑፍ ያሉ መረጃዎችን ሰብስቤያለሁ።

1.4.1. ቃለ መጠይቅ

ቃለ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰበያ ዘዴ፣ አንድ አጥኚ በጥናቱ ውስጥ ለሚያነሳቸው ሀሳቦች፣ ድርጊቶችና መቼቶች መረጃዎች ያስገኙልኛል ያላቸውን ጥያቄዎች አዘጋጅቶ፣ ስለጉዳዩ ያውቃሉ፣ መረጃ ይኖራቸዋል ብሎ የመረጣቸውን ሰዎች እየጠየቀ መረጃ የሚያጠናቅርበት ነው። ሰዎቹ ሲጠየቁ ድርጊቶችን፣ ለድርጊቶች የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ሀሳቦችን የጉዳዩ ባለቤት ሆነው ይገልፃሉ፣ ያብራራሉ (Kenneth, 1964:77-78)።

በዚሁ መሠረት የኦሮሞ ህዝብ ባህልና ህግ ላይ የጠለቀ እውቀት ያላቸውን የሀገር ሽማግሌዎች፣ ከህዝቡ መሀል የተገኙና በባህሉና ታሪኩ ላይ ጥናት ያደረጉና በማድረግ ላይ ያሉ ባለሙያዎች ሳፈላልግ ከዞኑ ባህልና ቱሪዝም ቢሮና የተለያዩ ሰዎች በሰጡኝ ጥቆማ መሠረት አነጋግሬ ፍቃደኝነታቸውን ካረጋገጥኩ በኋላ አብ ቦርቦር ቡሌ 60)፣ (አብ ጃተኒ ዲዳ፣ አብ ካሉ ጅሎ አብ ሰለሞን ጎዳና) የተባሉትን አራት ሰዎች በቁልፍ መረጃ ሰጪነት ተጠቅሜ ስራውን መጀመር ችያለሁ።

በዚህ የመጀመሪያ ዙር፣ የስም ስያሜ በቦረና እንዴት እንደሚሰጥ፣ ምን ምን ዓይነት የአሰያየም ሥርዓቶች እንዳሉ፣ ምን ምን አይነት ስም እንደሚሰየም፣ ታላቅ፣ ታናሽ፣ ወንድ፣ ሴት እንዴት እንደሚሰየም፣ ሲሰየም ምን ምን ባህላዊ ህጎች እንደሚከተሉ፣ በስያሜው በዓል ላይ የሚያስፈልጉ ባህላዊ ቁሶች፣ የሚቀርቡ ዜማዎች፣ የሚከወኑ መንፈሳዊ ድርጊቶች፣ የበዓሉ ተሳታፊዎችና ድርሻቸው ምን እንደሆነ የመሳሰሉትን ነጥቦች በማንሳት በቃለመጠይቅ ዘዴ ሰብስቤያለሁ።

ቃለመጠይቁን በተናጠል ስወስድ ተመሳሳይ ጉዳይ ላይ የተለያየ ምላሽ ለሰጡኝ ድጋሚ በአንድነት በጋራ እንዲያብራሩ በመጠየቅ እየተወያዩ የተቀራረበ መረጃ እንዲሰጡኝ አድርጌያለሁ።

1.4.2. ምልከታ

ምልከታ፣ ተመራማሪው ከውጭ ሆኖ ሌሎች ሰዎች የሚከውኑትን ድርጊት የሚመለከትበት መንገድ ሲሆን፣ ድርጊቱን ቀጥታ በተመለከተበት ሁኔታ የሚገልፀውም ይሆናል። በዚህ አገላለፅ ምልከታ ከዕይታው ገፅታ አንፃር ብቻ ሳይሆን ሌሎችን የስሜት ህዋሳት ማዳመጥ፣ መዳሰስና መቅመስንም በማሳተፍ ምሉዕ የሆነ መረጃ ለማግኘት ያስችላል። (Jackson, 1987:63, Kenneth, 1964:77)

ይህን የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ በሁለተኛው የመስክ ሥራ ክፍሌ ሙሉ በሙሉ ተገልግዬ ቀደም ሲል የተገኙትን መረጃዎች ተጨባጭ ለማድረግና ተጨማሪ መረጃዎችን ለማከል ችያለሁ።

በዓሉ የሚከበርበት ጊዜን መሠረት በማድረግ ወደ ሁለተኛው ዙር የመስክ ሥራ የተሠማራሁት ግንቦት 28 ቀን 1999 ዓ.ም. እስከ ሰኔ 30 ቀን 1999 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ነው። የአካባቢው የክረምት ማብቂያ ከግንቦት ወር መጨረሻ ጀምሮ ስለሚከበር የጉቢጣ በዓል በማጠያየቅ፣ በያቤሎ ወረዳ በደዲ (Dhaddii) ገጠር ቀበሌ፣ አብ አባሩፋ ጃተኒ ከሰኔ 14 ቀን 1999 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ሰኔ 17/1999 ዓ.ም.፣ ከሐምሌ 26 እስከ ሐምሌ 30 ቀን 1999 ዓ.ም. በአሬሮ አብ አብልቃድር አብዲ እንደሚያከብሩ መረጃ አገኘሁ። ከቦታው ቅርበትና ከተለያዩ ሁኔታዎች መመቻቸት አንፃር ትኩረት አድርጌ መረጃ የሰበሰብኩት፣ የአብ አባሩፋ ጃተኒን የበኩር ልጅ ስም ስያሜ በዓልን ነው። አሬሮ ላይ የተከበረው የጉቢጣ በዓል ላይም አቶ ተስፋዬ ዋቅቶላን ወክዬ መጠነኛ መረጃዎች ሰብስቤአለሁ።

በሦስት ቀን የበዓሉ ቆይታ የተመለከትኩዋቸውን በማስታወሻ መዝግቤያለሁ። የመቅረጫ መሣሪያዎችንም ተገልግያለሁ። በበዓሉ ክዋኔ ወቅት በመጀመሪያ ዙር የመስክ ሥራና የነበሩትን ድርጊቶች አስመልክቶ ያደረግሁትን ቃለ መጠይቅ፣ በበዓሉ ላይ ሲዘመሙ የነበሩትን በቴፕ፣ በፎቶግራፍ፣ በበዓሉ ጊዜ ደግሞ የተከወኑትን ድርጊቶች ተጨባጭ ለማድረግ የተቻለውን ሁሉ በፎቶግራፍና በቪዲዮ ካሜራ እንዲቀረፅ አድርጌያለሁ።

1.5. መቼት

በመስክ ሥራ ወቅት አንድ አጥኚ የፎክሎር ዘሮችን፣ ክዋኔዎችን ጠይቆና ተመልክቶ መረጃ ለማሰባሰብ ሦስት፣ ተፈጥሮአዊ፣ አርቲፊሻልና ቅንብር ተፈጥሮአዊ መቼቶች (ቦታና ጊዜ) ይገለገላል (ፈቃደ፣ 1991፣ 122-124፣ Kenneth, 1964:87-9)።

በዚህ በቦረና የበኩር ልጅ ስም ስያሜ በዓል አከባበር ጥናት ከነዚህ የመረጃ አሰባሰብ መቼቶች ሁለቱን ተግባራዊ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል። ጉዳዩን የሚያውቁትን አዋቂዎችና ባለሙያዎች ድርጊቱ በሌለበት እንዲገልፁልኝ በማድረግ /አርቲፊሻል መቼት/፣ በበዓሉ ላይ በመገኘት ተፈጥሮአዊ መቼትን በመመልከት ሁለቱን አቀናጅቼ ሠርቻለሁ።

1.6. ያጋጠሙ ችግሮች

የጥናቱን ሥራ ለማከናወን ከተነሳሁበት ጀምሮ የሁለተኛ ዙር የመስክ ሥራ አጠናቅቄ እስከተመለስኩበት ድረስ ያጋጠሙ ችግሮች ነበሩ። ከነዚህ ዋና ዋናዎቹና መገለፅ ያለባቸው በመስክ ላይ ያጋጠሙት ናቸው።

በመስክ ሥራ ላይ ለቃለ መጠይቅ የሚመረጡ ወይም የሚጠየቁ አንዳንድ ሰዎች ፈቃደኛ አለመሆን፣ በክዋኔ ጊዜ በተለይ በህብረት ሲያዜሙ በቴኘ ለመቅዳት ስፈልግ ቴፑ አንዳንዶቹ እንዳይጠጋቸው ስላደረጉ የድምፁ መራቅ ቃላቱን ለመለየት አስቸግሮኛል።

በበዓሉ ላይ ስለሚከወኑ፣ በተለይ ቃል ግጥሞችን ከመከወኛው ሰዓት ውጭ ማግኘት አለመቻል ሌላው ችግር ነው። በበዓሉ ላይ ሲቀርቡ ለመሰብሰብ ስሞክር የቦረና አሮሞዎች ዜማዎች አዝማች፣ ሙዚቃዊ ድምፅ የሚበዛባቸው፣ ሲከውኑ ደግሞ አንድ ሰው ቢበዛ ሁለት ስንኝ ብሎ ሌላው ሰው የሚቀበል ስለሆነ በቴኘ ለመቅዳት አመቺ አልነበረም። ከሚዜምበት ጊዜና ቦታ ውጭ እንዲያዜሙ ሲጠየቁ አይመጣልንም በማለታቸው፣ በቂ ቃል ግጥም ለመሰብሰብ አስቸጋሪ ነበር።

1.7. የተወሰዱ መፍትሔዎች

ፎቶግራፍና በቪዲዮ መቀረፅ፣ በቴኘ ድምፃቸውን ማስቀዳት የማይፈልጉትን፣ መረጃውን በቃል እንዲሰጡ በማድረግ፣ በምልከታና በማስታወሻ ብቻ በመውሰድ መረጃዎቹን ማግኘት ተችሏል።

የቃል ግጥሞቹን ከአውዱ ውጭ መከወን ይቸግረናል ያሉትን፣ በማግባባት ሁለት ሦስት ሆነው አብረው እያዜሙ፣ በማቋረጥ ስንኙን እንዲደግሙ በማድረግ እንዲሁም ባህሉን በአግባቡ የሚያውቁ የተማሩ ወጣቶችን፣ በዞኑ በተቋቋመ የኪነት ቡድን ውስጥ የታቀፉትንና በመድረክ ላይ በበዓሉ የሚዘወተሩትን ባህላዊ ዜማ የሚያቀርቡትን በመጠየቅ፣ በትንታኔ የቀረቡትን ቃል ግጥሞች መሰብሰብ ተችሏል።

በዚህ የጥናት ሥራ፣ ቋንቋን መነሻ ያደረጉ ችግሮች አላጋጠሙም። ኬኔት ለፎክሎር ባለሙያዎች ባዘጋጀው የመስክ ሥራ መመሪያ መጽሐፉ እንደጠቆመው የመስክ ሥራ መሠረት ያደረገ አጥኒ፣ የጥናት መረጃ የሚሰበስብበትን አካባቢ ህዝብ ቋንቋ ማወቅ እንደሚጠበቅበት (Kenneth, 1974:31) እንደገለፀው እኔም የቋንቋው ተናጋሪ በመሆኔ በዚህ ረገድ የተከሰተ ችግር የለም።

2. የጥናቱ አካባቢና ሕዝቡ

በዚህ ምዕራፍ ሥር፣ የዞኑ ተፈጥሮአዊ ገፅታ፣ ዞኑን ከአጎራባቾቹ ጋር ለማገናኘትና ለኑሮ አመቺ ለማድረግ የተዘረጉ መሠረተ ልማቶችን፣ የማህበራዊ አገልግሎቶችን፣ የህዝቡን ታሪክና ባህል በሚመለከት ጉልህ ጉልህ ነጥቦች ይጠቀሳሉ።

2.1. የቦረና ዞን መልክዓምድራዊ ገፅታ መሠረተ ልማትና ማህበራዊ አገልግሎቶች

ከኦሮሚያ አስራ ሰባት ዞኖች አንዱ ቦረና ነው። ዞኑ ይህን መጠሪያውን ያገኘው፣ በውስጡ ከሚኖረው የቦረና ኦሮሞ ነው።

የኦሮሚያ ክልል በ1985 ዓ.ም. ሲመሠረት ቦረና ዞን የአሁኑን የጉጂ ዞን አጣምሮ በመያዝ የተዋቀረ ሰፊ ዞን ነበር። በ1995 ዓ.ም. ደግሞ ቦረናና ጉጂ ተለያይተው እንዲደራጁ ተደርጓል። በዚህ በአሁኑ አደረጃጀቱ የቦረና ዞን፣ አበያ፣ ገላና፣ ቡሌ ሆራ፣ ዱግዳደዋ፣ ያቤሎ፣ ተልተሌ፣ አሬሮ፣ ሞያሌና ሚኦ የተባሉ አሥር ወረዳዎችን ይዟል። እንዲሁም 195 የገጠርና 9 የከተማ ቀበሌዎችም አሉት። ያቤሎ የዞኑ መስተዳድር ዋና ከተማ ስትሆን፣ ከአዲስ አበባ ወደ ደቡብ 565 ኪ.ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች።

ቦረና ዞን በስተሰሜን ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ህዝቦች ክልል፣ በሰሜን ምስራቅ በኩል ከጉጂ ዞን፣ በስተደቡብ ከኬንያና ከሱማሌ ክልል፣ እንዲሁም በደቡብ ምስራቅ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ህዝቦች ጋር ይዋሰናል።

2.1.1. መልክዓምድራዊ ገፅታ

የቦረና ዞን፣ ተራራማ፣ ሜዳማና ወጣ ገባ የበዛበት የመሬት አቀማመጥ አለው። ከተራራ ጉኔ፣ መልካ፣ ቱሌም የሚጠቀሱ ናቸው። ከአመት አመት የሚፈሱ ትላልቅ ወንዞች ገናሌ፣ ዳዋና ሰገን ዞኑን አቋርጠው ያልፋሉ። እንዲሁም በእርጥበት ወቅት አገልግሎት የሚሰጡ ምንጮችና ሰው ሠራሽ የውሃ ጉድጓዶች (Elaa) በብዛት ይገኛሉ። (Oromia Bureau of Planing and Economic Development, 2000:250)።

በዞኑ ከፍተኛ የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ደንና ቁጥቋጦ ይገኛል። ከነዚህ ውስጥ ጥብቅ ደንና ለእንስሳት ክብካቤ የተከለለ በያቤሎ ወረዳ ብቻ ይገኛል። ሰው ሠራሽ የመንግሥት ደን ዳዋ፣ አሬሮና ያቤሎ ወረዳዎች ውስጥ ተከልለዋል። በነዚህ የዞኑ የደን አካባቢዎች ዝንጀሮ፣ ቀበሮ፣ አጋዘን፣ አሳማ፣ የሜዳ አህያ አውራሪስ፣ ቀጭኔ፣ አንበሳ፣ ነብር፣ ጅብና ሌሎችም የዱር አራዊቶች ይገኛሉ።

በክርሰ ምድሩም ጥቅም ላይ ያልዋሉ በርካታ የማዕድን አይነቶች አሉ። እስከዛሬ ጥቅም ላይ ውሏል ሊባል የሚችለው በባህላዊ መንገድ እየወጣ ያለው የድሬና የተልተሌ ወረዳ የጨው ማዕድን ብቻ ነው። በዞኑ አብዛኛዎቹ ወረዳዎች ወርቅ፣ አስቤስቶስ፣ ኒኬል፣ ኖራን ጨምሮ የተለያዩ የድንጋይ ማዕድኖች ክምችት እንዳላቸው ከዞኑ ግብርና ልማት ጽ/ቤት የተገኘ መረጃ ይጠቁማል።

የዞኑ ጠቅላላ የመሬት ስፋት 56,000 ስኩዌር ኪሎ ሜትር ሲሆን፣ የዚህ 80 በመቶ ለከብት ርቢ /ለግጦሽ/ የሚውል ነው። ለእርሻ መዋል ይችላል የሚባለው የዞኑ መሬት ደግሞ 1,176,288 ሄክታር ሲሆን፣ እስከ አሁን የታረሰው 131,745 ሄክታር ብቻ ነው።

ከባህር ጠለል በላይ ያለው የዞኑ የመሬት ከፍታ በ500-2500 ሜትር መሀል ሲገኝ፣ የአየር ንብረቱ ደጋ፣ ወይና ደጋና ቆላ ነው። ከፍተኛውን ቦታ የሚይዘው ወይም 70% የሚሆነው ቆላው ነው። አማካይ የአየር ሙቀቱም በ18^{0} c-28^{0}c ይደርሳል።

ዞኑ በዓመት የሚያገኘው የዝናብ መጠን በአማካይ ከ450-650 ሚሊ ሊትር የሚደርስ ሲሆን፣ ይህንንም የሚያገኘው በዓመት ሁለት ጊዜ በሚጥል የዝናብ (ganna) ወቅት ነው። የአካባቢው የክረምት ወቅት ከመጋቢት እስከ ግንቦት ያሉትን ወራት የሚያጠቃልል ሲሆን፣ በዓመት ከሚገኘው ዝናብ 70% ይይዛል። የተቀረው 30% በሁለተኛው የዝናብ ወቅት "Hagayya" ነሐሴ ወር ውስጥ የሚጥለው ካፊያ መሰል የዝናብ አይነት ነው።

2.1.2. መሠረተ ልማትና ማህበራዊ አገልግሎቶች

ለአንድ አካባቢ ምጣኔ ሐብት ዕድገት የመሠረተ ልማትና የማህበራዊ አገልግሎቶች መስፋፋት ወሳኝነት አላቸው። በዞኑ የሦስት ወረዳ ከተሞች፣ ሞያሌ፣ ያቤሎና ቡሌ ሆራ የባንክ አገልግሎት ሲኖራቸው፣ ሰባት ትላልቅ የወረዳ ከተሞችም የሃያ አራት ሰዓት የኤሌክትሪክ አገልግሎት ያገኛሉ። ከአዲስ አበባ ኬንያ የሚዘልቀው ዋናው የአስፋልት መንገድ ከዞኑ ወረዳዎች አባያን፣ ቡሌ ሆራን፣ ዱግዳ ዳዋን፣ ያቤሎን፣ ድሬንና ሞያሌን ያቋርጣል። በአሁኑ ጊዜ የሁሉም ወረዳዎች ዋና ከተሞች ከዞኑ ዋና ከተማ ያቤሎ ጋር የተገናኙ ናቸው።

ከማህበራዊ አገልግሎቶች አንፃር ሲታይ ዞኑ የተወሳሰቡ ችግሮች አሉት። የህዝቡ የተበታተነ አሰፋፈር ለችግሮች መባባስ አንዱ ምክንያት ነው። የህዝቡ ኑሮ በከብት ርቢ ላይ መወሰን ከቦታ ቦታ እንዲዛወሩ አድርጓል። ይህ ደግሞ ለማህበራዊ አገልግሎት

አሰጣጥ አመቺ አለመሆንና ለሥርጭቱ እጥረት ምክንያት እንደሆነ ይነገራል። ለምሳሌ በጤና ዘርፍ ያለውን፣ አገልግሎት ብንመለከት እጅግ በጣም ዝቅተኛ ነው።

ከዞኑ አስተዳደር ጽ/ቤት የተገኘው መረጃ እንደሚያረጋግጠው በዞኑ አንድ ሆስፒታል ብቻ ይገኛል። እርሱም የአስፈላጊ ቁሳቁሶችና የባለሙያ እጥረት ያለው ከመሆኑም በላይ፣ የዞኑ ህዝብ ከሚኖርበት ርቆ ዞኑ መግቢያ ቡሌ ሆራ ወረዳ ውስጥ ይገኛል። አስቸኳይ ህክምና የሚያስፈልጋቸው የጤና ችግር የሚገጥማቸው የሞያሌ፣ የድሬ፣ የተልተሌ፣ የሚአ፣ የዳዋ፣ የአሬሮ ወረዳዎች ነዋሪዎች ለችግር የተጋለጡ ናቸው።

ግማሽ ያህሉ ወረዳዎች የጤና ጣቢያም የላቸውም። ያላቸውም ቢሆኑ በቂ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ባለሙያ የላቸውም። በእንስሳት ጤና አጠባበቅ ረገድም ችግሩ ከፍተኛ ነው (Oromia, Bureau of planning and Economic development,2000:250)።

በትምህርት ዘርፍም ያለው አገልግሎት ተመሳሳይ ነው። የዞኑ ወረዳዎች ያሉዋቸው አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በተለይ የ11ኛና 12ኛ ክፍል ትምህርት የሚሰጡ የሙያና የመሰናዶ ትምህርት ቤት ያላቸው ሞያሌና ያቤሎ ብቻ በመሆናቸው፣ የሌሎች ወረዳዎች አገልግሎቱን ለማግኘት ወደ ሁለቱ ወረዳዎች ከተሞች ሄደው ተከራይተው መማር ግድ ሆኖባቸዋል። ሞልቶላቸው ይህን የሚያደርጉትም ከቁጥር አይገቡም። ይህ መረጃ እስከተሰበሰበበት ጊዜ ድረስ ሚአ፣ ገላናና አሬሮ ወረዳዎች ደግሞ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (9-10) የላቸውም።

ሌላው በዞኑ ተደጋግሞ የሚነሳው ችግር የውሃ እጥረት ነው። ዞኑ የመሬት ላይና የከርሰ ምድር የውሃ እጥረት እንዳለው በጥናት ተረጋግጧል። በጣም የተስፋፉ የእንስሳት በሽታዎች፣ አፈሩ ለእርሻ ሥራ ተስማሚ አለመሆን፣ የግብርና ግብተ ምርቶች ውድነት፣ የገንዘብ እጥረት፣ ኋላ ቀርነትና የመሠረት ልማት እንደሚፈለገው አለመዳረስ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፣ በሌላ መልኩ ሲታይ ግን ዞኑ ከፍተኛ የከብት ሀብት፣ የግጦሽ መሬትና ያልተነካ የከርሰ ምድር ሀብት ክምችት አለው (Oromia, Bureau of planning and Economic development,2000:258) ።

በ1987 ዓ.ም. በተደረገው የቤትና የህዝብ ቆጠራ መረጃ መሠረት የቦረና ህዝብ ብዛት 1,024,082 ሲሆን በየዓመቱ የሚኖረውን የህዝብ ብዛት እድገት ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በ1999 /2007/ የዞኑ የህዝብ ብዛት 1,119,041 ይደርሳል ተብሎ ተገምቷል።

2.2. የህዝቡ ታሪካዊ ዳራ

የኦሮሞን ህዝብ አመጣጥ ወደኋላ ሄደው ያጠኑ የሀገር ውስጥና የውጭ የታሪክ ተመራማሪዎች ሥራ አንዳንዱ አወዛጋቢ ነው። ለምሳሌ ከሀገር ውስጥ አለቃ ታዬ

ገብረማርያምና አለቃ አፅመጊዮርጊስ ገብረ መሲህ ኦሮሞ ከውጭ ፈልሶ ገባ ብለው የፃፉት አንዱ ነው።

ከውጭ ፀሐፍት ደግሞ J.S.Trimingham፣ Enrico Cerrulli፣ I.M.Lewis እና Huntingford የኦሮሞ መነሻ መሬት ሰሜን ሶማሊያ ነው ሲሉ፣ Jamece Bruce ደግሞ በአሁኗ ሱዳን ሪፐብሊክ ሲናር የተባለ ቦታ ነው ይላል። ሌላው የአጥኚ ቡድን Herberts Lewis፣ Eike Haberland፣ Urlich Braukumber መሀመድ ሀሰን የመሳሰሉትን የሚያጠቃልለው፣ የኦሮሞ መነሻ ቦታ በአሁኗ ደቡብ ኢትዮጵያ በተለይ ባሌና ሲዳሞ በሚባሉ የቀድሞ ጠቅላይ ግዛቶች ነው ይላሉ። (የኦሮሞ ታሪክ እስከ አሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን፣ 1996:48-49)

በጥንታዊ ኩሽ ህዝብ ታሪክ ላይ ሰፊ ምርምር ያደረጉትን Ehret Chiristopher ሀሳብ በማጠናከር Margery Perham Paultshak የተባሉት ደግሞ፣ ኦሮሞ በሰሜን ምሥራቅ አፍሪካ ሰፍሮ የነበረው ኩሽ አንዱ አካል መሆኑንና አሰፋፈሩ ሰሜን ኢትዮጵያን እንደሚጨምር፣ ከዚያ ወደተለያዩ አቅጣጫ መሠራጨት እንደቻለ አስፍረዋል። (የኦሮሞ ታሪክ እስከ አሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን፣ 1996:50)

ወደኋላ ላይ የመጡ የታሪክ ተመራማሪዎች ሥራዎች፣ ከህዝቡ ሥነቃልና ፎክሎር የተገኙ መረጃዎች፣ አሁንም በህይወት ያሉ፣ የህዝቡን ታሪክ ከአያት፣ ቅድመ አያት ሲቀባበሉ እዚህ ያደረሱት አዛውንቶች፣ ኦሮሞ በፍልሰት እንዳልመጣ፣ ነባር ህዝብ መሆኑን ይጠቅሳሉ።

የታሪክ ተመራማሪው አሰፋ ጃለታ፣ ሪቻርድ ግሪንፊልድን ጠቅሶ ባቀረበው ጽሑፍ፣

> ኦሮሞዎች ከኤገርያ ፈልሰው መጡ፣ ከታንጋኒካ በጠላቶቻቸው ተገፍተው በኬንያ በኩል አድርገው ኢትዮጵያ ገቡ ይበሉ እንጂ፣ ... ቋንቋቸው፣ ባህላዊ አኗኗራቸውና የሚተዳደሩበት ሥርዓትና ታሪካቸው ከአፍሪካ ቀንድ አካባቢ የምሥራቅ ኩሽቲክ ቋንቋ ተናጋሪዎች ጋር የተቀራረበ ነው። እነዚህ የምስራቅ ኩሽቴክ ቋንቋ ተናጋሪዎች በታሪክ፣ በመልከዓምድር፣ በባህል፣ በቋንቋ የተያያዙ ህዝቦች ናቸው። ኦሮሞም የነዚሁ የአፍሪካ ቀንድ ነዋሪ ህዝቦች አካል ነው (Asafa, 1993 :17)።

በማለት የኦሮሞን ህዝብ ነባርነት አፅንዖት ሰጥቶ አቅርቧል።

መሀመድ ሀሰንም የተለያዩ በኦሮሞ ታሪክ ላይ ጥናት ያደረጉትን መረጃዎች ዋቢ በማድረግ ኦሮሞ ከውጭ በፍልሰት የመጣ ሳይሆን ከሀገሪቷ ጥንታዊ ህዝቦች አንዱ መሆኑንና ጥንታዊ መኖሪያው አሁን ባሌ ተብሎ የሚታወቀው አካባቢ እንደሆነ፣ የህዝቡ አፋዊ ታሪክም ይህንኑ እንደሚያረጋግጥ አስፍሯል (Mohammed Hassen, 1994:14)።

የኦሮሞ ታላቅ ተብሎ የሚታመንበት የቦረና ኦሮሞ አባላትም አሁን ሰፍረው የሚገኙበትን የጉጂንና የቦረናን ሰሜናዊ ምሥራቁን ክፍል መገኛቸው አድርገው

ይገልፃሉ። "ከአያት ቅድመ አያቶቻችን ሲነገር የቆየው ቦረና በቱሉ ነመደሪ አካባቢ ይኖ እንደነበር፣ ከዚያም እየተንቀሳቀሰ በዲሬ፣ በሊበን አካባቢ መሥፈር እንደጀመረና የገዳ ሥርዓቱ የተለያዩ በዓላት በዚሁ አካባቢ ይከበሩ እንደነበር ነው (ቦርቦር ቡሌ፣ ቃለመጠይቅ ሚያዝያ 24 ቀን 1999 ዓ.ም. ካሉ ጂሌ፣ ቃለመጠይቅ ሰኔ 12 ቀን 1999 ዓ .ም. ያቤሌ)።

በአሁኑ ጊዜ በቦረና ዞን የሚኖሩት በብዛት የቦረናና የጉጂ ኦሮሞዎች ናቸው። የቦረና ኦሮሞዎች፣ የቡሌ ሆራን ወረዳ ምዕራባዊ ክፍል ይዞ እስከ ኬንያ ጠረፍ በሚዘልቀው የዞኑ ቆላማ አካባቢዎች የሠፈሩ ሲሆኑ፣ የጉጂ ኦሮሞዎች ደግሞ በዞኑ ደጋና ወይናደጋ አካባቢዎች ይኖራሉ። (Tadhi Liben)።

ቦረና በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል። ሰቦና ጎና፣ እነዚህ ዋና ዋና ክፍሎች በመላው ቦረና ውስጥ የሚኖሩ ሲሆኑ፣ በገዳ ሥርዓት ውስጥ እኩል ቦታ አላቸው (ቦርቦር ቡሌ፣ ቃለመጠይቅ ሚያዝያ 24 ቀን 1999 ዓ.ም.፤ Asmarom: 1973:11)። ሁለቱ ክፍሎች እንደገና በንዑሳን ክፍሎች ይከፈላሉ።
አከፋፈላቸው የሚከተለውን ይመስላል።



(ቦርቦር ቡሌ ቃለመጠይቅ ሚያዝያ 24 ቀን 1999፣ Gammachu, 2002:35)

ሰቦ ሥር ያሉትም ንዑሳን ክፍሎች እንደ ጎናው፣ ሀሮሬማና ፉለሌ በመባል እንደገና ይከፋፈላሉ። ይህ ክፍፍል "mana" የሚለው ደረጃ ላይ ይገኛል። ከዚህ በታች ሲከፋፈል ደግሞ "Balbala" ወደሚለው ይወርዳል።

በ "mana" ደረጃ የሦስቱ ሰቦ ንዑሳን ክፍሎች፣ ዲገሉ ስድስት፣ መጣሪ ሰባት ከረዩ ደግሞ ሰላሳ ዘጠኝ ይይዛል። በቦረና ኦሮሞ ባህል ላይ ጥናት ያደረጉት እንደሚያቀርቡትና የጥናት አጋሬ (ቦርቦር ቡሌ) እንደሚያረጋጡት ይህ ክፍፍል በተለያዩ ማህበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ የህገዙ እንቅስቃሴ ውስጥ ከፍተኛ ቦታና ጠቀሜታ አለው።

2.2.1. ቋንቋ

ኦሮሞ አንድ የጋራ ቋንቋና ባህል ያለው ህዝብ ነው። ኦሮሞ የሚናገረው "Afaan Oromoo" የምስራቅ ኩሽ ቤተሰብ ከሆኑ አርባ የሚያህሉ ቋንቋዎች ውስጥ ይመደባል። ቦረናን ጨምሮ ሁሉም የኦሮሞ ህዝብ የአንድ ቋንቋ የተቀራረቡ ዘዬዎች (dialects) ተናጋሪ ነው (Asmarom: 1973:7)። በነዚህ ዘዬዎች ውስጥ ያሉ ቃላት የፍች ልዩነት የቋንቋውን ስፋት የሚያመለክቱ እንጂ አለመግባባትን የሚያስከትሉ አይደሉም።

የኦሮሞ ቋንቋ በሀገር ውስጥ ለዘመናት የንግግር ቋንቋ ብቻ ሆኖ ቆይቷል። ከበደ መርጊያ በ1975 ዓ.ም. "ሬዲዮ ድራማ በኢትዮጵያ" በሚል ርዕስ ለመጀመሪያ ዲግሪው ማሚያ ጽሑፍ ሲያዘጋጅ ስለሬዲዮ ስርጨት በጠቀሰው መረጃ ውስጥ ኦሮምኛ ቋንቋ በጣልያን ወረራ ወቅት ጣሊያኖች ለቅስቀሳ ሥራ በሬዲዮ ያስተላልፉበት እንደነበር ተገልጿልያ። በደርግ ዘመን በመንግሥት ደረጃ፣ በሳባ ፊደል ለመሠረተ ትምህርት መስጫ ይዘጋጁ የነበሩ የኦሮምኛ ጽሑፎች ታትመው ይሠራጩ ነበር። በሪሣ፣ ሳምንታዊ ጋዜጣም በዚሁ ፊደል ይታተም ነበር።

ከ1983 ወዲህ ለቋንቋው የላቲን ፊደል ተመርጦ ቋንቋው በሚነገርበትና በሚደመጥበት ሁኔታ እንዲዳፍ ከመደረጉም በተጨማሪ የኦሮሚያ ክልል የሥራ፣ የትምህርት፣ የምርምር እንዲሁም በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የትምህርት ዘርፍና ማስተማሪያ ቋንቋ ሆኖ እንዲያገለግል ተደርጓል። በርካታ መዝገበ ቃላት፣ የሥነቃልና የቋንቋ ጥናት ጽሑፎች፣ የትምህርት መማሪያ መጻሕፍት፣ የሥነጽሑፍ ሥራ ውጤቶች የተለየዩ ሳይንሳዊ የጥናት ሥራዎች እየተዘጋጁበት በመቅረብ ላይ ይገኛሉ።

2.2.2. ጋብቻ

በቦረና ጋብቻ የሚወሰነው የዘር ግንኙነት /ዝምድና/ መኖር አለመኖር ተጠንቶ ከተለየ በኋላ ነው። በቦረና ሁለቱ ዋና ዋና ክፍሎች፣ ሰቦና ጎና ሊጋቡ ይችላሉ።

በሌላ መልኩ ግን ጎና ጎናን፣ ሰቦ ሰቦን አያገባም። ሰቦ ለሰቦ ወንድምና እህት፣ ሰቦ ለጎና ግን አማች ነው ሊጋቡ ይችላሉ (Gammachuu:2002:35)።

ጋብቻን በተመለከተ፣ በተለይ ሰቦ ሰቦን አያገባም ጎና ጎናን አያገባም የሚለው የተደነገገው፣ "Boru Kallachaa" የተባለ ሰው አባ ገዳ ሆኖ በሚያስተዳድርበት ጊዜ ሲሆን፣ ከሌሎች ህጎች ጋር እንደገና እንዲፀና ተደርጎ ተወስኖ እስከ ዛሬ የዘለቀው ይህ የጋብቻ ህግ በ31ኛው አባገዳ፣ በ"Daawwee Gabboo Yaayyaa" የአስተዳደር ዘመን (1696-1704) ነው። (ቦርቦር ቡሌ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሚያዝያ 24 ቀን 1999)።

ይህ የጋብቻ ህግ፣ ቃሉ /መንፈሳዊ አባት/ ጋ ሲደርስ ይፈርሳል። ይኸውም የሰቦ አባል የሆነው የከረዩ ቃሉ የሰቦ ንዑስ ክፍል የሆነውን የመጣሪ ሜታን ሴት ልጅ ያገባል (Tadhi:2007:26)።

በቦረና የተለመደውና ተቀባይነት ያለው ጋብቻ፣ ወንዱ ትሆነኛለች ብሎ ያጫትን ሴት፣ ቤተሰቦቿ ተስማምተው የሚፈፀመው የጋብቻ አይነት ነው። የጋብቻው አከዋወን ረዥም ሂደት የሚጠይቅ፣ የወንዱን ትዕግሥት የሚፈታተን ነው። አንድ ወንድ ለጋብቻ የጠየቃትን ሴት ቤተሰቦቿ ሰጥተንሃል እስከሚሉ ዓመትና ከዓመት በላይ ሊቆይ ይችላል። ስጦታ ይዞ መመላለሱም አይቋረጥም። በዚህ የጋብቻ አፈፃፀም ሂደት በታጨዋ በኩል የሚደረግ ተሳትፎ የለም። ግን ሊያገባት ያሰበውን ሰው የማትፈልገው ከሆነ፣ አልፈልገውም የማለት መብቷ የተጠበቀ ነው። አትገደድም (ካሉ ጂሎ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሰኔ 12 ቀን 1999፤ Asmarom: 1973:23)።

የቦረና የጋብቻ ሥርዓት ሁለቱን ቤተሰብ ከማገናኘቱም ባሻገር፣ ለሴቷ ቤተሰብ የምጣኔ ሐብት ግንባታ ከፍተኛ ቦታ አለው። በተለይ ብዙ ሴት ልጆች ያለው ቤተሰብ በያንዳንዷ ሴት ልጅ "Qaraxaafi Gabbaraa" ተብሎ እንደ ጥሎሽ የሚሰጡት አራት አራት ከብቶች ይረከባል። በሌላ መልኩ ደግሞ ሙሽሪቷም አግብታ ከሄደች በኋላ ወደቤተሰቦቿ ተመልሳ መጥታ፣ ወደ እራሷ ቤት ስትሸኝ ከቤተሰቦቿ የሚበረከትላት ስጦታ አለ። ወላጆቿ፣ ወንድሞቿ፣ አጎቶቿ፣ አክስቶቿ የቤት ቁሳቁስ፣ ፍየሎች፣ በጎችና ከብቶች እንደአቅማቸው ይሰጧታል።

በቦረና አሮሞ ሴት ልጅ የኔነው የምትለው ሀብት ይህ ቤተሰቦቿ ከጋብቻ በኋላ የሚሰጡዋት ስጦታ ብቻ ነው። ቀደም ሲል ከቤተሰቦቿ ጋር በነበረች ጊዜ በስም ስያሜዋ (moggaasaa)ና በተለያየ ምክንያት የተሰጣት ከብት ወይም ቁሳቁስ ስሙ እንጂ፣ ንብረትነቱ የቤተሰቦቿ ነው። (ቦርቦር ቡሌ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሚያዝያ 24 ቀን 1999)።

በሌላ መልኩ ወንድ ልጅ ታላቅም ሆነ ታናሽ በስም ስያሜው (Gubbisaa/moggaasaa) በዓል ላይ እንዲሁም የተለያየ ሥራ ሠርቶ የሚያገኛቸው

ስጦታዎችን አግበቶ ሲወጣ ከቤተሰቡ ይካፈላል። በተለይ ታላቅ ልጅ አባቱ ሲሞቱ የአባቱን የግል ንብረት፣ መሣሪያ፣ ፈረስና የመሳሰሉትን የመውረስ፣ ቤተሰቡን የማስተዳደር ሙሉ መብት አለው (ቦርቦር ቡሌ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሚያዝያ 24 ቀን 1999)።

በቦረና የጋብቻ ባህል ከአንድ ሚስት በላይ ማግባት የተለመደ ነው። የመጀመሪያ ሚስት ያላገባች ድንግል መሆን አለባት። የመጀመሪያ በመሆኗም ታላቅ ናት። መጀመሪያ ላይ የወለደችው ወንድ ልጅ ከሆነ የስም ስያሜ በዓል ይዘጋጅለታል (Gubbisaa)። ለአባቱም ለዘሩ ታላቅ ይሆናል። የመጀመሪያዋ ሚስት ሳትወልድ ሁለተኛዋ ወይም ሦስተኛዋ ወንድ ልጅ ብትወልድ፣ የስም ስያሜ በዓሉን የምታዘጋጀው የመጀመሪያዋ ሚስት ናት። በልጁም ስም የምትጠራዋ ታላቋ ሚስት ናት።

ታላቋ ሚስት ዘግይታ ወንድ ልጅ ብትወልድ ልጇ ለዘሩ ታላቅ ይሆናል። ሁለቱም ወንዶች ልጆች በየራሳቸው ታላቅ ናቸው። ለመጀመሪያ ጊዜ ከሁለተኛዋ ወይም ከሦስተኛዋ ሚስት የተወለደው የአባት ታላቅ ልጅ ነው። በሁለተኛ ደረጃ ከመጀመሪያዋ ሚስት የተወለደው ደግሞ የዘር ታላቅ ልጅ ይሆናል። የታላቅ ሚስት ታላቅ ልጅ በመሆኑ በዘሩ ዘንድ ከፍተኛ ቦታ አለው። ለእናቱም ክብር ያጎናፅፉታል።

በውርስ ጊዜ የመጀመሪያው የአባት ወንድ ልጅ የአባቱን የግል ንብረት የተባሉትን ሲወርስ፣ በሁለተኛ ደረጃ ከመጀመሪያ ሚስት የተወለደው ደግሞ የወገኑን ንብረት ማለትም አባቱ ከአባቱ የወረሰውን የአያቶችን ንብረት ይወርሳል (ጃተኒ ዲዳ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሚያዝያ 22 ቀን 1999)።

በቦረና ለሴት ልጅ ህይወት ስምረት ልጅ መውለድ ወሳኝ ነው። በመሆኑም ሴቶች ከምንም ነገር በላይ ፈጣሪያቸውን የሚለምኑት ልጅ እንዲሰጣቸው ነው። መጀመሪያ ወንድ ልጅ የወለደች ደግሞ በማህበረሰቡ የላቀ ቦታ ስላላት ፀሎቷ የመጀመሪያ ልጇ ወንድ እንዲሆን ነው።

ሌላው ሳይጠቀስ የማያልፈው፣ በቦረና የጋብቻ ዋና ቁም ነገሩ፣ ልጅ ለመውለድ፣ የዘር ሀረግ መስመሩን ጠብቆ እንዲቀጥል ማድረግ እንጂ በያታዊ ግንኙነቱ በባለትዳሮቹ መሀከል ሊኖር ስለሚገባ መግባባት ወይም ፍቅር ይህን ያህል ቦታ የሚሰጠው አይደለም። ካልተግባቡ ሌላ አማራጭ አለ።

አንዲት አግብታ በትዳር ያለች ሴት ሌላ ፍቅረኛ "gaarayyuu" መያዝ ትችላለች። የተለመደና በግልፅ የሚሠራበትም ነው (Asmarom, 1973:18-19)። አሁን አሁን ከኤች.አይ.ቪ ኤድስ ጋር በተያያዘ ሁኔታ በባለሙያዎች ትምህርት እየተሰጠ

ልማዱ እንዲቀር ግፊት እየተደረገ ነው። ሆኖም ባህል ሆኖ የቆየ ድርጊት ስለሆነ አሁንም በተግባር ላይ እንዳለ ይነገራል።

ባለትዳሯ ሴት፣ ከትዳር ጓደኛዋ ውጭ ካለው ፍቅረኛዋ ጋር ስትሆን ለባልየው የሚገለፅበት አኳኋን አለ። ፍቅረኛው ይዞት የሚሄደውን በትር በር አስደግፎ ይገባል። ባልየው ያንን እያየ ወደ ቤት አይዘልቅም። ሌሎች ሚስቶች ካሉት ወደነርሱ ይሄዳል። ከሌለው እርሱም ተመሳሳይ ተግባር ይፈጽማል። /ሌላ ባለትዳር ጓደኛ/ ይይዛል እንጂ፣ ለምን ሆነ ብሎ ከሚስቱ አይጋጭም። በዚህ መሀል ጽንስ ተፈጥሮ የሚወለደው ልጅ የጋረዩው (የፍቅረኛዋ) ቢሆን፣ እንደ ቀድሞዎቹ ልጆች በህጋዊው ባል ይጠራል። የኔ ልጅ አይደለም የሚል ተቃውሞም አይቀርብም።

በፊት በፊት የቦረና ባልና ሚስት አይፋቱም። በመሀከላቸው ችግር ተፈጥሮ አንድ ቤት አብሮ መኖር ካልቻሉ እንኳ ሃዩዎች ጉዳያቸውን አይተው ፍቺ ሳይፈፀም የምትተዳደርበት ሀብት /ከብት/ ተሰጥቷት ተለያይተው እንዲኖሩ ያደርጋሉ። /ባልና ሚስትነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ/ በዚህን ጊዜ ሴቷ የፈለጋትን ፍቅረኛ ይዛ መኖር ትችላለች። በአሁኑ ጊዜ ግን የባህሉ ህጐች እየተጣሱ፣ ሴቷን ከቤት አስወጥቶ ፍቺ መፈፀም እየታየ ነው (ቦርቦር ቡሌ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሚያዝያ 24 ቀን 1999)።

2.2.3. ባህላዊ የጊዜ አቆጣጠር

የተለያዩ የታሪክ መዛግብት ኦሮሞ የራሱ የሆነ የዘመን አቆጣጠር እንዳለው ያትታሉ። ይህ የዘመን አቆጣጠር (calendar) በቦረና ኦሮሞዎች ዘንድ አሁንም ተግባራዊ ነው። በዚህ የቦረና የጊዜ መቁጠሪያ ዓመቱ አሥራ ሁለት ወራት ሲኖሩት፣ ወራቱ በአማካይ 29 እና 30 ቀናትን ይይዛሉ። የአመቱ የመጀመሪያ ወር “Abaraasa” የሚባለው ሲሆን፣ ይህ ወር ከአውሮፓውያን የመጀመሪያ ወር ጋር ይገጣጠማል። /ወንደሰን ተስፋዬ፣ 1991፣3/።

በዚህ የቦረና የቀን አቆጣጠር ዘዴ ውስጥ ሳምንት የሚባል ነገር የለም። የሚታወቁት በየወራቱ ያሉት 27 የተለያየ ስም ያላቸው በዓላት ናቸው (Gada Melba: 1988: 22)። የመጀመሪያው ቀን “Areerrii duraa” ፣ ተከታዩ፣ “Areerrii balloo” ፣ “Addulaa duraa” ፣ “Addulaa Balloo” ፣ “Garba duraa” ፣ “Garba Balloo”፣ “Bitaa duraa”፣ እያለ ይቀጥላል። እነዚህ ቀናት የየራሳቸው ፍች አላቸው። ለምሳሌ “Areerrii”፣ መሬት የተፈጠረበት ዕለት ነው ይባላል። “Aduulaa”፣ ፀሐይ የተፈጠረችበት፣ “Garba” ሰው የተፈጠረበት፣ “Bitaa” ጦርነት የሚታወጅበት ቀን ነው ይላሉ። ሌሎችም እንዲሁ የተለያዩ ነገሮች የተከሰቱባቸው ቀናት ናቸው። ከበዓላቱ ውስጥ የስም ስያሜ፣ የጋብቻና

የገዳ በዓላት የመሳሰሉ ትላልቅ በዓላት የማይከወኑባቸው ጥሩ ገድ የላቸውም የሚባሉ "Bitaa" የተሰኙ በዓላት ቀናት ናቸው (ወንደሰን ተስፋዬ 1991፣3)።

እነዚህ ጥሩና መጥፎ ገድ አላቸው የሚባሉት ቀናት "Ayyaantuu" በሚባሉ በተፈጥሮአቸው ልዩ ተሰጥኦ አላቸው፣ ይገለፅላቸዋል ተብሎ በሚታመንባቸው ሰዎች ተለይተው ይታወቃሉ። በዓላቱ በኮከብ ቆጠራ የሚደረስባቸው ናቸው። ይህን ገድ የማየት ሂደት ቦረናዎች "faroo" ይሉታል። ሲተርቱም "bara faroon tolte faarris, faaruunis ni tola" ፣ ይላሉ። አማርኛ ትርጉሙ፣ "ገዱ ጥሩ የሆነ ዘመን ሁኔታው፣ መዝሙሩ ሁሉ /ምስጋናውም/ ጥሩ ይሆናል" ማለት ነው። ገዱ ጥሩ የሆነ ዘመን ሁኔታዎች የተመቻቹበት የደስታና የፈንጠዝያ ጊዜ ይሆናል እንደማለት ነው። ስለዚህ ቦረናዎች አንድ ትልቅ ነገር ለመሥራት ሲተልሙ ወደሥራው ከመግባታቸው አስቀድመው "faroo" (ገዱ) ምን እንደሆነ ማወቅ ይሻሉ። የገዱን ምስጢር ለመለየትም ልዩ ተሰጥኦ ወዳላቸው Ayyaantuu ይሄዳሉ (ጃተኒ ዲዳ፣ ቃለ መጠይቅ ሚያዝያ 22 ቀን 1999)።

ከዚሁ ከጊዜ አቆጣጠር ጋር በተያያዘ የዓመቱ ወቅቶችም ተለይተው ይታወቃሉ። እነዚህ ወቅቶች አራት ናቸው። እነርሱም፣

1. ክረምት (Ganna) ረዥም የዝናብ ወቅት ነው። ከመጋቢት እስከ ግንቦት ይቆያል።
2. ቀዝቃዛማና እርጥብ አየር፣ አነስተኛ ካፊያ ያለበት (Adolessa)፣ ከሰኔ እስከ ነሐሴ ያለውን ጊዜ ይይዛል።
3. አጠር ያለ የዝናብ ወቅት (Hagayya)፣ ከመስከረም እስከ ህዳር ይዘልቃል።
4. ደረቅ ወቅት (Bona) ሞቃት፣ ነፋሻማና አቧራ የሚበዛበት ሲሆን፣ ከታህሣሥ እስከ የካቲት ያለውን ጊዜ ይሸፍናል።

ከነዚህ ወቅቶች ውስጥ ከፍተኛ በዓላት፣ እንደ ልጅ ስያሜ፣ የገዳ፣ የጋብቻ በዓላት የመሳሰሉት በብዛት የሚከወኑት የክረምቱ ወቅት ማብቂያ ግንቦት ወር መጨረሻ ጀምሮ ባሉት ጊዜያት ውስጥ እስከ ሁለተኛው ወቅት (Adolessa) ነው። ምክንያቱም፣ በዚህን ጊዜ ዝናብ ዘንቦ አባርቷል። በቂ ውሃ፣ ሣርና ወተት አለ። አርብቶ አደሩ ውሃና ሣር ፍለጋ ርቆ አይሄድም፣ የሚያርሰውም ሥራውን አጠናቆ ውጤት የሚጠበቅበት ጊዜ ነው። በሥራ የመጠመዱም ሁኔታ እንዲሁ የሚቃለልበት ወቅት በመሆኑ አመቺ ጊዜ ነው። ለዚህ ነው በየዓመቱ በነዚህ ወራት ትላልቅ በዓላት በሰፊው የሚከበሩት (ጃተኒ ዲዳ፣ ቃለ መጠይቅ ሚያዝያ 22 ቀን 1999)።

2.2.4. ገዳ

ገዳ የኦሮሞ ህዝብ ከጥንት ጀምሮ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ህይወቱን ይመራበት የነበረ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ነው። የገዳ ሥርዓት በ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ተግባራዊ መደረግ እንደጀመረ የሚገልፁ መረጃዎች አሉ። በቃል ያሉት መረጃዎች ደግሞ ከሚታወቁት 69 የገዳ የአስተዳደር ዘመናት (69x8=536ዓመታት) በፊት 25 ያህሉ ተግባራዊ ሥራቸውን ከውነው ማለፋቸውን ይገልፃሉ። ይህ ማለት የገዳ ሥርዓት በ12ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አካባቢ ኦሮሞዎች ይተዳደሩበት እንደነበረ የሚገልፅ ነው። በጽሑፍ ያለው ማስረጃ እስከ ዛሬ 69 የገዳ የአስተዳደር ዘመናት መቆጠራቸውን ሲያቀርብ ከ1456-1464 የቆየውን የገደዮ ገልገሎን የገዳ ዘመንን መነሻ አድርጎ ነው (Tadhi, 2007:3)።

በሥርዓቱ በየስምንት ዓመቱ ሥልጣን እየተረካከቡ ህዝቡን የሚያስተዳድሩ አምስት የገዳ ክፍሎች (ፓርቲዎች) ናቸው። እነዚህ አምስት ፓርቲዎች በተለያዩ የኦሮሚያ ዞኖች፣

1. ሆረታ/ሜልባ (Horata/Melba)
2. ሚቺሌ/ሙደና (Michillee/Muudana)
3. ዱሎ/ኪሎሌ (Duuloo/Kiilolee)
4. ሮበሌ/ሰቀ (Roobalee/Sabaqa)
5. ቢርመጂ/አሉአደ (Birmajii/Alu'ada)

(Mahamaad Usmaan, Kallacha 9/6/99)

እየተባሉ የሚጠሩ ሲሆን፣ በቦረና ተለይቶ የሚታወቀው የመጀመሪያዎቹ በየስምንት ዓመት ስልጣን እየተቀባበሉ ባለፉት አምስት አባገዳዎች ስም ነው። እነርሱም ቦሩ ገልማ፣ መዳ ገልማ፣ ሊበን ጀልዴሣ፣ አዲ ጋዮና አሬሮ ጌዶ ናቸው። በየአስተዳደር ዘመኑ ፓርቲውን የሚመሩ ዋናና ረዳት አባ ገዳዎች አሉ።

የገዳ ሥርዓት በአሁኑ ጊዜ በቦረናና በጉጂ እንደ ጥንቱ በተግባር ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ በምሥራቅ፣ በደቡብ ምዕራብና በምዕራብ ሸዋ ገጠሩ ክፍል ደግሞ የገዳ ሥርዓት አንዳንድ ህጎች ብቻ ከዘመናዊው ህግ ጎን ለጎን እያገለገሉ ይገኛሉ (Tadhi, 2007:26)።

በቦረና ህዝቡን የሚያስተዳድረው ገዳ በሦስት ይከፈላል። የመጀመሪያውና ህዝቡን በዋናነት የማያስተዳድረው አርቦራ ገዳ (Gadaa Arbooraa) የተባለው ነው። ሌሎች ሁለት ገዳዎች ደግሞ የዚህ የዋናው ገዳ ቅርንጫፎች /አካል/ ናቸው። እነርሱም በንዑሳን ጎሳዎች ስም የሚጠሩ የሀወጡና የኮሌ ገዳ ናቸው። ሁለቱ ቅርንጫፎች ተጣምረው ኮንቶማ ገዳ (Gadaa Kontomaa) ይባላሉ። ሦስቱም አንዳንድ አባገዳና ረዳት /ኤክስፐርት/ አላቸው።

በአንድነት ስድስቱ የቦረና ገዳ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች አዱላ "Aduulaa" በመባል ይታወቃሉ (ቦርቦር ቡሌ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሚያዝያ 24 ቀን 1999)።

የገዳ ሥርዓቱ የሚከናወንባቸው ደንቦችና መመሪያዎች በየስምንት ዓመት ለወር ያህል በሚቆይ ጉሚ ጋዮ ጉባኤ ላይ ቀርበው የተደነገጉ ናቸው። አሁንም ተግባራዊነታቸው በዚሁ ጉባኤ ላይ እየቀረበ ይገመገማል። ሌሎች የየዕለት ጉዳዮችና ችግሮች ደግሞ በአስቸኳይ ስብሰባዎች (kora) ላይ ቀርበው ውሳኔ ያገኛሉ። ጉሚ ጋዮ የሚለውን ስያሜ ያገኘው፣ ጉባኤው ከሚካሔድበት ዲሬ ወረዳ ጋዮ ከተባለው ቦታ ነው። ጉሚ "Gumii" ማለት ጉባኤ ማለት ነው። የጉባኤ ጉዳይ ከተነሳ ቦረና ከጉሚ ጋዮ ሌላ ሌሎችም ተመሳሳይ ጉዳዮች የሚታዩባቸው ከጋዮ ርቀው ያሉት በሊበን ወረዳ የሚኖሩ ቦረናዎች የሚገለገሉባቸው ጉሚ ዲቤ ኤልዶሎ (Gumii Dibbee Eeldaloo)ና የሞያሌ ወረዳ ቦረናዎች የሚገናኙበት ጉሚ ሰርቾ ለዩ (Gumii Serichoo layyuu)፣ ሰምጵር በለል (Simphir balal) የሚባሉ ነበሩ። እነዚህ በአሁኑ ጊዜ አገልግሎት አይሰጡም። ጉሚ ጋዮ የቦረና ኦሮሞ ብቻ፣ ጉሚ ዲቤ ኤልዶሎ ኦሮሞ የሆነ ሁሉ፣ ጉሚ ሰርቾ የቦረና የአስቸኳይ ጊዜ ስብሰባ የሚቀመጥበት፣ ጉሚ ሰምጵር በለል ደግሞ ተመሳሳይ ባህል ያላቸው የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች ይገናኙባቸው የነበሩ ናቸው። እነዚህ ጉባኤዎች አገልግሎት ያቆሙት የህገ-መንግስቱ የመተዳደሪያ ሥርዓት በምኒልክ ዘመን እንዲደናቀፍ ከተደረገ በኋላ ቀደም ሲል የነበረው ጠንካራ አንድነት መቀጠል ስላልቻለ ነው (ቦርቦር ቡሌ ቃለመጠይቅ፣ ሚያዝያ 24 ቀን 1999 እና ሰለሞን ጎዳና ቃለመጠይቅ፣ ሰኔ 21 ቀን 1999)።

ጉባኤዎቹ በሥርዓቱ ለፖለቲካዊ አስተዳደሩ ብቻ ሳይሆን ለተለያዩ ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊ ጉዳዮች፣ በተለይ ለተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና አጠቃቀም፣ ለችግር ወቅት የመረዳጃ ህጐች ተደንግገው የተቀመጡ ህጎችን በመመርኮዝ ህዝቡ በቀላሉ ተግባብቶ ኑሮውን የሚያራምድባቸው፣ ችግሮቹን የሚፈታባቸውን እያነሳ የሚወያይባቸውና የሚወስንባቸው ናቸው።

ህዝቡ የሚተጋገዝበት የተለያዩ ደንቦች አሉት። በተለይ "ቡሳ ጎንፋ" (Buusaa-Gonfaa) በሚል ስም የሚታወቀው የመረዳጃ ሥርዓት የህዝቡን አንድነት አጉልቶ የሚያሳይ ነው። ከቦረና አባላት መሀከል ችግር የገጠማቸው ካሉ ይረዳዳሉ። ይህ የመረዳዳት ባህል ህግ እንደሌሎቹ የባህል ጉዳዮች ህግ የተበጀለት በ31ኛው አባ ገዳ፣ በዳዌ ጎቦ ዘመን ነው። የቦረና ኦሮሞ ሆኖ የተቸገረን የማይረዳ ሰው ይህን ህግ ተላልፏል ተብሎ ይወገዛል። ለምሳሌ አንድ ሰው በድንገተኛ አደጋ አካሉ ከጎደለ፣ ችግር

ከደረሰበት የመርዳት የመንከባከብ ግዴታ አለባቸው (ጃተኒ ዲዳ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሚያዝያ 22 ቀን 1999)።

እያንዳንዱ አባል በዕድሜ ገደብ በተቀመጠለት የሥርዓቱ ደንቦች የየራሱ የሆነ የሥራ ድርሻና ማህበራዊ ደረጃ (social status) አለው። ቦርቦር ቡሌ እንደገለፁት እነዚህ በዕድሜ የሚከፋፈሉ ደረጃዎች ከህፃንነት ዕድሜ ይነሳሉ።

የመጀመሪያው ደበሌ (Dabbale) ነው። እነዚህ በዚህ ስም የሚጠሩ ወንዶች ህፃናት ከልደት እስከ ስምንት ዓመት ዕድሜ ያላቸው ሲሆኑ፣ በገዳ ሥርዓቱ በሥልጣን ላይ ያሉትን የአባ ገዳ ልጆችን ብቻ ይይዛል። እነዚህ ልጆች ተለይተው የሚታወቁት በፀጉር አሠራራቸው (Guduru) ነው። ፀጉራቸው እስከትከሻቸው ወርዶ ሊያድግ ይችላል፣ አይቆረጥም፣ በዛጐል እንዲያጌጥም ይደረጋል። ደበሌዎች ከፍተኛ እንክብካቤ ይደረግላቸዋል። ከእናታቸውና ከመንደራቸው ርቀው አይሄዱም። ደበሌዎች ፈጣሪና ሰውን የማገናኘት ሃይል ያላቸው ቅዱስ ፍጡሮች ናቸው ተብሎም ይታመንባቸዋል።

ሁለተኛው ትንሹ ጋሜ (Gaammee diqqo) ነው። በዚህ ሥር የሚመደቡት ዕድሜያቸው ከ8-16 ዓመት የሆኑት ናቸው። እዚህ ደረጃ ውስጥ የሚገቡት ደበሌ የሚባሉት የ"Ilmaan Kormaa" በገዳ ሥርዓቱ መሥመር ላይ (ሥልጣን ላይ) ያሉት (Active Gada members) ልጆች ከሆኑ፣ ኑራ (Nura) በተባለ የክብር ቦታ ሄደው ስም ተሰይሞላቸው ጋሜ ይሆናሉ። ከገዳ የጊዜ ቀመር ውጭ የተወለዱ "Ilmaan jaarsaa" ከሆኑ ግን በቤታቸው ይከበርላቸዋል። በዚህ ዕድሜ ገደብ ውስጥ ያሉት ታዳጊዎች የሥራ ድርሻ ብዙ ሳይርቁ ጥጃዎች መጠበቅ ነው።

ሦስተኛው ትልቁ ጋሜ (Gaammee Gugurdaa) ከ16-24 ዓመት ድረስ ያሉትን ያጠቃልላል። በዚህ እድሜ ጠንከር ያለ ሥራ ይጠበቃቸዋል። ከብቶችን ይዞ ርቆ መሄድ፣ ለከብቶቹ ከጥልቅ ጉርጓድ ውሃ አውጥቶ ማጠጣት።

አራተኛ፣ ኩሣ (Kuusaa) ከ24 እስከ 32 ዓመት ዕድሜ ያላቸውን የሚይዝ ሲሆን፣ ይህ ደረጃ በገዳ ሥርዓት ወሳኝ ቦታ አለው። የገዳ ባለሥልጣን የሚሆኑት በዚህ ዕድሜ ይመረጣሉ።

አምስተኛ፦ ገዳ (Gada) በዚህ ሥር የሚመደቡት ዕድሜያቸው ከ33 ጀምሮ ያሉት ናቸው። ወታደራዊ ሥራዎች የሚሠሩበት፣ የጋብቻ ሥርዓት መፈፀም የሚችሉበት ዕድሜ ነው።

ከዚህ በኋላ ያሉት አራት ደረጃዎች ዮባ የሚል መጠሪያ የሚሰጣቸው ሲሆኑ የገዳ ሥርዓት አዋቂዎች (ባለሙያዎች) ናቸው። ሥራቸው ለተከታዮቻቸው ምክር መስጠት ነው። የመጨረሻ ደረጃ ገዶሞጂ (Gadamojjii) ነው። ይህን ደረጃ በ88 ዓ

መታቸው ያጠናቅቁታል። ይህን ደረጃ ለሚጨርሱ በዓል ይዘጋጃል። ከገዳ ሥርዓት ውጭ የሆኑ ማለት ነው። ከዚህ በኋላ እንክብካቤ የሚደረግላቸው ጡረተኞች ይሆናሉ።ይህ የዕድሜ ክፍፍል ጉዳይ ሴቶችን አያካትትም።

2.2.5. ሃይማኖት

ከቦረና አሮሞ አብዛኛው የገጠር ነዋሪ ነባር የሆነውን የአሮሞ ሃይማኖት የሚከተል ሲሆን በከተሞች ነዋሪ የሆኑት ብዙዎችና የገጠሩ ጥቂቶቹ የተለያዩ የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ናቸው። የነባር ሃይማኖቱ ተከታዮች በአንድ ፈጣሪ "Waaqaa" የሚያምኑ ሲሆኑ፣ ሰላም እንዲኖር፣ ደምኖ እንዲዘንብ፣ ከብቶች እንዲረቡ፣ ትውልድ እንዲቀጥል ይህንኑ "Waaqaa" ይማፀናሉ። እምነቱም ዋቄፈና (Waaqeffannaa) በመባል ይጠራል።

2.2.6. ቃሉ

ቃሉ በቦረና አሮሞዎች ዘንድ ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠው መንፈሳዊ አባት ነው። ቃሉ እንደ አባ ገዳ በየስምንት ዓመቱ ሥልጣን ለተከታዩ አያስረክብም። እስከ ህይወቱ ማብቂያ በሥልጣን ላይ ይቆያል። ሲሞት ልጁ ይወርሰዋል። የቦረና ዋና ዋና ክፍሎች ሰቦና ጎና የየራሳቸው ቃሉ አላቸው። የሰቦ ቃሉ ደቦ ከተባለው የከረዩ ንዑስ ክፍል የሚገኝ ነው። የጎና ቃሉ ደግሞ ከአዲቱ የፋለሌ ንዑስ ጎሣ ይመረጣል (Asmarom: 1973:47)።

> የቃሉ ትልቁ ተግባር አባ ገዳ የሚሆነውን ሰው መሾም፣ በቦረና ንዑሣን ጐሣዎች መሀከል የሚፈጠሩትን አለመግባባቶች መዳኘት፣ ለህዝቡ ሰላምና ጤና እንዲሰጠው፣ ከብቶች እንዲረቡ፣ ትውልድ እንዲቀጥል ፈጣሪን "Waaqaa" ይማፀናል፣ ይፀልያል፣ ሕዝቡን በየአጋጣሚው ይመርቃል (ቦርቦር ቡሌ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሚያዝያ 24 ቀን 1999)።

"የቦረናን አሮሞ እንደ ድልድይ ሆኖ ከፈጣሪ ጋር የሚያገናኘው ቃሉ ነው ተብሎ ይታመናል" (Baxter 1978:162)።

ቃሉ፣ በአማርኛ "ቃልቻ" ተብሎ ከሚነገርላቸው ባለዛሮች ጋር ግንኙነት የለውም። ቃሉ፣ "ይህን አደርግልሃለሁ አንተ ደግሞ መለማመኛ አምጣ" አይልም። በገዳ ሥርዓት በተደነገገው ደንብ መሠረት ለቃሉ የሚደረግለት "ጉማቱ" (Gumaata) መታያ ማቅረብ ብቻ ነው። አባገዳዎችም ሆኑ ተራው ህዝብ ቃሉ ጋ ለመመረቅ ሲሄዱ ለጉማቱ የሚሆን ኮርማ (ወይፈን) በራሳቸው ተነሳሽነት ይዘው ይቀርባሉ። ቃሉዎች በቁጥርም የተመጠኑ ናቸው። ቦረና ሁለት ቃሉዎች ብቻ አሉት፣ አንዱ የሰቦ ሁለተኛው የጎና ነው።

"ቃሉ ሥራ አይሰራም። ሥራው መንፈሳዊ ሥራ ብቻ ነው። የጦር መሣሪያ ወይም ሰው የሚጎዳ ነገር በእጁ አይገዛም። እንደበቱም ቁጥብ ነው።" (ካሉ ጂሎ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሰኔ 12 ቀን 1999 ዓ.ም.)።

በቦረና ቃሉና አባገዳ የጠበቀ ቁርኝት አላቸው። ቃሉ መርቆ ካልሾመው አባገዳነቱ አይረጋገጥም። ይሁን እንጂ ቃሉ አስተዳደረዊ እገዛ ከማድረግ አልፎ የፖለቲካ ጉዳይ ውስጥ አይገባም። (አለማየሁ ኃይሌ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሚያዝያ 6 ቀን 1999 ዓ.ም.)

2.2.7. ምጣኔ ሐብት

የቦረና ህዝብ አብዛኛው አርብቶ አደር ሲሆን፣ ጥቂቱ በደጋና ወይናደጋ አካባቢ ነዋሪ የሆነው ደግሞ ግብርናና ከብት ርቢን አጣምሮ ይሠራል። ለእርሻው ዘርፍ የሚውለው መሬት ከአንድ ሚሊዮን ሄክታር በላይ ሲሆን የተለያዩ የእህል ዘሮች እንደ በቆሎ ማሽላ፣ አደንጓሬ፣ ጤፍ፣ ስንዴና የተለያዩ ጥራጥሬዎች ያበቅላል። ቡሌ ሆራ ወረዳ ደግሞ ከእህል ዘሮች በተጨማሪ በቡና አምራችነቷ ትታወቃለች። ይሁን እንጂ የቦረና ኦሮሞ ህይወት ከከብት ሀብት ጋር የተያያዘ ነው። ከቦረና ዞን መሬት 80% የሚሆነውም ለከብት ርቢ የሚውል ነው። ህዝቡ በዚህ የግጦሽ መሬት ላይ፣ የቀንድ ከብቶች፣ ፍየሎች፣ በጎች፣ ግመሎችና የጋማ ከብቶችን ያረባል። የህዝቡ ምጣኔ ሐብትም ከከብቶቹ በሚገኘው ወተትና የወተት ተዋፅኦ፣ በሬ፣ በግና ፍየል ሽያጭ ላይ የተመሠረተ ነው።

በአሁኑ ጊዜ የቦረና ኦሮሞዎች ከብቶች፣ ፍየሎች፣ በጎችና ግመሎቻቸውን የሚሸጡበት የገበያ ማዕከል አንድ የግል ድርጅት በያቤሎ ወረዳ በኬ በተባለ ቦታ በዘመናዊ መንገድ አዘጋጅቶላቸው ይገበያዩበታል። ገበያው በሳምንት እሑድ ቀን የሚውል ከእንስሳት በተጨማሪ የተለያዩ የንግድ ቁሳቁሶችና ሸቀጣሸቀጦችም የሚቀርቡበት ትልቅ ገበያ ነው። "የቦረና መርካቶ" የሚል ቅፅል መጠሪያም አለው።

በተለያየ አጋጣሚዎች የሚሰበሰበው ሥጦታ-የጋብቻ ጥሎሽ፣ በስም ስያሜና በተለያዩ በዓላት ላይ የሚቀርቡ ስጦታዎችም የህዝቡ የምጣኔ ሐብት ምንጭ ናቸው። ወንድ ልጅ አግብቶ ሲወጣ ከቤተሰቡ መካፈሉ፣ ታላቅ ወንድ በውርስ የአባቱን ንብረት መረከቡ፣ የህዝቡን የምጣኔ ሐብት አመሠራረት ያሳያል (Tadhi, 2007:28)።

3. ክለሳ ድርሳን

በዚህ ርዕስ ሥር በቦረና ህዝብ ባህልና ፎክሎር ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶች፣ በተለይ ከቦረና ኦሮሞ በኩር ልጅ ስም ስያሜ ጋር የተያያዙ፣ በስም ስያሜ ላይ የተደረጉ ምርምሮችና ርዕሰ ጉዳዩ መሠረት የሚያደርጋቸውን ጽንሰ ሀሳቦች የያዙ ሥራዎች ይዳሰሳሉ።

3.1. የተዛማጅ ሥራዎች ዳሰሳ

3.1.1. የቦረና ኦሮሞን ባህል /የፎክሎር ዘሮች/ መነሻ አድርገው የቀረቡ ተዛማጅ ጥናቶች

የፎክሎር ዘሮችን ወይም የየማህበረሰቡን የፎክሎር ዓይነቶች ጥናት ወይም ስብስብ መረጃዎችን ማግኘት የምንችለው ከአጠቃላይ ከሀገር ወይም የየብሔረሰብ የባህል ጥናት መረጃዎች ውስጥ ነው። ይህም ማለት የፎክሎር ዘሮች ለየብቻቸው ተሰብስበው ወይም ተጠንተው አናገኝም ማለት ነው። የሀገራችን የፎክሎር ዘርፍ ስብስብና ጉዳዩን የሚመለከቱ ጥናቶች፣ በሀገራችን አንዳንድ በጉዳዩ ላይ በተለይ ባህል፣ ከመጠበቅና ከማቆየት አንፃር የተመለከቱ ግለሰቦች፣ መሰብሰብና ማሳተም የጀመሩት በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይና በኋላ ነው። በዓለም ደረጃም በአውሮፓ ጋዜጦች ላይ ጉዳዩን የሚመለከቱና ስብስቦች ታትመው መውጣት የጀመሩት በዚሁ ጊዜ ነው። (Feqade, 2001,48:59)። ይህም ቢሆን በተለይ በአውሮፓውያን የተሰበሰቡና የተጠኑ የፎክሎር ዘርፎች፣ ፎክሎርን በፎክሎርነቱ ለማጥናት ታቅደው የተደረጉ አይደሉም። ሌሎች ጉዳዮችን ፍለጋ ለምሳሌ የህዝቡን ታሪካዊ አመጣጥ፣ ሃይማኖቱን፣ ቋንቋውን ለማወቅ በሚያደርጉት ጥረት ውስጥ ያገኙዋቸውን የፎክሎር ዘሮችን እግረ መንገድ ለመረጃዎቻቸው ማጠናከሪያ ተጠቅመው የተገኙ ናቸው።

የሀገራችን የፎክሎር ዘርፎች ሥራዬ ተብለው መጠናትና መሰብሰብ የጀመሩት፤ ቃሉ ራሱ ታውቆ ትኩረት ተሰጥቶት የጥናት ርዕሰ ጉዳይ የሆነው ፣ ከ1970ዎቹ ወዲህ ነው (Feqade, 1984:8)። ይህ ሁኔታው ደግሞ ዘርፉ ገና ያልተነካ የጥናት ምንጭ መሆኑን ያስገነዝባል።

የኦሮሞ ብሔረሰብም የተለያዩ የፎክሎር ዘርፎች ስብስብና ጥናት ከላይ የተጠቀሰው ታሪክ ተጋሪ ስለሆነ፣ ገና ያልተዳሰሱ የፎክሎር ዘሮች አሉት። የተጠኑና ያልተጠኑትን ለመለየትም እራሱን የቻለ ጥናት ማካሄድ ያስፈልጋል። አጠቃላይ የተባሉትን ጥናቶች መመርመር ይጠይቃል። ከ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ አውሮፓውያን የአፍሪካን ህዝብ፣ የጥናት ትኩረታቸው አድርገው ሲነሱ፣

የኢትዮጵያን ህዝቦች ባህል፣ ቋንቋ በሚፈልጉት አቅጣጫ አጥንተዋል። የኦሮሞም የቋንቋ፣ የታሪክና ባህል ጥናትም በዚሁ ሂደት ውስጥ ማለፉ ይጠቀሳል። እነዚህም ጥናቶች በአብዛኛው አጠቃላይ የሚባሉት ውስጥ የሚካተቱ ናቸው።

በየደረጃው ወደ ተለያዩ የኦሮሞ ክፍሎች የቋንቋ፣ የታሪክና የባህል ጉዳዮች ጥናት እያጠበብነው ስንወርድም ልንጠቃቅሳቸው የምንችላቸው የሀገር ውስጥና የውጭ /አውሮፓውያን/ አጥኚዎች የሥራ ውጤቶችን እናገኛለን።

የአውሮፓም ሆኑ የሀገር ውስጥ አጥኚዎች በተለይ ከፎክሎር ዘሮች ስብስብና ጥናት አኳያ ሲታይ፣ አውሮፓውያን ተጓገዦች፣ የፖለቲካ መልዕክተኞች፣ የሃይማኖት ሰዎች ወደ ኢትዮጵያ በመጡ ጊዜ የተለያዩ ብሔረሰቦችን ሥነቃላት ሲሰበስቡ የኦሮሞንም ሥነቃል ሰብስበው በመጽሐፍ አሳትመዋል። ለምሳሌ አውሮፓውያኑ ኤንሪኮ ቼሩሊ፣ ማሪዮ ባሬሎ፣ ሮጃር ቻምበርድ፣ ማርቲን ሞሬና፣ ትሩዝሊ እና በዜግነት ኢትዮጵያዊ የሆኑት ክላውድ ሳምነር በተለያዩ የኦሮሞ ሥነቃል ሥራዎቻቸው የሚጠቀሱ ናቸው (Feqade, 2001,50:52)።

ከሀገር ውስጥ ነጋሦ ጊዳዳና አዲሱ ቶሎሣ በከፍተኛ የትምህርት ስልጠናቸው ወቅት የሥነቃል ዘሮችን በማጥናትና በመተንተን ለብሔረሰቡ የታሪክ ማጣቀሻ መረጃዎች መሆን እንደሚችሉ በጥናቶቻቸው አረጋግጠዋል (Feqade, 2001, 67:68)።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል በመጀመሪያ ደረጃ ዲግሪ ትምህርት ማብቂያ ላይም በርካታ ተማሪዎች የብሔረሰቡን የሥነቃል ዘሮችን፣ የብሔረሰቡ ማንነት መገለጫ የሆኑትን ጋብቻ፣ እምነትና የተለያዩ የባህል ዘርፎችን የጥናቶቻቸው ርዕሰ ጉዳይ አድርገው አቅርበዋል። (Feqade, 2001, 60)

እነዚህን የጥናት ሂደቶች ወደተለያዩ የኦሮሞ ክፍሎች እያጠበብን፣ ለምሳሌ ቦረናን መነሻ አድርገን ስንቃኝ፣ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር አጥኚዎች በመጣጥፍ /አርቲክል/ ደረጃ በተለያዩ ጋዜጦች፣ መጽሔቶች፣ ኮንፈረንሶችና የቅድመ ምረቃና ድህረ ምረቃ ትምህርት ተከታታዮች የመመረቂያ የጥናት ጽሑፎች ርዕሰ ጉዳይ ሆነው የቀረቡትን ሥራዎች መጥቀስ ይቻላል።

የቦረና ኦሮሞ እንደሌላው አካባቢ ኦሮሞዎች ላለፉት ዘመናት ጨቋኝ ሥርዓቶች ሙሉ በሙሉ ስላልተጋለጠ፣ አንፃራዊ በሆነ መልኩ ሲታይ ከሌሎች አጎራባች ብሔር ብሔረሰቦች ጋር ሳይቀላቀል በመቆየቱና አካባቢውን ለቆ ርቆ ባለመሄዱ ጥንታዊ ባህሉን ጠብቆ ለመኖር ችሏል (Baxter 1978, Asmarom 1973)። በመሆኑም የበርካታ የታሪክና የአንትሮፖሎጂ ምሁራንን ትኩረት መሳብ ችሏል።

ከነዚህ ምሁራን መሀከል Paul Trevor William Baxter, አንዱ ሲሆን፣ በቦረና ኦሮሞ ባህል ላይ በርካታ የምርምር ሥራዎችን አቅርቧል። ዋና ዋናዎቹ በተለይ ከዚህ ጥናት ጋር ተያያዥነት ያላቸው የበኩር ልጅ ስም ስያሜ በዓልና ሌሎች የተለያዩ በበዓላት የሚገለፁ ጉዳዮች ክዋኔዎቻቸው የሚደጋገሙትን የገመገመበት ጽሑፉን ያቀረበበት፣ "Repetition in Certain Boran Ceremonies" 1965, 62-78 የሚል ርዕስ ባለው መጣጥፉ ነው።

በዚህ መጣጥፉ የበኩር ልጅ ስም ስያሜ በዓልና ሌሎች ከአንድ ደረጃ ወደ ተከታዩ የሚሸጋገሩበት እንደ ከደበሌ ወደ ጋሜ፣ ከጋሜ ወደ ኩሣና መጨረሻው ደረጃ ገደሞጂ በዓል የሚደጋገሙ /ተመሳሳይ/ ድርጊቶች መከናወናቸውን ገልጿል። በተለይ በበዓላቱ ላይ "ገልማ" (Galma) ወይም ዳስ መስራት፣ የባለጉዳዩ ፀጉር መላጨት፣ ለድርጊቶቹ መከወን የአያንቱ አስፈላጊነት ወይም የጊዜ አቆጣጠር እውቀት /ጥሩና መጥፎ ገድ ያለባቸውን ቀናት ለመለየት/ ተደጋጋሚ ድርጊቶች መሆናቸውን ዘርዝሮ፣ ለበኩር ልጅ የአያቱ ስም እንደሚወጣለት፣ በመጨረሻም የአባቱ ንብረት ወራሽ መሆኑን አብራርቷል።

Baxter, "Being and Becoming Oromo" በሚል ርዕስ ከJan Hultin Alessandro ጋር አርትኦቱን በሰራውና የራሱንም መጣጥፍ ባቀረበበት የ1996 ዕትሙ ውስጥ፣ በርከት ያሉ መጣጥፎች ተካትተዋል። አብዛኛዎቹ በቦረና ኦሮሞ ጉዳይ ላይ ያተኮሩ ናቸው። እነዚህም ስለ ገዳ ሥርዓቱ ዲሞክራሲያዊነት፣ በገዳ ሥርዓት ውስጥ ስላለው በዕድሜ ክልል ላይ የተመሠረተ የማህበረሰቡ ክፍፍል፣ ስለ ህዝቡ አርብቶ አደርነት፣ ስለማንነቱና ስለመተዳደሪያው፣ ስለ ቦረና ሰላም፣ ከአጎራባች ጎሣዎች ጋር ስላለው ግንኙነትና ግጭት የሚያወሱ መጣጥፎች ናቸው። በዚሁ መጽሐፍ "Sources of Life and Identity" የሚለውን መጣጥፍ ያቀረበችው Gudrun Dahl የተባለች አጥኚ በገዳ ሥርዓቱ ውስጥ ስላለው እኩልነትና የደረጃ ተዋረድ የህዝቡን የፖለቲካ አስተሳሰብ፣ ከጎረቤቶቹ ጋር ስላለው ግንኙነት፣ በከብቶች እርባታ ላይ ስለተመሠረተው ሕይወቱ፣ ስለ እምነቱ ጽፋለች።

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ንዑስ ርዕስ አድርጋ "To be the First" በሚል ያቀረበችው በቦረና ህዝብ አመለካከት ከፍተኛ ቦታና ትኩረት የሚሰጠው በመጀመሪያ ለተወለደ ወንድ ልጅ መሆኑን "Boraan dominant ideology puts a heavy emphasis on being the first born son, the angaafa" (Dahl, 1996:172) በማለት ገልፃለች። ቀጥላም ከታናናሾቹ በበለጠ በአባቱ ጉዳይ ውስጥ የሚያገባው፣ የሚወክል፣ የአባቱን አብዛኛውን ንብረት የሚወርስ መሆኑንም ጠቅሳለች።

እንዲሁም በቦረናዎች ዘንድ ስም ስያሜ ከሁሉ ቅድሚያ የሚሰጠው መሆኑንም ጠቁማ፣ የደበሌ ጉቢሣ፣ የበኩር ልጅ ጉቢሣ፣ ሞጋሳና በእስልምና ተከታዮች ዘንድ

የሚታወቀው ዋቅላል የስም ስያሜ አይነቶች መሆናቸውን ገልፃለች። የደበሌ ስም ስያሜ ለሥርዓቱ መቀጠል ወሳኝ መሆኑን፣ የሌሎች የስም ስያሜዎች ደግሞ ለግለሰቦቹ በቦረናነት መገለጫነታቸው ከፍተኛ ቦታ እንዳላቸው ጠቅሳለች።

"Age, generation and Time some features of East African Age Organization" በ1978 በታተመውና አርትአቱን Baxter በሠራው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ Borana age sets and generation sets Gada, a puzzle or a maze? በሚል ርዕስ የራሱን መጣጥፍ አቅርቧል። በዚህ መጣጥፍ ውስጥ በኢትዮጵያና በኬንያ ውስጥ ያሉትን ቦረናዎች የገዳ ሥርዓትና በውስጡ የተካተቱትን የባህል ሥርዓቶች በዝርዝር ከተመለከተ በኋላ፣ በሁለቱም ሀገር ያሉት ቦረናዎች ተመሳሳይ ቋንቋ፣ ባህልና የሚተዳደሩበት የገዳ ሥርዓት እንዳላቸው፣

> ... Boran language and culture are extraordinarily homogenous, I could not detect any differences in dialect between any parts of Borana land nor, with the exception of the changes in ritual practice and dress adopted by those who have joined Islam. ... all Boran, except those who have accepted Islam, share the same beliefs and participate in the Gada system. (163). በማለት ገልጿል።

Baxter, "Stock management and diffusion of property Rights Among Borana" በሚለው መጽሐፉም፣ በቦረና አሮሞዎች ዘንድ፣ ንብረት ሁሉ የወንዶችና በእነርሱ እጅ የሚተዳደር መሆኑን፣ ታላቅ ልጅ የአባቱ አብዛኛው ንብረት ወራሽና በስም ስያሜው በዓ ል ላይ "ሀንዱራ" በሚል ስም ስጦታ ተሰጥቶት የግል ንብረት ማካበት የሚጀምር መሆኑን አቅርቧል።

ሌላው የአንትሮፖሎጂ ምሁር አስመሮም ለገሠ ነው። "Gada, Three Approaches to the Study of African Society" በሚለው እ.ኤ.አ. የ1973 እትም መጽሐፉ የቦረናን ህዝብ ከገዳ ሥርዓት ጋር በተያያዘ ሁኔታ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ህይወቱን በጥልቀት መርምሯል። አሮሞ ለታላቅ ልጅ የሚሰጠውን ቦታ፣ በተለይ የቦረና አሮሞ ለታላቅ ልጁ ከስም ስያሜ ሥነሥርዓት ጀምሮ ትኩረት በመስጠት፣ በማህበራዊ፣ ባህላዊና ኢኮኖሚያዊ የማህበረሰቡ እንቅስቃሴ ውስጥ የላቀ ቦታ እንዲኖረው ከታች እየኮተኮተ የሚያዘጋጀው መሆኑን አሳይቷል።

ሳህሉ ኪዳኔ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ እ.ኤ.አ በ1996 ለሁለተኛ ዲግሪው ማሟያ ጽሑፉን ሲያዘጋጅ መሠረት ያደረገው የቦረናን አሮሞ ትረካዊ የፎክሎር ዘሮችን ነው። የጥናቱ ወረቀት "Borana Prose Narratives Thematic Analysis" የሚል ርዕስ ያለው ሲሆን፣ "Mammaaksaa, Duridurii, Argaadhageettii" የተባሉትን ትረካዊ የፎክሎር ዘሮች

ሰብስቦ በመተንተን የህዝቡን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት፣ አመለካከቱን ከትረካዎቹ ትንታኔ አውጥቶ አሳይቷል።

ገመቹ ታዬ፣ በማህበረሰባዊ የትምህርት ክፍል /Anthropology/ እንዲሁ፣እ.ኤ.አ በ2002 የሁለተኛ ዲግሪውን የማሟያ ጽሑፍ ሲያዘጋጅ፣ የቦረና ኦሮሞ በድርቅ ወቅት ወይም የዝናብ እጥረት ሲያጋጥመው ችግሩን ለመቋቋም የሚገለገልባቸውን ባህላዊ ዘዴዎች ተንትኖ አሳይቷል።

በዚሁ መሠረት ቦረናዎች፣ የድርቅ ችግር መምጣቱን በሚያመለክቱ ምልክቶች ላይ ክትትል በማድረግ ቅድመ ዝግጅት ያደርጋሉ። ያለውን ሣርና ውሃ በቁጠባ መገልገል የሚቻልበትን ዘዴዎች ተግባራዊ ያደርጋሉ። የጣሸ ቦታና ውሃን በደረቅ ወቅት በዝናብ ወቅት እየተባለ በፈረቃ መገልገል የሚቻልበትን ዘዴ ይዘረጋሉ።

ችግሩ ከደረሰ በኋላ ደግሞ ባህላዊ የመረዳዳት ዘዴዎች ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋሉ። ትርፍ የምትታለብ ላም ያለው፣ ለሌለው ችግር እስከያልፍ ያውሳል። ተራ መስጠት (Dabaree) አይነት ዘዴ ነው።

ከላይ እንደተጠቀሰው የቦረናን ኦሮሞ ባጠኑት ምሁራን ሥራ ውስጥ አጠቃላይ በሆነ መልኩ ከባህሉ ጋር አጣምሮ ከማቅረብ ውጭ በበኩር ልጅ ስም ስያሜ ላይ ወይም የስም ስያሜውን መነሻ አድርጎ የቀረበ ወጥ ጥናት አላገኘሁም። ይህም ሲባል በበኩር ልጅ ስም ስያሜ ላይ ምንም ጽሑፍ አልቀረበም ማለት አይደለም። በህትመትና ኤሌክትሮኒክስ የህዝብ መገናኛዎች የቀረቡ አጫጭር ጽሑፎችና ፕሮግራሞች አሉ።

የኦሮሚያ ክልል የማስታወቂያና ህዝብ ግንኙነት ቢሮ በየሳምንቱ የሚያሳትመው "ከለቻ ኦሮሚያ" ጋዜጣ፣ በ1989 ዓ.ም. የካቲት 6 ቀን ዕትሙ፣ ባህል ገፅ ላይ "Sirna Moggasa Maqaa Booranatti" (የስም ስያሜ ሥነሥርዓት በቦረና) በሚል ርዕስ ገመቹ ታዬ አጭር መጣጥፍ አቅርቧል። በርዕሱ ሥር በሰፈረው ጽሑፍ ውስጥ የተካተተው ፍሬ ነገር፣ ለስም ስያሜ በተለይ ለታላቅ ልጅ ስም ስያሜ፣ በዓል ተዘጋጅቶ የሚከወኑ የተለያዩ ድርጊቶች መኖራቸውን የሚገልጽ ነው። በዓሉ ሲዘጋጅ ጊዜ ተወስኖለት እንደሚዘጋጅ በጽሑፉ ውስጥ ተጠቁሟል። ይኸውም ጊዜ ዝናብ በሚዘንብበት፣ ከብቶች ጠቀም ያለ ሣር ግጠው ጥሩ ወተት በሚሰጡበት፣ ቤቱ ሙሉ በሆነበት የአካባቢው ክረምት ወቅት እንደሆነ ያትታል። በዓሉ አራት ቀናት እንደሚቆይ፣ እያንዳንዱ ቀን የየራሱ ክንዋኔዎችና ስም እንዳለውም ይገልፃል።

በዚሁ ጋዜጣ፣ በተጠቀሰው ገፅ ላይ በ1998 ዓ.ም. ህዳር 29 ቀን በወጣው ዕትም፣ "Oromoon Booranaa Angafa ni Gubbisa" (የቦረና ኦሮሞ በኩር ልጅን ይሰይማል) በሚል ርዕስ እላይ እንደተገለፀው ተመሳሳይ ይዘት ያለው ጽሑፍ፣ መስፍን ተሾመ አቅርቧል።

በሁለተኛው የጋዜጣው ጽሑፍ ዘርዘር ያሉ ነገሮች ተካትተዋል። በቦረና የስም ስያሜ በሁለት እንደሚከፈል፣ ጉቢሣና ሞጋሣ ተብሎ እንደሚታወቅ አብራርቷል። ጉቢሣ፣ የታላቅ (የበኩር ልጅ)፣ ሞጋሣ ደግሞ የሴት ልጅ (የመጀመሪያ ልጅ ብትሆንም) እና የታናናሽ ወንዶች ልጆች ስም መሰየሚያ ሥርዓት መሆኑን ይጠቅሳል።

በዚህኛው የጋዜጣው ዕትም የቀረበው ጽሑፍ፣ በዓሉ ለሦስት ቀን እንደሚቆይ ይገልፃል። በሁለቱ የጋዜጣው ጽሑፎች መሀከል አንድነትና ልዩነት ይታያል። የበዓሉን ቀናት ብዛት የመጀመሪያው አራት ብሎ ሲያቀርብ፣ ሁለተኛው ሦስት በማለት አንባቢን ያምታታሉ። የሁለቱም አቀራረብ አጠቃላይ ነው። ለእያንዳንዱ ክዋኔ መልስ አይሰጡም። ድርጊቶች ይከወናሉ ይላሉ እንጂ ለምን እንደሚከወኑ ፍንጭ አይሰጡም። ለምሳሌ ይጨፈራል፣ ይመረቃል ከማለት ውጭ ምን ተብሎ እንደሚጨፈር፣ እንደሚመረቅ፣ ምርቃቱንና ጭፈራውን ማን እንደሚመራ፣ ማን እንደሚቀበል አይገልፁም።

በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን፣ "ሃገሬ" በሚለው የአማርኛ ፕሮግራም ጥቅምት ወር 1998 "ጉቢሣ-መቃባሳ" በሚል ሰላሳ ደቂቃ የፈጀ ዝግጅት ተላልፏል። የዚህም ዝግጅት ጽሑፍ ይዘት በሁለተኛ ጊዜ በጋዜጣው ላይ ከቀረበው ጋር አንድ አይነት ነው። ልዩነቱ የቴሌቪዥን በተንቀሳቃሽ ምስል የተደገፉ ድርጊቶችን የሚያሳይ በመሆኑ ብቻ ነው።

ስለዚህ እነዚህ በተለያየ ጊዜ በመገናኛ ብዙኃን የቀረቡት የበኩር ልጅ ስም ስያሜ በዓል ላይ ያተኮሩ አጫጭር ጽሑፎች መጠነኛ መረጃ ይሰጣሉ እንጂ እንደ ጥናት ሥራ ዝርዝር ጉዳዮችን አንስተው ትንተና ስለማያደርጉ ከኔ ጥናት ይለያሉ።

3.1.2. በስም ስያሜ ላይ የቀረቡ ተዛማጅ ሥራዎች

በዚህ ንዑስ ክፍል የሚቃኙት የሰው ስም ስያሜን ርዕሳቸው አድርገው የቀረቡ ስምንት የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፎች እና በየቋንቋ ጥናት ጉባኤዎችና ጥናታዊ መጽሔቶች የቀረቡ ጽሁፎች ናቸው። እነዚህ ጽሑፎች የተገኙት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ዋናው ግቢ ቤተመጻሕፍት ውስጥ ነው። የዲግሪ ማሟያ ጽሑፎቹ በሙሉ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል የቀረቡ ናቸው።

እነዚህም፦

አብረሃም ስዩም፣ "የትግርኛ የሰው የተዐውኦ ስሞች" በሚል ርዕስ በ1963 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ዲግሪው ማሟያ ጽሑፉን አቅርቧል። ዓላማ ያደረገው፣ የትግርኛ የሰው የተዐውኦ ስሞችን ትርጉም፣ የሚሰየሙበትን ምክንያቶች፣ ስሞቹ የሚኖራቸውን ቅርፅና ይዘት አጥንቶ ለተከታዩ ትውልድ መዝግቦ ማስተላለፍ ነው።

ጥናቱን በአምስት ክፍል ከፍሏል። በየክፍሉም በሚያስተላልፉት መልዕክት መሠረት ከፋፍሏቸዋል። እንዲሁም አብዛኛዎቹን ስሞች በቃል ግጥምና በተረት ውስጥ በማስገባት የሚሰጡትን ፍች አሳይቷል።

ጉልላት አበራ፣ "የጎጃም የሰው የተዐውኦ ስሞች" በሚል በ1963 እንዲሁ ለመጀመሪያ ዲግሪው ማሟያ ጽሑፍ አቅርቧል። የዚህ ጥናት ዓላማ፣ በርስበርስ ግንኙነት፣ በቴክኖሎጂ እድገት ሰበብ ለውጥ ሊመጣ ስለሚችል የአካባቢው ቀደምት የአሰያየም ስርዓት ሳይለወጥ ወይም ሳይዳቀል ለተከታዩ ትውልድ ቀርያ ለማቆየት ነው ይላል።

የጥናቱ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ከትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር የስድስተኛና የሰምንተኛ ክፍል ተፈታኞች ስም መዝገብ፣ ከሚያውቃቸው የጎጃም ተወላጆች በአጠቃላይ 200 ያህል ስሞች ሰብስቧል። እነዚህንም ስሞች ሰላም ወዳድነት፣ አለኝታነት፣ ምትክነት፣ ሀብትና ሀብታምነት ገላጭ በሚሉና በመሰል ይዘቶች ከፋፍሎ ተንትኗቸዋል። የጥናቱ አቀራረብ የምርምር መልክ የተከተለ አይደለም። ማጠቃለያ የለውም።

ኢብራሂም ሰይድ፣ "በወለጋ ኦሮሞ የሰው የተዐውኦ ስሞች" የሚለውም በ1974 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ሌላው ጽሑፍ ነው። የጥናቱ ዓላማ፣ የኦሮምኛ ስያሜ እየቀነሰና የስሞቹ ፍቺ እየተረሳ በመሆኑ ስሞቹን ሰብስቦ ከነትርጉማቸው ማቆየት ነው ይላል። ኢብራሂም የተዐውኦ ስሞች ይበል እንጂ በይዘት ከፋፍሎ ባስቀመጠው ውስጥ የጓደኛሞች መጠራሪያ ስሞች፣ የቤተሰብ፣ የባሪያ ስም የሚባሉትን የሰዎቹ የይፋ መጠሪያ ያልሆኑትን ሁሉ አካቶ 526 ያህል ስሞች ሰብስቧል። ስሞችን በሚሰጡት ፍቺ መሠረት ከፋፍሎ አቅርቧል። ሀብታምነትን፣ ምኞትን፣ ቅራኔን፣ ችግርን፣ ደስታን፣ ፍቅርን፣ ወዘተ. የሚያመለክቱ ስሞች በማለት ተንትኗል።

ርዕሱ የተዐውኦ ስም ሆኖ ሳለ፣ ስም የተባሉ እንደ የምራት ስም፣ የባሪያ ስም፣ የጓደኞች መጠራሪያ ስም ሁሉ በማካተት ከርዕሱ ወጥቷል። በመጨረሻም ከጥናቱ ስለተገኘው ውጤት ያለው ነገር የለም። ማጠቃለያም የለውም።

ሳሙኤል ጎንደሬ፣ "የሰው ተዐውኦ ስሞች በጋሞ ብሔረሰብ" በሚል ርዕስ በ1975 ዓም. ለመጀመሪያ ዲግሪው ሟሟያ ጥናታዊ ጽሑፍ አቅርቦ ነበር። የዚህ ጥናት ዓላማ ዘርዘር ያለ ነው። ይኸውም የህዝቡ ባህል እምነት መግለጫ የሆነውን ስም መመርመርና ማጥናት፣ ከሌሎች የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ጋር ባለው የርስ በርስ ግንኙነት ሰበብ የባህል መቀላቀል ስላለ የብሔረሰቡ ስም ተቀላቅሎ የራሱነቱን ሳያጣ በጽሑፍ ማቆየት የሚሉ ናቸው። አጥኚው ይህን ዓላማውን ለማሳካት መረጃውን በህዝብ መህል ገብቶ በማጠያየቅ መሰብሰቡን ጠቅሷል።

ስለጋሞ ብሔረሰብ ስሞች እንደገለፃው ከሆነ የብሔረሰቡ የስም አወጣጥ ሥነሥርዓት ለአንድ ልጅ ስም ሲሰጥ የስሙ የመጀመሪያ ፊደል ከቅርብ ዘመዶቹ ስም የመጀመሪያ ፊደል ጋር ተመሳሳይ ሊሆን ይገባል። ፊደላቱ ከተመሳሰሉ ፍች የመስጠት አለመስጠት ይህን ያህል ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ አይደለም።

ፍች ያላቸውም አብዛኛዎቹ የችግር፣ የብሶት፣ የሀዘን፣ የጥላቻ፣ የቅራኔ እንዲሁም የደስታ መግለጫ እንደሆኑ አብራርቷል። በብሔረሰቡ ለልጅ፣ የሞተ ሰው፣ የአማትና የአማች ስም እንደማይሰየምም ገልጿል።

አያሌው ምትኩ፣ "የአሪ ብሔረሰብ የስም አወጣጥ" በሚል ርዕስ በ1976 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ዲግሪው ማሟያ ጽሑፍ አቅርቧል። በጥናቱ አላማ ተብሎ የቀረበው በስም ስያሜ አማካይነት የሚገለፁትን የአሪን ብሔረሰብ የባህል ገፅታዎች ማሳወቅ ነው የሚለው ነው። መረጃዎቹ የተሰበሰቡት በጽሑፍ ሠፍሮ ከሚገኘውና ከህዝቡ እንደሆነ ጠቅሷል።

የአሪ ህዝብ የስሞች አጠቃላይ ይዘት የህዝቡን የወደፊት ምኞት፣ ያሳለፈውን ሀዘን፣ ደስታና ቅሬታ እንዲሁም እምነቱን የሚያንፀባርቁ እንደሆኑ አትቷል።

ደብሪቱ ተፈራ፣ "የደራሼ /ጊዶሌ/ ብሔረሰብ የተፀውኦ ስሞች አሰያየም ስልት" በሚል ርዕስ በ1978 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ዲግሪዋ ማሟያ ጽሑፍ አቅርባለች። አጥኚዋ የጽሑፉ ዓላማዎች ብላ ያቀረበቻቸው የብሔረሰቡን ባህልና ወጉን፣ ሥነልቡናዊ አመለካከቱን በስም ስያሜዎች አማካይነት ማሳየት እና፣ በባህል መወራረስ ሰበብ የአሰያየም ስልቶች እየተለወጡ ስለሆነ የብሔረሰቡ የስም አሰያየም ባህል ሳይለወጥ በጽሑፍ ለማቆየት የሚሉ ናቸው።

የደራሼ ህዝብ ቋንቋ የምሥራቃዊ ኩሽ ቋንቋ መሆኑን፣ ይህ ቋንቋው ከኮንሶና ከኦሮሞ ህዝብ ቋንቋ ጋር መቀራረቡንም ጠቁማለች። ደራሼዎች ለልጆቻቸው የሞተ ሰው ስም አይሰይሙም። እንዲሁም መጀመሪያ የተወለደ ልጅ ሁለተኛ የተወለደ ልጅና ከዚያም በኋላ የተወለደ ልጅ ስም ተለይቶ እንደሚታወቅም አሳይታለች።

የብሔረሰቡ ስሞች ይዘታቸው፣ ምኞትን፣ ተስፋን፣ ሰላምን፣ ተተኪነትን፣ ጥበበኝነትን የሚያመለክቱ መሆናቸውን በመጥቀስ በዝርዝር አቅርባለች።

ጌታሁን ላምቤቦ፣ "የሰው ስም አወጣጥ በሀዲያ ብሔረሰብ" በሚል ርዕስ በ198ዐ ለመጀመሪያ ዲግሪው ማሟያ ጽሑፍ ሲያቀርብ ዓላማ አድርጎ ያስቀመጠው፣ የብሔረሰቡን የስም አወጣጥ ታሪክ፣ የአሰያየም ልማድና ሥልት ላይ በማተኮር የስሞቹን ፍች ተንትኖ ማሳየት፣ በስም አወጣጡ አማካይነት የብሔረሰቡን ባህልና ወግ ማሳወቅ የሚሉትን ነው።

የመረጃው አሰባሰብ አዋቂዎችን በማነጋገር፣ ከትምህርት ጽህፈት ቤቶች ከስምንተኛ ክፍል የተማሪዎች የስም ዝርዝር መዝገብ በመውሰድ እራሱም የብሔረሰቡ አባል በመሆኑ የሚያውቀውን በመጨመር 646 ያህል ስሞች መሰብሰቡን ጠቅሷል። በስሞቹ ይዘት ትንተና ውስጥ ስሞቹ ሀብትና ብልፅግናን፣ ሰላምና እርቅን፣ ክብርና ደስታን መልካም ምኞትን፣ ጀግንነትን፣ ዘር፣ ነገድ፣ ጎሣን የሚያመለክቱ መሆናቸው ተብራርቷል። በማጠቃለያው የብሔረሰቡ ባህላዊ የአሰያየም ስልት በትምህርት፣ በሃይማኖትና በንግድ መስፋፋት ምክንያት እየተለወጠ መምጣቱን ጠቁሟል።

ብርሃኑ ሐንካራ፣ "የሰው ስም አወጣጥ በሲዳማ" ብሎ በ1980 ለመጀመሪያ ዲግሪው ማሟያ ጽሑፍ አቅርቧል። የጥናቱ ዓላማ በስም አወጣጥ ሥርዓቱ አማካይነት የሚተላለፉትን መልዕክቶችና የብሔረሰቡን ባህል ማሳየት፣ መዝግቦ ማቆየትና ለብሔረሰቡ ስም መለወጥ ምክንያት የሆኑ ማህበራዊና ባህላዊ ጉዳዮችን መጠቆም እንደሆነም ነጥብ በነጥብ አስፍሯል። በመቀጠልም ስሞቹ በሚያስተላልፉት መልዕክት /ይዘት/ መሠረት መልካም ምኞት፣ ቁጣን፣ ቅራኔን ወዘተ የሚገልው እያለ ከፋፍሎ ተንትኗል።

በማጠቃለያው የሲዳማ ብሔረሰብ ስሞች በተለያዩ ምክንያቶች እየተለወጡ መጥተው በተለይ በከተሞች በአባትና አያት ደረጃ ብቻ እንደሚገኙ ጠቁሟል።

በየቋንቋ ጥናት ጉባኤዎችና ጥናታዊ መጽሔቶች ላይ የቀረቡት ስም ስያሜ ላይ ያተኮሩት አምስት ጥናቶች ናቸው። የመጀመሪያው፣ Almagor U. የተባለ ሰው እ.ኤ.አ. በ1972 “Name-Oxen and Ox-names among the Dassanetch of South West Ethiopia” በሚል ርዕስ የደሳነች /ኑዌር/ ህዝብ የስም ስያሜን በተለይ በእንስሳት ስም የሚሰጥ የስም ስያሜን የቃኘበት ነው።

ይህ በእንስሳት በተለይ በበሬዎች ስም መሰየም በአርብቶ አደሮች ዘንድ የተለመደ መሆኑ በጥናቱ የተጠቀሰ ሲሆን፣ በደሰነቾች የበሬ ወይም የእንስሳት ስም የሚሰየመው ከአንድ ደረጃ ወደ ተከታዩ በሚደረግ ሽግግር ጊዜ ነው። መጠሪያነቱም በተወሰኑ የአንድ ቡድን አባላት ዘንድ የሚታወቅ መሆኑ ተገልጿል። በደሰነች ከእንስሳት ስም ውጭ፣ ልጁ የተወለደበትን ጊዜና ሁኔታ የሚያንፀባርቁ ስሞችም እንደሚሰየሙ ጥናቱ አትቷል።

በዚህ ጥናት ውስጥ ከቦረና ኦሮሞ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ጉዳይ አለ። ይኸውም ለበኩር ልጅ የሚደረግ ትኩረት ነው። በደሰነቾች ዘንድ ልጅ በተወለደ ጊዜ "የእንብርት ላም" የሚል ስጦታ በአባት እንደሚሰጥ ተገልጿል። በቦረናም የበኩር ልጅ ስም ሲሰየም “Horii Handhuraa” ይሰጣል። ሆሪ ሃንዱራ አማርኛ ትርጉሙ፣ የእምብርት ከብት የሚል ነው። በደሰነች አንድ ልጅ ስም ሲሰየምለት፣ ሰያሚው ከብት ይሰጠዋል ይላል። ይህ

ስሞታው የወደፊት መተዳደሪያው ነው የሚለውና የአባቱ ወራሽና በቀዬው የሚቀር ታላቅ ልጅ ነው የሚለውም ከቦረናዎች የበኩር ልጅ ሕይወት ጋር ተመሳሳይነት አለው።

ኒቆዲሞስ ኢድሪስ እ.ኤ.አ በ1991 ዓ.ም. "Traditional Name and Naming among Kunama" በሚል ርዕስ ለቋንቋዎች ጥናት ተቋም አምስተኛ ዓመታዊ ሴሚናር ጥናታዊ ጽሑፍ አቅርበው ነበር። የጥናቱ ዓላማ በኩናማ ብሔረሰብ ያለው ልማዳዊ ሥምና የአወጣጥ ሥርዓቱ በየጊዜው በሚደረገው የለውጥ እንቅስቃሴ ተቀይሮ አሻራው ሳይጠፋ መዝግቦ ማቆየት፣ እንዲሁም ስሞቹ ምን ምን ፍች ወይም መልዕክት እንደሚያስተላልፉ ለማሳወቅ ነው የሚል ነው።

በጽሑፉ ላይ እንደቀረበው፣ በኩናማ ለልጅ ስም የሚወጣው፣ በዓል ተዘጋጅቶ ነው። በዓሉ የሚዘጋጀው ለብሔረሰቡ አባላት የሚያመች የዕረፍት ጊዜ ተመርጦ ነው። ለበዓሉ በእንግድነት ተጠርቶ ለሚመጣ የሚበላና የሚጠጣ ነገር ይዘጋጃል። በበዓሉ ላይ የተገኘ ሰው ሁሉ ለልጁ ስም ያወጣል። በበዓሉ ላይ ያልተገኘ ደግሞ ሊሰይምለት የፈለገውን ስም በመልዕክት ያደርሳል /ይልካል/። በዚህ መልኩ አንድ ልጅ በርካታ ስሞች ይኖሩታል።

ስሞቹ በይዘት ተከፋፍለው የቀረቡ ሲሆኑ፣ በክፍፍሉ ውስጥ የክብትን ፍቅር፣ ቁጣን፣ አሸናፊነትን፣ ችግርን የሚገልፁና ተሰያሚው የተወለደበትን ጊዜና ሁኔታ መሠረት በማድረግ የሚሰየሙና ሌሎች የእንስሳት ስምም የሚሰየምበት ሁኔታ መኖሩም ተቃኝቷል።

አለማየሁ ጉርሙ፣ እ.ኤ.አ በ2000 ዓ.ም. በአሥራ ሁለተኛው ዓመታዊ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም ጉባኤ ላይ ያቀረቡትን፣ የክሰታንኛን ቋንቋ ስሞች ቅርፅና ይዘት የሚተነትን ጥናታዊ ጽሑፍ ይመለከታል። አለማየሁ፣ ስሞቹን በይዘት ሲከፋፍሉዋቸው ምን ምን መልዕክት ያስተላልፋሉ የሚለውን ጥያቄ መሠረት አድርገው ነው። በዚሁ መሠረት ደስታን፣ ማግኘትን፣ መቀራረብን፣ መልካም ምኞትን፣ ምክር መስጠትን የሚገልፁ በማለት ከነ ፍችያቸው አቅርበዋል። ስሞቹ የሚያሳዩዋቸውንም ቅርፃዊ ገፅታ ቃኝተዋል። ድርብ ቃል፣ ዓረፍተ ነገር መሰል በማለት ከፋፍሏቸዋል።

አረጋ ኃ/ሚካኤል ስለ አኘዋ ማህበረሰብ ስም ቅርፅና ይዘት የሚተነትነውን ጥናታቸውን "A Sociolingustic Approach to Anywa Personal Names: A Contribution to Socio-Onomastic Studies in A Nilo-Saharan Language" በሚል ርዕስ እ.ኤ.አ በ2005 ዓ.ም. በኢትዮጵያ የትምህርት ጥናት ባለሙያዎች ማህበር መጽሔት ቅጽ 2 ቁጥር 1 ላይ አሳትመዋል። ይህ ጥናት የአኘዋን ስሞች ቅርፅና ይዘት የሚተነትን ሲሆን፣ ከቅርፅ አንፃር የስሞቹን ቃላት፣ የተገነቡበትን ፊደላትና ስሞቹ ላይ የሚያስከትሉትን የፍች

ልዩነት የሚመለከት ነው። ከይዘት አቅጣጫ የቀረበው ደግሞ የስም ስያሜ ክዋኔዎችንና በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን ቁብ የሚያሳይ ነው።

በጥናቱ መሠረት በአኙዋ ስሞች በአጋጣሚ የሚወጡ ሳይሆኑ በማህበረሰቡ እያንዳንዱ አባል በህይወቱ ውስጥ አስቦበት ከሚከውነው ወሳኝ ጉዳዮች አንዱ መሆኑ ተጠቅሷል። ስሞቹ የማህበረሰቡን አመለካከት፣ ልጁ የተወለደበትን ሁኔታና ጊዜ፣ ምኞት፣ አጠቃላይ ባህርይና ገፅታ ገላጭ ሆነው ይገኛሉ።

በጥናቱ ትንታኔ መሠረት የአኙዋ ቋንቋ ቅርፁ ከቋንቋው ተነባቢና አናባቢ ድምፆች ይነሳል። ፆታ አመልካች ድምፆችና ፊደላት በሰረዝ ይያያዛሉ። ለምሳሌ በቋንቋው U (የእንግሊዝኛ ዩ) የተጨመረበት የወንድን ፆታ ሲያመለክት፣ ከፊቱ A ... የተጨመረ ደግሞ የሴት ፆታ አመልካች ይሆናል። በሌላ መልኩ ደግሞ እንደ ወንዝ ሐይቅ፣ ዛፍ የመሳሰሉ ስሞች ሲሰየሙላቸው ደግሞ ፆታ የማይለዩ ለወንድም ለሴትም መጠሪያ እንደሚሆኑ ታትቷል። በአኙዋ ስሞች የሚሰየሙባቸው አጋጣሚዎች እንዳሉም ተጠቅሷል። እነዚህም ከቤት ውጭ የሚሰየሙ፣ ስሞች፣ የመለያ ስሞች (ልጁ የተወለደበትን ጊዜና ሁኔታ መሠረት በማድረግ የሚሰየሙ) እና አንድ ሰው ከአንድ ደረጃ ወደ ተከታዩ ደረጃ ሲሸጋገር የሚሰየሙ ስሞች ናቸው።

የሚሰየመው ስም የበሬ ወይም የሚወዱት እንስሳ ስም ነው። ሴቶች ከአንድ ደረጃ ወደ ተከታዩ የሚሸጋገሩበት ሥርዓት ቢኖርም የስም ለውጥ እንደማያደርጉና በባላቸው ስም እንደሚጠሩ በጥናቱ ተገልጿል። ከደረጃ ሽግግር በፊት ያሉት ልጆችም በእንስሳት፣ በመንደራቸው ውስጥ በሚታወቁ በትላልቅ ዛፍ ወይም ሌላ ቋሚ ቁሳቁስ ሊጠሩ እንደሚችሉም ተጠቅሷል።

ባዬ ይማም፣ "Personal Names and Identity Formation Across-Cultural Perspective" በሚል ርዕስ፣ በስም ስያሜ ላይ ያቀረቡት ጥናት፣ IVO Strcker እና Jean Lydall አርትኦቱን በሠሩት "THE PERILS OF FACE" መጽሐፍ፣ የ2006 እትም ውስጥ ለንባብ ቀርቧል።

በጥናቱ መግቢያ ላይ፣ ስለስም ምንነት፣ ስም በቋንቋ በባህል፣ በተለይ በማህበራዊ ሕይወት ውስጥ ያለውን ቦታና የሚይዘውን ፍች ገልፀው፣ የተለያየ ባህልና ማህበራዊ ሕይወት የሚመሩ ህዝቦች ባሉበት፣ ስም የማንነት፣ የሃይማኖት፣ የታሪክ፣ የአካባቢና የማህበራዋ ደረጃዎች ማመልከቻ እና ተምሳሌት እንደሆነም አብራርተዋል።

ጥናቱ በአራት ክፍል የተከፈለ ነው። በመጀመሪያው ክፍል፣ አጥኚው ለሚያስተምሩት ኮርስ፣ ገመቹ ታዬ የተባለ ተማሪያቸው እ.ኤ.አ 2000 ለኮርሱ ማሚያ ላዘጋጀው ወረቀት የሰበሰበውን የቦርና አሮሞን የስም ስያሜ የሚመለከቱ መረጃዎችን

መሠረት አድርገው ያቀረቡት ነው። በዚህ ክፍል፣ የቦረናን የስም ስያሜ ሥነሥርዓት ሂደትን፣ ማህበራዊነትና ሥነአምሮአዊ ውጤትነት አቅርበዋል።

በተጠቀሰው ክፍል የቀረበው፣ የጥናቴ ርዕሰ ጉዳይ የሆነውን የቦረና ኦሮሞ በኩር ልጅ ስም ስያሜን መሠረት ያደረገ ስለሆነ በዝርዝር ቀርቦ አንድነትና ልዩነቱን ማሳየት ያስፈልጋል።

በዚህ የጥናቱ ንዑስ ክፍል የቦረና ኦሮሞዎች ትልቁ ባህል ጉቢሣ የስም ስያሜ መሆኑን፣ በቦረናዎች ዘንድ የስም ስያሜ በየትኛውም ጊዜ፣ ልጅ ተወልዶ ሁለት ዓመት ሳይሞላው በፊት እንደሚፈፀም፣ የመሰየሚያው ጊዜ በገናብ ወቅት ከሚያዝያ እስከ ጥቅምት ባለው ወቅት መሆኑ ተዘርዝሯል። በተጨማሪም በዓሉን ለማክበር "አያንቱ" ማማከር፣ ለበዓሉ ገልማ እንደሚያስፈልግ፣ የገልማው ሥራ ሲጀመር ለመስዋዕት በሬ እንደሚቀርብ፣ የገልማው ሥራ አምስት ቀን እንደሚፈጅ፣ አምስቱ ቀናት ደግሞ ሙከሙራ፣ የየባ፣ ጉያ እጃርሳ፣ ጉያ እጃርሳ በሉ፣ ጉያ ጂለበሉ እንደሚባሉ፣ የሚሰየመው ልጅ የራስ ፀጉር ግማሽ እንደሚላጭ ተገልጿል።

ይህ የጥናቱ ንዑስ ክፍል ባነሳቸው አብዛኛዎቹ ድርጊቶች ከጥናቴ ጋር ይመሳሰላል። ወደ ዝርዝር ጉዳዮች አፈፃፀም ሲዘለቅ ግን በርካታ ልዩነቶችን ይታያሉ።

ለምሳሌ፣ የቦረና የስም ስያሜ በየትኛውም ጊዜ ይከወናል የሚለው አጠቃላይ ሆኗል። እኔ መረጃ አቀባዮቼን ጠይቄ በተረዳሁትና በምልከታ እንደተከታተልኩት፣ የስም ስያሜ በተለይ ጉቢሣ በአካባቢው የክረምት ወቅት ሳይሆን ወቅቱ ማብቂያ ዝናቡ ቆም ሲል ከግንቦት ወር መጨረሻ እስከ ነሐሴ ወር መጨረሻ በብዛት የሚደረግ መሆኑን። ልጅ ተወልዶ ሁለት ዓመት ከመሙላቱ በፊት ይሰየማል የሚለውም የተሳሳተ ነው። የመሰየሚያው ዕድሜ የሚወሰነው በገዳ ዘመኑ ነው። ማለትም አንድ ልጅ በተወለደበት የገዳ ዘመን /በስምንት ዓመት ውስጥ/ መሰየም አለበት ነው እንጂ ሁለት ሦስት ዓመት የሚል የለም። ለምሳሌ እኔ በአካል ተገኝቼ ያየሁት የአብ አባሩፋ ጃተኒ ልጆች ዕድሜ ስድስትና አምስተ ዓመት ነው። የስም ስያሜ መከወኛው "ገልማ" ሥራ አምስት ቀን ይቆያል፤ ሲጀመር የመስዋዕት በሬ ይታረዳል የሚሉት የጥናቶቹን ልዩነት የሚያሳዩ ድርጊቶች ናቸው። በቃለመጠይቅና በምልከታ በሰበሰብኩት መረጃ፣ መስፍን ተሾመ የተባለ ሰው በከለቻ ጋዜጣ ላይ ባሳተመው ጽሑፍና የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን "ሀገሬ" ፕሮግራም ባቀረበው መሠረት የአዳራሹ ሥራ ከእንጨት ቆረጣ ዕለት ጀምሮ እስከ በዓሉ ማብቂያ ጊዜ ሦስት ቀን ብቻ ይቆያል። ቀናቱም፣ ሙከሙራ፣ የየባ እና ጂለ በሉ (ጉዳ) ተብለው ይታወቃሉ። የገልማው ሥራ ሲጀመር፣ ቀዱዳው ወጋ አድርጎ በሚተክለው እንጨት ሥራ "ደራራ" ይጨመራል እንጂ የሚታረድ የመስዋዕት ከብት የለም። ከብት ለበዓሉ ተመርቆ የሚታረደው በሦስተኛው ቀን ሌሊት አሥራ አንድ ሰዓት የንጋት ኮከብ

መውጣቱ ሲረጋገጥ ነው። እርሱም የሜዲቻ ከብት ይባላል። ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ በበዓሉ ቤት የሚታረዱ በሬዎችና ፍየሎች ለእንግዶች ማስተናገጃ ነው። ሲታረዱም ምንም ዓይነት የተለየ የመስዋዕት ማቅረቢያ ክዋኔ አልታየም። የልጁ የፀጉር አለጫጨትም ግማሽ የራስ ፀጉር ሳይሆን ወደ ቀኝ ወደ ግራ በማስመር የማኾንጎንጎር አይነት ነው።

ሌሎች ይህንን የኔን ጥናት የሚለያዩ ብዙ ድርጊቶች አሉ። በጥናቱ አራተኛና አምስተኛ ምዕራፍ ውስጥ በዝርዝር ቀርበዋል።

ባጠቃላይ በዚህ የተዛማጅ ሥራዎች ንዑስ ክፍል ሥር፣ የተዐውኦ ስምና አሰያየምን ርዕሳቸው አድርገው የተዘጋጁ የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያና በተለያዩ ጥናታዊ ጉባኤዎች ላይ የቀረቡ ጥናቶች፣ የተዐውኦ ስሞቹን ሰብስበው ከሚያስተላልፉት መልዕክት አንፃር /በይዘት/ ከፋፍለው መተንተናቸው ከጥናቴ አንድ ንዑስ ክፍል ጋር አንድነት እንዲኖራቸው ያደርጋቸዋል። የተቀራረቡ ይዘቶችና ንድፈ ሀሳቦችን ማንሳታቸውም አንድነታቸውን ያሳያል።

ከልዩነት አንፃር ሰታዩ፣ የጥናቴ ትኩረት በበኩር ልጅ ስምና የስያሜ በዓል ሂደት ላይ ነው። ይህም በመሆኑ ከስሞቹ ይዘት ትንታኔ በተጨማሪ ለስያሜው የሚዘጋጀው በዓል አከዋወንና የክዋኔዎች ውጤት የሆኑ የፎክሎር ዝርያዎችን ነቅሶ በማውጣት ምንነታቸውን መግለፅ፣ በስም ስያሜው በዓል ላይ ያላቸውን ቦታ በመተንተን ማሳየት የጥናት ሥራዬን ከተዛማጅ ሥራዎቹ ይለየዋል።

3.2. ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት

3.2.1. ከፎክሎር ዘርፍ አንፃር

የስም ስያሜ እንደ አቀራረቡ በማህበረሰባዊ ሥነልሳን፣ በአንትሮፖሎጂ፣ በፎክሎር የሙያ መስኮች ውስጥ ሊጠና ይችላል። እንዳቀራረቡ ሲባል ስም በስምነቱ ብቻ በማህበራዊ ሥነልሳን፣ ስያሜው በበዓል የታጀበ ከሆነ ደግሞ የማህበረሰቡን የተለያዩ ባህላዊ ክዋኔዎችን ስለሚያካትት በአንትሮፖሎጂ እንዲሁም በፎክሎር ሊጠና ይችላል ነው። ይህ ጥናት ትኩረት የሚደረገው በስም ስያሜው በዓል ፎክሎራዊ ገፅታ ላይ ስለሆነ በፎክሎራዊ መልኩ ጎልተው የሚታዩትን ክዋኔዎችን ያስቃኛል።

"ፎክሎር ኢመደበኛ በሆነ ሁኔታ ስለዓለም፣ ስለራሳችን፣ ስለማህበረሰባችን፣ ስለዕምነታችን ስለባህላችንና ወጋችን፣ በቃላት በሙዙቃ፣ በልማድ፣ በድርጊት በምናሳያቸው፣ በባህርይ፣ በቁሳቁስ፣ በክዋኔ የሚገለፅና የሚለዋወጥ፣ በውስጡ የፈጠራ

ሂደት የሚታይበት የርስ በርስ መገናኛ የሆነ የጋራ ዕውቀት ነው" (Martha, 2005:8) የሚለው አንዱ ነው።

የፎክሎርን ተግባራዊ ባህርይ ስንመለከት ይህ ፍች ሁሉንም የሚያስማማ ይመስላል። Dundes ደግሞ ለፎክሎር ፍች ከመስጠት ይልቅ በውስጡ ሊካተቱ የሚችሉትን በቁጥር በርካታ የሆኑትን ዘርዝሮ ማቅረብን መርጠዋል። (Dundes: 1965:1-3) የስም ስያሜም ከቀረቡት ዝርዝሮች አንዱ ነው።

Dorson የተባለው ሌላው የዘርፉ ባለሙያ ደግሞ የፎክሎር ዘሮችን መድበዋቸዋል። "Oral folkore, Social folk custom, material culture, folk arts" በማለት፣ (Dundes, 1972:1-4) ፤ ፈቃደ አዘዘም Dorson ንን በመከተል "ሥነቃል፣ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት፣ ሀገረሰባዊ ልማድ እና ቁሳዊ ባህል" በማለት አማርኛ ፍች ሰጥተው አቅርበዋል (ፈቃደ፣ 1991፣ 10-16)። እነዚህ አጥኚዎች በዓላት፣ የተለያዩ የማህበረሰብ አባላት የሚሳተፉባቸው፣ ህገባዊ ክዋኔዎች ግልፅ ሆነው የሚታዩባቸውን በማህበራዊ ልማድ ውስጥ የሚካተቱ መሆናቸውን ገልፀዋል።

በእንዲህ መልኩ የፎክሎርን የተለያዩ ገፅታዎች ማለትም ይዘቱን ቅርውንና የአቀራረብ መልኩን፣ ተግባሩን፣ ባህርያቱን እንዲሁም ሥርጭቱንና ታሪካዊ አነሳሱን መሠረት አድርገን የምንመለከትበት ወይም የምንተነትንበት የመከፋፈያ ዘዴን (genre) ዝርያ ልንለው እንችላለን (Ben Amos, 1982:66)።

የፎክሎር ዝርያ ከተፈጠረበት አውድ አንፃር ሲጠና የምርምር ሂደቱን ማስፋት ብቻ ሳይሆን በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ የአገላለፅ ልዩነቶች ለማሳየትና በውስጡ የተካተቱትን በትኖ ለማየት መሠረት (መነሻ) ይሆናል (Ben Amos, 1982:31)።

የዚህ ጥናት ርዕስ አንደሚያመለክተው የስም ስያሜ ሲሰጥ በዓል ይዘጋጃል። በዓል ደግሞ በባህርይው ብዙ ፎክሎራዊ ድርጊቶችን ሊያካትት ይችላል። ብዙ ሰዎች ተጠርተው ይመጣሉ። የምግብ ዝግጅት ይኖራል። በዓሉ ላይ የሚገኙት ሆኑ አዘጋጆቹ ከወትሮ የተለዩ ጌጣጌጦችና አልባሳትን ይለብሳሉ። በዓል ሲባል ደግሞ መደሰትን ያመለክታል። ይህም በገጣሬ፣ በዘፈን፣ በአካላዊ እንቅስቃሴ ሊገለፅ ይችላል። በአል በርካታ ሰዎች የሚሰባሰቡበት፣ በአደባባይ የሚከበር መሆኑን፣ በሌላ መልኩ ደግሞ በዓል የተወሰኑ ቡድኖች የሚያዘጋጁትና የሚሳተፉበት፣ የመከወኛ ጊዜና ቦታ ያለው፣ ከቡድኑ አባላት አንዱ ከአንድ ደረጃ ወደሌላ ደረጃ መሸጋገሩ የሚበሰርበት መሆኑን ያብራራሉ (Dorson: 1972:165)

በመቀጠልም፣ በዓላት ሰዎች እርሰ በርስ እንዲገናኙ፣ ሀሳብ እንዲለዋወጡ አብረው እንዲደሰቱና ግንኙነታቸው ቀጣይነት እንዲኖረው የሚያደርግ ዋንኛ የፎክሎር ዘር (genre) መከሰቻ መሆኑን ያረጋግጣሉ (Dorson: 1972:167-168)።

የተለያዩ ድርጊቶች በሚከወኑባቸው በዓላት ላይ በርካታና የተለያዩ ባህርይ ያላቸው ሰዎች የመሳተፋቸውን ያህል፣ እንዲሁ የተለያዩ የፎክሎር ዝርያዎች ተደራርበው እናገኛቸዋለን። ከቁሳዊ ባህል፣ አልባሳትን፣ ጌጣጌጦችን፣ የወግ ቁሳቁሶችን፣ ምግብ፣ መጠጥ፤ ከማህበራዊ ልማድ አምልኳዊ ገፅታ ያላቸውን ድርጊቶች፣ የማህበራዊ ደረጃ ዕድገት፣ ከትውን ጥበባት የሚደመሩ ጭፈራዎችን፣ ድራማዊ ክዋኔዎችን፣ ከሥነቃል ዝማሬዎችን ምርቃት የመሳሰሉትን ነቅሰን ማውጣት እንችላለን። የዚህ ጥናት መጨረሻው ክፍልም በእንዲህ መልኩ በተገኙ የፎክሎር ዝርያዎች ላይ ያተኩራል።

3.2.2. ከስም አንፃር

ስም በብዙ መልኩ ሊገለፅ ይችላል። የሰው የተዐውኦ ስም፣ የቅፅል ስም፣ የጋብቻ ስም፣ የነሣ /የቤተሰብ ስም/ የቦታ ስም፣ የእንስሳት፣ የእፅዋት ስም ወዘተ ተብሎ ሊጠቀስና ሊጠና ይችላል።

ከነዚህ ውስጥ ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር የሚቀራረበው የተዐውኦ ስም ነው። ስለዚህ የተዐውኦ ስም ምንድነው? አመጣጡስ ምን ይመስላል? የሚሉትን ጥያቄዎች ማየት ያሻል።

ስም አንድ ሰው ወይም አንድ ነገር ከሌላው ተለይቶ የሚታወቅበትና የሚጠራበት ቃል ወይም የቃላት ስብስብ ሲሆን፣ የራሱ የሆነ ፍችም ይኖረዋል (Aregga Hailemicheal, 2005,41. (Smith, 1967,Vii) ። ታሪካዊ አመጣጡም ሲታይ፣ የፈጣሪ ስጦታ (gift of God.) የሆነው ቋንቋ ከሰው ልጅ መፈጠር ጋር እንደተጀመረ፣ የስም ስያሜም ከቋንቋ መፈጠር ጋር አብሮ መከሰቱ ከትውልድ ትውልድ ሲነገር ቆይቷል (Smith: 1967:168)።

ልጅ ሲወለድ ስም የሚሰይሙት በአብዛኛው ወላጆች፣ አያቶችና የቅርብ ዘመዶች ናቸው። ሲሰይሙም እንዲተላለፍላቸው የሚፈልጉትን መልዕክት ያዘለ ስም በመምረጥ ያከናውናሉ። የፍችው ቀጥታ ምንነት በሰያሚው አእምሮ ውስጥ የሚወሰን ሲሆን፣ መነሻ የሚያደርጉት ስም የወጣለት ልጅ፣ በተወለደ ጊዜ፣ የተከሰተ ሁኔታን፣ ከመወለዱ በፊት ያጋጠማቸውን ችግር፣ ደስታ፣ ወደፊት የሚመኙትን በጎ ነገር ሊሆን ይችላል (Aregga, 2005:41, Smith, 1967:4)። ከውጭ የሚመለከተውም ሰው (ስሙን ያልሰየመው) የባህሉ ባለቤት ከሆነ በስሙ አማካይነት ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት፣ ወይም የስሙ ፍች ምን እንደሆነ በቅርበት ሊገምት ወይም ሊያውቅ ይችላል።

የአንዳንድ ማህበረሰብ አባላት የሚያወጡዋቸው ስሞች ቅርፃዊ አቀነባበራቸውን (የፊደላት አቀማመጥን) ብቻ በመመልከት ሰይመው ወደ ይዘቱ ሲዘለቅ ግልፅ የሆነ ፍች የሌላቸው ሆነው ይገኛሉ። "አንዳንድ ሰዎች ስምህ ምን ማለት ነው? ምን ፍች አለው? ሲባሉ፣ ስም ነው ትርጉም የለውም ይላሉ" (Smith, 1967:115)።

በአብዛኛው ማህበረሰብ ዘንድ ለልጅ በህይወት የሌለ ሰው ስም አይወጣም። በሞት የተለየ ሰው ስም ከወጣለት የሞት መንፈስ ወደ ልጁ ይመጣል ተብሎ ይፈራል (Smith, 1967:218)። በሌላ በኩል ደግሞ ሞትን ሳያስቡ የአባታቸውን፣ የእናታቸውን፣ የቅድመ አያቶቻቸውን ወይም የታዋቂ ሰውን ስም ለልጆቻቸው የሚያወጡ ሰዎች፣ የማንነታቸው ማቆያ ወይም ማሸጋገሪያ አድርገው ፍላጎታቸውን የሚገልፁበት መንገድ ሆኖ ይገኛል (Smith, 1967:186)።

አንዳንድ ጥንታዊ አኗኗርን መሠረት ያደረጉት ደግሞ ለልጆቻቸው የተለያዩ የዱር እንስሳትን ስም ያወጣሉ /ይሰይማሉ/። ይህንንም የሚያደርጉት የልጃቸውን ባህርይ ወይም አካላዊ አወቃቀር ማለትም፣ በአካል ግዝፍናና ጥንካሬ፣ በባህርይ ደግሞ የዋህ፣ ታታሪ፣ ቁጡ፣ ብልጣብልጥ መሆናቸውን በመመልከት ከእንስሳቱ ባህርይ ጋር በማዛመድ ይሰይማሉ (Smith, 1967:181)።

በሌላ መልኩ ደግሞ በአንዳንድ ማህበረሰብ የስም ስያሜ ሥነሥርዓት ከፍተኛ ቦታ ተሰጥቶት በዓል ተዘጋጅቶለት ይከናወናል። ይህም ስም የሚሰየምለትን ልጅና ቤተሰቡን ከነበረበት ደረጃ ወደ ሌላ የላቀ ደረጃ መሸጋገርን ያመለክታል። ምክንያቱም በዓላት እነዚህን በማህበረሰብ መሀከል ያሉትን ከደረጃ ወደ ደረጃ እንቅስቃሴዎችን ለማመልከት የሚዘጋጁ ናቸው። በሌላ አባባል የሰው ልጅ ተወልዶ በተለያዩ የዕድገት ደረጃዎች ውስጥ እያለፈ እስኪሞት የሚያደርጋቸው ሽግግሮች በበዓላት ይገለፃሉ (Gluckman, 1962:2)፣(Gennep, 1960:3)። ለምሳሌ የክርስትና በዓል፣ የክርስትና ስም የሚሰየምበት ብቻ ሳይሆን ህፃኑ ወደ ክርስትና እምነት ተከታዮች መቀላቀሉን ከማብሰሩም በላይ የደረጃ ለውጡንም ያመለክታል። ባህላዊውም ስም ቢሆን፣ ስም ያልነበረው ልጅ መጠሪያ ከሌለው የሚለይበትን፣ የራሱ ስም ከማግኘቱ ባሻገር፣ በወጣለት ስምና በተዘጋጀው በዓል ማብሰራያነት ወደ ማህበረሰቡ መደመሩን የሚረጋገጥበት የማንነቱ መገለጫና የማህበረሰቡ ባህል ማሳያ መንገዶች አንዱ ሲሆን፣ ቤተሰቦቹንም፣ በየግላቸው ከሚጠሩበት ነጠላ ስማቸው፣ "የዕገሌ አባት፣ የእገሌ እናት" መባልን ያነናዕፉቸዋል። (Aregga, 2005:41)

በኩር ልጅ አባትና እናቱ ሁለት ሆነው ጀምረው ወደሶስት ማደጋቸውን፣ ዘር መቀጠላቸውን ያፈሩትንና ወደፊት የሚያፈሩትን ሀብትና ንብረት፣ ከወላጆቻቸው

የወረሱትን፣ የትውልድ ታሪክና ባህል በቀጣይነት የሚያወርሱትን ማግኘታቸው ማብሰሪያ ነው። በማህበረሰቡም ውስጥ ቀጣይ ትውልድ መጨመሩን ያመለክታል።

የስም ስያሜን ሥነሥርዓት የደረጃ ለውጥ ማህበረሰባዊ ባህርይ እንዲኖረው የሚያደርገው፣ ማህበረሰቡ በሰፊው የሚያከብረውና የሚሳተፍበት ሲሆን ነው። ይህ ደግሞ በብዛት ተግባራዊ ሆኖ የሚታየው በወንድ ልጅ የስም ስያሜ ጉዳይ ላይ ነው (Gennep 1960:62)።

እነዚህ በዚህ በንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት ንዑስ ርዕስ ሥር የቀረቡት ነጥቦች፣ በቦረና ኦሮሞ የበኩር ልጅ ስም ስያሜ በዓል ክዋኔዎችም ውስጥ ጎልተው የሚታዩ መሆናቸውን በሚከተሉት ምዕራፎች ውስጥ እንመለከታለን።

4. የቦረና የስም ስያሜ ሥርዓትና የፎክሎር መከሰቻ አውድ

4.1. የስም ስያሜ በቦረና

የቦረና የስም ስያሜ ሥርዓት ሁለት መልኮች አሉት። እነሱም Moggaasaa (ሞጋሳ) እና Gubbisaa (ጉቢሣ) ይባላሉ። ቀጥለን ሁለቱን በዝርዝር እንመለከታለን

4.1.1. Moggaasaa (ሞጋሳ)

የሞጋሳ ቀጥታ ትርጉሙ ስም ስያሜ ነው። በዚህ የስም ስያሜ ሥርዓት፣ ስም የሚወጣላቸው የቦረና አሮሞ ልጆች፤ ሴቶችና ታናናሽ ወንዶች ናቸው።

አፈፃፀሙ ቀለል ያለ፣ ጥቂት ሰዎችን የሚያሳትፍ፣ ቤት ባፈራው ዝግጅት ብቻ በአንድ ቀን ውስጥ የሚጠናቀቅ ነው። የአሠያየሙ ሥርዓት ውጣ ውረድ የሌለበት ቢሆንም አስፈላጊው ሥነሥርዓት እንዲሟላ ይጠይቃል። "Moggaafni sagalee annan nyaatamu qofa dhiyeessitee maqaa baasan. Akki itti baasan garuu tokkuma" (ቦርቦር ቡሌ፣ ቃለመጠይቅ ሚያዝያ 24 ቀን 1999)።

ይኸውም፦ የስም ስያሜው መከወኛ ቀን በAyyaantuu (አያንቱ) እንዲረጋገጥ ይደረጋል። /ገዱ ጥሩ የሆነ ቀን ይመረጣል/። የሚሰየመው ስም በአካባቢው በሕይወት ካሉ ሦስት ልጆች፣ ወላጆቻቸውም በህይወት የሚገኙ ስም ጋር የተመሳሰለ እንዲሆን ይጠበቃል። አባት ለተሰያሚው /ለተሰያሚዋ/ ስመታ ይሰጣል። የስም ስያሜው ሥነሥርዓትም ማታ ላይ ይከናወናል። በሥነሥርዓቱ ላይ የተገኙ ሁሉ የቀረበውን በልተው፣ ጠጥተው ጨፍረው ደስታቸውን ይገልፃሉ።

4.1.2. Gubbisaa (ጉቢሣ)

ጉቢሣ ለታላቅ ወንድ ልጅ ስም ስያሜ በዓል የተሰጠ መጠሪያ ነው። ጉቢሣ በሁለት መልክ ሊታይ ይችላል። የመጀመሪያው የደበሌ ጉቢሳ (Gubbisaa-Dabballee) ሲሆን፣ ሁለተኛው የበኩር ልጅ ስም ስያሜ (Gubbisa Angafaa) ነው።

4.1.2.1. Gubbisaa-Dabballee (የደበሌ ጉቢሣ)

ደበሌ ጉቢሣ በገዳ ሥርዓቱ ደበሌ በሚለው የዕድሜ ክልል ሥር የታቀፉት ወደ ተከታዩ የዕድሜ ክልል "ጋሜ" (Gaammee) ሲሸጋገሩ የሚከወነውን የስም ስያሜ ሥርዓት የሚመለከት ነው። በዚህ የስም ስያሜ ሥርዓት፣ ስም የሚሰጣቸው በገዳ ሥርዓ

ቱ በያአ (yaa'aa) ውስጥ የታቀፉ (የወቅቱ የገዳ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት) ደበሌዎች ናቸው።

የገዳ ሥርዓቱ የየፓርቲዎቹ መሪዎች (አባገዳዎች) በስልጣን ዘመናቸው ከስምንቱ ዓመት ውስጥ ከሚከወኑት አንዱና ትልቁ፣ ተመርጠው አራት ዓመት እንደሠሩ፣ የአራት ዓመት የሥራ ክንውን ማስገምገም ነው። በዚህ በግምገማ ወቅት በሥልጣን ዘመኑ ከደበሌ ወደ ጋሜ ደረጃ ሊሸጋገሩ የተዘጋጁትን ደበሌዎች ይሰይማል።

የነዚህ በገዳ ሥርዓቱ ወላጆቻቸው በሥልጣን ላይ ያሉት ደበሌዎች የስም ስያሜ ሥነሥርዓት በወላጆቻቸው ቤት የሚዘጋጅ አይደለም። በየስምንት ዓመቱ የሚከወን የየፓርቲው አንዱ ተግባር በመሆኑ፣ ነገሌ ከተማ አቅራቢያ ባለው "ኑራ" (Nuraa) በተባለ የገዳ በዓላት መከወኛ ቦታ ይፈፀማል።

ደበሌ፣ በገዳ ሥርዓቱ የሥልጣን እርከን የስምንት ዓመት ቆይታ ላይ ያሉትን የምክር ቤት አባላት ወንዶች ልጆች ዕድሜያቸው እስከ ስምንት ዓመት ያሉትን በሙሉ ያጠቃልላል። አንድ ቤተሰብ በስምንት አመቱ ውስጥ አከታትሎ ያፈራቸው ልጆች ካሉ ሁሉንም ይይዛል። የስም ስያሜ በዓሉ ለነዚህ በየቤተሰቡ ላሉት ደበሌዎች ሁሉ በጋራ አንድ ጊዜ የሚከወን ይሆናል።

በበዓሉ ሥነሥርዓት አከዋወን መሠረት በታቀደለት ጊዜ የደበሌን ደረጃ አጠናቀው ወደ ጋሜ የሚሸጋገሩ ወንዶች ልጆች ያሏቸው አባቶች ከመኖሪያ አካባቢያቸው ጉዟቸውን ወደ ኑራ ያደርጋሉ። በገዳ ሥርዓቱ ስልጣን ላይ ያሉት ሁሉ በበዓሉ ላይ ይገኛሉ። ኑራ ላይ የየደበሌዎቹ ቤተሰቦች ለየራሳቸው የበዓሉን መከወኛ Galmaa (ገልማ) ይሠራሉ። በዚህ በዓል ላይ ሌሎች ሁለት ዋና ዋና ተግባራትም ይከወናሉ።

የመጀመሪያው፣ እያንዳንዱ የደበሌ አባት ልጁን ይዞ በበዓሉ ገልማ ውስጥ ይገኛል። እናትየው ወተትና ውሃ ቀላቅላ ከእንጨት በተዘጋጀ ሳህን መሰል ዕቃ ታቀርባለች። እናትየዋ ይህን የውሃና ወተት ውህድ በልጁ ወጉር ላይ እያንጠባጠበች እንዲርስ ተደርጎ አባትየው ይላጨዋል። ወጉር የመላጨቱ ሥነሥርዓት የራሱ የሆነ ደንብ አለው። ለምሳሌ በዚህ በዓል ላይ አንድ ቤተሰብ ከአንድ ልጅ በላይ ይዞ የሚቀርብ ከሆነ ወጉር መላጨቱ ከታላቅ ጀምሮ ወደ ታናሽ ይሸጋገራል። ከዚያ በኋላ የተላጨው አናታቸው ላይ ትንሽ ጨርቅ ጣል አድርገው እርቃናቸውን ከገልማ ይወጣሉ። ይህን የሚያደርጉት በዓሉን ለማክበር የመጡት ትኩረት ለመሳብና ለማሳቅ ነው። (ቦርቦር ቡሌ፣ ሚያዝያ 24 ቀን 1999፣ ቃለመጠይቅ)።

በማስከተል አባትና እናት ልጆቹን ይዘው ለስም ስያሜ ሥነሥርዓት አፈፃፀም ተዘጋጅተው ወደሚጠባበቁዋቸው የኑራ አካባቢ አባ ገዳ ጋ ይሄዳሉ። እያንዳንዱ አባት ለልጁ እንዲወጣለት ቀደም ብሎ የመረጠውን ስም በመጥቀስ እንዲሰየምለት ይጠይቃል። ብዙውን ጊዜ በቤተሰብ የቀረበው ስም ይፀድቃል። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ አባገዳው የሚሰጠው ስያሜ አለ። ጀልዴሣ የሚል ስም ብዙውን ጊዜ የሚሰየመው በአባ ገዳው ነው።

በዚሁ የደበሌ ስም ስያሜ ወቅት ልጅ የሌላቸው ሴቶች፣ ልጅ እንዲሰጣቸው በዓሉ የሚከበርበት ዋርካ (Odaa) ሥር ሆነው ይፀልያሉ። ከሥርዓቱ ፍፃሜ በኋላ ሁሉም ወደ መጡበት መኖሪያቸው ይመለሳሉ።

ይህ የሽግግር በዓል ካለፈ በኋላ በባህርይም ሆነ በቋንቋ አጠቃቀም ረገድ ለውጥ ይታያል። በዓሉ እስከሚከበርና ስም እስከሚወጣ ድረስ "አንቺ" እየተባለ የሚጠራው ደበሌ፣ እንደ ወንድ መጠራት ይጀምራል። የቅፅል ስሙም አባገዳ ባወደቀው አዲስ ስም ብቻ ይተካል። ለደበሌ የሚወጣው ስም የአያቱ ስም ነው።

4.1.2.2. Gubbisaa Angafaa (የበኩር ልጅ ስም ስያሜ)

ይህኛው ጉቢሣ ከሁለቱ የስም ስያሜ አይነቶች ይለያል። ጉቢሣ የቦረና ኦሮሞ የሆኑ ሁሉ ለመጀመሪያ ወንድ ልጅ ስም ስያሜ፣ በቤታቸው የሚያዘጋጁት ትልቅ በዓል መጠሪያ ነው። በቦረናዎች አጠራር ጂለ ጉቢሣ (Jila Gubbisaa) በመባል ይታወቃል። "Jila" ትልቅ ክብረ በዓል፣ ትዕይንቶች የሚበዙበት ብዙ ሰዎች የሚሳተፉበት የበዓል አይነት ነው። አንድ ቤተሰብ ከታላቅ ልጅ ተከትለው የተወለዱ ታናናሽ ልጆች ወንዶችም ይሁኑ ሴቶች ቢኖሩት፣ በዚሁ በጉቢሣ በዓል ላይ ሌላ ዝግጅት ሳያስፈልግ ይሰየማሉ (ni moggaafamu)። የበዓሉ ባለቤት ግን የበኩር ልጁ ነው።

ይህንኑ አብ ቦርቦር ቡሌ፣ "Gubbifni mucaa qara dhalaniifi. Namni fiixa qabu gosa qabu waamee namni heddu itti hirmaatu kan gurra kennaniif. Namni ijoollee kudhan qabaatullee kan gubbisu tokkuma. Guyyaa gubbisa mucaa qaraa madhaa kan ta'an lamallee moggaasuu ni danda'a..." ብለዋል።

የበኩር ልጅ ስም ስያሜ ጉቢሣ በዓል ታስቦበት፣ ሰፋ ያለ ዝግጅት ተደርጎ የሚፈፀም በዓል ነው። አንድ የጉቢሣ በዓል ባለጉዳዮች (warra jilaa) በመጀመሪያ ጊዜ ላፈሩት ለታላቅ ልጃቸው ስም ለመስየም ሲወስኑ ወደ ዝግጅቱ ከመገባቱ አስቀድሞ ለበዓሉ መከወኛ ያቀዱት ቀን ረዘም ያለ ጊዜ ሲቀረው፣ ለዘመዶቻቸው ለወገኖቻቸው፣

ለንጣቸው፣ ለጓደኞቻቸው፣ "የታላቅ ልጃችን የስም ስያሜ በዓል በ..... ስለሆነ እንድትገኙልን" ብለው ይናገራሉ።

የጉቢጣ በዓል ጉዳይ የልጁ ወላጆች የብቻ ጉዳይ አይደለም። የወገኑ፣ የንጣው ሁሉ ጉዳይ ነው። እነዚህ የታላቅ ወንድ ልጅ ወላጆች፣ ለበዓሉ ዝግጅት አቅም የሚያንሳቸው ቢሆን እንኳ ከዘመዶቻቸው ባሻገር የንጣ አባል የሆኑ ሁሉ እገዛ አድርገው፣ በዓሉ አስፈላጊ በሆነ አኳኋን እንዲፈፀም ይደረጋል።

Gubbifni dirqama. Namni ilma gubbifachuuf horii dhaballee gosti seera ittiin walgargaaru waan qabuuf horiin bahee ni gubbisa. Boorana ta'ee kan hin gubbifne seera cabse jedhamee waan gosaaf godhan hin godhaniif garuu yakka qaba hin jedhan gosa keessaa baha malee (ቦርቦር ቡሌ ቃለ መጠይቅ ሚያዝያ 24 ቀን 1999)

ስም ያልተሰየመ ልጅ በአጋጣሚ ቢሞት እንኳ ቀብሩ የሚፈፀመው ቤት ውስጥ ነው። ከማህበረሰቡ አልተቀላቀለም ወይም ሙሉ ሰው አልሆነም ማለት ነው። ጉቢጣ የቦረናነት ምልክት፣ የማንነት መገለጫና መለዮ ስለሆነ ተስተጓጉሎ የሚቀር እንዳልሆነ አብ ቦርቦር ተናግረዋል።

የጉቢጣ በዓል የሚያዘጋጅ ቤተሰብ (warra jilaa) የበዓሉን መከወኛ ጊዜ ጠቅሶ ወገኑንና ንጣውን ከመጥራቱ አስቀድሞ ለበዓሉ የሚስማማውን ጊዜ /ቀን/ /ጥሩ ገድ የሆነ/ ለይቶ ለመወሰን እራሱ ካላወቀ ወደ Ayyaantuu (አያንቱ) ይሄዳል። አያንቱ ልዩ መንፈሳዊ ተሰጥኦ ያላቸው ሰዎች ናቸው። "Asaastuu Waaqaa" ተብለውም ይታወቃሉ። ይህ ማለት ከፈጣሪ ወይም ከአምላክ ጋር ግንኙነት አላቸው ተብለው የሚታመንባቸው ናቸው። ጥሩና መጥፎ ገድ የሚውልበትን ቀን ለይቶ የማወቅ ችሎታም አላቸው ስለሚባል፣ የጉቢጣው በዓል ቀን ጥሩ ገድ ባለው ቀን ላይ እንዲውል ይጠየቃሉ። እነርሱም ኮከብ ቆጥረው፣ በወር ውስጥ ካሉት ሃያ ሰባት በዓላት መካከል "ቢታ" (Bitaa)፣ "ጊዳዳ" (Gidaadaa) የተባሉ በዓላት ባልዋሉባቸው ቀናት ውስጥ የስያሜ በዓሉን እንዲከውኑ ይናገራሉ።

በጉቢጣ ስም ስያሜ ሥርዓት "እልማን ኮርማ" የተባሉት፣ ማለትም በገዳ ሥርዓቱ ቀመር መሠረት አድርገው የተወለዱ ልጆች በሙሉ የስም ስያሜያቸው በተመሳሳይ ጊዜና ቀን የሚወሰን እንጂ፣ ባለቤቱ በዚህ ቀን ይመቸኛል ብሎ መወሰን አይችልም። በግለሰቡ ደረጃ ሊወሰን የሚችለው ዓመቱን መምረጥ ብቻ ነው። በዚህኛው ዓመት ያልሞላለት በተከታዩ ዓመት ሥርዓቱ በሚፈቅደው ጊዜ እንዲፈፀም ያደርጋል።

እልማን ጃርሣ የተባሉትም (በገዳ ሥርዓቱ መውለድ ከሚገባቸው ዕድሜ ዘግይተው የተወለዱ) ይህን ድንጋጌ የሚጠብቁ ቢሆኑም ልጆቻቸው ከአንድ ዓመት በላይ

ዕድሜ ማስቆጠር ሲጀምሩ የተመቻቸው ጊዜ፣ ጥሩ ገድ ያለውን ቀን እራሳቸው ካላወቁ፣ በአያንቱ አስለይተው፣ ዘመዶቻቸውን፣ የጎሣ አባሎቻቸውን ጠርተው ያከብራሉ። በእልማን ኮርማና በእልማን ጃርሣ የጉቢጣ በዓል አከባበር መሀከል ያለው ልዩነት በዓሉ የሚወስደው ጊዜ ብቻ ነው። ይኸውም፣ የእልማን ኮርማ ልጆች የጉቢጣ በዓል መሰየሚያ ገልማ ሥራ ሦስት ቀን የሚቆይ ሲሆን፣ የእልማን ጃርሳ መሰየሚያ ገልማ በሁለት ቀን ውስጥ የሚጠናቀቅ ይሆናል።

የቀናቱ ስፋትና ጥበት የድርጊቶችን መብዛትና ማነስ አያመለክቱም። የቀናቱ ልዩነት፣ በገዳ ሥርዓቱ የጊዜ ቀመር መሠረት ተወልደው ለበዓሉ ለደረሱት ክብርና ክብደት ለመስጠት ሦስት ቀን እንዲሆን ተደረገ እንጂ፣ የገልማው ሥራ ክብደትና ውስብስብነት ከሁለት ወደ ሦስት ቀናት ቆይታ አላሳደጉትም። (ቦርቦር ቡሌ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዝያ 24 ቀን 1999 ዓ.ም.)

የበዓሉ ባለጉዳዮች (አባጅላና ሃደ ጅላ) ቀኑን ለይተው ካወቁ በኋላ ጥሪያቸውን ያስተላልፋሉ። የበዓሉ ጊዜና ቀን እስኪደርስ በቤታቸው የሚያስፈልገውን ዝግጅት አጠናክረው ይቀጥላሉ። ለዝግጅቱ እናትና አባት የየራሳቸው የሆነ የሥራ ድርሻ አላቸው።

በቦረና አሮሞ የሥራ ክፍፍል መሠረት፣ በቤት ውስጥ የሚከወነውና የመኖሪያ ቤት ግንባታ በሴቷ ትከሻ ላይ የወደቀ ጉዳይ ነው። በውጭ የሚሠሩ፣ የበዓላት ጉዳይ (jila tolchuu)፣ የአካባቢውን ሰላም መጠበቅ (ወታደራዊ ሥራ)፣ ከብቶች ሣርና ውሃ ወዳለበት እሩቅ ቦታ ማሠማራት፣ ከጥልቅ ጉድጓድ ለከብቶች ውሃ ማውጣትና ማጠጣት የወንዱ ድርሻ ነው (ቦርቦር ቡሌ፣ ቃለ ምልልስ ሚያዝያ 24 ቀን 1999 ዓ.ም.) ።

በዚሁ የሥራ ድርሻ መሠረት ለበዓሉ የልጁ እናት ከቆዳ የሚሠራ "ከሎ" (kaloo) ታዘጋጃለች። ከሎ ለጉቢጣ በዓል አስፈላጊና ዋንኛ አልባሳት ከሚባሉት መሀከል አንዱ ነው። ለማዘጋጀት ከቆዳ በተጨማሪ ዛጎል ያስፈልጋል። ዛጉሉ ደግሞ በገዳ ሥርዓቱ በሥልጣን ላይ ያሉ ቤተሰቦች ከሆኑ ከደበሌ ወደ ጋሜ ሽግግር ሲደረግና ፀጉር ሲላጭ ተለቅሞ ከሚቀመጠው እንጂ ተገዝቶ ከሚቀርበው አይዘጋጅም።

ይህን በዛጎል ያጌጠ ከሎ የሚለብሱት የልጁ እናት፣ አባትና ሴት አያቶቹ ናቸው። ለበዓሉ ቢያንስ አምስት ከሎዎች ያስፈልጋሉ። እናት አንድ፣ ሁለቱ ሴት አያቶችም አንዳንድ፣ አባትየው ሁለት።

እልማን ጃርሳ ከሆኑ ደግሞ፣ ከሎ አዘጋጅተው ልጃቸውን ከሰየሙ ቤተሰቦች ይዋሳሉ። ሲዋሱ እንዲሁ በደረቁ አውሶኝ ብለው አይጠይቁም። "ደራራ ተንቦ" እጅ መንሻ ይዘው ነው። ይህ ደራራ የሚባለው ቡና፣ ወተት፣ ትንባሆ፣ ሰርዶን የጠቃልላል። እነዚህ ቁሶች መለማመኛ (መማፀኛ) ናቸው። (ካሉ ጂሎ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ሰኔ 12 ቀን

1999 ዓ.ም.)። ሌላው እናትየው የምታዘጋጀው ለበዓሉ ተሳታፊዎች ማስተናገጃ የሚውል ቅቤ፣ ቡና፣ ማጣፈጫዎችን እንዲሁም የምግብና መጠጥ ዝግጅት ዕቅድ ይሆናል።

በአባትየው በኩል የሚደረገው ዝግጅት፣ በእናትየው የቀረበውን ዕቅድ መርምሮ ካሉት ከብቶች ውስጥ ሊሸጡ የሚችሉትን መርጦ፣ ለበዓሉ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች በተለይ ለምግብና መጠጥ ማዘጋጃ የሚውሉትን መግዛት ነው። ከዚህ በዓል ላይ መቅረት የማይችሉ እንደ "ደራራ ተንቦ" ያሉት በዚህ ግገር ውስጥ ይጠቃለላሉ።

4.2. የበኩር ልጅ ስም ስያሜ በዓል ክዋኔዎች ሂደት

በ1999 ዓ.ም. በቦረና ዞን በያቤሎ ወረዳ ከተከበሩት የበኩር ልጅ ስም ስያሜ በዓላት እኔ በአካል ተገኝቼ የተመለከትኩትና ሙሉ የክዋኔ መረጃዎች የሰበሰብኩት ከያቤሎ ከተማ ወደምዕራብ አቅጣጫ ሰላሳ ኪሎ ሜትር ርቆ ከሚገኝ ዳዲ (Dhaddii) ከተባለ የገጠር ቀበሌ ነው።

በዚህ በተጠቀሰው ቀበሌ ከሰኔ 14 ቀን እስከ ሰኔ 17 ቀን 1999 ዓ.ም. የቆየውን የበኩር ልጅ ስም ስያሜ በዓል ያከበሩት አባሩፋ ጃተኒ የተባሉ ሰው ናቸው።

አብ አባሩፋ ጃተኒ የቦረና ተወላጅ፣ የሰቦ ጎሣ አባል ሲሆኑ፣ የከተማ ነዋሪ፣ የተማሩና የአንድ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ባልደረባ ናቸው። በዓሉን ከቤተሰቦቻቸው ጋር፣ በትውልድ መንደራቸው ለማክበር ሄዱ እንጂ፣ አሁን የዳዲ ነዋሪ አይደሉም።

ባለጉዳዩን መማርና ከተሜነታቸው ከባህላቸው ሊያርቃቸው አልቻለም። እንዲያውም ቤተሰባቸውን ጠቅልለው ወደ ትውልድ መንደራቸው እንዲሄዱና በባህሉ መሠረት የልጃቸውን ትልቁን በዓል እንዲከውኑ፣ ከቤተሰብ የወረሱትን የባህሉን ወግ እንዲያጠነክሩ አደረጋቸው እንጂ።

አብ አባሩፋ የከተማ ነዋሪ በመሆናቸው የከተማ ጓደኛና ቤተዘመድም ስለጠሩ በበዓሉ መከበሪያ መንደር ለከተሜዎች ማስተናገጃ ማረፊያ ድንኳን ከዋዜማው ጀምሮ ተክለዋል። የበዓሉን ክዋኔ ቀርያ ማቆየት እንዲቻል የበዓሉ ትልቁ ክዋኔ የሚፈፀምበት ዕለት ሌሊቱን ስለሚጨምር የኤሌክትሪክ ብርሃን ለማግኘት ጀኔሬተር አዘጋጅተዋል። እኔም በቦታው የደረስኩት በበዓሉ ዋዜማ ዕለት በመሆኑ ይህን ቅድመ ዝግጅት ተመልክቻለሁ። የእንግዶች መቀበያና መመገቢያ ሁለት ትላልቅ ድንኳኖች፣ አባሩፋ፣ ባለቤታቸውና ልጆቻቸውም የመንደሩ ነዋሪ ስላልሆኑ ትንሽ ድንኳን፣ ለዞኑ የባህልና ቱሪዝም አባላት፣ ለእኔም ለብቻ ድንኳን አዘጋጅተዋል።

በበኩር ልጅ ስም ስያሜ በዓሉ የሦስት ቀን ቆይታ ውስጥ በዋዜማውና በየዕለቱ የተለያዩ ክዋኔዎች ተስተናግደዋል። በአብ አባሩፋ ቤት የዋዜማው ዕለት ሁለት ሰዎች ሀዩ (Hayyuu) የተባሉ በማህበረሰቡ ትልቅ ቦታ የሚሰጣቸው ተመርጠው የእንጨት ሁሉ ታላቅ የተባለ፣ የወደ*ማ (Waddeessaa) ሁለት እንጨት ቆርጠው አመጡ። እነዚህ ሰዎች እንደወትሮው ውሎአቸው አለባበስ ሳይሆን ለበዓል ቀን የሚያስፈልገውን አለባበስ አሟልተው ነው የተገኙት። በራሳቸው ላይ የቦረና መለያ ምልክት የሆነውን ሱሬ ሩፋ (Surree Ruufaa) ጠምጥመው፣ በእጃቸው ሆሮሮ (Horooroo) የአባገዳ በትር አይነት፣ ከአውራሪስ ወይም ከቀጭኔ ቆዳ የሚዘጋጅ መግረፊያ መሰል፣ ሊቾ (Lichoo) ይዘው፣ እንጨቱ ወደሚገኝበት ቦታ አመሩ። ከሆሮሮ በስተቀር ዱላ ወይም ጦር አይያዝም። ይህ የሚያመለክተው ማንንም የማይነኩ ሰላማዊ መሆናቸውን፣ እንዲሁም ሌላው አካል ይህን ተገንዝቦ እንዳይተናኮላቸው ማሳወቂያ ዘዴ ነው። (ካሉ ጂሎ፣ ቃለ መጠይቅ ሰኔ 12 ቀን 1999፣ ጃተኒ ዲዳ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዝያ 22 ቀን 1999)።

ሀዩዎች ቆርጠው ያመጡትን ወደ*ማ (Waddeessaa) ከበዓል መከበሪያው ደጃፍ የከብቶች በረት ምልክት ከሆነው ቡቱሜ (Butume) ጎላ አስቀመጡት።



አባጂላው (አባሩፋ ጀተኒ)

በዚሁ በዋዜማ ዕለት በበዓሉ መከበሪያ መንደርና አካባቢው ካሉት ከቦረና አባላት መካከል ቶርበን ጅላ (torban jilaa) የተባሉትም ተመረጡ። ቶርበን ጂላ የበዓሉ ዋና ምሶሶ የሆኑ፣ ሰባት አባላትን የያዘ የበዓሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሊባል የሚችል ነው።

በዚህ በቶርበን ጅላ አወቃቀር ውስጥ የቦረና ሁለቱ ትላልቅ ክፍሎች ስብጥር ጎልቶ ይታያል። ይኸውም የጉቢሣ በዓል የተዘጋጀለት ልጅ አባት አባ ሩፋ ጃተኒ የሰቦ አባል ናቸው። የቶርበን ጅላው አባላት አባትየውን ጨምሮ፣ አራቱ የሰቦ አባላት ሲሆኑ፣ የተቀሩት ሦስቱ ደግሞ የጎና ጎሣ አባላት እንዲሆኑ ተደረገ። እነዚህም አባላት ሲመረጡ ታላቅ ታናሽነታቸውን ለመለየት የየትኛው ንዑስ ጎሣ አባል እንደሆኑ እየተጠየቁ የታላቅ ጎሣ አባል ለሆኑ ቅድሚያ እየሰጡ መረጡዋቸው። ለምሣሌ ከሰቦ ንዑሳን ጎሣዎች ድገሉ ከጎና ደግሞ ሩለሌ ታላቅ ናቸው።

ከነዚህ ከሰባቱ የበዓሉ አስፈፃሚ አባላት አንዱ ቀደዱ (Qadadduu) ተብሎ ተመረጠ። ቀደዱ የበዓሉ ሥነሥርዓት መሪ ነው። ቀደዱ ከሁለቱ ዋና ዋና የቦረና ክፍሎች የአንዱ አባል መሆን ይችላል። ቀደዱን ለመምረጥ የሚያስፈልገው መስፈርት፣ ተመራጩ በገዳ ሥርዓቱ በሉባ (luba) ደረጃ ውስጥ ያለፈ መሆን ነው። ሉባ ማለት አባገዳ ለመሆን የሚያስችሉትን ሂደቶችና ደረጃዎች ያጠናቀቀ ማለት ነው። በዚህ መሠረት በዋዜማው ዕለት ቶርበን ጅላዎቹና ቀደዱው ማን እንደሆኑ ተለይቶ ታወቀ።

4.2.1. Muka Muraa (**የመጀመሪያው ዕለት - "ሙከሙራ"**)

የሙከሙራ ቀጥታ አማርኛ ትርጉሙ እንጨት ቆረጣ የሚል ነው። በዚህ በመጀመሪያው ዕለት ጥሪ የተደረገላቸው ከሩቅ የሚመጡ ቤተዘመዶች፣ የጎሣ አባላት፣ ጓደኞቻቸው አብዛኛዎቹ ተገኝተዋል ማለት ይቻላል።

ዕለቱ ሰኔ 14 ቀን 1999 ነው። በዚህ ዕለት፣ ከጠዋቱ አንድ ሰዓት አካባቢ የበዓሉ ባለጉዳዮች፣ እናት፣ አባት፣ የልጁ የሴት አያቶችና ልጁ ከወትሮ የተለየ ልብስ ለብሰው ወጡ። ሴቶች ከሥር "Gorfoo" ጎርፎ (ከቆዳ የተሠራ ቀሚስ) ከላይ ለጉቢሣ በዓል የተዘጋጀውን "ከሎ" ደርበዋል። በእጅ ሲቄ (ቀጭን በትር) ይዘዋል። አባት (Abbaa jilaa) ደግሞ ከታች ሽርጥ ከላይ ሴቶች እንደለበሱት አይነት ሁለት ከሎ ለብሰዋል፣ በእጃቸው፣ ዳኒሣ በትር እና ሊቾ ይዘዋል። እራሳቸው ላይ ሱሬ ሩፋ ጠምጥመዋል። አባሩፋ ከበኩር ልጃቸው በተጨማሪ ታናሹንም በዚሁ በዓል ላይ በሞጋሣ ሥርዓት ለማሰየም ይዘው ስለቀረቡ ለሁለቱም ልጆች አንድ አይነት አዳዲስ ልብስ አልብሰዋቸዋል።

አባጂላ፣ ሃደጂላና አዩት ለጉዚማ የሚያስፈልገውን አለባበስ ተጎናጽፈው

እንዲህ ባለ ሁኔታ የባህልና የበዓል ልብስ ለብሰው ካቀረቡ በኋላ የበዓሉ አዘጋጅ እናት (Haadha jilaa) ወ/ሮ ከሹ አባሩፋ አነስ ያለ ቁርበት ይዛ ከፊት እየመራች ከከብቶች በረት ገባች። ከኋላ ደግሞ ሌሎች ሴቶችና የአባጅላው እናት ተከትለው የለሰለሰ ቁርበት ይዘው በትንሽ ቢላዋ መሰነጣጠቅ ጀመሩ። ይህን ሰነጣጥቀው በነብ ቀደው ያወጡትን በልጁ እናት በወ/ሮ ከሹ አባሩፋ እጅ ላይ አጠለቁላት። ይህን የወግ ቁስ (Saqaa) ሰቃ ይሉታል። የታላቅ ወንድ ልጅ እናት መሆኗ የሚገለፅበት ነው። ተጉልትለው በተንጠለጠሉት ጫፎች ላይ ዶቃና የተለያዩ ድምፅ የሚሰጡ ማጌጫዎችም ሰካኩበት። ያንን ተሰነጣጥቆ በእጇ ልክ የተዘጋጀውን ቆዳ አጥልቃ አስቀድማ ይዛ በቀረበችው ቁርበት ላይ፣ ከበረት አዛባ በቀኝ በኩል ያለውን አንስታ በበረቱ መውጫ በቀኝ በኩል በረቱ ውስጥ እንደ መከመር ሞለል አድርጋ ተወች። ከበረቱ በግራ በኩል ባለው አካባቢም እንዲሁ አነሳስታ ከበረቱ ውጭ የከብት በረት ምልክት ነው ከሚባለው ከቡቱሜ (Butumee) እንጨት በኋላ ሞለል አድርጋ እንደመከመር አደረገች።

ከሁሉ ሥራ በፊት አዛባ ማንሳቱ አካባቢ ማፅዳት መቅደሙን ለማመልከት ነው። ከብቶች ከበረት ሲወጡ እንዳይረጋገጡ ቀድሞ ማንሳት ስለሚያስፈልግ ነው።

ለሃደ ጂላዋ ሰቃ ለማዘጋጀት ቁርበት መተልተል ሲጀመር

በዓሉ ቡተጀመረበት ዕለት ሃደ ጀላዋ ከበረት አዛባ ስታነሳ

ከዚያ በኋላ ወደቤት ተመልሰው "ቡነቀላ" አዘጋጅተው፣ ተመረቁ። ቡነቀላውን ያዘጋጁት የአባሩፋ ባለቤት የቅርብ ዘመድ የሆኑ ወ/ሮ ሲሆኑ ምረቃውን የሰጡት በሀዩ ደረጃ ያሉ ሽማግሌ ናቸው። ምረቃው በጣም ረዥም ነው።

Bobba'aan nagayaa	-	የሚሰማራ ሰላም
Bobbaan nagayaa	-	ስምሪት ሰላም
Oolmaan nagayaa	-	ውሎ ሰላም
Galchuun nagayaa	-	መመለስ ሰላም

እያለ የዕለቱን እንቅስቃሴ ከመመረቅ ጀምሮ፣ ህዝቡን፣ ሥርዓቱን፣ አካባቢው ሰላም እንዲሆን የሚመኝ ሀሳብ እያቀረበ ጉዳዩን እያሰፋ ይሄዳል። ቡነቀላው ተመርቆ ከቀረበ በኋላ ቀምሰው፣ የልጁ እናት መጥረቢያ ይዛ ሌሎች ሴቶችን እየመራች ሀንደራካ (Handaraaka) የተባለ እንጨት ቆረጣ ሔዱ። እንጨቱን መጀመሪያ እራሷ ቆርጣ፣ ለሴቶች ቅርንጫፎቹን ከፋፍላ እርሷ እየመራች፣ መደመ እንጨት ተቆርጦ የተቀመጠበት

ቦታ ላይ አሳረፉ። ይህ ሀንደራክ የተባለ እንጨት ከወይማ ቀጥሎ የሚቆረጥ ለበዓሉ ገልማ እንደ መሠረት መጣያ የሚወሰድ ነው። (ጃተኒ ዲዳ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ሰኔ 14 ቀን 1999)

ሀንደራክውን ቆርጠው አምጥተው ካስቀመጡ በኋላ ካርሌ የሚባል ዘፈን ዘፈኑ። ቁጥራቸው አነስተኛ ስለነበር አልደመቀላቸውም። ለትንሽ ደቂቃ ወጉን አድርሰው አቆሙ። የዘፈኑ ይዘት ባለጉዳዮቹን በተለይ አባትየውን የሚያሞግስ ነበር።

ሃደጂሳዋ ሀንደራክ /የመሠረት መጣያ/ እንጨት በሴቶች ታጅባ ቆርጠው ሲመለሱ

በዚህ እንጨት ቆረጣ ዕለት (muka muraa) ከሰባት ሰዓት በኋላ ጀምሮ ብዙ ሰዎች ከየአቅጣጫዉ፣ ወጣት፣ አዋቂ ሳይቀር ለገልማ ሥራ የሚውል እንጨት ቆርጠው ወደበዓሉ ቦታ ሲያጓጉዙ ዋሉ። ትላልቅ ለቋሚ የሚሆን እንጨት ወንዶች፣ ቀጫጭኑን ለማገርና ለሣጋ የሚሆነውንና በገልማው ግርግዳና ጣራ እንዲለብስ የሚደረገውን ሣር ሴቶች ቆርጠው፣ አጭደው አመጡ። እዚህ ላይ በዐረናዎች ዘንድ ለበዓል ሆነ መደበኛ መኖሪያ ቤት ለመስራት የሚቆረጠው እንጨት እንደ ተገኘ አይደለም። ሊቀጥል የሚችል ቅርንጫፍ ታይቶ ይቆረጣል እንጂ ግንዱ አይነካም። ለደን ከፍተኛ ጥበቃ ያደርጋሉ።

ለገልማው መሥሪያ የተቆረጠውም እንጨት፣ ሣሩም እንደ መይማውና ሀንደራክው ከበረቱ ደጃፍ ተከምሮ አደረ። ይህ ዓይነቱ የቤት ሥራ ላይ ትብብር የኖረው፣ ጉዳዩ በዓል ስለ ሆነ እንጂ የወትሮ ቤት ሲሠራ እንጨት ቆርጠው የሚሠሩት ሴቶች ብቻ ናቸው።

እንጨትና ሣሩን ሲያንጉዙ የዋሉትንና በእንግድነት ከሩቅ ተጠርተው የመጡት ሁሉ ወደ ቤት ገብተው እንዲስተናገዱ ተደረገ።

መጀመሪያ በበዓሉ ቤት ውስጥ ለተሰበሰቡት እንግዶች፣ አባትየው፣ (Abbaa jilaa) ትንሳሄና ለምለም ቅጠል ይዞ ለእያንዳንዱ ሰው "እነሆ ለምለም" (Hoodhaa! daraaraa) ብሎ ሰጣቸው። እነርሱም፣ "saawwaafi namaan daraari" "በሰው በክብት ለምልም" ብለው ተቀበሉ። ይህ ድርጊት በውስጡ "እንኳን ደህና መጣችሁ፣ ይህን በዓል መርቁልኝ" የሚል መልዕክት ይዟል። የታዳሚዎቹም ምላሽ መሠረታዊ የሆነ ምርቃት ነው። ሀብትና ልጅ አብሮ ይስጥህ ማለት ነው።

ቡንቀላ ቀርበ ሲመረቅ

በመቀጠል ወተትና ውሃ ተቀላቅሎ ለውሃ ጥም ተሰጣቸው በበረናዎች ዘንድ ውሃ ባዶውን መጠጣት እሴት፣ ድርቅ አመልካች ነው። ውሃ ወተቱ ላይ የሚቀላቀለው ጥም እንዲቆርጥ ነው። ከሥጋና ከበቆሎ የተዘጋጀ ንፍሮ የመሰለ ምግብ በትላልቅ ጉድጓዳ ኘላስቲክ ሳህን በቡድን በቡድን ቀርቦላቸው በሉ። ቡንቀላም ተዘጋጅቶ ተከፋፈለ። እስከ በዓሉ ማጠናቀቂያ ቀን ለመቆየት መስነው ከመጡት የሩቅ አካባቢ እንግዶች በቀር ሌሎቹ የፅለቱን ሥራ በዚሁ አጠናቀው ወደየቤታቸው ተመለሱ። የበዓሉ ባለቤቶች እናትና አባት የሚመጡትን ተከታይ እንግዶች እየተቀበሉ፣ ይዘው የሚያመጡትን "ጉማቲ" እየተረከቡ ሲያስተናግዱ ዋሉ። ለሚያድሩት አስፈላጊው መስተንግዶ እንዲደረግ ላስቀመጡዋቸው አስተናጋጆች እየነገሩ፣ ሰው በተገቢው መንገድ ሲስተናገድ አመሸ። ወተት፣ ጠጅ፣ አረቄ፣ በመጠጥነት፣ ለምግብ፣ ፍየል፣ በሬ ታርዶ እየተዘጋጀ ቀረበ።

ቡነቀላ የማያቋርጥ የመስተንግዶ አይነት ነው። በቦረና ቡና ተቆልቶ፣ ተወቅሞ፣ ተፈልቶ አይቀርብም፣ በቡነቀላ መልክ ብቻ ነው። (ኮራ ጉዮ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሰኔ 14 ቀን 1999)

ሴቶች የገልማው መስሪያውን እንጨት ቆርጠው ሲመጡ

4.2.2. Yayyabaa (ሁለተኛው ቀን- የየባ)

በዚህ ቀን ከሚሠሩ ሥራዎች መሀከል ትልቁ፣ የህፃኑ ስም የሚሰየምበትን የበዓል ዳስ "ገልማ" (Galma) መሥራት መጀመር ነው። የስም ስያሜው በዓል የእልማን ኮርማ ከሆነ የገልማው ስራ ይጀመራል እንጂ በዕለቱ አይጠናቀቅም። ማጠናቀቅ ቢቻልም እንዲያድር ይደረጋል። ከእንጨት ቆረጣው ጀምሮ እስከሚጠናቀቅበት ዕለት ድረስ ሦስት ቀን እንዲፈጅ ይደረጋል። ይህ ሁሉ በዓሉ ትልቅ በዓል ስለሆነ ለበዓሉ ለሚሠራው ገልማም ክብደት ለመስጠት ነው። (ካሉ ጂሎ፣ ቃለመጠይቅ ሰኔ 12 ቀን 1999 ዓ.ም.)

በዚህ በሁለተኛው ቀንም እንደ እንጨት ቆረጣው ዕለት ከጠዋቱ አንድ ሰዓት አካባቢ፣ ከብቶች ከበረት ሳይወጡ፣ የልጅ እናት፣ በወጉ ለብሳ ከታች ጎርፎ፣ ከላይ ከሎ፣ በእጇ ሲንቄ ይዛ፣ ሰቃ በቀኝ እጇ አጥልቃ፣ አነስተኛ ቁርበት ይዛ ከኋላ ጥቂት ሴቶች እየተከተሉ ከበረቱ ገባች። በበረቱ ውስጥ በቀኝ በኩል ያለውን አዛባ በቁርበቱ ላይ አንስታ በቀኝ ከበረቱ መውጫ የመጀመሪያ ዕለት ሞለል አድርጋ ከከመረችው ላይ ጨመረች። በግራ በኩል ያለውን እንደትላንትናው አነሳስታ ከበረቱ ውጭ ከተቀመጠው ቡቱሜ ጋ ከተከመረው ላይ ጨመረች።

ከበረቱ ከተመለሰች በኋላ፣ ለገልማው እንደመሠረት መጣል የሚቆጠረውን የሀንዳራካ እንጨት በገልማው መሥሪያ ቦታ ላይ ከአማቷ ጋር አኖሩ። አቀማመጡም ከገልማው በር ትይዩ "ቦሮ" ላይ ነው።

ቀጥሎ የተከወነው የገልማውን ሥራ ማስጀመር ነው። የጉዚማ ሥነሥርዓት የሚፈፀምበትን ገልማ ሥራ የእንጨት መትከያ ጉድጓድ ቆፍሮ ያስጀመረው "ቀደዱ" ተብሎ የተመረጠው ሰው ነው። ከቀደዱ በፊት ማንም መጀመር ወይም ማስጀመር አይችልም። የበዓሉ ባለቤት (Abbaa jilaa) እንኳ ምሳሩን መሰንዘር የሚችለው ከቀደዱ ቀጥሎ ነው ይባላል። ለዚህም ነው መሰለኝ አባሩፋ ቀደዱው መሬቱን ቆፍሮ እንጨቱን ተክሎ ለማጥበቅ ከላይ ሲመታ ያዙለት እንጂ ቀድመው ምንም አላደረጉም።

የገልማው ሥራ በቀደዱው ሲጀመር

ቀደዱው ይህን የገልማውን ሥራ ሲጀምር "mucaan siif haa bulu, haaguddatu" (ልጅህ ይኑርልህ ይደግልህ) ብሎ የመሥሪያ እንጨቱን ልክ "ሀንዳራካው" እንጨት የተቀመጠበት ላይ ነው የተከለው። አባትየው ከዚያ ቀጥሎ ተከለ። ከዚያ በኋላ ሌሎች የበዓሉ ተሳታፊ ወንዶች ዙሪያውን ቋሚ በማቆም የገልማውን ሥራ ማገዝ ጀመሩ። በባህሉ ቤት መሥራት የሴቶች ድርሻ ስለሆነ ከቋሚ ተክላና ዋና ማገር በኋላ ሙሉ በሙሉ ተረክበው መሥራት ጀመሩ። እናትየዋና አያቱ በንሮ የበሩ ትይዩ ሀንዳራካ እንጨት ከተቀመጠበት ቦታ ጀምረው ሳጋ መጠቅጠቅ ጀመሩ፣ ሌሎችም ተከተሉዋቸው። ወንዶች ማሰሪያ ልጥ እያቀበሉዋቸው፣ ሴቶቹ በዋናነት ገልማውን ሠሩ። በዚህን ጊዜ

ሴቶቹ ካርሌ ማዜም (kaarilee dhaahatu) ጀመሩ። ካርሌ የዜማ ስም ነው። ሴቶች ሁልጊዜ ቤት ሲሠሩ የተለያየ ዜማ ያዜማሉ። በገልማው ሥራ ላይ ሲያዜሙት የነበረው፣

Abbaa jilaa taatee, harka lichoon daaxxee

ባለጉዳይ ሆነህ እጅህ በሊቾ ደመቀ

Abbaa biyyaa taatee dubbiin sibarbaaddee

ባለ ሀገር ሆነህ ጉዳይ ሁሉ አንተን አለ። የሚል ነው። ይዘቱ ማሞገሥ ነው።

የገልማው ሥራ በተጀመረበት ጊዜ

ለገልማው ሥራ ተቆርጦ የመጣው እንጨት በሙሉ ተሠርቶበት ሲያልቅ ሁለቱ የወደ፡ሣ እንጨት እዚያው ቀረ። በዓሉ በሚያበቃበት ሦስተኛው ቀን ማታ ወደ ገልማው ይጣል ተባለ።

በዚህ በሁለተኛውም ቀን የበዓሉ ባለቤቶች (warra jilaa) ክብት አርደው ወተት በገፍ ተዘጋጅቶ የበዓሉ ተሳታፊዎች ሁሉ ተጋበዙ። ከግብዣው በተጨማሪ ሴቶችን በገፍ ተዘጋጅቶ የበዓሉ ተሳታፊዎች ሁሉ ተጋበዙ። ከግብዣው በተጨማሪ ሴቶችን ወራቸውን ቅቤ ቀቡዋቸው። ቅቤ የመቀባቱ ድርጊት ላደረጉት አስተዋፅኦ ምስጋና የማቅረቢያ አንዱ መንገድ ነው። (ከሸ አባ ሩፋ /ሃደ ጅላ/፣ ቃለመጠይቅ፣ ሰኔ 14 ቀን 1999)

4.2.3. Jila guddaa /Galma afaan goodan/ (ሦስተኛው ቀን ጂላ ጉዳ)

ሦስተኛው ቀን የበዓሉ ማጠናቀቂያ ቀን ነው። ገልመ አፋን ጎደን የሚለው የኦሮምኛ ቃል በቦረናዎች ገልማው በር የሚበጅለት ዕለት ወይም ትልቁ የበዓል ዕለት፣ የስም ስያሜው ሥርዓት የሚፈፀምበት ቀን ተብሎም ይታወቃል።

በዚህ በሦስተኛው ቀን በርካታ ድርጊቶች ተከናወኑ። የበዓሉ የመጨረሻ ቀን በመሆኑም የተጠሩት ሁሉ በዚህኛው ቀን ተሟልተው የተገኙ ይመስላል። ሁሉም "ጉማቲ" ስጦታ ይሰጣሉ። የሚያመጡት ስጦታ የተለያየ ነው። ከባለ ጉዳዩ ጋር ባለው ቅርበት፣ ግንኙነትና ውለታ መሠረት ሳይሆን አይቀርም ከፍና ዝቅ የሚለው የቀንድ ከብት የሰጡም ነበሩ። ይህ ጉማቲ ሌላ ስሙ ሀንዱራ (Handhuuraa) ነው። ሀንዱራ በህይወት ያሉ እንደ የቀንድ ከብት፣ በግ፣ ፍየል ያሉትን ይይዛል። የበዓሉ ባለቤት ለታዳሚዎች የሚያርደው ከብት ባይኖረው ለሀንዱራ የመጣው ከብት ታርዶ መስተንግዶው ሞቅ ያለ ይሆናል። የተቀረውም የበዓሉ አዘጋጆች ንብረት ሆኖ ምጣኔ ሀብታቸውን ያደራጁበታል።

ሃንዱራ ሲረከቡ

በዚህ በሦስተኛውም ቀን ጠዋት ከብቶች ከበረት ሳይወጡ እናትየው በተጀመረው አለባበስ፣ አዛባ ካነሳች በኋላ፣ የዕለቱ ሥራ ክንዋኔ ተጀመረ። እስከ አሥር ሰዓት ድረስ የገልማው አንዳንድ ሥራዎች ተሠርተው ተጠናቀቁ። ባለጉዳዮቹ ከየአቅጣጫዉ የሚነርፉትን እንግዶች እየተቀበሉ፣ ሰላምታ እየሰጡ ወደ ገልማው ይመሩዋቸዋል። በገልማው ውስጥ ያሉ አስተናጋጆች ደግሞ ለእንግዶች ወተት፣ ቡናቀላ እየሰጡ ያስተናግዳሉ። ገልማው መሠራት በጀመረ ዕለት ነው እንግዳ በውስጡ እንዲስተናገድ ክፍል ተቆርጦለት፣ መንበር ገብቶ፣ የምድጃ ቦታ ተዘጋጅቶና እሳትም መንደድ የጀመረው። በዚሁ ገልማው መሠራት በጀመረበት ዕለት ከሰዓት በኋላ ኩቹ የተባሉ ወጣቶች ትልቅ ወፍራም እንጨት ቆርጠው አምጥተው በማጋደም አዳራሹን ለሁለት ከፍለውታል። ይህ ሂደት Gulantaa baasuu (ክፍል መለየት) እንደማለት ነው። የልጁ ስም ሲሰየም ከጉለንታው እንጨት በስተኋላ (ወደ ጓዳ) ሆነው ነው።

ገልማው ተሠርቶ ከተጠናቀቀ በኋላ ይህን ይመስላል

አመሻሽ ላይ ከኩሬ ውሃ (Bishaan Haaroo) በግመል ተጭኖ መጥቶ፣ አባትየው ወጉን በውሃው እየተራሠ ተላጨ። የላጨችውም ባለቤቱ ናት። ሲላጭ ወጉ ሙሉ በሙሉ መልጭ ተደርጎ አልነበረም። አነስተኛ የሆነ በአንድ ጣት መጠን የሚለካ አናቱ ላይ እንዲቀር ተደረገ። ይህ ሳይላጭ የቀረው ወጉ ጉቱ (Guutuu) በመባል ይታወቃል። ጉቱ ማስቀረት ወይም ጉቱ የወንድ ልጅ አባትነት ምልክት ነው። ይህ ጉቱ፣ ሰውየው የገዳ ሥርዓት ደረጃዎችን አልፎ ጡረታ ክልል እስከሚገባ ጊዜ ድረስ ከሌላው ወጉ ረዘም ብሎ በመታየት ይቆያል።

አባጀላው ወጉን ሲላጭ

ተሰየሚው ልጅ ወገር ሲላጭ

የገዳ ሥርዓት ደረጃዎችን ሲጨርስ ልክ እንደ ጉዚ፣ በዓል ተዘጋጅቶለት ገደሞጂ ተብሎ ወጉን ሙሉ በሙሉ ተላጭቶ ጡረታ ዕድሜ ውስጥ ይገባል። ወገር መላጨት ከአንድ ደረጃ ወደ ተክታዩ መሸጋገርን ያመለክታልና። (ካሉ ጂሎ፣ ቃለ መጠይቅ ሰኔ 12 ቀን 1999)

ቦርቦር ቡሌ እንደገለፁት "ጉቱ" ሁለት መልክ አለው። አንዱ የጀግንነት ሌላው የታላቅ ወንድ ልጅ አባት መግለጫ በመሆን። ሁለቱ ተለያይተው የሚታወቁበት ገፅታም አላቸው። የጀግንነቱ አመልካች ጉቱው ላይ ቀይ ክር ይታሰራል። የታላቅ ወንድ ልጅ አባት መሆኑን ለመግለፅ የቀረው ጉቱ ደግሞ ከመደበኛው ወገር ረዘም ከመታየት ውጭ የሚታወቅበት ልዩ መልክ የለውም። አንድ አባት ጉቱ ሊኖረው የሚችለው ለታላቅ ወንድ ልጁ የጉዚ በዓል አክብሮ ወጉን ተላጭቶ አስቀርቶት ሲገኝ ብቻ ነው።

በዚሁ በአመሻሹ ሰዓት ከብቶች ወደ በረት ተሰብስበው ከታለቡ በኋላ ስም የሚሰየምለት ልጅም በገልማው በር ላይ ተቀምጦ አባትየው ወጉን ላጨው። ሲላጨው የታለበው ትኩስ ወተትና ከኩሬ የመጣው ውሃ ተቀላቅሎ በማሪስ ነው። ሁለተኛውንም ልጅ በተመሳሳይ ሁኔታ ላጨው። አለሜጨቱ ሙልጭ (ፅድት) ተደርጎ አይደለም። ወዲያ ወዲህ በማስመር ነካ ነካ አድርጎ ነው የተወው። ቦርቦር ቡሌና ካሉ ጂሎ እንደገለፁልኝ አለሜጨቱ የጉቢጣ በዓል ባለቤትነቱን ለማመልከት ነው። ከሌሎች ልጆችም ተለይቶ ይታወቅበታል። የተላጨው ወጉም አልተጣለም። ፍጮ በሚመስል ከእንጨት በተዘጋጀ ዕቃ ተቀመጠ። ሲወለድ የታተበው እምብርቱ ሲደርቅ የሚወድቀው ክፍልም ተቀምጦ ለዚህ በዓል ቀርቧል። በቦረና በአጠቃላይ በኦሮሞ በደረጃ ለውጥ ጊዜ አንዱ የስመታ ማስገኛ ዘዴ ነው። ለምሳሌ በሸዋ ኦሮሞ አንዲት ሴት ሳትዳር በፊት ሳዱላ /ቀሬ/ እየተላጨች፣ ዳርና ዳሩን ሹሩባ እየተሰራች ትቆያለች። ከተዳረች በኋላ ግን በባሏ ቤት ዝግጅት ተደርጎ ከሳዱላዋ አካባቢ ወጉር ተቆርጦ /ተላጭቶ/ በላም ጀርባ ላይ ይደረግና ያቺ ላም ትሰጣታለች። ይህ ሥርዓት ቀሬ ቡሱ /ቀሬ ዱቹ/ ይባላል። በአማርኛ ሳዱላ ማስደፈን ማለት ነው። ከእምብርት ላይ የሚወደቀው እትብትም እንዲሁ የባለቤትነት መግለጫ ስለሆነ አይጣልም ስጦታ መጠየቂያ ወይም መስጫ ነው። እንደመድሃኒትም ይቆጠራል። ለሆድ ቁርጠት መከላከያ በአንገት ይታሰራል። (አለማየሁ ጎይሌ፣ ቃለመጠይቅ፣ ስልክ፣ ታህሣሥ 3 ቀን 2000)

ልጆቹ ወጉራቸውን በተገለፀው መልክ እንዲላጩ መደረጉ ከአባትየው አለሜጨትም እንዲለይ ነው። የመላጨት ድርጊቱ የደረጃ ለውጡን ለመግለፅ ነው። ስም ያልነበረው ልጅ ስም ሊኖረው ነው። ወደማህበረሰቡ ተቀላቀለ ማለት ነው። ሙልጭ አለማድረጉ ደግሞ የስም ስያሜ ሥርዓቱ የሚያዘውና ከሌላው አለላጨት የሚለይበት ነው። ከተላጩ በኋላ በእጃቸውና በአንገታቸው ላይ ከነሀስ መሰል ብረት የተዘጋጁ ጌጣጌጦች ተደረጉላቸው።

ልጆቹ ወጉራቸውን ከተላጩ በኋላ

ምሽቱን ከሚከወኑ የዕለቱ ሥራዎች የመጀመሪያው ቶርበን ጅላዎቹ "ቆቲ" (Qotii) ለመቁረጥ ወደ ደን መጓዝ ነው። ቆቲን ቦረናዎች የበዓል እንጨት (muka jilaa) ይሉታል። ቆቲ የእንጨቱ የወግ ስም ሲሆን በእንጨትነቱ ሚኤሣ (Mi'eessaa) የሚል ስም አለው።

በመርሃ ግብሩ መሠረት ቶርበን ጅላዎቹ ቆቲ ለመቁረጥ ጫካ ገቡ፣ የቆቲ እንጨት በጫካው በብዛት ነበር። ሆኖም መጀመሪያ ላይ ያዩትን ቆቲ አልቆረጡም። ደራራ የተባለ (ወተት) በሥሩ አፍስሰው አለፉ። ይህ ድርጊት ወየምሱ (Wayyoomsuu) ይባላል። ይህ የሚደረገው እንጨቱን እንዳ አዩ መቁረጡ ማስደንገጥ ስለሚሆን ለማክበር ነው። (ጃተኒ ዲዳ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሰኔ 15 ቀን 1999)

ከዚያ በኋላ የሚገኘውን ቆቲ መጀመሪያ ሰንዝሮ የቆረጠው ቀደዱ ተብሎ የመሪነት ቦታ የተሰጠው ሰው ነው። ሌሎቹ እርሱን አገዙት። ቆቲን የመቁረጥ ሂደት፣ ተከታዩ ክዋኔ ስም የማውጣት ሥነሥርዓት መሆኑን ይጠቁማል። በጉቢጣ የስም ስያሜ ሥርዓት ቆቲ ሳይቆረጥ ስም መውጣት አይቻልም። በማስከተል ቆቲውን ቆርጠው በአባጅላው መሪነት እያዜሙ ተመለሱ። ዜማዎቹ ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው መቅረብ የሚገባቸው ናቸው። ቆቲውን ተሸክመው አዳራሹ በር እስከሚደርሱ ድረስ ሁለት ዜማዎች ብቻ አቀረቡ። የመጀመሪያው ኢያን ገሎ ቲያ ኤጊ (Iyyaan galoo tiyya eegi) የሚለው ነው። ይህ ዜማ የቀረበበት ግጥም በውስጡ የህፃናትን ባህርይና ከቤተሰቦቻቸው ጋር ያላቸውን ግንኙነት የሚያሳዩ ስንኞች አሉት።

ወደ በዓሉ መከወኛ መንደር ሲዳረሱ ያዜሙት በሁለተኛ ደረጃ ያለውን ቡልቱሞ ቡሌ (Bultumoo bulee) የሚባለውን ነው። ይህንንም ዜማ መሪ ሆኖ የጀመረው አባትየው ነው። ሌሎቹ እየተቀበሉት አስተጋቡ። ይዘቱ እንደ መጀመሪያው ዜማ የወላጅና የልጅ ግንኙነትን የሚያንፀባርቅ ነው። ከዚህ ባሻገር፣ በቦረና የአንድ ሰው መታደል የሚለካው ልጅ ወልዶ ስም ለመሰየም መድረስ ስለሆነ አባትየው ይህን ዜማ ሲያሰማ "እኔ ለዚህ ዕድል በቅቻለሁ፣ እድለኛ ነኝ በፈጣሪ (አምላክ) የተስፋ ስፍራ አድሬለሁ" እንደማለት ነው። (ሰለሞን ጎዳና፣ ቃለመጠይቅ፣ ሰኔ 22 ቀን 1999)

ዜማዎቹን እያደመቁ ቆቲውን ተሸክመው ከበዓሉ አዳራሽ በር ላይ ደረሱ። ቀጥሎም ቆቲውን በበረቱ መግቢያ ግራና ቀኝ፣ በገልማው በር ግራና ቀኝ፣ ከገልማው ጉን ካለው ቤት ደጃፍ፣ ገልማ ውስጥ ገብተው አለፍ አለፍ ብለው ወደ ጓዳ መግቢያ፣ ምሰሶ አካባቢ ቆፍረው ተከሉ። አብ ጃተኒ ዲዳ አንዳሉት የቆቲው ቅጠል ጠውልጎ አስከሚረግፍ የልጁ ወላጆች ከገልማው ወደሌላ አካባቢና ቤት አይሄዱም (አይዛወሩም)።

ቆሬ ቆርጠው ሲመጡ በአባጂላው መሪነት

ከዚህ ክዋኔ በኋላ ቶርበን ጅላዎቹ ከልጁ ወላጆች፣ አያቶች ጋር በገልማው ውስጥ በተዘጋጀው የእሳት ማንደጃ ቦታ ላይ ስም ለማውጣት ተዘጋጁ። አቀማመጣቸው ሥርዓት አለው። አባትየው ልጁን አቅፎ በስተቀኝ ተቀመጠ። እናትየው ከእርሱ ለጠቀች፣ አያትየዋ በስተግራ በኩል ተቀመጡ። ወንድ አያት የሉም።

ቀጥሎ አባት ለልጁ እንዲወጣለት የመረጡትን ስም፣ ከራሳቸው ስም ጋር በማጣመር አቀረቡ። አብ አባሩፋ ጃተኒ ለልጃቸው የአያት ስም ለመሰየም ስለወሰኑ "ጃተኒ አባሩፋ በሉ" ሲሉ አያቶቹ፣ ቶርበን ጅላዎቹና በገልማው የተገኙ ታዳሚዎች በመንደሩ ተመሳሳይ ስም ያላቸውን፣ እናት አባታቸው በህይወት ያሉትን ሦስት ልጆች ስም አከታትለው ሦስት ጊዜ ጠሩ። አስከትለውም "Abbiyyeefi haadhakee bulfadhu, loon guddoo bobbaasii, jabbiyyoo guddoo tissi" አሉ። "እናት አባትህን ያቆይልህ፣ ብዙ ከብቶች አሠማራ፣ ብዙ ጥጆች አግድ" ማለት ነው። በዚሁ ለልጁ የተመረጠለት ስም ፀደቀ። የአባሩፋ ታናሽ ልጅም በዚሁ በበኩሩ ልጅ ስም ስያሜ በዓል ላይ ለመሰየም ተዘጋጅቶ ስለነበር፣ በተመሳሳይ ክዋኔ ተሰየመ። እርሱንም አባትየው ታቅፎ "አብዱብ

አባሩፋ በሉ!" ሲሉ፣ ቶርበን ጂላዎቹና በገልማው ውስጥ ካሉት ተመሳሳይ ስም ያላቸውን የሚያውቁ ደግመው ጠርተው፣ እንደ በኩሩ፣ "Abbiyyeefi haadhakee bulfadhu, loon guddoo bobbaasii, jabbiyyoo guddoo tissi" አሉ። የርሱም ስም ወደቀለት። አባትየው ካሰየመ በኋላ እናትየውም በኩሩንም ታናሽየውንም በተመሳሳይ ሁኔታ ታቅፋ ያጨላቸውን ስም እየጠራች አሰየመች።



አባት በዙር ልጅን አቅፎ ለስያሜ እንደተቀመጠ

ከስም ስያሜው ቀጥሎ ቡነ ደሃ (buna dhahaa) የተባለ ሥነሥርዓት ተከናወነ። አስራ አራት ፍሬ ቡና (Torban lama) ተቆጥሮ ዙሪያውን ከበው ለስም ስያሜ በተቀመጠበት በረመጥ (ፍም) በተሞላ ምድጃ ውስጥ ጨመሩት። ቡናውን ቆጥረው የጨመሩት ከቤተሰብ አንዲት ሴት ናቸው። ሲንጣጣ አውጥተው፣ ታልቦ በቀረበ ትኩስ ወተት ውስጥ ጨመሩት። ከዚያ ቶርበን ጅላዎቹ እየተቀባበሉ ወተቱን እየተጎነጩ ሁለት ሁለት ፍሬ ቡና ከውስጡ ወስደው አኘኩ።

አብ ጃተኒ ዲዳ በገለፁት መሠረት ይህ ቡነ ደሃ ሥርዓት በሌሎችም በዓላት ላይ ይከወናል። ሰው ሲሞትም ይደረጋል። የሚጨመረው የቡና ፍሬ ብዛት ግን ይለያያል። ይህ ሥርዓት ሰፊ ፍች አለው። በቦረና ኦሮሞ ቡና ክፈጣሪ የተሰጠ ነው፣ በህዝብ ይመሰላል ተብሎ ይታመናል። ቡና መጀመሪያ በቦረናዎች ዘንድ ጥቅም ላይ ሲውል

የመገልገያ ቁሳቁሶች ባለመኖራቸው የቡናን ፍሬ ቆጥረው በእሳት ፍም ውስጥ አብስለው ወተት ውስጥ በመጨመር ይቃመሱ ነበር። ያንን የጥንቱን አጠቃቀምና ተምሳሌትነቱን ለማስታወስ በትላልቅ የሽግግር ክዋኔዎች የጉቢጣ፣ የጋብቻ የሞት ወቅት፣ ቡና ደሃ ብለው ይከውኑታል።

ከቡና ደሃ (Buna dhahaa) ሥነሥርዓት በኋላ "ሆ! ሃሩሶ" የሚል መግቢያ ዜማ ብለው ቆቲ ቆርጠው ሲመለሱ ካዜሙዋቸው ኢያንገሎና ቡሉቱሞ ቡሌ ጀምረው ስድስት የሚሆኑ ዜማዎችን አከታትለው አሰሙ። እነዚህ ስድስት ዜማዎች ለጉቢጣ በዓል ብቻ የሚዜሙ መሆናቸውን አራቱም የመረጃ አቀባዮች አብ ቦርቦር ቡሌ አብ ካሉ ጂሎ፣ አብ ጃተኒ ዲዳና አብ ሰለሞን ጎዳና ቅደም ተከተላቸውን በመጥቀስ ገልፀውልኛል። ቀደም ሲል ቆቲ ቆርጠው ሲመለሱ ካቀረቡዋቸው ከሁለቱ ተከትለው የቀረቡት "ሰገዴ መለዮ" (Sagadee Mallayyoo)፣ "አሸኔ ዶዮ" (Ashanee Dooyyoo)፣ "ኢልሜ ሆዮ" (Ilmee hoo yoo)፣ እና "ሙዳ" (Muudaa)፣ የተሰኙ ናቸው። እነዚህ ተዚመው ሲያበቁ፣ ከቶርበን ጅላ፣ እናትና አባት እና አያቶች በቀር የተቀሩት ታዳሚዎች ወዲያና ወዲህ ተዘዋውረው የፈለጉትን ዜማ እያዜሙ መጨፈር፣ መደሰት ጀመሩ።

ከሌሊቱ ከስምንት ሰዓት እስከ ዘጠኝ ሰዓት ባለው ጊዜ መሀከል ኩቹ የሚል ስያሜ ያላቸው ዕድሜያቸው ከ16 ዓመት በላይ የሆኑ ወጣቶች በረት በር ላይ ተሰብስበው በበዓሉ ላይ ለእነርሱ ተብሎ የሚዘጋጀውን ኮቼ (Kochee) የሚባለው የምግብ ዓይነት እንዲቀርብላቸው የምግቡን ማቅረቢያ ባህላዊ ዕቃ "ዲቤ (Dibbee) " ይሰጠን እያሉ በዘፈን መጠየቅ ጀመሩ። እነዚህ ወጣቶች በሁለት ቦታ ተከፍለው ለየብቻ ሲዘፍኑ ስለነበር ቶሎ አልተሰጣቸውም። ገልማ ውስጥ፤ "የተዘጋጀው በአንድ ዕቃ ነው እንዴት እናድርግ? አሁን ለአንዱ ቡድን ቢሰጥ ይጣሉበታል።" ይባባሉ ነበር።

ኩቹዎች፣ ኮቼ ጠይቀው በሥርዓቱ ሲሰጣቸው መርቀው ተከፋፍለው ይበላሉ። በክፍፍሉ ላይ አለመስማማት ቢፈጠር ተኮራርፈው አይለያዩም። በትግል ይዋጣልን ተባብለው፣ ታግለው አሸናፊው ታውቆ በዕርቅ ይለያያሉ (ሀሮ ኤሌማ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሰኔ 15 ቀን 1999)። ወጣቶቹ ለመጣላት ሙከራ አድርገው ነበር። ግን አንዳንድ ሰዎች መሀል ገብተው አስማሙዋቸው። ቡድን ለይተው መጫወትና መጠየቅ ትተው፣ አንድነት ፈጥረው ቀረቡ "ኮቼው ዲቤው" ተሰጣቸው። ተከፋፍለው በልተው ወደ ጭፈራቸው አመሩ።

ከኮቹ አባላት በከፊል

በዚህ በሦስተኛው ቀን ሌሊቱን ሙሉ መኝታ ይዞ የተኛ ሰው የለም። ቶርበን ጅላዎችና የልጁ ቤተሰቦችም በገልማው ውስጥ ነው የቆዩት። በስም ስያሜው ሥነሥርዓ ት መሠረት እስከ አስራ አንድ ሰዓት ድረስ ለስም ስያሜ ከተቀመጡበት አይነሱም። ሀፃናትም ቢያንቀላፉ በዕቅፍ ይቆያሉ እንጂ መኝታ ይዘው አይተኙም። በውስጣቸው መች ይነጋልን እያሰቡ፣ በጫወታ በጭፈራ ያሳልፋሉ። የንጋት ኮከብ ታይታ የሜዲቻ ከብት (horii meedhichaa) እርድ ለመፈፀም ጥድፊያ አለ። በመሀል አደናቃፊ መንፈስ እንዳይኖር ይፈራል። የስም ስያሜው በዓል ፍፃሜ ማረጋገጫው እርዱ ነውና (ካሉ ጂሎ፣ ቃለ መጠይቅ ሰኔ 12 ቀን 1999 ዓ.ም.)።

ሊነጋጋ ሲል፣ አስራ አንድ ሰዓት አካባቢ "ሆሪሜዲቻ" (Horii meedhichaa) ለማረድ ዝግጅት ተደረገ። ቶርበን ጅላዎቹ ሊታረድ የተዘጋጀውን ከብት ከበረቱ እንዳለ ለማረጋገጥ ሦስት ጊዜ ተመላልሰው በአባጂላው መሪነት አዩ። ይህ የዕርድ ሥርዓት ከኮቢሣ በዓል ክዋኔዎች የግድ የሆነ ነው። ተመላልሰው አይተው መኖሩን ካረጋገጡ በኋላ ቶርበን ጅላዎቹ፣ ሀዩዎቹ፣ አያቶቹ፣ የቅርብ ቤተሰብ የሆነ ሁሉ የበሬውን ጀርባ በሊቾ፣ በእጅ እየዳሰሱ ተራ በተራ መረቁ። ይህን ድርጊት አሬሪ (Areerii) ይሉታል። ከተመረቀ በኋላ የበሬውን ቀንድ የልጁ አባት ይዞ ሌሎችም አግዘው ከጣሉት በኋላ ቀደዱው ባርኮ ታረደ።

በበዓሉ መጨረሻ የሜዲቻ ክብት ለእርድ ቀርቦ ሲመረት

ከዚህ የክብት እርድ በጣም ተፈላጊውና ባህላዊው ጉዳይ ከሥጋው ይልቅ በቆዳው ላይ ይመሠረታል። በሬው ታርዶ እንደተንጋለለ ከእንብርቱ ዙሪያ ቆዳ ተቀርፎ ወጥቶ በአባትየው እጅ ላይ ተጠለቀለት። ከዚያው በእንብርት ዙሪያ ካለው ቆዳ እንደገና ተቀፍፎ ለእናት በአንገቷ ላይ እንድታጠልቅ ተደረገ። ይህ ሜዲቻ ይባላል። የሚታረደው በሬ እራሱ የሜዲቻ ክብት በሚል ስያሜ ነው የሚታወቀው (የሚጠራው)። አብ ጃተኒ ዲዳ እንዳሉት፣ በቦረና ባጠቃላይ በኦሮሞ፣ እምብርት ልዩ ትርጉም አለው። እምብርት መነሻና መድረሻ ነው ተብሎ ስለሚታመንበት ታላቅነት፣ የንብረት ባለቤትነት ይገለፅበታል። ለዚህም ነው የተቢማ በዓል ባለቤቶች አባትና እናት የታላቅ ልጃቸው በዓ ል መሆኑን ለመግለፅ ከእንብርት ዙሪያ ተቀፍፎ የተዘጋጀው ሜዲቻ በእጅና በአንገት ላይ የተጠለቀላቸው።

ቀጥሎ ከበሬው ቁርጭምጭሚት አካባቢ ቆዳ በቀጭን በቀጭኑ ተተልትሎ አባትየው፣ ስም የተሰየመላቸው ታላቅና ታናሽ ልጆች፣ ቶርበን ጅላዎቹ በእጃቸው ላይ አጠለቁ። የቀረው ቆዳ በቀጫጫኑ ተሰንጥቆ ጉማታ ላመጡ እንግዶች ተከፋፈለ።

የታረደው ክብት ሥጋም ተከፋፍሎ ጉማቱ ባመጡ ሰዎች ዕቃ ውስጥ ተከቶ ሲሄዱ እንዲወስዱ ተዘጋጀ። ይህ ጉማቱ የመጣበት ዕቃ ባዶ እንዳይመለስ ተብሎ

የሚሰጥበት ሆኔታ "ጉማ" ተብሎ ይታወቃል። አብ ሰለሞን ጎዳና እንዳሉት ጉማቱ በመጣበት ዕቃ ከትቶ መመለስ መረዳዳት፣ መተጋገዝ ሲያስፈልግ አብረን ነን የማለት ያህል ነው። ብድር መላሽ ያድርገኝ አይነት መልዕክት አለው።

አከፋፈሉ ሲጀመር፣ የበሬውን ቀኝ እጅ ለ"ዋታ"፣ አንድ ታፋ ለ"ቱምቱ" በገልማው በር በኩል ጣራው ላይ እንዲቀመጥ ከተደረገ በኋላ ነው የተረፈው በየዕቃው የተከተተው። ዋታ ቦረናዎች በንቀት የሚመለከቱዋቸው የቦረና ኦሮሞ አባላት የሆኑና በአዳኝነት የሚታወቁ ናቸው። ቱምቱም የተለያዩ ከብረታ ብረት የሚሠሩ ጌጣጌጥ የሚያዘጋጁ ባለሙያዎች ናቸው። ይህ የሜዲቻ በሬ ሥጋ የሚሰጣቸው፣ ዋታ የልጅ ወጉር የሚከተትበት እንደ ጮጮ የመሰለ እንጨት ስለሚያዘጋጁ፣ ቱምቱም በልጁ እጅና አንገት ላይ የሚደረግ እንደ ካቴና የሚታይ የእጅና የአንገት ጌጥ ስለሚያዘጋጁ ነው። (ገልገሎ ዶዮ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሰኔ 17 ቀን 1999)

ጠዋት ላይ ልጆቹ ሲወለዱ ያተቡት እትብት ደርቆ ሲወድቅ ጠብቀው ያስቀመጡትንና የተላጨ ወጉራቸውን አንድነት በጮጮ ውስጥ አድርገው ውሃና ወተት ጨምረውበት አቀረቡ። ሁለት ላሞች ከነጥጆቻቸው ተነድተው መጥተው፣ የልጆቹ ወጉርና እትብት የተቀላቀለበት ወተትና ውሃ በላሞቹና ጥጃዎቹ ጀርባ ላይ ፈሰስ ተደረገ። አብ ጃተኒ ዲዳ እንደተናገሩት የዚህ ድርጊት ሂደት "ሀንዱራ" (Handhuuraa) ይባላል። ከብቶቹም ሀንዱራ ተብለው ይጠራሉ። ሀንዱራ ማለት ስጦታ እንደማለት ነው። የልጆቹን እትብትና ወጉር በከብቶቹ ጀርባ ላይ ማድረግ "ከዛሬ ጀምሮ የናንተ ንብረቶች ናቸው።" ማለት ነው። ሀንዱራ የባለቤትነት መግለጫ ወይም ማመልከቻ ነው። በአማርኛ እትብቴ የተቀበረበት ቦታ፣ ሀገር ማለት የኔ የግሌ፣ ሀገሬ እንደሚባለው፣ ከእምብርት ታትቦ ደርቆ የሚወድቀውን ቆዳ ለይቶ ለስጦታ ብሎ ማስቀመጥ በቦረና የባለቤትነት ማረጋገጫ ቁስ በመሆኑ ነው። እነዚህን ከብቶች ሁለቱም የተሰየሙ ታላቅና ታናሽ ልጆች እየነዱ በረቱ ውስጥ ሦስት ጊዜ ገብተው ወጡ። ሦስት ጊዜ ገብተው መውጣታቸው፣ በእነዚህ የሥጦታ ከብቶች ቤተሰብ እናስተዳድራለን ማለት ነው። በዚህ ሂደት ሦስት ቁጥር አባትና እናት ልጅን ለመወከል ይውላል። ማለትም ልጁ አድጎ አግብቶ፣ ወልዶ አባወራ ይሆናል። በስጦታው ያስተዳድራል ነው። በጉጂ በዓል ላይ ብዙውን ጊዜ ጊደሮች ተመርጠው ይሰጣሉ። ጊደሮችን ብቻ መርጦ መስጠቱም እራሱን የቻለ ትርጉም አለው።

ጊደሮች ወደፊት ተራብተው ልጁን ባለብዙ ከብት ሊያደርጉት ይችላሉ። ስለዚህ የወደፊት ሀብታምነቱን ለመግለፅ ጊደሮች ብቻ ተመርጠው ይሰጣሉ።

በስም ስየሜው በዓል ላይ የቀረቡት ሁሉ በልጁ ስም የመጡ ስጦታዎች በመሆናቸው ሀንዱራ በመባል ይታወቃሉ። (ደበሶ አዲ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሰኔ 17 ቀን 1999)

በልጁ ስም በመምጣታቸውም እንደራሱ ንብረት ይቆጠራሉ። ልጁ ካደገ በኋላ ባጋጣሚ ከአባቱ ጋር አለመግባባት ቢፈጠር አባትየው የሰጠውን ጊደሮችና በስሙ ሀንዱራ ተብለው የተሰጡት ከብቶች ሁሉ እንዲሰጡት መጠየቅ ይችላል። ህጉ (ገዳ) ይፈቅድለታል። በመሀከላቸው ሰላማዊ ግንኙነት ካለ ግን ልጁ እነዚህን የሀንዱራ ከብቶችና ቀደም ሲል አባትየው በተለያየ ምክንያት የሰጠውን ስጦታ፣ የተራቡት ጭምር ትዳር መስርቶ እስኪወጣ ድረስ ሀብትነቱ የአባት ነው። (ቦርቦር ቡሌ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሚያዝያ 24 ቀን 1999)

ልጆቹ የሀንዱራ ከብቶች ነድተው ከተመለሱ በኋላ "Guddadha abbaafi haadha keessan bulfadhaa" የሚል የመጨረሻው አጭር ምርቃት ተሰጠ። ቀጥታ ትርጉሙ እደጉ አባትና እናታችሁን አሳድጉ የሚል ነው። አድጋችሁ ለወግ ማዕረግ ደርሳችሁ ወላጆቻችሁን ለመጦር ያብቃችሁ ነው ፍችው። ከዚያ በኋላ ሁሉም ወደየቤቱ ተንቀሳቀሰ። በዓሉም በዚሁ አበቃ።

5. በስም ስያሜ በዓል አጋጣሚ የቀረቡ የፎክሎር ዝርያዎች ትንታኔ

በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር፣ በስም ስያሜ በዓሉ አፈፃፀም ሂደት የተገኙ የበዓሉ መለዮ የሆኑ የፎክሎር ዝርያዎች ተለይተው የሚገለፁበትና የሚተነተኑበት ይሆናል። አገላለፁና አተናተኑም የፎክሎር ዝርያዎቹ በቀረቡበት አውድ ውስጥ ካላቸው ቦታ አንፃር በመቃኘት ነው።

5.1. ለበኩር ልጅ የሚወጡ ስሞች

በአንድ የቦረና ኦሮሞ የበኩር ልጅ ስም ስያሜ በዓል ላይ ለአንድ ልጅ የሚወጣው ስም አንድ ብቻ ነው። አሰጣጡ፣ የአያት ወይም በአካባቢው በህይወት ካሉ፣ ሦስት ተመሳሳይ ስም ካላቸው እየተመረጠ የሚሰጥ ስለሆነ የአሰያየም ዘይቤው በቦረና የሚወጡ ስሞች ውስን እንዲሆኑ፣ ድግግሞሽ እንዲኖረው የሚያደርግ ነው። በዚህ በድግግሞሽ ውስጥ የበኩር ልጅ ስም ስያሜ ምን ምን ጉዳዮችን መሠረት ያደርጋል? ስሞቹ ምን ምንድናቸው? የሚለውን መመልከት ያስፈልጋል።

በቦረና የየትኛውም ልጅ (ታላቅ፣ ታናሽ፣ ሴት) ስም ሲሰየም መነሻ የሚያደርጉት ቤተሰቡ የነበረበትን ሁኔታ፣ ልጁ (ልጅቱ) የተወለደበትን (የተወለደችበትን) ቦታ፣ ጊዜንና ወቅት ነው። የጎሣ፣ የበዓላት መከበሪያ ቦታዎችና የታዋቂ ሰዎች /አባገዳዎች/ ስምንም ለልጆቻቸው ይሰይማሉ።

ልጁ የተወለደበትን ጊዜ/ወቅት መሠረት ያደረገ ስም

Boruu (ቦሩ)	ጠዋት የተወለደ
Galgaloo (ገልገሎ)	ማታ የተወለደ
Guyyoo (ጉዮ)	ቀን የተወለደ
Waariyyoo (ዋሪዮ)	ምሽት የተወለደ

ልጁ በሚወለድበት ጊዜ ባለው ሁኔታ ላይ ተመስርተውም ስም ይሰይማሉ።

Godaanaa (ጎዳና)	ጉዞ /አካባቢ ለቀው ሲሄዱ
Bonayyaa (ቦነያ)	ደረቅ ወቅት
Soraa (ሶራ)	ዝናባማ ጊዜ
Alaakee (አላኬ)	በተለየ ምክንያት ቤተሰቦቹ ከሠፈሩበት መንደር ውጭ የተወለደ
Waaqoo (ዋቆ)	ወላጆች ሳይወልዱ ቆይተው ወደ መጨረሻ የተገኘ፣ የፈጣሪ ስጦታ

በቦረና ጊዜው የደረቅ ወቅት ሆኖ ቤተሰቡ ለከብቶች ሣርና ውሃ ፍለጋ ርቆ በሚኬድበት ጊዜ ወንድ ልጅ ቢወለድ ጎዳና (Godaanaa) ይሉታል። ሣርና ውሃ ፍለጋ የሚደረገውን ጉዞ ለማመልከት ነው። የጊዜውን ደረቅነትና ወቅቱን ለመግለፅ ደግሞ ቦነያ "Bonayyaa" የሚል ስም ይሰይማሉ። በክረምት፣ ዝናቡ አላስገባ አላስወጣ ብሎ ሰው በየቤቱ ተሰባስቦ በሚቀመጥበት ጊዜ የተወለደም ሶራ (Soraa) በማለት ይሰይሙታል።

የገዳ ሥርዓት መከወኛ ቦታዎች የበኩር ልጅ ስም ሆነው ይመረጣሉ። ለምሳሌ፣

Liiban	ሊበን
Gaayyoo	ጋዮ
Nuuraa	ኑራ
Areeroo	አሬሮ
Doyyoo	ደዮ

ጋዮ በድሬ ወረዳ የሚገኝ የአንድ ቀበሌ ስም ነው። ይህ ቀበሌ ደግሞ በገዳ ሥርዓት ውስጥ ከፍተኛ ቦታ አለው። ይኸውም በገዳ ሥርዓቱ በየስምንት ዓመቱ የስልጣን ርክክብ የሚደረግበት፣ በርካታ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ህጎች ረቅቀው የሚታወጁበት ጉባኤ (ጉሚ ጋዮ) የሚቀመጥበት ቦታ ነው።

ይህንን ስም ለበኩር ልጅ ስም መሰየምም ለልጁ የዚህን የተከበረ ቦታ ስም በመስጠት ማክበር ነው።

ኑራም በነገሌ ከተማ አቅራቢያ የሚገኝ የገዳ ሥርዓት በዓል መከበሪያ ቦታ ነው። ኑራ ጎልቶ የሚታወቀው በገዳ ሥርዓት በደበሌ ዕድሜ ክልል ስም ስያሜ ጉዳይ ነው። ይህም ቦታ በሥርዓቱና በህዝቡ ከፍተኛ ክብር የሚሰጠው ነው። ለክብሩ መዘከሪያነት የበኩር ልጅ ስምም ይሰየምበታል። ደዮም በዓል የሚከበርበት ቦታ ነው።

የበኩር ልጅ ስም በዱር እንስሳት፣ በትላልቅ የእንጨት ዘሮች፣ መንፈሳዊ ሰዎች ወይም ቁስ ስምም ይሰየማል።

Qaallichaa (ቃልቻ)	ክብር የሚሰጠው እንጨት
Jaldeessaa (ጀልዴሳ)	የዱር እንስሳ /ዝንጅሮ/
Dhaddachaa (ደደቻ)	የእንጨት ዓይነት
Kallachaa (ከለቻ)	ባህላዊ ቁስ /የአባገዳነት መግለጫ/

ጀልዴሳ ስም የሚወጣላቸው ልጆች ደበሌዎች ናቸው። ከደበሌ ወደ ጋሜ በሚደረግ ሽግግር ወቅት ይህ ስም ለሁሉም የደበሌ አባላት ይሰጣል። እነዚህ ልጆች የሚለዩት በአባት ስም ብቻ ይሆናል። ጀልዴሳ የሚለው ስም ልጆቹ ስም ለመሰየም እስከሚቀርቡበት ጊዜ ድረስ ወጉራቸውን ሳይላጩ አጎፍረው ስለሚቆዩ ያንን

የጉራማነታቸውን ለመግለፅ የሚሰጥ ነው። (ሰለሞን ጎዳና፣ ቃለመጠይቅ ሰኔ 22 ቀን 1999)

5.2. ቃል ግጥሞች

በበዓሉ የሦስት ቀን ቆይታ ከሚከወኑ በርካታ ፎክሎራዊ ድርጊቶች መሀከል ቃል ግጥም የሆኑ ዜማዎች ተጠቃሽ ናቸው። የበዓሉ ልዩ ዜማዎች ሁልጊዜ የማይዜሙ ሲሆኑ፣ በበዓሉ መጨረሻው "Galma Afaan goodan" /jila balloo/ በተባለው ቀን ስም ከመሰየሙ በፊትና በኋላ ይቀርባሉ። ስም ከመውጣቱ በፊት ቆቲ ቆርጠው ሲመለሱ በ "ኢያንገሎ" እና "ቡሉቱሞ ቡሌ" ዜማዎች አጅበው ነው።

5.2.1. Iyyangaloo (ኢያንገሎ)

ኢያንገሎ የመጀመሪያው የጉቢጣ በዓል ዜማ ነው።

Iyyaan galoo tiyya eega	ተጫዋቹን እጠብቃለሁ
Haagaloo qabatee	ሃገሎ በአንገቱ አንጠልጥሎ
Simphirree gaadatee	ወፍ በወንጭፍ ይመታል
Haagaloon qilliftee	ሀገሎ አቃጨለች
Taphaa bakkaafatee	ተጫወተ እየተንገዳገደ
Caara yaabbii tika eega	ጥሻ እየጠበቀ(እየተንጫጫ ጥሻ ይጠብቃሉ)
Diidaa Baaraa qotee	ከሜዳው "ባራ" ቆፍሮ /ባራ የሚበላ ሥር/
Baree qundhii kuttee	ወፍሮ የእጹ ላይ እስር ሰረሰረው
Diidaa fardoo raaree	ፈረስ ኋላ ሆኖ እየነዳ
Abboo badhaafatee	አባቱን አሰደሰተ
Diidaa Caamee gootee	ከዋለበት ለቤት የሚሆን ይዞ እየገባ
Hayyoo badhaafatee	እናቱን አስደሰተ
Iyyaan galoo tiyya eega	ተጫዋቹን ጠብቃለሁ
Tuutoo addaan duraa	ባለ ቁንጮ አናት
Boruun waaqaan duraa	ጠዋት ሳይነጋ
Guddaan warra duraa	የመጀመሪያ ልጅ
Lafa Liiban duraa	ከመሬት ሊበን የመጀመሪያ
Ibidda irraa daandee	በእሳት ዙሪያ እየሄደ
Harkaan galoo daandee eega	እኔ በእጅ እጠብቃለሁ

Galaan gulloo daandee	መሬት ላይ ሲንከባለለል
Shunxoon dhulaandhula eega	ጥበቃ ያስፈልገዋል
Ulaannaan urgooftee eega	መሽኛው አልቅት መሳይ
	ጠረኑ ለኔ ያውደኛል

ይህ ዜማ አባትየው ከቶርበን ጅላዎቹ ጋር ቆቲ ቆርጠው ሲመለሱ እያዜመላቸው እየተቀበሉት የሚስተጋባ ነው። በዚህ ግጥም ውስጥ ህፃናት ደጃፍ ላይ መዳኽ ከጀመሩበት አንስቶ ከብቶች አግደው ለቤተሰቦቻቸው አገልግሎት የሚሰጡበት ድረስ የሚያሳዩትን ባህርይና አካላዊ እንቅስቃሴ ያስጨብጣል። በዝርዝር ለማየት ከግጥሙ አንዳንድ ስንኝ ወስዶ መተንተኑ አስፈላጊ ነው። እያንዳንዱ ስንኝ የየራሱ ፍች አለውና።

"Haagaloo qabatee" - የሚለውን ስንኝ፣ ብንመለከት፣ Haagaloo - ቃጭል መሰል ድምፅ የሚሰጥ ቁስ ነው።

በቦረና በገጠሩ ክፍል ቁጥቋጦ በበዛበት፣ ልጆች ከቤት ወጥተው ሲጫወቱ ሳያውቁ ርቀው እንዳይሄዱና እንዳይጠፉ ዱካቸውን ለመያዝ /ለመከተል/ አንገታቸው ላይ "ሀገሎ" ይታሰርላቸዋል። ወዲያና ወዲህ ሮጠው ሲጫወቱ ድምፁ ያሉበትን የሚጠቁም ስለሆነ ስለመኖራቸውና ችግር ያልደረሰባቸው መሆኑን የሚከታተሉበት ቁስና ዘዴ ነው።

"Simphirree gaadatee" የሚለውም ስንኝ የራሱ መልዕክት አለው።

ልጁ አድጎ በሀገሎ ድምፅ ክትትል ከሚደረግለት ጥበቃ ደረጃ ሲያልፍ፣ በአካባቢው ያሉትን እንስሳት ይከተላል። የመጀመሪያዋ ወፍ ትሆናለች። ወፏን ቀርቦ ለመያዝ በክር ወይም በልጥ ወንጭፍ አዘጋጅቶ መትቶ ለመጣል የሚያደርገውን ጥረት ማሳያ ነው።

"Caara yaabbii tika eega"

በዚህኛው ስንኝ ልጁ ለቤተሰብ አገልግሎት መስጠት መጀመሩን ይገልፃል። እየተጫወተ ጥጆች ይጠብቃል። የሚል መልዕክት አለው። ልጅ ሥራው መጫወት ነው ምን ጥቅም አለው? እንዳይባል እየተጫወተም ቁምነገር ይሠራል የሚል አባባል በውስጡ አዝሏል።

"Diidaa Baaraa qotee"

ልጁ ውጭ ሲውል፣ ይጫወታል፣ በዚያውም ጥጆች ይጠብቃል። በዚህን ጊዜ መመገብ አለበት። ምግብ ፍለጋ ወደቤቱ አይመለስም፣ በሚውልበት ቦታ ያለውን

በተፈጥሮ የተዘጋጀ ፍራፍሬ፣ ሥራሥር፣ ቅጠላ ቅጠል ይመገባል። በዚህኛው ግጥም ውስጥ ያለውም "Diidaa Baaraa qotee" የሚለው ስንኝ ልጆች በአካባቢው ከመሬት ተቆፍሮ የሚበላውን "በራ" የተባለ ውሃ አዘል ሥራሥር ተመግበው እንደሚውሉ ለማመልከት ነው። እንዲሁም ልጆች ለሆዳቸው የማያስቸግሩ በአካባቢው የተገኘውን በልተው፡ ሲጫወቱና የአቅማቸውን አገልግሎት ሲሰጡ እንደሚውሉ ያመለክታል።

Diidaa fardoo raaree	ከፈረስ ኋላ ሆኖ እየነዳ
Abboo badhaafatee	አባቱን አስደሰተ
Diidaa Caamee gootee	ከዋለበት ለቤት የሚሆን ይዞ እየገባ
Hayyoo badhaafatee	እናቱን አስደሰተ

እነዚህ ደግሞ ልጁ የሌላ አካል ድጋፍ ከመጠበቅ፣ ጫወታ ብቻ ከመከታተል ደረጃ አልፎ አገልግሎት በመስጠት ቤተሰቦቹን ከልፋት ማሳረፉን የሚያመለክቱ ስንኞች ናቸው። አባቱ በየቀኑ የሚከውነውን ለግመሽ የተሠማሩ ከብቶችና የጋማ ከብቶች ሰብስቦ ወደ ቤት መመለስ፣ እንዲሁም ውጭ ውሎ ሲመለስ ለቤት ውስጥ አገልግሎት የሚውል እንደ ማገዶና ሌሎች ቁሳቁሶችን ይዞ በመግባት እናቱን ማገልገሉንና ማሳረፉን ያትታሉ።

ከዚህ ኢያንገሎ ዜማ ግጥም የምንገነዘበው፣ ልጅ ርቆ እንዳይሄድ፣ ጉዳት እንዳይደርስበት እንዴት እንደሚጠበቅ፣ ቤተሰብ ለልጅ የሚያሳየውን ፍቅር፣ እንዲሁም ልጅ ለቤተሰቡ ማድረግ የሚገባውን ድጋፍ ነው። በጉጂ በዓል ወጣት፣ ልጅ፣ አዛውንት የሚሳተፍበትና ዜማውም የማይቀር በመሆኑ ወጣቱ ከዜማው የልጅ መብትና ግዴታ ምን እንደሆነ ይማርበታል። ባህሉም ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፈው በዚሁ መንገድ ነው።

5.2.2. Bultumoo bulee (ቡልቱሞ ቡሌ)

ይህ ዜማ በሁለተኛ ደረጃ የሚቀርብ በአባትየው የሚዜምና ቶርበን ጅላዎቹ በተቀባይነት የሚሳተፉበት ነው።

Bultumoo Bulee yoo hoo	ቡልቱም ቡሌ ዮ ሆ
Bulegaa marabbaa yoo hoo	አድሬያለሁ ተመስገን
Bultumoo hee, waaq naabulchi	አምላክ ቡልትምን አሳድግልኝ
Karra naa bani yaa abbee	ልጄ በር ክፈትልኝ
Warri dhaarritoo yoo hoo	እነ ዳሪቶ!
Dharraa kee hin baane yaa abbaa koo	ጌታዬ ናፍቆትህ አልወጣልኝም

Bultumoo waaq naabulchi	አምላክ ቡልቱምን አሳድግልኝ
Karra naa bani yaabbee	ልጄ ሆይ በር ክፈትልኝ
Kateeba Areeroo, Reerrii yaammatee abbaa koo	የአሬሮ ልጅ ጎሳውን ጠራ
Akka galaana dhiibuu dachaa abbaa koo	እንደ ሸለቆ ጎርፍ ድርብ
Akka goobanaa dhiibamaa dhufe abbaa koo	እንደ ጠዋት ኮከብ እየገፋ መጣ
Akka dhaddacha guddaa daraaree abbaa koo	እንደ ትልቁ "ዳደቻ" አበበ

በዚህ ግጥም የመጀመሪያዎቹ ስድስት ስንኞች ውስጥ የሰፈረው ፍሬ ጉዳይ ልጁ ተወልዶ ለዚህ በዓል መብቃቱን አምላክን ማመስገን፣ ለወደፊትም እድጎ እንዲያገለግለው ከበር ቆሞ እንዲጠብቀው አምላኩን የሚማፀንበትና ለልጁ ያለው ፍቅር የጠና መሆኑን የገለፀባቸው ናቸው። በመጨረሻ ላይ የመጡት አራት ስንኞች ደግሞ የልጁን ትልቅነት፣ ታላቅነትን ወደፊትም አድጎ የሚያብብ መሆኑ በንፅፅር የቀረበበት ነው። በተጨማሪም ልጁ የተወለደበትን ጊዜና ሁኔታም ለማመልከትም የሚያገለግሉ ናቸው።

ይህ ዜማ አባትየውና ቱርበን ጅላዎቹ ከሚያከናውኑት እንቅስቃሴ ጋር የተጣመረ ነው። ኢያንገሎና ቡልቱሞ ቡሌ ቀደም ሲል እንደተገለፀው "ቆቲ" ቆርጠው ሲመለሱ በጉዞ ላይ የሚዜሙ ግጥሞች ናቸው። በተለይ ቡልቱሞ ቡሌ ወደ በዓሉ መከወኛ ቀዬ ሲቃረቡ የሚዜም በመሆኑ በቃል ግጥሙ ውስጥ "karra naa bani yaabbee" የሚለው ስንኝ፣ ገልማው በር ላይ ተደርሶ የሚባልና ወዲያው በር ተከፍቶ ወደ ገልማው የሚገባበት ነው። በሩ የሚከፈተው በሀሳብ እንጂ በፊትም ክፍት ነው። ገብተው አይቆሙም፣ አይቀመጡም። ይዘውት ያመጡትን "ቆቲ" በተዘጋጀለት ቦታ ተክለው፣ ለስም ስያሜ የተዘጋጀው ቦታ ላይ ይቀመጣሉ። ስም ከወጣ በኋላ ቦታ ቀይረው "ሆ ሃሩሶ" የሚል መግቢያ መሰል አጭር ዜማ በአባትየው መሪነት ያሰማሉ።

ይህ አጭር ዜማ ፀሎታዊ ይዘት አለው። ወንድ ልጅ ስጠኝ ባርክልኝ የሚል መልዕክት በውስጡ አዝሏል። አቀራረቡ፦

1. Hoo harusoo	ሆ! ሃሩሶ
Maalimallayyaa	ምን ይበጃል (ምን ይሻላል)
Abbeeraa uumaa	የፈጣሪ ልጅ
Ilma naa uumi abbaa	ልጅ ፍጠርልኝ (ልጅ ስጠኝ)
2. Hoo haruusoo	ሆ! ሃሩሶ
Maalimalayyaa	ምን ይበጃል (ምን ይሻላል)

Abbeeraa uumaa	የፈጣሪ ልጅ
Ilma naa uumi abbaa	ልጅ ፍጠርልኝ (ልጅ ስጠኝ)
3. Hoo haruusoo	ሆ! ሃሩሶ
Maali malayyaa	ምን ይበጃል (ምን ይሻላል)
Abbeeraa uumaa	የፈጣሪ ልጅ
Ilma naa uumi abbaa	ልጅ ፍጠርልኝ (ልጅ ስጠኝ)

በቁጥር የተጠቀሱት አባትየው ሲል፣ ቶርበን ጅላዎቹና በገልማው ውስጥ ያሉት ተከትለው ያሉትን ስንኞች በማዜም ይቀበሉታል። ሦስት ጊዜ አከታትለው ብለው ያበቃሉ። ሆ! ሃሩሶ የሚለው ቃል ትክክለኛ ትርጉሙ በውል ባይታወቅም በልጅ ስም ስያሜ ጊዜ ይቀርባል። አባትየው ቃሉን ሦስት ጊዜ በዜማ ሲጠራው፣ ቶርበን ጅላዎቹና በገልማው ውስጥ የተገኙ የበዓሉ ታዳሚዎች እየተቀበሉ ያስተጋባሉ። አባትየው አሁንም ተመልሶ ከላይ የተጠቀሱትን ሦስት ስንኞች ይላል።

እነዚህም ስንኞች፣ ልጅ እሻለሁ ፍጠርልኝ አንተ /አባቴ/ የሚል ምልጃ አዘል መልዕክት የያዙ ናቸው። በውስጣቸው ሰፋ ያለ ፍች ይዘዋል። ስሜ የሚጠራበት፣ ዘር፣ ታሪክና ባህል የሚተላለፍበት ልጅ ስጠኝ ብቻዬን አታስቀረኝ ማለት ነው። ይህን የአባትየውን ፀሎት መሰል ዜማ ተቀባዮቹ አከታትለው ሦስት ሦስት ጊዜ በመድገም ተራ በተራ ተቀባብለው ከተዳረሰ በኋላ፣ ቀደም ሲል ካዜሙት "ኢያንገሎ" ሆ ሀሩሶ የሚለውን አጭር ዜማ ጀምረው፣ "ቡልቱሞ ቡሌን" አስከትለው ወደ ሦስተኛ ዜማ ይሸጋገራሉ።

5.2.3. Sagadee Mallayyoo (ሰገዴ መለዮ)

Sagadee Sageeto qaba	ሰገዴ 'ሰጌቶ' አለው
Ka duraa Arboora qaba	ታላቅ (ጀግና) "አርቦራ" አለው
Arboora Bulee Dhaddachaa	የቡሌ ዳደቻ "አርቦራ"
Hawwaxuu Dhaddacha Yaayaa	የደደቻ ያያው ሀወጡ
Konnituu Waasolee Booraa	የዋሶሌው ቦራው ኮንቱ
Konnituu Waasolee Booraa	

ይህ ግጥም ሙሉው ሲቀርብ፣ የሰው ልጅ ተወልዶ፣ አድጎ እስኪሞት ድረስ የሚያሳልፋቸውን የህይወት ውጣውረድ የሚያሳይ ዓይነት ሲሆን፣ ከህፃናት ጋር የተያያዘ ጉዳይ በመጀመሪያው ስንኞች አካባቢ ጎልቶ ይታያል።

"Sagadee Sageeto qaba" ሰገዴ ሦር አለው። /አነስ ያለ ሦር/ የሚለው ስንኝ፣ ልጁ አድጎ ከጥንጆች ጋር ከመንደሩ ወጣ ብሎ ሲያግድ አነስ ያለ ከእርሱ አቅም የሚመጣጠን ሦር ይዞ ይወጣል። ትናንሽ እንደፍልፈል ያሉ አውሬዎች ይገድልበታል። አጋጥሞት ገድሎ ከገባ አባት ስጦታ ሰጥቶ ያበረታተዋል። (ጃተኒ ዲዳ፣ ቃለመጠይቅ ሚያዝያ 22 ቀን 1999)

Ka duraa Arboora qaba" የመጀመሪያ አርቦራ አለው፣ ይህ ማለት፣ አብ ጃተኒ እንዳሉት ልጁ አድጎ ለጀግንነት ይበቃል። ለጀግንነቱ ምልክት አርቦራ ክንዱ ላይ ያደርጋል ነው። አርቦራ ከዝሆን ጥርስ የሚዘጋጅ ከክንድ በላይ የሚጠለቅ ሲሆን፣ ማንም ተራ ሰው አያደርገውም። ጠላት ወይም ትላልቅ አውሬ የገደለ ጀግና እንጂ። ስለዚህ ለህፃኑ መዜሙ አድገህ ለቁምነገር ትበቃለህ የሚል ምኞት ለመግለፅ ነው። ከዚሁ ጋር በአርቦራ የተሰየመ ስም ያለውን አርቦራ ቡሌ ዳደቻ (አባገዳ) ያነሳል። ይህ አባገዳ ዝነኛና ትልቅ ታሪክ የሠራ ሰው መሆኑንም በማስታወስ ልጁን ለትልቅ ባለታሪክነት ትበቃለህ ለማለት በስም ስያሜ በዓሉ ላይ ያቀርቡታል።

5.2.4. Ashanee Dooyyoo (አሸኔ ዶዮ)

አሸኔ ዶዮ የሰው ስም ነው። በቦረና ለመጀመሪያ ጊዜ ጫት በመቃም ልምዱን ያስፋፋ ሰው ነው ተብሎ ይታወቃል። ይህንኑ ለማስታወስ በስሙ ይዜምበታል። ይህ ዜማ የጫት ማሞገሻ ነው። በቦረና ኦሮሞ ጫት በአሁኑ ጊዜ በከተማ እንደምንመለከተው ለጊዜ ማሳለፊያ ተብሎ የሚቃም ወይም የሱስ ማስታገሻ ሆኖ የሚቀርብ አይደለም። ጫት በትላልቅ በዓላት ላይ የሚቀርብ፣ አዛውንቶች በአካባቢያቸው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ (አስተዳደራዊ) ጉዳዮች ላይ ሲወያዩ የሚቀርብ የመስተንግዶ፣ የመነጋገሪያ አንዱ ቁስ ነው። (ጃተኒ ዲዳ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዝያ 22 ቀን 1999)

Ashanee Doyyoo lattuu haasaa tolte

Baallisee yoo ha yoo haa,
Har'a ardaan nagayaa ayyana baballisa

Sagadaa sagadi kiyya araada
Ta lagaa Guula baate tiksituun guurte

አሸኔ ዶዮ ለጫወታ የተመቸች
ለምለም
ቅጠሏ፣ አቤት! አቤት!
ዛሬ አካባቢው ሰላም ነው በዓላችን
ይሳካል፣
ዐሎቴ ለአምሮት ነው
ከጉለ ወንዝ የበቀለችን ለምለም እረኛ
የቆረጣት

Ta qilxaa gooda baate goduun yaamte	ከቅልጣር ጎዳ አካባቢ የበቀለችን ለምለም ሁሉም ፈለገው
Araadee hammaadhe lattuu uuba'ii nyaadhe	ሱስ ይዞኝ ሳልመርጥ ቃምኩ
Ubbayiin aadaa lattuu balchaan oolaa	የለምለም አያያዝ ባህሉ በቅጠል ሸፍኖ ነው
Daroleen baatee, lattuu namni dare hin cabsu	በዳሮሌ አካባቢ የበቀለን ለምለም የታረዘ ሰው አይቆርጠውም
Mana gubbisaan baate lattuun goduu gabbistee	የጉቢጣ በዓል የተከበረበት፣ ለምለም በዓሉን አገዘፈው
Arbooleen baatee lattuu miilli arrayyaa	በአርቦሌ፣ አዲስ ለምለም ወጣች (በቀለች)

ግጥሙ ጫት ለጫወታ የሚመረጥ፣ ሰላም መኖሩን፣ መግባባትን፣ አብሮ መኖርን የሚያበስር፣ ያገኘው ሰው ሁሉ የማይቆርጠውና የተከበረ መሆኑን ያወሳል። ከስም ስያሜ ጋር በተያያዘ ሁኔታ፣ mana gubbisaan baate lattuun gooduu gabbistee የሚለው ስንኝ የበኩር ልጅ ስም ስያሜ በተካሄደበት ቤት የበዓል ማድመቂያ ማሞቂያ መሆኑን ይገልፃል።

5.2.5. Ilmee Hooyoo (እልሜ ሆዮ)

በዚህኛው ዜማ ለልጁ የተሰየመው ስም፣ የተሰየመበት ዘመን እየተጠቀሰ ይሞገሳል። ዘመን ሲባል በአማርኛ የክርስትና /አርቶዶክስ/ እምነት ዘመነ ዮሐንስ ዘመነ ማቲዮስ እንደሚባለው አይነት በቦረና አሮሞዎች ዘንድም በየስምንት ዓመቱ የሚቀያየሩ ዘመናት አሉ። የአንድ ጉቢጣ በዓል አክባሪ ወይም ተሰያሚም በዓሉን ያከበረበት ዘመን በዚህ ዜማ ውስጥ እየተጠቀሰ ይዜምለታል። እነዚህ ዘመናት "Daraaraa" /ዶራራ/፣ "Libaasa" /ሊባሰ/፣ "Fullaasa" /ፉላሰ/፣ "Mardiida" /መርዲዶ/ የተባሉ ናቸው። ለምሳሌ አሁን ያለው የቦረና አባገዳ የሊበን ጀልዬጣ የገዳ ዘመን /የሥልጣን ዘመን/ "Daraaraa" /ዶራራ/ የተባለው ነው። እነዚህን ሁኔታዎች ከግጥሙ መመልከት ይቻላል። ግጥሙ የሚቀርበውና የሚታወቀው በ "Sabbaqa" ዘመን ነው። (ጃተኒ ዲዳ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዝያ 22 ቀን 1999)

Ilmee hoo yoo, ilmaan sabbaaq duulaa	እልሜ ሆዮ የሰባቅ ዱላ ልጆች
Sabbaaqii duula qabataa	ሰባቅ ጦር ይይዛል
Mucaan abbaa qabataa	ልጁ አባቱን ይይዛል

Mucaan maqaa baafata	ልጁ ስም ይሰየማል
Maqaa Boruu baafata	ቦሩ የተሰኘ ስም ይሰየማል
Boruun Waaqaa angafaa	ንጋት ለብርሃን ታላቅ ነው /ቦሩ ለእምላክ ታላቅ ነው/
Boruu abbaa angafaa	ቦሩ የተባለ ልጅ ለአባት ታላቅ ነው
Boruu eenyu wallaala	ቦሩን ማን ያጣዋል /ሁሉም ያውቀዋል/

ከዚህ ዜማ ግጥምም ብዙ ቁምነገር መምዘዝ ይቻላል።

Mucaan abbaa qabataa

Mucaan maqaa baafata

የተባሉትን ስንኞች ብንመለከት በጽሑፉ ላይ ግልፅ ሆኖ የሚታይ ነገር የለም። ግን የስም ስያሜው ሲሰጥ በድርጊት የሚገለፀውን ደምረን ስንመለከት ሰፊ ትርጉም እናገኛለን። እነዚህ ሁለት ስንኞች በጥሬ ትርጉማቸው ልጅ አባቱን ይይዛል፣ ስም ይወጣለታል ነው። በድርጊት ሲገለፅ ግን ስም የሚወጣለት ልጅ ስም ሊሰየምለት በአባቱ ተይዞ ከቶርበን ጅላዎቹ መሀከል ሲገኝ፣ አባትየው ሁለት እግሩን ከፈት አድርጎ ልጁን መሀል በማስገባት በሁለት እጆቹ የአባቱን ጉልበቶች እንዲይዝ ይደረጋል። እዚህ ላይ ነው ሰፊው ፍች የሚመጣው። ይኸውም ጉልበቱን መያዙ ወደእኔ የሚያስተላልፈውን ታሪክ፣ ባህል፣ አደራ እቀበላለሁ፣ እወርሳለሁ ብሎ ቃል የሚገባበት፣ ብድሩን እመልሳለሁ የሚልበት ሲሆን፣ በሁለት እግሩ መሀል ገብቶ መሰየሙ ደግሞ ከእርሱ ተወለድኩ፣ ከጉያው ወጣሁ በማለት አባትነቱን ለማረጋገጥ ነው። (ሰለሞን ጎዳና፣ ቃለመጠይቅ፣ ሰኔ 21 ቀን 1999)

በሌሎች ስንኞችም እንዲሁ ጠለቅ ያለ ፍች ያላቸው ቃላት ሠፍረው እናገኛለን።

Boruun Waaqaa angafaa

Boruu abbaa angafaa

Boruu eenyu wallaala

አብ ሰለሞን እንደገለፁት የመጀመሪያው ስንኝ ውስጥ ያለው "Boruu" የሰው ስም አይደለም። በቦረናዎች ንጋት ማለት ነው። በስንኝ ውስጥ ንጋት ከቀን ቀድሞ የሚመጣ ታላቅ (የመጀመሪያ) መሆኑን፣ ሁለተኛው ስንኝ ውስጥ ያለው Boruu ደግሞ የተሰየመው ልጅ ነው። ለአባቱ የመጀመሪያ ልጅ ነው። ንጋትና ልጁን በንፅፅር የሚያቀርብ፣ ታላቅ ቀድሞ የተገኘ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው። በሦስተኛው ስንኝ ይህንኑ ቃል ሲደግም፣ /Boruu eenyu wallaala/ ይህንን ቁምነገር ወይም እውነታ ማን ያጣዋል ግልፅ የሆነ ነገር

ነው። ታላቅ ነህ፣ ታላቅነትህም ይታወቃል ማለቱ ነው። የዚህ ዜማ ግጥሞች ከዘመን ዘመን ሲወረሱ የመጡ ናቸው። የሚሰየመው ስም ግን እንደ ቤተሰቡ ምርጫ ይለዋወጣል። በግጥሙ ውስጥ የሰየሙትን እየተኩ ሊያሞግሱበት ይችላሉ።

5.2.6. Alii Aliyoo (አሊ አልዮ)

ይህኛው ዜማ "ቃሉ" የሚሞገስበት ነው። ከታላቅ ልጅ ስም ስያሜ ጋር የሚያያይዘውና እንዲዜም የሚያደርገው፣ ስም የሚሰየምለት ልጅ አድጎ፣ እንዳባቶቹና አያቶቹ ለወግ ለማዕረግ (ለአባገዳነት) ደርሶ ቃሉ ይሾመዋል፣ ይመርቀዋል የሚል ምኞት የሚገለፅበት መሆኑ ነው።

Alii Aliyoo Simuudaa	አሊ አሊዮ ይሾምሃል
Ali Gurraachaa sumuudaa	አሊ ጉራቻ ይሾምሃል
Gurraacha Yaayyaa simuudaa	ጉራቻ ያያ "
Yaayyaa Muunyoo simuudaa	ያያ ሙኞ "
Moonaa Curruuxxee "	ከግቢው ድኽህ
Daraaraa Dheeddee "	ለምለሙን ግጠህ
Daraaraa Marraa "	የለመለመ ሣር
Waaq sifeesse "	ፈጣሪ ባረከልህ
Daraaraa ilmaa "	የልጅ አበባ
Waaq Urgeesse "	ፈጣሪ አሳደገ

በዚህ ዜማ ግጥም ስንኞች ውስጥም የተለያዩ መልዕክት ያዘሉ ቃላት ይገኛሉ። ቃላቱ ላይ ላዩን ሲመለከቱዋቸው ተራ ይመስላሉ፣ ከቦረና ህዝብ አኗኗር አንፃር ዘልቀው ሲመለከቷቸው ግን ደረብረብ ያለ ፍች ይዘዋል።

ከላይ እንደተጠቀሰው አሊ አሊዮ ከዚህ በፊት የሚታወቅ መንፈሳዊ ሰው (ቃሉ) ነው። ቃል ግጥሙ አድገህ እንደርሱ ያለ መንፈሳዊ አባት ይሾምሃል፣ ይመርቅሃል የሚል መልዕክት ብቻ አልያዘም። በሌላ መልኩ፣ የተለያዩ የገዳ ሥርዓት ደረጃዎች ውስጥ አልፈህ ሊቅ (ሀዩ) ሆነህ የሥርዓቱን መንፈሳዊ አባት የመምረጥ ደረጃ ትደርሳለህ የሚል ሀሳብም አለው። በሥርዓቱ የነበረው ቃሉ በሞት ሲለይ ሌላ ተተኪ የሚመረጠው በሀዩዎች ስለሆነ አድገህ በማህበረሰቡ ትልቅ የተባለ ቦታ ሁሉ ትደርሳለህ፣ የዕድሜ ባለፀጋ ትሆናለህ የሚል ነው።

Moonaa Curruuxxee simuudaa

Daraaraa Dheeddee simuudaa

Daraaraa Marraa simuudaa

Waaq sifeesse simuudaa

እነዚህ ስንኞች ደግሞ የተፈጥሮ ሀብት በሰው ህይወት ውስጥ ያለውን ቦታ ለማመልከት የቀረቡ ናቸው። አቀራረቡ ለከብት ይመስላል ግን ለሰው ነው። ይኸውም፦

ከግቢው ድኸህ /ተንቀሳቅሰህ/

ለምለም ግጠህ

የሣር ለምለም

ለምለም የሚግጥ፣ ያውም ሣር የሚግጥ፣ እንስሳ ነው። ለከብት የተገጠመ ይመስላል። የቦረና አሮሞ ህይወቱ ኑሮው የተመሠረተው በከብት ላይ ነው፣ ከብት የሚኖረው ደግሞ የለመለመ በቂ ሣርና ውሃ ሲኖር ነው። በአካባቢው ሰውም ሰው ሆኖ የሚንቀሳቀሰው፣ ያፈራው ከብት በልቶ ጠጥቶ የሚኖረው ሳር ሲኖር ነው። ሣር በመኖሩ ልጅ ይኖራል ለማለት ነው። (ሰለሞን ጎዳና፣ ቃለመጠይቅ፣ ሰኔ 19 ቀን 1999) በሌላ መልኩ ግን በደጃፉ ድኸህ ሣር፣ ቆሻሻውን አንስተህ በልተህ ትውላለህ። ወይም ልጅ ደጅ ሲውል ያገኘውን ጥሩ፣ መጥፎ ሳይል ወደ አፉ ያስገባል፣ እግዜር አንተ ጠብቅ፣ የጤና አድርግለት የሚል የፀሎት መልዕክት ያዘለም ነው። (ካሉ ጂሎ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሰኔ 12 ቀን 1999)

እነዚህ ስድስቱ ዜማዎች ቀደም ተከተላቸውን ጠብቀው ከቀረቡ በኋላ፣ ወንዱ ሴቱ፣ ወጣቱ በቡድን በቡድን ሆነው የፈለጉትን የፍቅር፣ የባህልና የከብት ሙገሣ ዜማዎች እያዜሙ፣ እየጨፈሩ ደስታቸውን ሲገልፁ ያድራሉ (ካሉ ጂሎ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሰኔ 12 ቀን 1999)። አባሩፋ ቤትም የሆነው ይኸው ነው።

5.2.7. Kaarilee jila Gubbisaa (ካሪሌ - ሴቶች የሚያዜሙት)

ሴቶች የገልማውን መሠረት መጣያ ሀንደራካ እንጨት ቆርጠው ከተመለሱ ጊዜ ጀምሮ በሦስቱ ቀን የበዓሉ ቆይታ በተለይ የገልማው ሥራ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ በእጅ እየሠሩ በአፋቸው ያዜማሉ። ሥራቸውን ካጠናቀቁም በኋላ በቡድን በቡድን ሆነው ያዜማሉ። የዜማዎቻቸው ይዘት በአብዛኛው የበዓሉ አዘጋጆች፣ የልጁ አባትና እናት ሙገሣ ላይ ያተኮረ ነው።

Abbaa jilaa taatee, harka lichoon daaxxee

ባለድግሥ ሆነህ እጅህ በሊኾ ደመቀ

Abbaa biyyaa taatee, dubbiin sibarbaaddee

ባለሀገር ሆነህ ጉዳይ ሁሉ አንተን አለ

Torban jilaa taatee daannisaan mardaadde

ቶርበን ጅላ ሆነህ ዳኒሳ ይዘህ ተንሳፈደደህ

Abbaan jilaa gurraacha surree ruufaa

ባለበዓል ጥቁሩ፣ ሱሬ ሩፋ የጠመጠመ

Ayyoon jilaa diimtuu mataa yuubaa

የበዓሉ እናት ቀይ ወጉረ ረኾማ

Warri jilaa akkuma baanan jira	ባለ በዓሎች እንደሚወራላቸው ናቸው
Gololchituu jilaa abbaatu fandii fila	ጥሩ የበዓል አስተናጋጅን ባለቤቱ ይመርጣል

በዚህ ዜማ አባጅላውና ሃደ ጅላዋ በእጃቸው የሚይዟቸው የወግ ቁሳቁሶችና ተፈጥሮ የለገሣቸው ገፅታና ውበት ሳይቀሩ እየተጠቀሱ ይሞገሱበታል። ለበዓሉ የሚመርጧቸው አስተናጋጆች እንኳ ሳይቀሩ እየተጠቀሱ ማሞገሻ ይሆናሉ። ሴቶች ይህንን ዜማ የሚያዜሙት የጉቢሣውን በዓል ገልማ በሚሠሩበት ጊዜ ነው።

ገልማው ተሠርቶ ካበቃ በኋላ ደግሞ ከብቶችን ያሞግሳሉ።

Galoosame hagaloo malaan dhaane	ከብቱ እንዲገባ ደወል አሰማ
Galuu didee tissaan dhaane	አልገባ ሲል እረኛው መታው
Faayoon bulee, duba bulee	ፋዮ ውጭ አደረ
Faayoon kiyyaa bule Burree dhaanee	የኔ ፋዮ አደረ፣ ቡሬ ተመታ
Hinbullu buleen jette	አናድርም አለ
Hinbullu dheebuun jette	በጥም አናድርም አለ

በዚህ ዜማ ግጥም ውስጥ ያለው ሀሳብ ከብቶች ወደ ቀዬ እንዲሰበሰቡ ከግጦሽ ቦታ እረኞች ሲነዱዋቸው ያለውን ሁኔታ የሚያሳይ ነው። አልነዳ ብለው ወደ መጋጥ ሲያተኩሩ መመታታቸውን፣ ሳይገቡ ከበረት ውጭ ማደራቸውን፣ ከብቱ መጠማትን የማይፈልግ፣ ወደ ውሃ ለመሄድ ሲጥር ወደ ተቃራኒ አቅጣጫ መነዳትን እንደማይሻ የሚያሳይ ነው። ዜማው የሚደምቀው በከበሮ አይደለም። ቁርበት መሬት ተነጥፎ ዙሪያውን ክብ ሰርተው በእግራቸው እየረገጡት ልዩ ምት በሚያክሉበት ጊዜ ነው።

ሴቶች በጉቢሣ በዓል ላይ፣ ከባለ በዓሉና ከከብቶች ጋር የተያያዘ ሁኔታ በማጣቀስ ሲያዜሙ ሶስቱን ቀን ባለጉዳዮቹን ሲያስደስቱ ይቆያሉ። ለራሳቸውም ተደስተው ቀናቱን ያሳልፋሉ።

5.2.8. Sirba Jaalalaa Kuchuu (ኩቹ የሚባሉ ወጣቶች የሚያዜሙት የፍቅር ዘፈን)

እነዚህ ኩቹ የሚባሉ ዕድሜያቸው ከ16 ዓመት በላይ የሆኑ ወጣቶች በጉቢሣ በዓል ላይ የራሳቸው የሆነ የሥራ ድርሻና ባህላዊ ክዋኔዎች አሉዋቸው። የበዓሉ የመጀመሪያ ቀን ለአዳራሹ መሥሪያ እንጨት ቆርጠው ያመጣሉ። በሁለተኛው በበዓል ዕለት፣ የገልማው ሥራ በሚጀመርበትም ቀን ገልማው ውስጥ የሚሠራውን ጓዳ መሰል ክፍል መለያ እንጨት ያቀርባሉ። "Gulantaa baasuu" ይሉታል። በሦስተኛው ቀን የአዳራሹ

ማጠናቀቂያ ሥራ ላይ የገልማውን ጣራ በሣር የሚከድኑት እነዚሁ ኩቹዎች ወጣቶች ናቸው።

ወጣቶቹ በበዓሉ ላይ የሚያዜሙዋቸው ዜማዎች በይዘት ከበዓሉ ጋር ምንም ግንኙነት የላቸውም። ያፈቀሯትን ወይም፣ ሊያፈቅሯት ያሰቡዋትን ሴት ያሞግሣሉ።

እነዚህ ወጣቶች ካዜሙዋቸው ውስጥ "ሆሃሜ" (Hoo hammee) በከፊል እንመልከት

Hoo hammee hoyyoo(2)	መግቢያ አይነት ነው
Waaqi boru bonaa	ሰማዩ ነገ በጋ ነው
Amma roobee gannaa	አሁን ዘነበ ክረምት ነው
Salloo mataa gannaa	ውቧ ወጉሯ የራሰ (በቅቤ)
Cirrii foora bultee	ጭሪ (የወፍ አይነት) ከብቶች የተሠማሩበት ያደረች (ጭሪ ለውበት የምትጠቀስ ወፍ ናት)
Foora galaa duultee	ከርቀት የምትመለስ
Omacha galaa dhuddee	የግመል ወተት ጠጥታ ያደገች
Diidi gufuu hinqabne, silaa gunnaa tolaa	እንቅፋት የሌለበት ሜዳ ለሌሊት መንገድ ይመቻል
Mormi lafee hin qabne silaa sirbaa ta'aa	አጥንት የሌለው አንገት ለዘፈን ይመቻል
Guntatni lafee hinqabne silaa irribaa tolaa	አጥንት የሌለው አጎጠጌ ለመኝታ ይመቻል

እያሉ የሴቷን ተክለ ሰውነትና ባህርይ እየጠቀሱ ማሞገስ በወጣቶቹ የተለመደ ነው። ይህች የሚያሞግሷት ሴት ያልተዳረች ልጃገረድ መሆን የለባትም፣ ልጃገረድን ማሞገስ ክልክል ነው። ኩቹዎች የሚያሞግሷቸው ሴቶች ባለትዳሮች ናቸው። አሞግሰው ብቻ አይተውም። ከባል ተሸሽገው ይስማሉ። ይህ ሁኔታ በባህሉ የተለመደ ስለሆነ ፊት ለፊት ካላየ፣ ወሬውን ቢሰማ እንኳ ባል ሚስቴን አማገጥክ ብሎ ከወጣቱ አይጣላም። ሚስቱንም ለምን ተደረገ ብሎ አይጠይቅም። ወጣቶቹም ከመሳም ያለፈ ፍላጎት አያሳዩም። (ሀሮ ኤሌማ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሰኔ 15 ቀን 1999)

ከወጣቶቹ ሌላ አዋቂ ወንዶችም ሌሊቱን ከብቶች የሚያሞግሱበትን ዜማ ከበሮ እየመቱ እየደጋገሙ እያዜሙ እስከንጋቱ ድረስ በዓሉን ሲያደምቁት አድረዋል።

5.3. ቁሳዊ ባህል

ቁሳዊ ባህል የሚዳሰስ፣ የሚቀመስ፣ የሚታይ፣ የሚሸተት ተጨባጭ ቁሶችን አጠቃሎ የሚይዝ ነው።

በቦረና ኦሮሞ የበኩር ልጅ ስም ስያሜ በዓል ላይ በርከት ያሉ የቁሳዊ ባህል አይነቶች ይቀርባሉ። በዚህ በምልከታ በተቃኘውም የጉቢሣ በዓል ላይ ቀርበዋል። በዚህ ንዑስ የቁሳዊ ባህል የፎክሎር ዘር (genre) ሥር ሊጠቀሱ የሚችሉት የቁሳዊ ባህል ዘሮች አልባሳት፣ በእጅ የሚያዙ የወግ ቁሶች፣ የበዓሉ መለዮ የሆነው ገልማ፣ ገልማው ውስጥ የሚካተቱ ልዩ ልዩ እንጨቶች፣ ከምግብ፣ ቡነቀላ፣ በስሙታ የሚመጣ "ጉማተ"፣ "ኮቼ" እንዲሁም ለበዓሉ ከሚታረድ በሬ ቆዳ የሚዘጋጁ ቁሶች "ሜዲቻና ጋዲ" ሊጠቀሱ ይችላሉ።

5.3.1. አልባሳት

አልባሳት አንድ ማህበረሰብ ከሌላው ተለይቶ የሚታወቅባቸው ሆን ብሎ የሚያዘጋጇቸው ልብስና ጌጣጌጥን የሚያካትት ሲሆን፣ ሲጠና ከሚመረትበት ጀምሮ ለአገልግሎት እስከዋለበት ድረስ ያለውን ሂደት ማጠቃለል ይቻላል።

5.3.1.1. Kalloo (ከሎ)

የቦረና ኦሮሞ ከሌላው ተለይቶ የሚታወቅባቸው የራሱ የሆኑ አልባሳት አሉት። በዚህ ጥናት ላይ የሚቀርቡት ከበኩር ልጅ ስም ስያሜ በዓል ጋር የተያያዙት ብቻ ናቸው።

ከሎ በሌላ በዓል ላይ የማይለበስ የበዓሉ ልዩ ምልክት ነው። ለጉቢሣ በዓል "ከሎ" መልበስ የግድ ነው። ከሎ የሚዘጋጀው ልጁ አያት ካሉት በአያቱ፣ አያቱ ከሌሉ ደግሞ እናቱ ታዘጋጃለች። ከሎ በኦሮምኛ ስሙ መረዳት እንደሚቻለው ቆዳ ነው። ከሎው የሚዘጋጀው፣ ቆዳው ተወጥሮ፣ ተፍቆ፣ ከደረቀ በኋላ፣ በማለስለሻ (የጉሎ ፍሬና ሞራ) ታሽቶ እንደ ልብ መተጣጠፍ ከቻለ በኋላ ልክ በልጅ ማዘያ-አንቀልባ መልክ አምሮ ይቆረጥና በሌላ ልብስ ላይ መደረብ እንደሚያመች ተደርጎ፣ አንገት ላይ ማጥለቂያ እንዲኖረው ተደርጎ ይዘጋጃል። በዚህ ብቻ አያበቃም። የጉቢሣን ከሎ፣ ከሎ የሚያደርገው በመልክ በመልኩ የሚሰካካለት ዛጎል (Gulmaa) ነው። ዛጎሉ ከገበያ ተገዝቶ አይቀርብም። በደበሌ ዕድሜ ክልል ውስጥ የቆዩ የእልማን ኮርማ ልጆች ወደ ጋሜ ደረጃ ሲሸጋገሩ፣ አድጎና በዛጎል አጊጦ የነበረው ዐጉራቸው ይላጫል። ዛጎሉ ደግሞ በቤተሰቡ ውስጥ ለሚወለድ ታላቅ ወንድ ልጅ የስም ስያሜ በዓል ለከሎ ዝግጅት ተብሎ ተለቅሞ ይቀመጣል። የእልማን ጃርሣ የሆኑት ከሎ ካላቸው ቤተሰቦች ተውሰው በአሉን ያከብራሉ።

ከሎ የሚለብሱት የልጁ ወላጆችና ሴት አያቶች ብቻ ናቸው። በዓሉን ልዩ ከሚያደርጉት ድርጊቶች አንዱ ይህ የከሎ ልብስ ነው። አለባበሱም ሥርዓት አለው። አባትና እናት ከሎ ሲለብሱ ከትከሻቸው ወረድ አድርገው ነው። ከሎ ተሰባሪ ነገሮች የተንጠላጠሉበት ስለሆነ ለመቀመጥ አያመቻቸውም። ተዘዋውረው እንግዶቻቸውን እንዲያስተናግዱ ሆን ተብሎ የሚደረግ ነው። ከሎ የታላቅ ወንድ ልጅ ወላጅነት (ቤተሰብነት) መለያ ምልክት ነው። (ሰለሞን ጎዳና፣ ቃለመጠይቅ፣ ሰኔ 21 ቀን 1999)።

5.3.1.2. Marxoo (**መርጦ**)

የመርጦ አማርኛ ትርጉሙ ሽርጥ ወይም ግልድም ማለት ነው። በቦረና ኦሮሞ ለግልድም የሚዘጋጀው ልብስ በድሮ ጊዜ ከአቡጀዲ ጨርቅ ነበር። አሁን አሁን ግን ለዚሁ ተብለው ከውጭ የሚገቡ ጨርቆችን መገልገል ተለምዷል።

የቦረና ወንድ ቀበቶውን ፈትቶ ግልድም የሚለብሰው በትላልቅ ባህላዊ በዓላት ላይ ነው። ከነዚህ ባህላዊ በዓላት የበኩር ልጅ ስም ስያሜ አንዱ በመሆኑ አባት አገልድሞ ከላይ በደረበው ባለ ጥለት ዘርፍ ያለው፣ ነጠላ መሰል ልብስ ላይ፣ ሁለት ከሎ ይለብሳል። አባትየው ሁለት ከሎ መልበሱ አንድ ከሴቶቹ ለመለየት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በወንድነቱ ክብር ለመስጠት ነው (ቦርቦር ቡሌ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሚያዝያ 24 ቀን 1999)። የአባ ሩፋ አለባበስም ይህንኑ መንገድ የተከተለ ነው።

5.3.1.3. Gorfoo (**ጎርፎ**)

ጎርፎ የቦረና ሴቶች የሚለብሱት ከፍየል ቆዳ የሚዘጋጅ ቀሚስ ነው። አዘገጃጀቱ፣ የፍየል ቆዳ በደንብ ተለፍፉ ከለሰለሰ በኋላ ለሴቶች በቀሚስ መልክ ሆሮ እንዲገጥም ተደርጎ ይዘጋጃል። ለማሳመር ጠርዙን ወጣ ገባ አድርገው ይከረክማሉ። ከመሀል ወደታች ደግሞ በመስመር ከፋፍለው በማቅለም ውበት ይሰጡታል። ጎርፎ፣ ሴት ልጅ ስትዳር ተዘጋጅቶ ይሰጣታል። የሚለበሰውም በበዓል ቀን ነው።

የልጁ እናት በዚህ መልክ የተዘጋጀውን ጎርፎ ከሥር ለብሳ ከላይ ከአባጅላው ጋር ተመሳሳይ የሆነ ከሎ ደርባለች። የልጁ ሴት አያቶችም ተመሳሳይ አለባበስ መከተል እንዳለባቸው አብ ቦርቦር ቡሌ ገልፀዋል። በዚህ በዓል ግን አያቶች ጎርፎ አለበሱም። እንደ ሌሎቹ ታዳሚዎች መደበኛውን የቦረና ኦሮሞ የባህል ልብስ ለብሰዋል።

5.3.1.4. Surree ruufaa (ሱሬ ሩፋ) በራስ ላይ የሚጠመጠም

ሱሬ ሩፋ ከነጭና የተለያየ ቀለም ካላቸው ክሮች በሽመና የሚሠራ በራስ ላይ የሚጠመጠም ፎጣ መሰል ልብስ ነው። ሱሬ ሩፋ ዘወትርና በሁሉም ሰው አይጠመጠምም። ባህላዊ በዓላት ላይ አባገዳዎች፣ ሀዩዎች፣ በቤት በሚከበሩ በዓላት የበዓሉ ከዋኞች ለምሳሌ ቶርበን ጂላዎች፣ አባጅላው ይጠቀሙበታል። በጉቢጣ ሱሬ ሩፋ የቦረናነት መለዮ አንዱ የወግ ቁስ ነው። ሱሬ ሩፋ ገዳን፣ ባህልን፣ ሰላምን፣ በረከትን፣ ዝናን አመልካች ሆኖ ይጠቀሳል። (ካሉ ጂሎ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ሰኔ 12 ቀን 1999)

5.3.2. በእጅ ላይ የሚጠለቁና የሚያዙ ቁሶች

በእጅ ላይ የሚጠለቁና የሚያዙ ባህላዊ (የወግ ዕቃዎች) የወንድና የሴት ተብለው ተለይተው ይታወቃሉ።

5.3.2.1. Daannisaa (ዳኒሣ)

ዳኒሣ የበዓል ዕለት በወንድ የሚያዝ በትር፣ የሚዘጋጅበት የእንጨት አይነት ነው። በትሩም በዚሁ ስም ይጠራል። ይህን ከዳንሳ የሚዘጋጅ በትር ሁሉም ሰው አይዘውም። የተለያዩ የገዳ ሥርዓት ደረጃዎች ላይ ሲደርሱና የልጅ ስም ስያሜ ሲዘጋጅ፣ የጉዳዩ ባለቤት የሆነው ሰው (አባትየው) እና ቶርበን ጅላዎች የሚይዙት በትር ነው። ዳኒሳ ለሚይዘው ሰው መደገፊያ፣ አጋዥ መመርኮዣ በመሆኑ በልጅ ይመሰላል። ልጅ አድጎ ለቁምነገር ሲበቃ ለቤተሰቡ፣ ለጎሣው፣ ለሀገሩ አጋዥ ደጋፊ ይሆናል ተብሎ በበዓሉ ላይ ይያዛል። (ካሉ ጂሎ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ሰኔ 12 ቀን 1999)

5.3.2.2. Lichoo (ሊቾ)

የበዓል ዕለት በወንድ በእጅ የሚያዝ ከአውራሪስ ወይም ከቀጭኔ ቆዳ የሚዘጋጅ አለንጋ (መግረፊያ) መሰል የወግ ቁስ ነው። በበኩር ልጅ ስም ስያሜ በዓል ላይ ሊቾ የሚይዙት ወዴሣ የሚቆርጡ ሁለት የተመረጡ ሀዩዎች፣ ቶርበን ጅላዎቹና የበዓሉ ባለቤት የልጁ አባት ብቻ ናቸው። እነዚህ በእጅ የሚያዙ ዳኒሣና ሊቾ የበዓሉንና የያገቡን የክብር ደረጃ የሚያመለክቱ ልዩ ባህላዊ ቁሶች ናቸው። ሊቾ የህግ ማስከበሪያ ነው ተብሎም ይታመንበታል። ለበዓሉ ሊቾ ያላዘጋጀ ሰው ጮቆርሳ የተባለ ሣር ይይዛል እንጂ በትሩን ብቻ አይይዝም።

ሊቾም እንደ ዳኒሳ የሚወክለው ወይም የሚመስለው ጉዳይ አለው። ሊቾ ስልጣንን ይመሰላል። በዚህ በጉቢጣ በዓል ላይ የጉዳዩ ባለቤት፣ ወሳኙ አባት በመሆኑ ሊቾ ይይዛል። ሊቾ የህግ ማስከበሪያ በመሆኑም የጉቢጣ በዓል ወሳኝ እንጨት ወዴሣ

ሲቆረጥ የባህሉ ማስፈፀሚያ በመሆኑ ቆራጮቹና ተሸክመው የሚያጓጉዙት ሊኾን ይይዛሉ፣ የህጋዊነታቸው ማረጋገጫ ነው። ቶርበን ጅላዎቹም የበዓሉ አስፈፃሚ አካላት በመሆናቸው ሊኾ ይይዛሉ።

5.3.2.3. Meedhichaa (ሜዲቻ)

ሜዲቻ በስም ስያሜው ማብቂያ ዕለት ወደ ንጋቱ ላይ ከሚታረደው ከብት ቆዳ የሚዘጋጁ የወግ ቁስ ነው። ሜዲቻ ከበሬው እንብርትና ቁርጭምጭሚት አካባቢ ተተልትሎ ወጥቶ፣ የልጁ አባት፣ እናት፣ አያቶቹ፣ ቶርበን ጂላዎቹና እራሱ ልጁ፣ ሴቶች በአንገት ላይ ወንዶች በእጅ ላይ እንዲያጠልቁት የሚደረግ ቆዳ ነው።

ሜዲቻ ለወትሮ ጉዳይ ከሚታረድ ከብት አይዘጋጅም። እንደ ጉቢሣ፣ በገዳ ሥርዓት ውስጥ ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ በሚደረግ የሽግግር ማብሰሪያ በዓል፣ እንዲሁም በገዳ ሥርዓት የየስምንት ዓመት ጉባኤ ላይ ከሚታረዱ ከብቶች ነው። በተለይ ሜዲቻ በበዓላት ጊዜ እጅ ላይ የሚጠለቅና የሚጠራቀም ስለሆነ የሜዲቻው ብዛት የአጥላቂውን ሰው ክብር፣ ሀብት፣ የትላልቅ በዓላት አዘጋጅነት ወይም በትላልቅ በዓል ላይ በክብር ታዳሚነት መገኘት ያመለክታል። (ቦርቦር ቡሌ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሚያዝያ 24 ቀን 1999)

ሜዲቻ ግን ለእንግዳ ማስተናገጃ ከታረደ በሬ ተዘጋጅቶ በእጅ ላይ ሊጠለቅ ይችላል። እዚህ ላይ ግንዛቤ ሊያገኝ የሚገባው፣ ለእንግዳ ከታረደ ከብት የተዘጋጀ ሜዲቻ ተጠልቆ ከተወሰነ ሰዓት ወይም ጊዜ በኋላ ሊጣል ይችላል። በጉቢሣና በሌሎች ትላልቅ ባህላዊ በዓላት ላይ ከታረደ በሬ የተዘጋጀው ሜዲቻ ግን እስከ መቼውም አይጣልም፣ በዘወትር ቀን አይደረግም። በበዓላት ጊዜ ባለሜዲቻው አድርጎት "አባጅላ" እንደነበር ወይም የክብር ታዳሚ ሆኖ ማሳለፉን ያሳይበታል። ክብር ያገኝበታል። (ካሉ ጂሎ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ሰኔ 12 ቀን 1999)

5.3.2.4. ሲንቄ (Siinqee)

ሲንቄ ቀጭን በሴቶች የሚያገ የወግ በትር ነው። በኦሮሞ ሴት ልጅ ከተዳረችበት ዕለት ጀምሮ በባህላዊ በዓላት፣ በሽምግልና ቦታ፣ መብታቸውን ለማስከበር ወደ ሀገር ሽማግሌዎች፣ አባገዳዎች ጋ ሲሄዱ ይይዙታል። ሲንቄ የያዘች ሴት ክብር አላት። አትሰደብም፣ አትመታም። በጉቢሣ በዓል ላይ የልጁ እናት፣ ሴት እያቶቹና በዓሉ ላይ የተገኙት ሴት እንግዶችም ይዘዋል። ክብረ በዓል ላይ ያሉ መሆናቸውን ያረጋግጣል።

5.3.2.5. ሰቃ (Saqqaa)

ሰቃ ከቆዳና ከተለያዩ ሲጋጩ ድምፅ ከሚሰጡ ቁሳቁሶች ለሴት የሚዘጋጅና በእጅ ላይ የሚጠለቅ የወግ ቁስ ነው። ይህ ሰቃ የሚዘጋጀው፣ ለበኩር ልጅ ስም ስያሜ በዓል ሲሆን፣ የበዓሉ የመጀመሪያ ዕለት (muka muraa) እናትየው ከሎሬ ጎርፎ ለብሳ ትንሽ ቁርበት ይዛ ከበረት አዛባ ለመጥረግ ስትገባ የሚዘጋጅላትና የሚሰጣት የበኩር ልጅ እናትነት፣ የጉቢሣ በዓል አዘጋጅነቷንና አዘጋጅታ ማለፏን የምታረጋግጥበት የወግ ቁስ ነው። ይህንን ለማመልከት ሌሎች ሴቶችም ይህን ሰቃ እጃቸው ላይ አጥልቀው በበዓሉ ላይ ተገኝተዋል።

5.3.3. መሰየሚያ ገልማውና በውስጡ የሚካተቱ

ገልማ የበዓል መከወኛ ዳስ ነው። ገልማን ልዩ የሚያደርገው ለበዓል ስለሚዘጋጅ የሚሠራበት ደንብ አፈፃፀምና ለሥራው የሚያስፈልጉ ባህላዊ ክዋኔዎችና ቁሳቁሶች ናቸው።

5.3.3.1. Galma Jila Gubbisaa (መሰየሚያ ገልማ)

የበኩር ልጅ ስም ስያሜ ገልማም፣ የበዓሉ አንዱ መለዮ ነው። ገልማ ሳይሠሩ የበኩር ልጅ ስም ስያሜ አይከወንም። ገልማውን ልዩ የሚያደርገው፣ ቅርፁ፣ ስፋቱ ወይም የሚሠራበት ቁሳቁስ አይደለም። በህዝቡ የሚሰጠው ቦታ እንጂ፣ ከስሙ ብንነሳ ለጉቢሣ የሚሠራው ዳስ "ገልማ" ይባላል። ገልማ በኦሮሞ ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠው በዓል የሚከበርበት አዲስ ዳስ መሰል ቤት ነው። የወገናሞች መገናኛ፣ ቁምነገር መነጋገሪያና ማስፈፀሚያ ቦታ ነው። ገልማ መባሉ ለክብሩ እንጂ በቅርፁ እምብዛም ከሌላው የአካባቢው ቤት ተለይቶ አይደለም። በአጠቃላይ ገልማውን ልዩ የሚያደርጉት ተሠርቶ እስካበቃበት ጊዜ ድረስ የሚከወኑ ድርጊቶችና የማስፈፀሚያ ደንቦች ናቸው።

ይህን ገልማ የሚሠሩ ሰዎች፣ በተለይ ግንባታውን የሚያስጀምሩ እነ ማን እንደሆኑ፣ እንዴት እንደሚጀመር የሚወስኑ ሥነሥርዓቶች በገዳው ሥርዓት ተደንግገው የተቀመጡ ናቸው። ከእንጨቱ ቆረጣ ጀምሮ ተሠርቶ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ደረጃ በደረጃ የሚከወኑ ድርጊቶች አሉ።

የ"ሙከሙራ" ዕለት (የመጀመሪያው ቀን) ለገልማው ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችና ሰዎች መዘጋጀታቸው (ሃዩና ቶርበን ጂላዎቹ)። እነዚህ የተመረጡ ሀዩዎች ወዴጣ ለበቁረጥ ሲሄዱ በእጃቸው "ሆሮሮ" (የአባ ገዳ በትር) መያዛቸው ለበዓሉ ገልማ

የሚደረገውን ክብር ያመለክታል። በመጨረሻ ቀን ተቆርጦ በገልማው የተለያየ ቦታ ላይ ለሚተከለው ቆቲ የሚሰጠውም ክብር ገልማ በበዓሉ ውስጥ የያዘውን ቦታ ያሳያል። ቦረናዎች በባህላዊ አኗኗራቸውና በአካባቢያቸው አየር ሁኔታ ሰበብ ከቦታ ቦታ ሲዘዋወሩ የመኖሪያ ቤታቸውን አፍርሰው እንጨቱን በግመል ጭነው ወደ አዲሱ የሠፈራ መንደራቸው ይወስዱታል። ለጉቢጣ በዓል የተሠራውን "ገልማ" ግን አያፈርሱም። ባለበት ትተውት ይሄዳሉ። ይህም ገልማ ምን ያህል እንደሚከበር የሚያመለክት ነው። ስም ስያሜው እንደተፈፀመ ያንን አካባቢ ለቀው እንዲሄዱ የሚያስገድድ እንደ ውሃና ሣር ፍለጋ ጉዞ ቢኖር፣ በገልማ ውስጥና በአካባቢው የተተከለው ቆቲ ቅጠል ጠውልጎ እስኪረግፍ ለቀው አይሔዱም። (ጃተኒ ዲዳ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሚያዝያ 24 ቀን 1999 ቦርቦር ቡሌ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዝያ 24 ቀን 1999)።

5.3.3.2. Waddeessaa (ወዴሣ)

ወዴሣ የእንጨት አይነት ነው። በቦረና ኦሮሞች ዘንድ ወዴሣ ከሰው ልጅ ቀጥሎ የተፈጠረ ታላቅ እንጨት ነው ተብሎ ስለሚታመንበት ለበኩር ልጅ ስም ስያሜ በዓል ክብር የመጀመሪያ ክንዋኔ የሚጀመርበት ሆኗል።

አንድ በኩር ልጁን በጉቢጣ በዓል የሚያሰይም አባት አስቆርጦ ያቀረበውን ወዴሣ እንጨት ለበዓሉ ወቅት ብቻ ሥርዓቱን ለመሙላት የሚጠቀምበት አይደለም። የወዴሣው እንጨት በበዓሉ ማጠናቀቂያ ሦስተኛው ቀን ማታ ላይ አባትየውና ልጁ ወጉራቸውን ተላጭተው ወደ ገልማው ለስም ስያሜ ሲገቡ አብሮ ገብቷል። ስም ተሰይሞ፣ "ሆ ሀሩሶ" ከተባለ በኋላ የልጁ አባት የለበሰውን ነጠላ መሰል ልብስ ጉልበቱ ላይ ዘርግቶ በስለት የወዴሣውን ጫፍ እንደ መላጨት ፋቅ ፋቅ አድርጎ የሚረግፈውን ፍቅፋቂ በገልማው ወደ ጓዳ ያለ ቦታ ላይ ረጭቶታል። ይህን ድርጊት ሰው ልብ አድርጎ በማይከታተለው ጊዜ ነው የከወነው። ወዴሣው የልጁ ተምሳሌት ተደርጎ ይወሰዳል። ጫፉን የሚፈቀፍቀው እንደተሰየመው ልጅ ወጉር መላጨት ከነበረበት ደረጃ መሸጋገሩን ለማመልከት ነው። ልጁ በህይወት እስካለ ድረስ ከቤት አይለይም። መኖሪያ አካባቢ ሲቀይሩም ይዘውት ይሔዳሉ። (ገልገሎ ዶዮ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሰኔ 14-16 ቀን 1999)

5.3.3.3. Qotii (ቆቲ)

ቆቲ የእንጨት ዓይነት ነው። መደበኛ ስሙ mi'eessaa (ምኤሣ) ነው። ቦርናዎች የበዓል እንጨት ይሉታል። በጉቢጣ በዓል ማክበሪያ ገልማ ደጃፍ፣ በረትና ገልማ ውስጥ ይሰካካል። ቆቲ የሚቆርጡት ቶርበን ጂላዎች ሲሆኑ፣ ሲቆርጡ እንዳገኙት ሳይሆን

አንዱን አልፈው ሁለተኛውን በሥሩ ደራራ አፍሰው፣ ማክበራቸውን ከገለው በኋላ ነው። ቆቲ እራሱን ብቻ ሳይሆን የበዓሉን ገልማም ያስከብራል። ቆቲ ተቆርጦ የሚቀርበው ከነቅጠሉ ሲሆን፣ በገልማ ውስጥ የተተከለው ቆቲ ቅጠሉ ደርቆ እስኪረግፍ የጉቢጣ ባለጉዳዮች ገልማውን ለቀው አይሄዱም። ለምለምነት፣ የልጅ ለጋነት የተፈጥሮ ሀብት ክቡርነት የሚገለፅበት ነው።

5.3.3.4. Handaraaka (ሀንደራክ)

ሀንደራክም የእንጨት ዓይነት ነው። የሙክሙራ ዕለት መጀመሪያ የሚቆረጠው ሀንደራክ ነው። የሚቆርጡትም ሴቶች ናቸው። እነዚህ ሴቶች በሚሰየመው በኩር ልጅ እናት ይመራሉ። ዱር ሄደው ሀንደራክውን ቆርጠው ከበረቱ ደጃፍ ያስቀምጡታል። በሁለተኛው ዕለት የገልማው ሥራ ሲጀመር እንደ መሠረት የተቀመጠው ይህ ሀንደራክ ነው። መሠረቱን በገልማው Boroo (ቦሮ) የተባለ አቅጣጫ ላይ ያኖሩት የልጅ አያት (የአባት እናት) እና የልጁ እናት ናቸው። ይህም ክዋኔ፣ የሚሠራው ገልማ የበዓል፣ የተከበረ፣ መሠረት ያለውና ከቤተሰብ ወደ ልጅ የሚተላለፍ ወግ መሆኑ የሚገለፅበት ነው።

5.3.4. ሌሎች

በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር የተገለፁት የቁሳዊ ባህል አካል ሆነው በይዘታቸው የተለያዩ ናቸው።

5.3.4.1. Gumaata (ጉማቶ)

ጉማቶ የወለደች ሴት፣ የገዳ ሥርዓት ያከበረ ሰው፣ የግርዛት በዓል ያከበረ ልጅ መጠየቂያ ቁስ ነው። በአብዛኛው ጊዜ ጉማቶ ለምግብ ነክ መጠየቂያዎች የሚሰጥ ስም ነው። አንዳንድ ጊዜ ልብስ፣ ሌሎች የስጦታ ዕቃዎችና ገንዘብም ጉማቶ ተብለው ይጠራሉ።

በጉማቶ መልክ ሕይወት ያላቸው እንደ በግ፣ ፍየል፣ ከብት፣ ግመል የመሳሰሉት በስጦታነት ለጉቢጣ ሲሰጡ ሀንዱራ (Handhuuraa) የሚል ስያሜ ይኖራቸዋል። ሀንዱራ ብዙ ጊዜ በዘመድ፣ በቅርብ የቤተሰብ አባላት ታስቦበት ልጁንና አባትየውን ለመርዳት የሚሰጥ ነው።

አባጅላው የሚያርደው ከብት ከሌለው፣ ከሀንዱራው ከብት ታርዶ ጉዳዩ ይከወንበታል። የአባጂላው ቤት ዝግጅት የተሟላ ከሆነ ደግሞ ተነድተው የመጡት የሀንዱራ ከብቶች ከበረቱ ካሉት ላይ ተጨምረው ንብረቱን ያበራክቱለታል።

በአጠቃላይ ይህ የ"ጉማቱ" ወይም የ"ሀንዱራ" ሂደት የቦረና አሮሞን የመረዳዳትና የምጣኔ ሐብት አገነባብ ባህላዊ ዘዴን ያሳያል።

የሀንዱራ ከብቶች በሙሉ በልጁ ስም የሚመጡ ናቸው። በመጨረሻ የበዓሉ ቀን የልጁ የተላጨ ፀጉሩና የወደቀ ዕትብቱ በወተት ተቀላቅሎ አባትየው በሰጠው ከብቶች ጀርባ ላይ እያፈሰሱ እንዲነዳቸው የሚደረጉትም የሀንዱራ ከብቶች ይባላሉ። እነዚህ የሀንዱራ ከብቶች በሙሉ የልጁ የግል ንብረት ናቸው። የቦረና አሮሞ ልጁን ባለንብረት ማድረግ የሚጀምርበት አንዱ አጋጣሚ በዚህ የስም ስያሜ በዓል ሰበብ የሚሰጠው ጉሙተ መሆኑን ካለው ክዋኔ ሂደት መገንዘብ ይቻላል።

5.3.4.2. Kochee (ኮቼ)

ኮቼ ባህላዊ የምግብ አይነት ነው። በአብዛኛው አሮሞ ዘንድ ኮቼ ከሥጋ የሚዘጋጅ የምግብ ማባያ ሆኖ ይታወቃል። በቦረና አሮሞዎች ግን ኮቼ ከጉበስና ቅቤ የሚዘጋጅና ለጉቢጣ በዓል ለኩቹ ወጣቶች የሚቀርብ ባህላዊ ምግብ ነው። አዘገጃጀቱ ጉበስ ተንጣጥቶ በሽርክቱ ከተፈጨ በኋላ የተነጠረ ቅቤ በደንብ ተጨምሮበት ታሽቶ ዲቤ በተሰኘ ባህላዊ ዕቃ ተከትቶ ለወጣቶች ይቀርባል። ምግቡ አካል ይገነባል ተብሎም ይታመናል። ለዚህም ነው ለወጣቶቹ ተለይቶ የሚዘጋጀው (ወ/ሮ ከሹ አባሩፋ /የተሰየመው ልጅ እናት/ ቃለመጠይቅ፣ ሰኔ 14 ቀን 1999)

5.3.4.3. Gaadii ጋዲ

ጋዲ ከበሬ ቆዳ የሚዘጋጅ፣ ላም ስትታለብ እግሯ የሚታሰርበት ነው። የሚዘጋጀው ለበዓል ከታደረ በሬ ቆዳ ብቻ ነው። በዚህ በጉቢጣ በዓልም በበዓሉ ላይ ተጠርተው "ጉማቱ" (Gumaata) ስጦታ ለሰጡ ሰዎች፣ የተቀረው የበሬው ቆዳ በቀጫጭኑ ተቀዳዶ በቦረና ውስጥ ባላቸው የንዑሣን ክፍሎች ታላቅነት ቅደም ተከተል እንዲደርሳቸው ተደረገ። ይህ በቀጫጭኑ ተሰነጣጥቆ የሚከፋፈለው ቆዳ፣ ጋዲ (Gaadii) ይባላል። ላም ሲታለብ እግር የሚታሰርበት ነው።

ይህ ጋዲ የመከፋፈሉ ሥርዓት የራሱ የሆነ ትርጉም አለው። ይኸውም ህዝቡ በጋራ የሚከውኑዋቸውን ለማመልከት፣ ጉዳይ ጉዳዬ፣ ችግሩንም ደስታውንም ተጋርተን

እንወጠዋለን ለማለት፣ ለመተሳሰራቸው ተምሳሌት መሆኑን ለማሳየት የሚያደርጉት ነው። (ገልገሎ ዶዮ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሰኔ 16 ቀን 1999)

5.4. መንፈሳዊ ይዘት ያላቸው

በዚህ ንዑስ ክፍል ሥር የተጠቃለሉት ለስም ስያሜው በዓል መሳካት ምርቃት የተሰጡባቸውና መልካምነቱ የተለካባቸው ቁሶች ናቸው።

5.4.1. Bunaqalaa (ቡነ ቀላ)

ቡነ ቀላ በኦሮሞ ባህል በትላልቅ በዓላት፣ እንደሠርግ፣ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓላት እንደ እሬቻ፣ በገዳ ሥርዓት ውስጥ በሚከበሩ ከደረጃ ወደ ደረጃ የሚደረጉ የሽግግር ማብሰሪያ በዓላት፣ በጉቢጣ ሆነ በሞጋጣ ሥነሥርዓት ላይ፣ ከየትኛውም የበዓላት ማክበሪያ ሥነሥርዓቶች ቀድሞ የሚከወን ነው።

ቡነቀላ፣ ቀጥተኛ አማርኛ ትርጉሙ የቡና እርድ ማለት ነው። ቡና አይታረድም፣ ግን የዕርድ ተምሳሌት ነው። የሚሰጠው ክብርና ቦታም በሬ አርዶ ከማቅረብ አይተናነስም። (አለማየሁ ኃይሌ፣ ቃለመጠይቅ፣ ሚያዝያ 6 ቀን 1999)

ቡነቀላ የሚዘጋጀው፣ ድፍን እሸት ቡና (የቀላው) ተለቅሞ፣ ጫፍ ጫፉ እየተቆረጠ (ይህን የመቁረጡን ሂደት ነው ማረድ የሚለው ተግባር የሰጡት) ለዚሁ በተዘጋጀ ሸክላ (ማሰሮ) የተነጠረ ቅቤ ተጨምሮ እሳት ላይ ይጣዳል። ቅቤው እንደውሃ እየተንተከተከ ውስጡ ባለው ቡና እየተመጠጠ በመጨረሻ መንጣጣትና መብሰል ይጀምራል። እዚህ ደረጃ ሲደርስ በቦረናዎች የጉቢጣ በዓል ላይ እንደታየው የታለበ ወተት ተጨምሮበት በጮሌ ተገልብጦ፣ ተመርቆ ከልጅ ቤተሰቦችና ቶርበን ጅላዎች ተጀምሮ ሁሉም ተሳታፊ እየተነነጨ እንዲቃመስ ይደረጋል። ሲነነጭ ቡናው አብሮ የደረሰው እድለኛ ነው ይባላል።

ይህ የቡነቀላ ሥነሥርዓት አቀራረቡ በውስጡ መንፈሳዊ ይዘት አለው። ለጥጋብ ወይም ለሱስ የሚቀርብ ምግብ ወይም መጠጥ አይደለም። ቡነ ቀላ አምላክ መለመኛ፣ መመረቂያ ነው። አንድ በዓል በቤት ውስጥ ሆነ በአደባባይ ቢከበር ክዋኔው የሚጀመረው በምርቃትና በቡነቀላ ነው። የቦረና ኦሮሞ የቡናን ፍሬ በቦረና ህዝብ ይመስለዋል።

5.4.2. Buna Dhahaa (ቡነ ደሃ)

ቡነደሃ ሁልጊዜ የሚቀርብ ክዋኔ አይደለም። በጉቢጣ፣ በጋብቻና ሰው ሲሞት ነው። አዘገጃጀቱ፣ የቡና ፍሬን ቆጥሮ ረመጥ ውስጥ በመጨመር ሲንጣጣ አውጥተው የታለበ

ወተት ውስጥ በመጨመር ለታዳሚዎች እንዲጎነጩት ማድረግ ነው። ይህ የቡናደሃ አቀራረብ እንደበዓላት ይለያያል። በሠርግ በዓል ላይ በጮጮ ከወተት ጋር ተሰጥቶ ሁሉ ሰው እንዲቀምሰው ይደረጋል። በጉቢጣ የሚጨመረው ፍሬ አሥራ አራት ነው ቶርበንጅላዎቹ ብቻ ይጎነጫሉ ሁለት የቡና ፍሬም ያገኛሉ። በሠርግ ላይ እድለኛ ነው የሚያገኘው። ቡና ደሃ ከአንድ ደረጃ ወደ ተከታዩ ሲሸጋገሩ የሚከወን የገድ መለኪያ ነው።

5.4.3. Daraaraa (ደራራ)

ደራራ መመረቂያ ቁስ ነው። የተለያዩ ሥነሥርዓቶች በሚከወኑበት የመጀመሪያና የማጠናቀቂያ ጊዜ ምርቃት የሚሰጥበት ነው። በእጅ የሚያዘው መመረቂያ እንደየአካባቢው ይለያያል። በአብዛኛው፣ ሰርዶ ወይም ለምለም ቅጠል አለዚያ በፈሳሽ መልክ ወተት /ማር/ በአፍ ተጎንጭቶ በመርጨት ይመረቃል። ይህ ድርጊት በኦሮምኛ "ቢፋ" ይባላል። የመመረቂያው ቁስ ወተት ወይም ማር ሊሆን ይችላል። ደራራ በእጅ የሚያዝ ወይም በፈሳሽ መልክ የሚቀርብ ይሆናል። በአንድነት "ደራራ" ይሉታል።

በቦረና ኦሮሞ የጉቢጣ በዓል የመጀመሪያው ዕለት ለበዓሉ ተጠርተው የመጡትን እንግዶች፣ አባትየው ለምለም ቅጠል ይዞ "Hoodhaa daraaraa" "እነሆ ለምለም" ብሎ በሚሰጣቸው ደራራ ቁስ በዓሉ በይፋ ይጀመራል። እንኳን ደህና መጣችሁ የሚል ይዘት ይኖረዋል። እነርሱም ሲመልሱ "namaafi sa'aan daraari" "በሰው በእንስሳ ለምልም" ብለው የበዓሉ ሥነሥርዓት ይጀመራል።

የጉቢጣን "ከሉ" የሚዋሱ ከሆነም ይህን "ደራራ" የተባለውን ነገር ይዘው ነው። "ደራራ" ከለምለም ቅጠል ወተትና ማር በተጨማሪ እንደ ቡና፣ ትንባሆ፣ የመሳሰሉትን የመማለጃ ቁሶችንም ያካትታል። በመሆኑም ለከሉ ውሰት፣ ለጋብቻ ጥያቄ ሲሄዱ ከለምለም ቅጠሉ ጎን ለጎን ቡና ወይም ትንባሆ ይይዛሉ። አጠቃላይ መጠሪያቸው ደራራ ነው። መለመኛ ወይም መማለጃ ማለት ነው።

በጉቢጣ ገልማ ውስጥ የሚተከለውንና ከፍተኛ ክብር የሚሰጠውን የቆቲ እንጨት ለመቁረጥ ሲሄዱም "ደራራ" ይዘው ሲሆን፣ ሲቆርጡም ደራራውን ከሥሩ አፍሰው ነው። እዚህ በዓል ላይ የቀረበው ደራራ ወተት ነው። ይህንንም ሂደት "wayyoomsuu" ይሉታል። ወዮምሱ ማክበርን ያንፀባርቃል። "ደራራ" መማለጃ፣ የክብር መግለጫ መሆኑን ይህኛው የቆቲ ቆረጣው ሂደት እራሱ ያረጋግጣል። በዚሁ በደራራ ስም በበዓሉ ላይ ለተገኙ "ተንቦ" (ትንባሆ)፣ ተዘጋጅቶ ይታደላል። በጣት በጣታቸው እየቆነጠሩ

ይቀምሳሉ። አፋቸው ውስጥ አቆይተው ይተፉታል። ተንቦ /ትንባሆ/ የማኘቃቅት ባህርይ አለው።

5.4.4. Eebbaa (ምርቃት)

በኦሮሞ ባህል ማንኛውም ሥራ፣ በዓል፣ ትንሽ ትልቅ ሳይባል፣ ሲጀመርና ሲጠናቀቅ ምርቃት ይሰጥበታል። ሲመረቅ ደግሞ የሚያዝ ነገር ያስፈልጋል።

በአባሩፋ የጉቢጣ በዓል ላይ የመጀመሪያው ቡነቀላ በተዘጋጀ ጊዜ ምርቃት ተሰጥቶ ነበር። አሰጣጡ፦

ቡነቀላ ያዘጋጀች ሴት፣ ቡናውን ይዛ ቀርባ ጭልፋ በመሰለ ዕቃ እየቀዳች እየመለሰች ሀዩ የሆነ፣ የተለያዩ የገዳ የዕድሜ ደረጃዎች ውስጥ ያለፈ ሰው ይመርቃል። ምርቃቱ ረዥም ነው በከፊል የሚከተለውን ይመስላል።

መራቂ	ምርቃት ተቀባዮች	መራቂ አማርኛ ትርጉም	ተቀባይ
Bobba'an nagayaa	Nagahi	የሚሠማራ ሰላም	ይድረስኝ
Bobbaan nagayaa	Nagahi	ስምሪት ሰላም	ይድረስኝ
Olmaan nagayaa	Nagahi	ውሎ ሰላም	ይድረስኝ
Galchuun nagayaa	Nagahi	መመለስ ሰላም /አሰሚርቶ ማስገባት/	ይድረስኝ
Barri nagayaa	Nagahi	ዘመኑ ሰላም	ይድረስኝ
Bariin nagayaa	Nagahi	ንጋት ሰላም	ይድረስኝ
Waareen nagayaa	Nagahi	ረፋዱ ሰላም	ይድረስኝ
Waariin nagayaa	Nagahi	ምሽቱ ሰላም	ይድረስኝ
Elmaan nagayaa	Nagahi	ከብት ማለብ ሰላም	ይድረስኝ
Elmituun nagayaa	Nagahi	አላቢዎች ሰላም	ይድረስኝ
Elmaa gaadii nagayaa	Nagahi	የወተት አካባቢ ሰላም	ይድረስኝ
Tissa huleen nagayaa	Nagahi	የወተት ማለቢያ ቁሳቁሶች ሰላም አጋጁ እረኛና ማጋጃው በትር ሰላም	ይድረስኝ
Liiban Dirreen nagayaa	Nagahi	ሊበንና ድሬ ሰላም	ይድረስኝ
Gadaan sadeen nagayaa	Nagahi	ሦስቱ ገዳዎች ሰላም	ይድረስኝ
Raabaa Kuusii nagayaa	Nagahi	ለራባ ኩሣ ሰላም	ይድረስኝ
Gosa Booranaa Sabboo Gonaa nagayaa	Nagahi	ለቦረና ኅሣዎች ለሰቦና ጎና ሰላም	ይድረስኝ

እያለ ይቀጥላል።

Waarii nagayaa

Elmituun nagayaa

Tissa huleen nagayaa

Gadaa sadeen nagayaa

Raabaa Kuusii nagayaa

የሚሉት በውስጣቸው ዘርዘር ያለ ነገር ይዘዋል።

Waarii nagayaa የሚለው ምሽቱ ሰላም የሚል የአማርኛ ትርጉም አለው። በምሽት ውስጥ ደግሞ ብዙ ድርጊቶች ይከወናሉ። ከብቱ፣ ቤተሰቡ ወደ ቤት ተሰብስቦ በአንድነት የሚቆይበት፣ እራት በልተው፣ የሚያመሻሽ እንደቡነቀላ ተዘጋጅቶ ቤተሰብ የሚጨዋወትበት ወቅት ነው። በጫወታዎች ውስጥ ደግሞ ብዙ ቁምነገሮች፣ አዝናኝ ድርጊቶች ይኖራሉ። እነዚህ ድርጊቶች ሁሉ ሰላም ይሁኑ ለሰላም ይዋሉ ነው ምርቃቱ።

Elmaa gaadii nagayaa - ወተት የማለቡ ሥራ የሚታለብባቸው የማለቢያ ሥርዓቱ ሰላም እንደ ማለት

Tissa huleen nagayaa - ከብት አጋጆች ሰላም

ይህም በውስጡ ጠለቅ ያለ ትርጉም አለው። ወተት ማለብ የሚቻለው፣ ጥሩ የወተት መጠን ሊገኝ የሚችለው፣ በቂ ሣርና ውሃ ሲኖር፣ ወቅቱ ለም ሲሆን ነው። ምርቃቱም ከብቶች ተራብተው በረቱ ይሙላ፣ ከብቶቹ የሚግጡትን ሣርና የሚጠጡትን ውሃ በበቂ አግኝተው ወተት ይስጡን፣ ከነሱ ጋር ሲወጡ ሲገቡ፣ ሲወጡ ሲወርዱ የሚውሉ እረኞችም ሰላም ይሁኑ። እነዚህ ሲኖሩ ነው የምንኖረው የሚል መልዕክት የያዘ ምርቃት ነው።

Gadaan sadeen nagayaa	Nagahi	ሦስቱ ገዳዎች ሰላም
Raabaa Kuusii nagayaa	Nagahi	ለራባ ኩሣ ሰላም

እነዚህ ሁለቱ ስንኞች ደግሞ ምርቃቱ ጠለቅ እያለ መሄዱን ያሳያሉ። ይኸውም ሦስቱ ገዳዎች ሰላም ሦስቱ ገዳዎች አርቦረ፣ ኮኒቱና አወጡ ናቸው። ሰላም ይሁኑ። ይኸኛው አስተዳደሩ፣ ሀገሩ ሰላም፣ ይሁን ማለት ነው። ተከትሎ ያለው ስንኝ ራባ ኩስ የሚለው፣ በገዳ ሥርዓቱ የስምንት ዓመት የስልጣን ሽግግር ተከታዩ ማን እንደሆነ ይታወቃል። አሁን ያለውን ገዳ የሚተካ ተከታዩ ሥልጣን ተረካቢ ራባ ነው። ኩስ ደግሞ ከርሱ ቀጥሎ ያለ ነው እነርሱ ሁሉ ሰላም ይሁኑ ነው። እዚህ ላይ ለግለሰቦች አይደለም ለተከታዮቹ ሥልጣን ተቀባይ ፓርቲዎችም ጭምር ነው። ቅደም ተከተሉ ሳይዛባ በሰላም ይሂድ ማለት ነው።

ምርቃቱ በዚሁ አይነት የአካባቢው የተፈጥሮ ሀብት ሳይቀር ይመረቃል። ትንሽ ትልቅ ሳይል ለህዝቡ ህይወት አስፈላጊ የሆኑ ሁሉ ይመረቃሉ።

ሌላው ምርቃት ስም ሲሰየም አባትየው፣ ለምሳሌ በምልከታው ከተከታተልኩት ጀተኒ አባሩፋ በሉ ብለው ሲጀምሩ አያቶቹ፣ ቶርበን ጂላዎቹ ታዳሚዎቹ ሦስት ተመሳሳይ ስም ያላቸው እነርሱና ወላጆቻቸው በህይወት ያሉትን ይጠሩና አስከትለው ይመርቃሉ። ምርቃቱ፣

Abbeetiifi haadha kee bulfadhu

Loonguddoo bobbaasi

Jabbiyyee guddoo tiksi የሚሉትን ስንኞች ይይዛል።

Abbeetiifi haadha kee bulfadhu የሚለው ስንኝ ብቻውን ሰፊ ትርጉም አለው። የመጀመሪያው እናት አባትህ ዕድሜ ይኑራቸው ማለት ይሆናል። ሌላው፣ እናት አባትህን የምትጦርበት ሃብት ንብረት ይኑርህ፣ አትጣ ሲሆን፣ ጥላቻ መቃረንና መለያየት ሳይገጥማችሁ ሙሉ ዕድሜያችሁን በሰላም አብራችሁ ኑሩ የሚል መልዕክትም በውስጡ ይዟል።

በሁለተኛው ስንኝ፣ Loon guddoo bobbaasi/jabbiyyee guddoo tiksi ያለውን ደግሞ በሀረግ ደረጃ ከፍለን ብንመለከት በየራሳቸው ሰፊ መልዕክት ያስተላልፋሉ።

Loon guddoo bobbaasi – ብዙ ከብት አሠማራ ይህ ማለት በአጭሩ ባለ ብዙ ሀብት /ከብት/ ሁን፣ አትጣ ማለት ነው።

Jabbiyyee guddoo tiksi – ብዙ ጥጆች አግድ

መልዕክቱ የልጁን ጥጆች የማገድ ተግባር መግለፅ አይደለም። ብዙ ጥጆች ይኑሩ ማለት ብዙ ላሞች ይታለቡ፣ ከፍተኛ የወተት ምርት ይኑር ማለት ነው። ስለዚህ ለልጁ ይህ ምርቃት ሲሰጥ የሚኖሩህ ከብቶች የሚራቡ፣ ከፍተኛ ጥቅም የሚሰጡ ይሁኑ ነው። በሌላ አባባል ደግሞ ለቤተሰቦችህ የምትታዘዝ ሁን ነው።
ባጠቃላይ ምርቃት ጥሩ ምኞት የሚገለፅበት፣ አንዱ የቦረና ህዝብ የፎክሎር ገፅታ ነው ማለት ይቻላል።

6. ማጠቃለያ

የቦረና ኦሮሞ የበኩር ልጅ የስም ስያሜ በዓልን (Gubbisaa) ከፍተኛ ቦታ ሰጥቶት፣ አቅዶ ከፍተኛ ወጪ አወጥቶ ደግሦ ወገኑን፣ ወዳጅ ዘመዱን ጠርቶ ያከብረዋል። በዓሉም በቦረና ኦሮሞዎች ባህልና መተዳደሪያ ሥርዓት ጥብቅ ህጎች የሚመራ በመሆኑ በክዋኔዎች የተሞላና የተለያዩ የፎክሎር ዝርያዎች (genres) መከሰቻ ነው ማለት ይቻላል።

የበዓሉ መነሻ የሆነው ስም በቦረና የሚሰየምበት ህግ አለው። የበኩር፣ የታናሽና የሴት ልጅ ስም የሚሰየመው ወላጆቻቸው የመረጡላቸው ሲሆን፣ የሚመረጠው በአካባቢ ተመሳሳይ ስም ያላቸው፣ ወላጆቻቸው በሕይወት ያሉት የሦስት ሰዎች (ልጆች) ስም መሆን አለበት። የአያት ስም የተመረጠ ከሆነም ኑዛዜ ወይም ልጅ (ልጂቱ) ሲወለድ (ስትወለድ) አያትየው በህይወት የነበሩ መሆን አለባቸው። ይህ የሚያመለክተው የምርጫው ትኩረት ይዘቱ ላይ ሳይሆን፣ ሕያው መሆኑ ላይ ነው። ይህ ደግሞ በአንድ መንደር ወይም አካባቢ ተመሳሳይ ስሞች እንዲኖሩ፣ በመጠንም ውስን እንዲሆኑ ያደርጋል። ከዚህ ባሻገር የሚሰየሙት ስሞች ይዘት ሲቃኝ በአብዛኛው ተሰያሚዎቹ የተወለዱበትን ቦታ፣ ጊዜ፣ ቀናት፣ ወቅቶችና ሁኔታዎች እንዲሁም የሰያሚዎችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች፣ እምነትና አተያይ የሚያንፀባርቁ ናቸው።

የቦረና የበኩር ልጅ ስም ስያሜ ሦስት ቀን በሚቆይ በበዓል የታጀበ ስለሆነ ብዙ ሰዎችን የሚያገናኝ፣ የሚያወያይ፣ ውለታ የሚያዋውል ከመሆኑ ባሻገር የህዝቡን ማህበራዊና፣ ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት፣ እምነትና አተያዩን የሚያንፀባርቁ የተለያዩ የፎክሎር ዝርያዎች መቅረቢያ ሆኖም ይገኛል።

በዚሁ መሠረት በስም ስያሜው /ጉቢሣ/ በዓል ላይ የታዩት የፎክሎር ዝርያዎች ከሞላ ጎደል ፈቃደ አዘዘ ዶርሰንን ተከትለው በአራት የከፈሉዋቸውን የፎክሎር ዝርያዎች ሥነቃል፣ ቁሳዊ ባህል፣ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት፣ ሀገረሰባዊ ልማድ ሥር ሊጠቃለሉ የሚችሉ ናቸው፣ ማለት ይቻላል።

በሥነቃል ሥር የሚመደቡት ለጉቢሣ በዓል ብቻ ተብለው የሚዘመሩ /የሚዜሙ/ "ኢያንገሎ"፣ "ቡሉቱሞ ቡሌ"፣ "ሰገዴ መለዮ፣ አሸኔ ዶዮ"፣ "እልሜ ሆዮ"፣ "ሊዮ ኢልዮ" የተሰኙ የቃል ግጥም አይነቶች ናቸው። እነዚህም የበዓሉ ልዩ መለዮ ከመሆናቸውም በላይ በይዘታቸው የቦረናን ኦሮሞ የልጅ አያያዝ፣ ለልጅየሚሰጠውን ቦታ፣ የልጆችን የሥራ ድርሻ፣ መብትና ግዴታ የሚያንፀባርቁ፣ በየስም ስያሜው በዓል /ጉቢሣ/ በመዘመር ባህሉን ከትውልድ ትውልድ ለማስተላለፍ ከፍተኛ ቦታ ይዘው የቆዩ የቦረና የፎክሎር ሀብት ናቸው።

በቁሳዊ ባህል ረገድም የበዓሉ ልዩ መለዮ የሆኑት፣ ከሎ፣ ሰቃ የሚጠቀሱ ሲሆኑ በሌሎች ትላልቅ በዓላት እንደ ጋብቻና የተለያዩ የገዳ ሥነሥርዓቶች ላይ የሚለበሱ፣ እንደ ጎርፎ፣ መርጦ፣ ሱሬፍፉ በእጅ የሚያዙ ዳኒሣ፣ ሊቾና ሲንቄ፣ በበዓሉ ባለቤቶችና በበዓሉ አስፈፃሚ አካል /ቶርበን ጅላ/ መለበስና መያዝ የግድ መሆኑ፣ ለበዓሉ ገልማ ለማዘጋጀት፣ ልጅ በህይወት እስካለ ድረስ በቤተሰቡ እጅ የሚቆየውን ከሰው ልጅ ቀጥሎ ተፈጠረ የሚባለውን ወዴሣ የእንጨት አይነት ቆርጦ ማዘጋጀት፣ ሌሎችም የቁሳዊ ባህል የፎክሎር ዘሮች የጉቢሣን በዓል ትልቅነትና ከትውልድ ትውልድ ሲቀባበሉ እዚህ ያደረሱት የቦረና ኦሮሞ ማንነት መገለጫ መሆኑን ያስገነዝባሉ።

የስም ስያሜው በዓል የቦረና ህዝብ ታላቅን የማክበር ባህል ጎልቶ የሚንፀባረቅበት ነው። ታላቅነት በጎሣና በዕድሜ ተለይቶ ክብር የሚሰጠው ነው። ታላቅ የአባት ተተኪ የቤተሰብ አስተዳዳሪ የባህልና የታሪክ ወራሽ ነው።

የጉቢሣ በዓል የአንድ ቤተሰብ በዓል ብቻ ሳይሆን የቦረና ኦሮሞ የተለያዩ ክፍሎች፣ የቤተሰቡ ሁሉ ጉዳይ ነው። ይህም የሚገለፀው በበዓሉ አስፈፃሚ አባላት ቶርበን ጅላዎቹ ስብጥር ነው። በቶርበን ጂላዎቹ የቦረና ሁለቱ ዋና ዋና ክፍሎች መገኘት የግድ መሆን፣ በዓሉ ላይ የተጠራ ሰው ሁሉ ስጦታ-ጉማቱ መስጠት ለበዓሉ አፈፃፀም ስምረት ተብሎ በህብረት የሚከወን መሆኑን ያሳያል። የቦረና ኦሮሞ አባላት ከማጣት የተነሳ በአብሮነት የሚከውኑት ባህላቸው እንደይዳከም፣ ቀጣይነት እንዲኖረው፣ ተጋግዘው የሚያራምዱት የጋራ ጉዳይ መሆኑን በግልፅ ከማሳየቱም ባሻገር የምጣኔ ሀብት አገነባብ ዘዴያቸውን ያጎላል።

ይኸውም ለበዓሉ ባለቤቶች የሚመጣው ጉማቱና ሀንዱራ፣ በተለይ ሀንዱራው ከብት፣ ገንዘብን የሚያጠቃልል ስለሆነ ለነገ ኑሮአቸው ማደራጃ እንዲውልም ታስቦ የሚፈፀም ነው። ይህ የሚመጣው ስጦታ ልጁ አድጎ ቤተሰብ እስኪመሠርት የወላጆቹን ንብረት ቢሆንም ከተዳረ በኋላ የሚደራጅበት ስለሆነ በምጣኔ ሐብት በኩል ላለው የነገ ሕይወቱ አቅጣጫ አመልካች ነው።

በጉቢሣ የበኩር ልጅ ስም ስያሜ አሉታዊ ውጤት ያላቸው ልማድና ድርጊቶችም ነጥረው የሚታዩበት ነው። ይኸውም ዕድሜን መሠረት ያደረገው ክፍፍል ሴትን አለማቀፉ፣ ጉቢሣ በዓል የበኩር ልጅ ብቻ መሆኑ፣ በአንድ ቤተሰብ ልጆች መሀከል በፆታ ልዩነትና በአወላለድ ቅደም ተከተል የደረጃ ተዋረድ እንዲኖር ከማድረጉም በተጨማሪ፣ የሴት ልጅ ሰብዓናን አሳንሶ ያቀርባል። ሴት የመጀመሪያ ሆና ብትወለድም በጉቢሣ ሥርዓት እንድትሰየም አይፈቅድም። በታላቅነቷ የቤተሰቦቿ መጠሪያ ትሆናለች ቢባልም ወንድ ልጅ ተከትሏት ከተወለደ የእርሷ መጠሪያነት እንዲቀር ስለሚደረግ ሦሮ

ሥሮ ለሴት ልጅ የሚሰጠው ቦታ ዝቅተኛ መሆኑን ያሳያል። ይህም በመሆኑ በነዚህ ወገኖች ላይ የሚያሳድረው የምጣኔና የሞራል ተዕዕኖ ቀላል የሚባል አይሆንም።

ሴት ልጅ በቤተሰቧም ሆነ በተዳረችበት ቦታ በተለይ ካልወለደች በጀ ምንም ንብረት ስለሌለ ሕይወቷ መሪር ይሆናል። የመረጃ አቀባዬ፣ አቶ ካሉ ጂሎ "ሴት ምንም የላትም፣ የሌላ ጎሣ ናት" ያሉት ይህንኑ ይገልፃል። ሴት ልጅ በቤተሰቧ ስትዳር የሌላ ጎሣ አባል ጋ ትሔዳለች በሚል ትኩረት አይሰጧትም። ከተዳረች በኋላ በአባቷ እንኳ አትጠራም። የምትጠራው በባሏ ስም፣ ጎሣዬ የምትለውም የባሏን ጎሣ ነው። ተድራ ካልወለደች ደግሞ የሚሰጣት ክብር ከዚህም ይቀንሳል።

ታላቅ ወንድ ልጅ ከፍተኛ ቦታና ክብር በሚሰጠው በጉጂ መሰየሙና በጉማታ የሚመጡ የሀንዱራ ከብቶች ባለቤት፣ የአባቱ ወራሽና በቀዬ የሚቀር እርሱ ብቻ መሆኑ፣ በአንድ ቤተሰብ ልጆች መካከል የደረጃና የምጣኔ ሐብት አደረጃጀት ከፍተኛ ልዩነት እንዲኖር የሚያደርግ በመሆኑ፣ አንዳንድ በቤተሰብ መካከል ለሚፈጠር አለመግባባቶች መነሻ ሊሆን ይችላል ወደሚል ድምዳሜ ያደርሳል።

ባጠቃላይ የበኩር ለጅ ስም ስያሜ በዓል ጉጂ የቦረናን ኦሮሞ ባህላዊ የጠነከረ የርስ በርስ ግንኙነት፣ የመተጋገዝ ዘዴ፣ የባህል ህግጋት ጥንካሬ፣ እምነት፣ አተያይ፣ የምጣኔ ሐብት አያያዝን የሚያመለክት ባህል ነው።

ከዚህ በመነሳት እንደ ይሁንታ ልጠቅሰው የምሻው የቦረና ኦሮሞ ጉጂን መሰል የተለያዩ የፎክሎር ዘርፎች፣ ልማዳዊ ድርጊቶች፣ እምነቱና የመሳሰሉት በየራሳቸው ሊጠኑ የሚችሉ እስከ ዛሬ ያልተዳሰሱ አሉት። እነዚህ የተለያዩ የፎክሎር ዝርያዎችን አካትተው የያዙ ባህላዊ ክዋኔዎች አሁንም በተግባር ላይ ያሉ የህዝቡ ታሪክና ባህል ተጨባጭ መረጃዎች ናቸው። ስለዚህ ትኩረት ተሰጥቷቸው ቢጠኑ፣ ህዝቡንና አካባቢውን መሠረት አድርጎ ለሚወጠን ማንኛውም ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ሥራ መሳካት እገዛ ያደርጋሉ።

የዋቢዎች ዝርዝር

Alemayehu Gurmu. "Naming in Kistanne Notes on form and Content," In Proceeding of the 12th Annual Conference of the Institute of Language Studies, A.A, AAU Printing Press, 2000.

Almagor, U. Name-Oxen and Ox-names among the Dassanetch of South Ethiopia 1972.

Areggaa Hailemicheal. " A Sociolingustic Approach to the Study of Anyowa Personal Names: A contribution to Socio-Onomastic Studies In A Nilo-Saharan Language." Ethiopia Journal of Educational Researchers' Association. A.A Vol. 2 No 1, 2005: 39-53.

Asefa Jaleta. Oromia and Ethiopia: State Formation and Ethno National Conflict 1868-1992. Boulder and London: Lynne Rienner Publishers, 1993.

Asmarom Legesse. Gada, Three Approaches to the Study of African Society. New York: The Free Press. A Division of Macmillan Publishing Co. Inc. 1973.

Baxter, P.T.W, "Repetition in Certain Borana Ceremonies." In Africa System of Thought. London: International African Institute, 1955.

_____ Being and Becoming Oromo: Historical and Antropological Enquiries. Asmara: the Red Sea Press, Inc. 1996.

_____ "Stock Management and Diffusion of Property Right among the Borana." In Proceedings of the 3rd International Conference of Ethiopian Studies. Addis Ababa University, 1970,116-27.

Baxter, P.T.W, and Uri Almagor (ed). Age, Generation and Some Features of East African Age Organizations. London: C. Hurst and Company, 1978.

Baye Yimam. "Personal Names and Identity Formation Across-Cultural Prospective." THE PERILS OF FACE. Essays on cultural contact respect and self esteem in Southern Ethiopia. (Ed) Stirecker Ivo and Jean Lydal. London: Tranaction publisher, 2006:37-69.

Bukenya, Austin, Wanjiku M. Kabira, Okoth okombo (eds). Understanding Oral Literature. Nairobi: Nairobi University Press, 1994.

Dorson, Richard M. (ed) Folklore and Folklife: An Inturduction. Chicago and London: The University of Chicago press, 1970.

Dundes, A. (ed.) The Study of Folklore. Englewood Cliffs N,J,: Prentice-Hall, Inc. 1965.

Feqade Azeze. "The State of Oral Literature Research in Ethiopia: Retrospect and Prospect" Journal of Ethiopian Studies. V,34,No 1, Addis Ababa University, Institute of Ethiopian Studies, 2001:43-85.

_____ "Ethiopia Oral Literature: a Preliminary review and bibliography" 8th International Conference of Ethiopian Studies, November 26-30. Addis Ababa University, Institute of Ethiopian Studies, 1984:1-56,.

Gada Melba. Oromia: An Introduction to the History of the Oromo People. Khartoum, Sudan, 1988.

Gemachu Taye. "Indigenous Survival Strategies in the Face of Famine: The Case of Borana Oromo Southern Ethiopia," A.A.U. 2002 (M.A. thesis).

Gammachu Taayyee. "Moggaasa maqaa Booranatti." Kallacha Oromiyaa. (bara 1989, Guraandhala 6 ful.3)

Gennep, Arnold Van. The Rites of Passage. (Translated by Monika B. Vizedom and Gabrielle L. Caffe) London, Western Printing Service, 1960.

Gluckman, Mas. Ritual of Social Relations (Essays) (ed) Manchester, Manchester University Press, 1962.

Masfin Tashoomaa. "Oromoon Booranaa Angafa ni Gubbisa." Kallacha Oromiyaa. (lakk. bara 1998, Sadaasa 29 ful. 3)

Mohammad Hasen. The Oromoo of Ethiopia: a History 1570-1860. Trenton NJ. The Red Sea Press ,1994.

Nikodimos Idiris. "Traditional Name and Naming Among Kunama." 5th Annual Seminar of the Institute of Language Studies. Addis Ababa University, 1991.

Sahilu Kidane. "Borana Folktales: A Contextual Study". Addis Ababa University, 1996 (M.A.Thesis).

Sims, Martha C. and Marthin Stephen. "Living Folklore" An Introduction the Study of People and Their Traditons. Longan Ut. Utaha. State University Press, 2005.

Tadhi Liben. "Historical Assembly at Gayo." Borana Pastoral Development Bazar Bulletin. A.A. Mega Printing Press. 2007.

ሳሙኤል ጎንደሬ፤ "የሰው የተወው ስሞች በጋሞ ብሔረሰብ" የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ሥነጽሑፍ ክፍል፣ ድማጽ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ 1975።

ብርሃኑ ሐንካራ፤ "የሰው ስም አወጣጥ በሲዳማ ብሔረሰብ"፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል፣ የአርትስ ባችለር ማሚያ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ 1980።

አያሌው ምትኩ፤ "የአደሬ ብሔረሰብ የስም አወጣጥ" የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል፣ ድማጽ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ 1976።

አብረሃም ስዩም፤ የትግርኛ የሰው የተዐውኦ ስሞች፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል፣ ድማጽ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ 1963።

ኢብራሂም ሰይድ፤ "በወለጋ ኦሮሞ የሰው የተዐውኦ ስሞች" የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል፣ ድማጽ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ 1974።

ከበደ መርጊያ። ሬዲዮ ድራማ በኢትዮጵያ ለቋንቋዎችና ቲያትር ጥበባት ክፍል፣ ድማጽ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ 1975።

ጉልላት አበራ፤ "የጎጃም የሰው የተዐውኦ ስሞች" የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል፣ ድማጽ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ 1963።

ጌታሁን ተፈራ፤ "የሰው ስም አወጣጥ በሀዲያ ብሔረሰብ"፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል፣ ድማጽ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ 1980።

ደብሪቱ ተፈራ፤ "የደራሼ /ጊደሌ/ ብሔረሰብ የተዐውኦ ስሞች የአስያየም ስልት"፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል፣ ድማጽ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ 1978።

ፈቃደ አዘዘ፤ የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ሥነቃል ጥናት ቅኝት ግምገማና የሥነቃል ስብስቦችና ጥናቶች መዘርገር /ቢብሎግራፊ/፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ሐምሌ፣ 1977።

_____፤ <u>የሥነቃል መምሪያ</u>፣ አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፣ 1991።

መረጃ አቀባዮችና መረጃ የሰጡባቸው ጉዳዮች

ተራ.ቁ	ሙሉ ስም	ፆታ	የት/ደረጃ	ዕድሜ	ሥራ	የመኖሪያ አድራሻ	የመረጃ አይነት	መረጃ የሰጡበት ቀን	መረጃ የሰጡበት ቦታ
1	አብ ቦርቦር ቡሌ	ወንድ		60	አርብቶ አደር	ቦረና፣ ድሬ ወረዳ	ቃለ መጠይቅ ስለ ጉቢጣ፣ የቦረና ኦሮሞ ታሪክና ባህል	ሚያዝያ 24 ቀን 1999	ያቤሎ ወረዳ፣ ያቤሎ ከተማ
2	አብ ካሉ ጂሎ	ወንድ		48	አርብቶ አደር	ቦረና፣ ያቤሎ ወረዳ	ቃለ መጠይቅ የጉቢጣ በዓል አፈፃፀም ቅደም ተከተል፣ የቦረና ኦሮሞ ታሪክና ባህል	ሰኔ 12 ቀን 1999	ያቤሎ ከተማ
3	አብ ጃተኒ ዲዳ	ወንድ		38	የታሪክ ኤክስፐርት	ያቤሎ ከተማ	ቃለ መጠይቅ ስለ ጉቢጣና የቦረና ኦሮሞ ባህልና ታሪክ	ሚያዝያ 22 ቀን 1999፣ ሰኔ 12-17 1999 በተለያየ ጊዜ በስልክ፣ በፋክስ	ያቤሎ ከተማ ያቤሎ ወረዳ፣ ዳዲ አርብቶ አደር የገጠር ቀበሌ
4	አብ ሰለሞን ጎዳና	ወንድ	12ኛ ክፍል	36	ሪፖርተር	አ.አ.	ስለ ቦረና ኦሮሞ ባህል በተለይ ጉቢጣ አከዋወንና ደንብ፣ ስለ ቦረና ስሞች አይነትና ምንነት	የጥናቱ ርዕስ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የቦረና ኦሮሞ ባህል አስመልክቶ የቀረበላቸውን ጥያቄዎች መልሰውልኛል።	አዲስ አበባ
5	አዴ ሰሉ ዲዳ	ሴት	4ኛ	30	አርብቶ አደር	ቦረና ያቤሎ ዳዲ	በጉቢጣ ላይ ሴቶች ስለሚዘፍኑዋቸው ዘፈኖች	ሰኔ 14 ቀን 1999	ዳዲ አርብቶ አደር ቀበሌ

ተራ.ቁ	ሙሉ ስም	ፆታ	የት/ደረጃ	ዕድሜ	ሥራ	የመኖሪያ አድራሻ	የመረጃ አይነት	መረጃ የሰጡበት ቀን	መረጃ የሰጡበት ቦታ
6	አዴ ደቦ ደበሶ ደደቻ	ሴት		40	አርብቶ አደር	ያቤሎ ዳዲ	ሴቶች ስለሚዘፍኑትና በበዓሉ ላይ የሚያደርጉት አስተዋፅዖ	ሰኔ 14 ቀን 1999	ዳዲ አርብቶ አደር ቀበሌ
7	አብ አባሩፍ ጃተኒ /የተሰያሚው ልጅ አባት/	ወንድ	ዲግሪ	30	አስተባባሪ	ድሬ	ለበዓሉ ስለተደረገው ዝግጅትና ስለ በዓሉ አስፈላጊነት	ሰኔ 14-17/1999	ዳዲ አርብቶ አደር ቀበሌ
8	አዴ ከሹ አባሩፋ /የተሰያሚው ልጅ እናት/	ሴት	ማንበብና መፃፍ	25	የቤት እመቤት	ድሬ	በበዓሉ የሴቶች ድርሻ፣ የዝግጅት ሁኔታ፣ ስለባህሉ	ሰኔ 14-17 1999	ዳዲ አርብቶ አደር ቀበሌ
9	አብ ኑራ ጉዮ	ወንድ	ማንበብና መፃፍ	48	አርብቶ አደር	ያቤሎ	በዓሉ ላይ እንግዶች እንዴት እንደሚስተናገዱ ይዘውት ስለሚመጡ ስጦታ	ሰኔ 14 እና 15 ቀን 1999	ዳዲ አርብቶ አደር ቀበሌ
10	አብ ሀሮ ኤሌማ	ወንድ	ማንበብና መፃፍ	30	አርብቶ አደር	ያቤሎ	በበዓሉ ላይ ስለወጣቶች ድርሻና ስለሚዘፍኑት ዘፈን	ሰኔ 15 ቀን 1999	ዳዲ አርብቶ አደር ቀበሌ
11	አብ ገልገሎ ዶዮ	ወንድ	-	70	አርብቶ አደር	ያቤሎ	በበዓሉ ላይ ስለሚከወኑ ድርጊቶች	ሰኔ 14-16 ቀን 1999	ዳዲ አርብቶ አደር ቀበሌ
12	አብ ደበሶ አዲ	ወንድ	-	74	አርብቶ አደር	ያቤሎ	ስለ ጉቢሣ በዓል አከባበር	ሰኔ 14 ቀን 1999	ዳዲ አርብቶ አደር ቀበሌ
13	አብ ሃለኬ ዶዮ	ወንድ	-	54	አርብቶ አደር	ያቤሎ	የጉቢሣ በዓል ድርጊቶች ቅደም ተከተል	ሰኔ 14 ቀን 1999	ዳዲ አርብቶ አደር ቀበሌ

ተራ.ቁ	ሙሉ ስም	ፆታ	የት/ደረጃ	ዕድሜ	ሥራ	የመኖሪያ አድራሻ	የመረጃ አይነት	መረጃ የሰጡበት ቀን	መረጃ የሰጡበት ቦታ
14	አዴ ገልሞ ቦሩ	ሴት	10ኛ ክፍል	29	ሠራተኛ	ያቤሎ	የጉቢጣ ዓል ወቅት ዜማዎች በሌላ ጊዜ እንዴት እንደሚዜም	ሚያዝያ 23 ቀን 1999	ያቤሎ ከተማ
15	ዋሪዮ አሬሮ /ቡሬ/	ወንድ	10ኛ ክፍል	32	ሠራተኛ	ያቤሎ	የጉቢጣ ወቅተ ዜማዎች በሌላ ጊዜ እንዴት እንደሚዜም	ሚያዝያ 23 ቀን 1999	ያቤሎ ከተማ
16	አባገዳ ሂዶ ገልገሎ	ወንድ	-	52	አርብቶ አደር	ሊበን ወረዳ	የቦረና ኦሮሞ ታሪካዊ አመጣጥ	ሰኔ 12 ቀን 1999	ያቤሎ
17	አቶ አለማየሁ ኃይሌ	ወንድ	M.A.	48	ሠራተኛ	አ.አ.	ስለኦሮሞ ታሪክ አጠቃላይ ሁኔታ	ሚያዝያ 6 ቀን 1999	አዲስ አበባ
18	አብ ሳራ ዴራ	ወንድ	B.A.	36	ሠራተኛ	ያቤሎ	ስለቦረና መልካምድራዊ አቀማመጥና የተፈጥሮ ሀብት	ሚያዝያ 24 ቀን 1999	ያቤሎ
19	አዴ ሳኬ ዋቆ	ሴት	12+2	32	ሠራተኛ	ያቤሎ	ሴቶች በባህሉ ያላቸው ቦታ	ሚያዝያ 22 ቀን 1999	ያቤሎ
20	አብ ዋሪዮ ገልገሎ	ወንድ	-	65	አርብቶ አደር	አሬሮ	ስለ ጉቢጣ በዓል ክዋኔዎች ቅደም ተከተል	ሐምሌ 28 ቀን 1999	አሬሮ

ለመረጃ አቀባዮች የቀረቡ ጥያቄዎች በአማርኛ ትርጉማቸው

1. የኦሮሞ ህዝብ ታሪክ ምን ይመስላል?
   - ከየት መጣ? ለመጀመሪያ ጊዜ የሠፈረባቸው ቦታዎች የት ናቸው?
2. ከኦሮሞ ባህል ምን ምን ዋና ዋና ጉዳዮችን ማንሳት ይቻላል?
   - እምነቱስ እንዴት ይገለፃል?
3. የኦሮሞ ጎሣዎች ዋና ዋናዎቹ የትኞቹ ናቸው? አሰፋፈራቸውስ ምን ይመስላል?
4. የቦረና ኦሮሞ የት ይኖራል?
   - የአካባቢው መልካምድራዊ አቀማመጥ ምን ይመስላል? የተፈጥሮ ሀብቱስ?
5. ቦረናን ልዩ የሚያደርጉት የታሪክና የባህል እሴቶች ምን ምንድናቸው?
6. የቦረና ኦሮሞ ህዝብ በተለያየ ጊዜ የሚያከብራቸው በዓላት ምን ምንድናቸው?
7. ጉቢሣ አንዱ የሚከበር በዓል ነው ይባላል። እነማናቸው የሚያከብሩት?
8. ጉቢሣ ማለት እራሱ ምንድነው ?
9. ይህ በዓል በህዝቡ ዘንድ የሚሰጠው ቦታ ምን ይመስላል?
10. የጉቢሣ በዓል ለምን ይከበራል?
11. የጉቢሣ በዓል እንዴት ይከበራል ምን ምን ጉዳዮች /ድርጊቶች/ ይከወናሉ?
12. የጉቢሣ በዓል የበኩር ልጅ ስም ስያሜ ነው ተብሏል፣ የበኩር ልጅ ያልሆኑትስ እንዴት ይሰየማሉ?
13. በቦረና የተለያዩ የስም ስያሜ አሰጣጥ ሥርዓቶች አሉ ይባላል ልዩነታቸው ምንድነው ?
14. በኩር ወይም ታላቅነት ለቦረና ምንድነው ? በምን በምን ሁኔታዎች ይገለፃል?
15. የበኩር ልጅ ስም ስያሜ በዓል ለስንት ቀን ይቆያል?
   - በየቀኑ ምን ይሠራል፣ ለበዓሉ የሚያስፈልጉ ነገሮች /ቁሳቁሶች/ ምንድናቸው?
16. በዓመቱ ውስጥ የበኩር ልጅ ስም ስያሜ በዓል መቼ ይከበራል?
17. ጉቢሣ በዓል ከሆነ በዓልነቱን የሚገልፁ ዘፈኖች /ዝማሬዎች/ ምን ምንድናቸው?
18. ጉቢሣ በዓል ላይ የሚሳተፉ እድምተኞች እንዴት ይመጣሉ? እነማን ናቸው?
19. ለበዓሉ ጥሪ የተደረገላቸው ሰዎች ምን ይዘው ይመጣሉ?
20. በበዓሉ የሚሰየመው ስም እንዴት ይሰየማል? ማን ይሰይማል?
21. ተሰያሚው ልጅ ከስሙ ሌላ ከበዓሉ ምን ያገኛል?

22. ቤተሰቦቹ ከበዓሉ ምን ያገኛሉ?
23. የቦረና ኦሮሞ ሆኖ ይህን የስም ስያሜ የማያከብር አለ? የማያከብሩት እንዴት ይታያሉ?
24. በቦረና ኦሮሞዎች ዘንድ ልጅ እንዴት ይያዛል? በሴት ልጆችና በወንዶች ልጆች መሀከል ያለው ግንኙነትና ልዩነት ምንድነው?
25. የቦረና ኦሮሞዎች ጋብቻ እንዴት ይፈፀማል? ልጅ ከማፍራት አንፃር ትዳር ምን ቦታ አለው?
26. የምራት ልጆች የጉቢጣ በዓል እንዴት ይከበራል?
27. በቃሉና በአያንቱ መሀከል ያለው ግንኙነትና ልዩነት ምን ይመስላል?
28. በአባገዳና በቃሉ መሀከል ያለው ልዩነትና አንድነት ምንድነው?
29. በጉቢጣ በዓል ሆነ በሌላ ጊዜ የሚሰየሙ ስሞች ምን ምንድናቸው?
30. የወንድና የሴት ስሞች ይለያሉ?
31. በጉቢጣ ስም ስያሜ ሰበብ በታላቅና በታናናሽ ወንድሞች መሀከል ያለው ግንኙነት ምን ያህል ጠንካራና ሰላማዊ ነው?
32. ቶርበን ጂላዎች ምንድናቸው?
33. ቀደዱስ?
34. በቦረና ሴቶች ያላቸው ቦታና ክብር ምን ይመስላል?
35. ከታላቅ ሴት ልጅ ቀጥሎ የተወለደ ወንድ ልጅ የጉቢጣ በዓል ይዘጋጅለታል?

የቦረና ኦሮሞ የተፀውዖ ስሞችና የአማርኛ ፍችያቸው

ብዙውን ጊዜ ለታላቅ ወንድ ልጅ የሚሰየሙ ስሞች

ኦሮምኛ የአማርኛ ፍች /የተሰያመበት ሁኔታ/

1. Boruu (ቦሩ/ ---------- ጠዋት ለተወለደ ሰው የሚሰየም
2. Guyyoo /ጉዮ/---------- ቀትር ሰዓት የተወለደ
3. Alakee /አለኬ/ ---------- ከቤት ውጭ የተወለደ
4. Liiban/ቢበን/ ---------- ሊበን አከባቢ የተወለደ
5. Galamaa /ገልማ/---------- በበዓል መከወኛ ቤት ውስጥ የተወለደ ልጅ
6. Galgalo /ገልገሎ/---------- ማታ የተወለደ
7. Huqqaa /ሁቃ/---------- ቀጭን ሆኖ የተወለደ
8. Qaallichaa /ቃልቻ/--------- የተከበረ እንጨት በዚህ እንጨት የሚሰየም ስም ለገድ ነው፣ ለመልካምነቱ
9. Doyyoo /ዶዮ/ ---------- ዶዮ የቦታ ለምነው፣ የበዓል ማክበሪያ ቦታ ነው ይህ ስም በዚህ ቦታና በበዓል ቀን ለተወለደ ልጅ ይሰጣል
10. Jaldessaa /ጀልዴሳ/ -------- የዱር እንስሳ ስም ነው ዝንጀሮ/ ልጅ ደጋግሞ የሞተባቸው ተከታዩን ይሰይመውበታል፣ ከጽበሉ ወደ ጋሜ ለሚሸጋገሩ አባገዳ በዚህ ስም ይሰይማል
11. Bulee /ቡሌ/ ---------- የቀለም አይነት
12. Elmaa /ኤልማ/ ---------- ወተት /ላም በሚታለብበት ጊዜ ለተወለደ ይወጣል/
13. Gaayyoo /ጋዩ/ ---------- የቦታ ስም /የገዳ ሥርዓት የሚከወንበት ቦታ/ በቦታ ወይም በሥነሥርዓቱ መከወኛ ወቅት ለተወለዱ ልጆች ይሰየማል
14. Jiloo /ጂሎ/ ---------- በዓል /በበዓል ቀን ለተወለደ/ የሚሰየም

15. Jaatanii /ጃተኒ/ ---------- ረዳት

16. Areeroo /አሬሮ/ ---------- የቦታ ስም /በአባቢው ለተወለደ ሰው ይሰየማል

17. Diidaa /ዲዳ/---------- ገላጣ ቦታ

18. Waaqoo /ዋቆ/ ---------- /አምላክ /ለማመሰገን የሚሰየም፣ አምላኩ፣ ቆይቶ ለተወለደ የሚሰየም ይሰየማል

19. Nuuraa /ኑራ/---------- የቦታ ስም /የበዓል ቦታ / በአአባቢው ለተወለደ ይሰየማል

20. Dhaddachaa /ዳደቻ/ --------- የእንጨት አይነት ነው፣ ለጥሩ ምሾት ይሰየማል -እንደ ደደቻ እንጨት ተስፋፋ ቅርንጨፍህ ይብዛ ለማለት ነው

21. Gobbaa /ጎባ/ ---------- የዳበረ

22. Maalichaa /መልቻ/---------- ዘዳኛ

23. Yaayyaa /ያያ/ ---------- የጎሣ ስም

24. Dammichaa / ደምቻ/---------- ማሩ

ታናሽ ወንድ ልጆች የሚሰየሙባቸው

25. Aagaa /አጋ/ ---------- ሀብት የተገኘበት ጊዜ ለተወለደ የሚሰየም

26. Gadayyoo /ገዳዮ/---------- ገዳ /አስታሪቂነ አስተዳዳሬ/

27. Xaaxoo /ጣጦ/ ---------- የእንጨት ዓይነት /ፍሬው ጥቁር የሆነ/ ሲወለድ አፉ ጠቆር ያለ ልጅ የሚሰየምበት ነው፣ አፈጭቃ

28. Caaccuu /ጫጬ/ ---------- ያማረ

29. Dootii /ዶቲ/ ---------- የቀለም አይነተ ለፍቅር መግለጫ የሚሰየም

30. Mataa /መታ/ ---------- የሰውነት አካል /እራስ/፣ ታላቅ

31. Moluu /ሞሉ/ ---------- መላጣ /ሲወለድ ፀጉር የሌለው/

32. Danbalaa /ደንበላ/ ---------- ብዙ ውሃ ያለበት ቦታ በጥጋብ ጊዜ የተወለዳ ልጅ ይሰየምበታል ::

33. Gonboo /ጎንቦ/ ---------- የዕቃ ስም ነው:: ሲወለድ ወፍራም የሆነ ልጅ የሚሰየምበት

34. Daada /ደደ/ ---------- ሰላም፣ መረጋጋት የሰፈነበት

35. Soraa /ሶራ/ ---------- በዝናብ ወቅት የተወለደ

36. Godaanaa /ጎዳና/---------- ከቦታ ቦታ ዝውውር ሲደረግ የተወለደ ሰው የሚሰየምበት

37. Qottoo /ቆቶ/ ---------- መጥረቢያ /የሰላ/

38. Diimataa /ዲመታ/ ---------- ቀይ

39. Waariyoo /ዋሪዮ/ ---------- ምሽት

40. Diidolee /ዲዶሌ/ ---------- ሜዳ

41. Abguddaa /አበጉደ/ ---------- ታላቁ

42. Culkii /ጨልኪ/ ---------- ፅዱ

43. Taaraa /ታራ/ ---------- የወተት መናጫ: ሲወለድ ወፍራም የሆነ

44. Goollisaa / ጎሊሣ/ ---------- ዘንከታ /ረዥም/

45. Kiyyoo /ኪዮ/ ---------- የኔነህ

46. Gurree /ጉሬ/ ---------- የቀለም አይነት / ጥቁረት/

47. Gurraachaa /ጉራቻ/ ---------- የቀለም ዓይነት /ጥቁር/

48. Xuunnicha / ጡኒቸ/ ---------- ትንሽ /ሲወለድ ክብደቱ አነስተኛ የሆነ/

49. Jirma /ጅርመ/ ---------- ወፍራም

50. Bilaalaa /ቢላላ/ ---------- ፀጉሩ የሣሣና የተበታተነ

51. Bilisoo/ ቢሊሶ/ ---------- ነፃ የሆነ

52. Dabbasaa /ደበሳ/ ---------- ፀጉራም

53. Dhokataa /ዶካታ/ ---------- ድብቅ

54. Taanuu /ታኑ/ ---------- ያልተጠበቀ

55. Sanphaloo /ሰንጳሎ/ ---------- የቦታ ስም

56. Carfoolee /ጫርፎሌ/ ---------- መናጫ

57. Carfii /ጨርፊ/ ---------- መናጫ

58. Waaccuu /ዋጩ/ ---------- የእንጨት ዓይነት /ቀይ የሆነ/

59. Marquu /መርቁ / ---------- አጭሬ

60. Turee /ቱሬ/ ---------- አጭር /ድንክ/

61. Kanaa /ከና/---------- ይኸውነው

62. Qallaa / ቀላ/---------- ቀጭኑ

63. Gobbuu /ጎቡ/ ---------- ብዙ

64. Waacilee (ዋጭሌ/ ---------- የቦታ ስም

65. Abbaa Jirmaa / አባጅርማ/-------- ወፍራሙ

66. Abduuba /አብዱበ/ ---------- ከኋላ

67. Duuloo /ዱሎ/ ---------- ዘማች

68. Jabaa /ጀባ/ ---------- ጠንከራ

69. Godoo /ጎዶ/ ---------- ጠባብ

70. Naqataa /ነቀታ/ ---------- ሀብታም

71. Maraa / መራ/ ---------- በጉዞ

72. Buttee /ቡቴ/ ---------- ትልቁ /ወፍራም/ ውሃ የሚቀዳበት እንሥራ

73. Garbii /ገርቢ/ ---------- የእንጨት ዓይነት ክረምት ከበጋ ለምለም የሆነ

74. Diimaa /ዲማ/ ---------- ቀዩ

75. Taadhichaa /ታዲቻ/---------- ቀጭኑ

76. Garboolee /ገርቦሌ/ ---------- ባራዬ

77. Kottolaa /ኮቶላ/ ---------- አጭር ወፍራም

78. Garsee /ገርሴ/ ---------- የእንጨት ዓይት /ለምለም/

79. Duuba /ዱባ/ ---------- ኋላ

80. Yaraa / ያራ/ ---------- አቅመቢስ

81. Abkuula / አብኩሉ/ ---------- ውብ

82. Haroo /ሀሮ/ ---------- ሀይቅ: ውሃማ /ለም/

83. Gabaabaa /ገባባ/ ---------- አጭሬ

84. Dheeraa /ዴራ/ ---------- ዘንካታ/ረዥሞ

85. Alii /አሊ/ ---------- የውጭ

86. Jibicha /ጅብቻ/ ---------- ጠንካራ /ወይፈን/

87. Daalacha / ዳለቻ/ ---------- ለመልክ /ቀይ ወይ ጥቁር ያልሆነ/

88. Raamataa /ራመታ/ ---------- ጥጋብ

89. Foora /ፎረ/---------- ምቹ

90. Shoobaa /ሾባ/ ---------- ንፁህ

ለሴቶች የሚወጡ ስሞች

91. Qabballee /ቀበሌ/ ---------- የረጋች

92. Lookoo /ሎኮ/ ---------- ረዥም: እንከን የለሽ

93. Darmii /ደርሚ/ ---------- ቆንጆ /የፈረስ ግልገል/

94. Adii /አዲ/ ---------- ለመልክ ቀይ /ለፍቅር/

95. Dhakki /ዳኪ/---------- ትንሽ

96. Qaroo /ቀሮ/ ---------- ብልህ /ብልጥ/

97. Gubaalaa /ጉባላ/ ---------- ቆንጆ /አፈጭቃ/

98. Qamalee /ቀመሌ/ ---------- ብልጥ

99. Teessoo /ቴሶ/ ---------- ዘገየች

100. Xummee /ጡሜ/---------- ውብ /አፈጠባብ፡ ጡጦ አፍ/

101. Diiramuu /ዲረሙ/---------- ጠዋት የተወለደች

102. Horgoolee /ሆረጎሌ/ ---------- የግመል ግልገል /ፍቅር መግለጫ/

103. Cuquliisa /ጨቁሊሣ/ ---------- የወፍ አይነት - ውበትን ለመግለፅ

104. Jiloo /ጅሎ/ ---------- በበዓል ዕለት የተወለደች

105. Cuquloo /ጨቁሎ/ ---------- ውቧ

106. Taadhittii /ታዲቲ/ ---------- ቀጭኗ

107. Ruufoo /ሩፎ/ ---------- ገዳም

108. Elmaa /ኤልማ/ ---------- ሀብታሟ

109. Obaatuu /አባቱ/ ---------- ገዳም

110. Waaree /ዋሬ/ ---------- ሞቅሲል የተወለደች

111. Dabboo /ደቦ/ ---------- ወፍራም

112. Diqqoo /ዲቆ/ ---------- ትንሽ

113. Inseenee /ኢንሲኔ/ ---------- አልታሰብሽ /አልተጠረጠረሽ/

114. Alaakuu /አላኩ/ ---------- ውጭ የተወለደች

115. Kuulee /ኩሌ/ ---------- ውብ

116. Haa kuula /ሃኩላ/ ---------- ውበት ለአይን

117. Bilisoo /ቢልሶ/---------- ነፃ

118. Hadiidaa /ሀዲዳ/ ---------- ሚዳማ

119. Dheeratuu /ዴሬቱ/---------- ራዥም

120. Gogorrii /ጎጎሪ/ ---------- ጅግራ /ውብ/

121. Dureetti /ዱሬቲ/ ---------- ሀብታሟ

122. Galgaluu /ገልገሉ/---------- ምሽት

123. Galmoo /ገልሞ/ ---------- ገልማ ውስጥ የተወለደች

124. Guuyyaatuu /ጉያቱ/---------- ቀን የተወለደች

125. Haagannaa /ሀገና/---------- እርጥቢ /ገዳሟ/

126. Xaxoo /ጣጦ/ ---------- የእንጨት አይነት /ለምለም/

127. Dhalee /ዳሌ/ ---------- የኔነሽ /ወለድኩሽ/

128. Tarrii /ተሪ/---------- የአውሬ አይነት /ትንሽ/

129. Lootii /ሎቲ/---------- ጌጤ

130. Bonee /ቦኔ/ ---------- በበጋ የተወለደች

በጉቢሣ በዓል አጋጣሚ የተገኙ ቃል ግጥሞች

ኢያንገሎ (Iyyangaloo)

ኢያንገሎ የመጀመሪያው የጉቢሣ በዓል ዜማ ነው።

Iyyaan galoo tiyya eega	ተጫዋቹን እጠብቃለሁ
Haagaloo qabatee	ሃገሎ በአንገቱ አንጠልጥሎ
Simphirree gaadatee	ወፍ በወንጭፍ ይመታል
Haagaloon qilliftee	ሀገሎ አቃጨለች
Taphaa bakkaafatee	ተጫወተ እየተንገዳገደ
Caara yaabbii tika eega	ጥጃ እየጠበቀ(እየተንጫጨ ጥጃ ይጠብቃሉ)
Diidaa Baaraa qotee	ከሜዳው "ባራ" ቆፍሮ /ባራ የሚበላ ሥር/
Baree qundhii kuttee	ወፍሮ የእጁ ላይ እስር ሰረሰረው
Diidaa fardoo raaree	ፈረስ ኋላ ሆኖ እየነዳ
Abboo badhaafatee	አባቱን አስደሰተ
Diidaa Caamee gootee	ከዋለበት ለቤት የሚሆን ይዞ እየገባ
Hayyoo badhaafatee	እናቱን አስደሰተ
Iyyaan galoo tiyya eega	ተጫዋቹን ጠብቃለሁ
Tuutoo addaan duraa	ባለ ቁንጮ አናት
Boruun waaqaan duraa	ጠዋት ሳይነጋ
Guddaan warra duraa	የመጀመሪያ ልጅ
Lafa Liiban duraa	ከመሬት ሊበን የመጀመሪያ
Ibidda irraa daandee	በእሳት ዙሪያ እየሄደ
Harkaan galoo daandee eega	እኔ በእጅ እጠብቃለሁ
Galaan gulloo daandee	መሬት ላይ ሲንከባለል
Shunxoon dhulaandhula eega	ጥበቃ ያስፈልገዋል
Ulaannaan urgooftee eega	መሸኛው አልቅት መሳይ
	ጠረኑ ለኔ ያውደኛል

ቡልቱሞ ቡሌ (Bultumoo bulee)

ይህ ዜማ በሁለተኛ ደረጃ የሚቀርብ በአባትየው የሚዜምና ቶርበን ጅላምቹ በተቀባይነት የሚሳተፉበት ነው።

Bultumoo Bulee yoo hoo	ቡልቱም ቡሌ ዮ ሆ
Bulegaa marabbaa yoo hoo	አድሬያለሁ ተመስገን
Bultumoo hee, waaq naabulchi	አምላክ ቡልትምን አሳድግልኝ
Karra naa bani yaa abbee	ልጄ በር ክፈትልኝ
Warri dhaarritoo yoo hoo	እነ ዳሪቶ
Dharraa kee hin baane yaa abbaa koo	ጌታዬ ናፍቆትህ አልወጣልኝም
Bultumoo waaq naabulchi	እግዜር ቡልቱምን አሳድግልኝ
Karra naa bani yaabbee	ልጄ ሆይ በር ክፈትልኝ
Kateeba Areeroo, Reerrii yaammatee abbaa koo	የአሬሮ ልጅ ጎሳውን ጠራ
Akka galaana dhiibuu dachaa abbaa koo	እንደ ሸለቆ ጎርፍ ድርብ
Akka goobanaa dhiibamaa dhufe abbaa koo	እንደ ጠዋት ኮክብ እየገፋ መጣ
Akka dhaddacha guddaa daraaree abbaa koo	እንደ ትልቁ ዳደቻ አበበ

ሆ! ሃሩሶ

1. Hoo haruusoo	ሆ! ሃሩሶ
Maalimallayyaa	ምን ይበጃል (ምን ይሻላል)
Abbeeraa uumaa	የፈጣሪ ልጅ
Ilma naa uumi abbaa	ልጅ ፍጠርልኝ (ልጅ ስጠኝ)
2. Hoo haruusoo	ሆ! ሃሩሶ
Maalimalayyaa	ምን ይበጃል (ምን ይሻላል)
Abbeeraa uumaa	የፈጣሪ ልጅ
Ilma naa uumi abbaa	ልጅ ፍጠርልኝ (ልጅ ስጠኝ)
3. Hoo haruusoo	ሆ! ሃሩሶ
Maali malayyaa	ምን ይበጃል (ምን ይሻላል)
Abbeeraa uumaa	የፈጣሪ ልጅ
Ilma naa uumi abbaa	ልጅ ፍጠርልኝ (ልጅ ስጠኝ)

ሰገዴ መለዮ (Sagadee Mallayyoo)

Sagadee Sageeto qaba	ሰገዴ 'ሰጌቶ' አለው
Ka duraa Arboora qaba	ታላቅ (ጀግና) "አርቦራ" አለው
Arboora Bulee Dhaddachaa	የቡሌ ዳደቻ "አርቦራ"
Hawwaxuu Dhaddacha Yaayaa	የደደቻ ያያው ሀወጡ
Konnituu Waasolee Booraa	የዋሶሌው ቦራው ኮንቱ፡
Konnituu Waasolee Booraa	

አሸኔ ዶዮ (Ashanee Dooyyoo)

Ashanee Doyyoo lattuu haasaa tolte	አሸኔ ዶዮ ለጫወታ የተመቸች ለምለም
Baallisee yoo ha yoo haa,	ቅጠሏ፣ አቤት! አቤት!
Har'a ardaan nagayaa ayyana baballisa	ዛሬ አካባቢው ሰላም ነው በዓላችን ይሳካል፣
Sagadaa sagadi kiyya araada	ፀሎቴ ለአምሮት ነው
Ta lagaa Guula baate tiksituun guurte	ከጉለ ወንዝ የበቀለችን ለምለም እረኛ የቆረጣት
Ta Qilxaa gooda baate goduun yaamte	ተቅልጣ ጎዳ አካባቢ የበቀለችን ለምለም ሁሉም ፈለገው
Araadee hammaadhe lattuu uuba'ii nyaadhe	ሱስ ይዞኝ ሳልመርጥ ቃምኩ
Ubbayiin aadaa lattuu balchaan ollaa	የለምለም አያያዝ ባህሉ በቅጠል ሸፍኖ ነው
Daroleen baatee, lattuu namni dare hin cabsu	በዳሮሌ አካባቢ የበቀለን ለምለም የታረዘ ሰው አይቆርጠውም
Mana gubbisaan baate lattuun goduu gabbistee	የጉቢጣ በዓል የተከበረበት፣ ለምለም በዓሉን አገዘፈው
Arbooleen baatee lattuu miilli arrayyaa	በአርቦሌ፣ አዲስ ለምለም ወጣች (በቀለች)

እልሜ ሆዮ

Ilmee hoo yoo, ilmaan sabbaaq duulaa	እልሜ ሆዮ የሰባቀ ዱላ ልጆች
Sabbaaqii duula qabataa	ሰባቅ ጦር ይይዛል
Mucaan abbaa qabataa	ልጁ አባቱን ይይዛል
Mucaan maqaa baafata	ልጁ ስም ይሰየማል
Maqaa Boruu baafata	ቦሩ የተሰኘ ስም ይሰየማል
Boruun Waaqaa angafaa	ንጋት ለብርሃን ታላቅ ነው
Boruu abbaa angafaa	ቦሩ የተባለ ልጅ ለአባት ታላቅ ነው
Boruu eenyu wallaala	ቦሩን ማን ያጣዋል /ሁሉም ያውቀዋል/

የቃሉ ማሞገሻ

Alii Aliyoo Simuudaa	አሊ አሊዮ ይሾምሃል
Ali Gurraachaa sumuudaa	አሊ ጉራቻ ይሾምሃል
Gurraacha Yaayyaa simuudaa	ጉራቻ ያያ "
Yaayyaa Muunyoo simuudaa	ያያ ሙኚ "
Moonaa Curruuxxee "	ከግቢው ድኸህ
Daraaraa Dheeddee "	ለምለሙን ግጠህ
Daraaraa Marraa "	የለመለመ ሣር
Waaq sifeesse "	አምላክ ባረከልህ
Daraaraa ilmaa "	የልጅ አበባ
Waaq Urgeesse "	አምላክ አሳደገ

የልጁ ወላጆች የሚሞገሱበት በሴቶች የሚዘፈን

Abbaa jilaa taatee, harka lichoon daaxxee	ባለድግሥ ሆነህ እጅህ በሊቾ ደመቀ
Abbaa biyyaa taatee, dubbiin sibarbaaddee	ባለሀገር ሆነህ ጉዳይ ሁሉ አንተን አለ
Torban jilaa taatee daannisaan mardaadde	ቶርበን ጅላ ሆነህ ዳኒሳ ይዘህ ተንጎራደድህ
Abbaan jilaa gurraacha surree ruufaa	ባለበዓል ጥቁሩ ሰሬ ሩፋ የጠመጠመ
Ayyoon jilaa diimtuu mataa yuubaa	የበዓሉ እናት ቀይ ወጉረ ረዥሞ

Warri jilaa akkuma baanan jira	ባለ በዓሌች እንደሚወራላቸው ናቸው
Gololchituu jilaa abbaatu fandii fila	ጥሩ የበዓል አስተናጋጅን ባለቤቱ ይመርጣል

የከብት ማሞገሻ

Galoosame hagaloo malaan dhaane	ከብቱ እንዲገባ ደወል አሰማ
Galuu didee tissaan dhaane	አልገባ ሲል እረኛው መታው
Faayoon bulee, duuba bulee	ፉዮ ውጭ አደረ
Faayoon kiyyaa bule Burree dhaanee	የኔ ፉዮ አደረ፣ ቡሬ ተመታ
Hinbullu buleen jette	አናድርም አለ
Hinbullu dheebuun jette	በጥም አናድርም አለ

ኩቹዎቹ የወደዷትን ሴት የሚያሞግሱበት

Hoo hammee hoyyoo(2)	መግቢያ አይነት ነው
Waaqi boru bonaa	ሰማዩ ነገ በጋ ነው
Amma roobee gannaa	አሁን ዘነበ ክረምት ነው
Salloo mataa gannaa	ውቧ ወጉሯ የራሰ (በቅቤ)
Cirrii foora bultee	ጭሪ (የወፍ አይነት) ከብቶች የተሠማሩበት ያደረች (ጭሪ ለውበት የምትጠቀስ ወፍ ናት)
Foora galaa duultee	ከርቀት የምትመለስ
Omacha galaa dhuddee	የግመል ወተት ጠጥታ ያደገች
Diidi gufuu hinqabne, silaa gunnaa tolaa	እንቅፋት የሌለበት ሜዳ ለሌሊት መንገድ ይመቻል
Mormi lafee hin qabne silaa sirbaa ta'aa	አጥንት የሌለው አንገት ለዘፈን ይመቻል
Guntatni lafee hinqabne silaa irribaa tolaa	አጥንት የሌለው አንጠንጤ ለመኝታ ይመቻል

ምርቃት

መራቂ	ምርቃት ተቀባዮች	መራቂ አማርኛ ትርጉም	ተቀባይ
Bobba'an nagayaa	Nagahi	የሚሠማራ ሰላም	ይድረስኝ
Bobbaan nagayaa	Nagahi	ስምሪት ሰላም	ይድረስኝ
Olmaan nagayaa	Nagahi	ውሎ ሰላም	ይድረስኝ
Galchuun nagayaa	Nagahi	መመለስ ሰላም /አሰሚርቶ ማስገባት/	ይድረስኝ
Barri nagayaa	Nagahi	ዘመኑ ሰላም	ይድረስኝ

Bariin nagayaa	Nagahi	ንጋት ሰላም	ይድረሰኝ
Waareen nagayaa	Nagahi	ረፋዱ ሰላም	ይድረሰኝ
Waariin nagayaa	Nagahi	ምሽቱ ሰላም	ይድረሰኝ
Elmaan nagayaa	Nagahi	ከብት ማለብ ሰላም	ይድረሰኝ
Elmituun nagayaa	Nagahi	አላቢዎች ሰላም	ይድረሰኝ
Elmaa gaadii nagayaa	Nagahi	የወተት አካባቢ ሰላም	ይድረሰኝ
Tissaa huleen nagayaa	Nagahi	የወተት ማለቢያ ቁሳቁሶች ሰላም	ይድረሰኝ
Liiban Dirreen nagayaa	Nagahi	ሊበንና ድሬ ሰላም	ይድረሰኝ
Gadaan sadeen nagayaa	Nagahi	ሦስቱ ገዳዎች ሰላም	ይድረሰኝ
Raabaa Kuusi nagayaa	Nagahi	ለራባ ኩሣ ሰላም	ይድረሰኝ
Gosa Booranaa Sabboo	Nagahi	ለቦረና ጎሣዎች	ይድረሰኝ
Gonaa nagayaa		ለሰቦና ጎና ሰላም	

ስም ከተሰየመ በኋላ ከሚቀርቡት የከብቶች መዝሣ ዘፈን

Hoo, hoo simallellaa	ሆ ሆ እንከባከብሃለን
E, ee maaloo guddoo dhoofna	ኤኤ ትልቅ መላ እንፈጥራለን
Yoo guddoo hadi beshaa	ወዳጄ ከበሮን እንመታለን
E'ee dibbee qabaa jennaa	ኤ ኤ የከበሮን ድምፅ ተቀበሉ·
Dhageettee dibbee waariif dhoofnaa	ሰምተናል ከበሮውን ለምሽት ጨዋታ ብለን ነው የምንመታው·
Barraaqoo lukkun barii dhoofnaa	በማለዳ ዶሮ ንጋትን ታበስራለች
Bariitee karraa faayaa bantuun dhoofna	ሲነጋ የከብት በረት ከፋቾች ያስተውላሉ·
Yoos elmtuun gaadii dhoofna	በዚያን ጊዜ ከብት አላቢዎች የማለቢያ ዕቃቸውን ይዘው ይስተዋላሉ·
Waamii moonaatti nuu barfannaa	በዘያን ሁኔታ ላይ እያሉ ከብቶች በበረት አረፈዱ
E'ee sangaan abbaan marrannaa	ኤ ኤ የአባቴን ሰንጋዎች ድምጻቸውን አሰሙ·
Yoos abboon keenna dallannaa	በዚያን ጊዜ አባቴ ተናደደ
Ka'ee cufnaa gargannaa	ተነስቶ የበረት መዝጊያ እንጨቶችን በታተናቸው·
Dhageettee cufnaan shakkifnaa	ሰምተሃል የበረት መዝጊያ እንጨቶች ሼክ የሚል ድምጽ ሲያሰማ
Isatti aanee butumeen kukkifnaa	ከእርሱ ቀጥሎ የቡልቱሜ እንጨት ሲወድቅ ድምጽ ተሰማ
E'ee tissaan nuu dhaqqabnaa	ከብቶች ከበረት ወጥተው ስለሄዱ እረኛ ተከተላቸው ደረሰባቸው·
Waama arcumme diraan dhoofnaa	በአርጨሜ ጀርባ ጀርባቸውን መታቸው·
Ee guddoo fiiquu gurratti hoofnaa	በጆሮዋቸው ላይ አፏጨን
Tissaan lafoo dhaadhaatti baasaa	እረኛው ወደ በረሃ አካባቢ ወሰዳቸው·
E'ee tissan waaqaa shaooggannaa	እረኛው እግዚአብሔርን ለመነ
Yoo guduu waaqni dhugaa beeka	አ ጉዶ እግዚአብሔር እውነትን ያውቃል
Yoo suma duumassoo galmeeshaa	ወዲያውኑ ዳመና አነጎበበ
Yoo guddoo jaldoo gaddiseessaa	የተበታተነ ዳመና ጋረደ
E'ee gaaddisoon Hagayyaa	የበልግ ወቅት ደመና ነው·
	ጸሐዩ የበልግ መባቻ የደረቅ ወቅት ነው·

E’ee qallaan miilaa buunaa

ቀጠንጠን ያለና ካፊያ የመሰለ ዝናብ ጣለ

Dafnee nama haawwichaa waamnaa

በፍጥነት የከብቶችን እረኛ ጠራን

Waamnee ni hoggeenan jennaa

ጠርተን ወደ ዝናቡ አንባቢ እንምራቸው አልነው

Yoos hin hoggeenuun jennaa

እርሱ ግን አንመራቸውም አለ

Yoo gudoo ma diddaa gaafannaa

አሁንም ደግመን ለምን አልወሰዳቸውም እንዳለ ጠየቅነው

Deebsee lafan fagoo jennaa

አካባቢው እሩቅ ነው ሲል መለሰ

Ammalle daandiin martoo fennaa

መንገዱም አስቸጋሪና ጠመዝማዛ ነው አለ

Yoo guddoo hoggansaa waliigall a

በኋላ በመውሰዱ ላይ ተስማማን

Yoo san lammachoon burraandhaa

በዚያን ጊዜ ጊደሮች መቧረቅ ጀመሩ

Eegasii hawwichoon horiinaa

ከዚያ ላሞቹም መሮጥ ቀጠሉ

E’ee lolaan qallan dhufnaa

ኤ ኤ ቀጭን ጉርፍ መጣ

Waamii qulluu ambuuqqannaa

ከብቶቹ ከንጹህ ውሃ ተጎነጩ

Yoo dhabee booruu dhuudhuman

ሲያጡ ግን ድፍርሱን አግበሰበሱ

ሴቶች ለስም ስያሜ ከሚያዜሙት የገዳ ዘመናትን የሚዛልጹበት

Maakula malloliyyee e'ee maakulyyoo e'ee maakulaa

Fullaasaa malloliyyee e'ee Fullaasayyoo e'ee Fullaasaa

Sabbaqa malloliyyee e'ee Sabbaaqayyoo e'ee Sabbaaqa

Daraara malloliyyee e'ee Daraarayyoo e'ee Daraara

Libbaasa malloliyyee e'ee Libbaasayyoo e'ee Libaasa

Mardiida malloliyyee e'ee Mardidayyoo e'ee Mardiida

Moggisa malloliyyee e'ee Moggisayyoo e'ee Moggisa

ዘመኑ የመኩለ ነው አዎ የመኩለ ነው

ዘመኑ የፍላሳ ነው አዎ የፍላሳ ነው

ዘመኑ የሰባቀ ነው አዎ የሰባቀ ነው

ዘመኑ የደራራ ነው አዎ የደራራ ነው

ዘመኑ የሊባሳ ነው አዎ የሊባሳ ነው

ዘመኑ የመርዲዳ ነው አዎ የመርዲዳ ነው

ዘመኑ የሞጊሳ ነው አዎ የሞጊሳ ነው

- በሞጊሳ ዘመን ልጆች በዓል ተዘጋጅቶ ስም አይሰየሙም:: ጎዶሎ ዘመን ተብሎ ስለሚታወቅ በዚህ ዘመን የተወለዱ ልጆች በተከታዩ ዘመን ይሰየማሉ::

ዋና ዋና ክዋኔዎችን የሚያሳዩ ፎቶዎች



ቦርቦር ቡሌ

ካሉ ጀሎ



ጃተኒ ዲዳ

አባጂላው (አባሩፉ ጀተኒ)

አባጂላ፣ ሃደጂላና አያት ለጉዚማ የሚያስፈልገውን አለባበስ ተጎናጽፈው

ለሃደ ጂላዋ ሰቃ ለማዘጋጀት ቁርበት
መተልተል ሲጀመር

በዓሉ ቡቲጀመረበት ዕለት ሃደ ጀላዋ
ከበረት አዛባ ሲታነሳ

ሃደጂላዋ ሀንደራካ /የመሠረት መጣየ/ እንጨት
በሴቶች ታጅባ ቆርጠው ሲመለሱ

በጎቀሳ ቁርቦ ሲመረት

ሴቶች የገልማ መስሪያውን እንጨት ቆርጠው ሲመጡ

የገልማው ሥራ በቀደዱው ሲጀመር

የገልማው ሥራ ቡተጀመረበት ጊዜ

ሃንዱራ ሲረዝሙ



ገልማው ተሠርዶ ከተጠናቀቀ በኋላ ይህን ይመስላል

አባጂላው ወሩን ሲላጭ

ተሰየሚው ልጅ ወገር ሲላጭ



ልጆቹ ወራቸውን ከተላው በኋላ



ቆቲ ቆርጠው ሲመጡ በአባቂላው መሪነት

አባት በኩር ልጅን አቅፎ ለስያሜ እንደተቀመጠ

ከኩቹ አባላት በከፊል



በበዓሉ መጨረሻ የሜዲቻ ከብት ለእርድ ቀርቦ ሲመረት

እኔ ከዚህ በታች ፊርማዬን ያኖርኩኝ የድህረ ምረቃ ተማሪ፣ ይህ ጥናት የራሴ ሥራና በጥናቱም ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ጽሑፎች ምንጭ በትክክል የጠቀስኩ መሆኔን አረጋግጣለሁ።

ስም ዲቦታ ኸወሊ

ፊርማ

ጥር 30 ቀን 2000 ዓ.ም.